# ዳንኤል ት.መ.ማ.



ዳንኤል
----

መግቢያ
----

የመጀመሪያ ቀን
----------

በዚህ ት.መ.ማ. ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ የሆነውን የዳንኤልን መጽሐፍ እናጠናለን። ዳንኤል በጣም ጠቃሚ የሆነ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው። በመጽሐፉ የተጠቀሱት ታሪኮች ተቃውሞና ችግር ቢደርስባቸውም በየትኛውም ሥፍራ ያሉ ክርስቲያኖች በእምነት ጸንተው መቆም እንዳለባቸው ያስተምረል። በተለያየ ችግር ውስጥ ብናልፍም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፤ ዓላማውንም በሕይወታችን ይፈጽማል። በጣም አስደናቂ ትንቢቶች ያሉበት መጽሐፍ ነው፤ አንዳንዶቹ ተፈጽመዋል፤ ሌሎቹ ደግሞ ወደፊት ይፈጸማሉ። ስለዚህ የዳንኤል መጽሐፍ፡- «የትንቢት ቁልፍ» በመባል ይጠረል። በመጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔር ከዳንኤል ጊዜ እንሥቶ ኢየሱስ ክርስቶስ መላውን ዓለም ለመግዛት እንደገና እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሁኔታ ገልጾአል። በጠቅላላው መጽሐፉ ውስጥ የሚታየው ዋነኛው ሐሳብ፡- እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ነው የሚል ነው። እርሱ የሕዝቡ የበላይ የሆኑትን ተቆጣጣሪና ተንከባካቢ ነው። የመንግሥታትንም የበላይ ተቆጣጣሪ እርሱ ነው።

ይህን መጽሐፍ ስታጠና በመመሪያው መጽሐፍ ላይ ያለውን በጥንቃቄ አንብብ። በጥንቃቄና ረጋ ብለህ ጥያቄዎቹን መልስ። የእግዚአብሔርን ቃል በግላችን እንዴት አድርገን ማጥናት እንዳለብን ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህንንም ማወቅ የምንችለው የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረንን በማጤንና ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነው። ወደ ኮሜንታሪው ከመሄድህ በፊት ጥያቄዎቹን መመለስህንና በተሰጠህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይም ጊዜህን ወስደህ ማሰቡን አትዘንጋ። ይህ ሲሆን ኮሜንታሪው ያልጠቀሳቸውን አንዳንድ ሐሳቦች ልታይ ትችላለህ። ኮሜንታሪ፡- በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ላለው አሳብ ትርጉም ነው ተብሎ የተሰጠ የአንድ ሰው ብቻ ትርጉም መሆኑን አትርሳ። በመልሶቹ ላይ አሰላስል፤ እንዲሁም የምታጠናቸውንም ትምህርቶች በሕይወትህ ውስጥ ውስጥ ለማዋሐድ ሞክር። የእግዚአብሔር ቃል የምናጠናው ብቻ ሳይሆን፥ የምንታዘዘውም ነው። ሮሜ 15:4:- «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» ይላል።

ይህ መጽሐፍ እንደ ጥናት መመሪያ ብቻ ሳይሆን እንደ ኮሜንታሪም እንዲያገለግል ነው የተዘጋጀው። መጽሐፈ ዳኔልን በግልህ ስታጠና ወይም ስታስተምር ይህን መጽሐፍ እንደ ማብረሪያ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

መልሶቹን በጸብተር ላይ ጻፋቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከሌለህ ለጥናትህ እንዲረዳህ ለማግኘት ሞክር። ከዚህ ኮርስ በተጨማሪ ስለ ትንቢተ ዳንኤል የሚያብራራ ሌላ መጽሐፍ የምታጠና ከሆነ በጣም ይረዳሃል።

ተማሪውን በጥናቱ እንዲረዳት ትምህርቶቹ በአምስት ቀናት ተከፍለዋል። እያንዳንዱን ትምህርት በአንድ ጊዜ ለመጨረስ ሞክር። በአተረጓጎም ረገድ ሲታይ በሁሉም አመለካከት ችግር የማይፈጥር አንድም የለም። ፀሐፊውም የሺህ ዓመቱን የንጉሥና ጊዜ እንደተዓረው አጽርኦ ነው የወሰደው። ይህም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሁሉም ግልጽ ሆኖ የተዓረ ነገር እንደሆነ ነው የሚያምነው። ስለዚህም እኔ ለዳንኤል መጽሐፍ የምሰጠው አተረጓጎም ይህን ሣስተኛውን አመለካከት የሚያንፀባርቅ ይሆናል። በምታጠኑበትም ጊዜ የእኔ አንድ የአተረጓጎም ዘዴ እንደሆነ አስተውሉ። ሌሎች ኮሜንታሪዎች /ማብራሪያዎች/ ወይም ሰዎች የዳንኤልን የትንቢት መጽሐፍ በተለየ መልኩ ማጤንን ይፈልጉ ይሆናል።

የዮሐንስ ራዕይ ትንቢቶች ከዳንኤል ትምህርቶች ጋር ተመሳሳይነት ስላላቸው ዳንኤልና ራዕይን ማነፃፀሩ በጣም ይጠቅማል።

1. የብዙዎቹ ትምህርቶች የመጀመሪያ ቀን ጥናት በሣምንቱ ውስጥ ሊሰጡ ካሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጭር ጥሞናን ያዘለ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ቃል በህይወታችን እንዴት መተርጎም እንዳለበት የሚያሳይ ምሳሌ ነው። ብዙ ጊዜ ከዛ ትምህርት ልንማረው የምንችለውን ዋናውን ነገር ያጠቃልላል።

2. አንዳንዶቹ ትምህርቶች በሦስት ቀን ሌሎቹም በአራት ቀን ሊያልቁ ይችላሉ። ከሣምንቱ ስብሠባ በፊት ሁሉንም ትምህርት ለመጨረስ የሚያስችል በቂ ጊዜ እንዳለህ አረጋግጥ።

3. በትምህርቱ ውስጥ ማመሣከሪያ ጥቅሦች አሉ። ተመልከት የሚሉትን ጥቅሦች እንድትመለከት ይሁን። ተመልከት የማይሉትን ጥቅሦች ግን በቂ ጊዜ ሲኖርህ ልታጠናቸው ትችላለህ ወይም ደግሞ ለበኋላ ልታቆያቸው ትችላለህ።

ቀጥሎ ያሉት ጥቂት ነጥቦች የመጽሐፉ ዓላማዎች ናቸው:-

1. ይህን መጽሐፍ ከጨረሰ በኋላ ተማሪው ከጠቅላላው ከዳንኤል መጽሐፍ ትምህርቶች ጋር ይተዋወቃል።
2. በትንቢቱ እንደተገለጸው ተማሪው በትውልዶች መካከል ያለውን አጠቃላይ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይረዳል። የዳንኤልም ትንቢት ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር እንዴት እንደተስማማ ሊያይ ይችላል።
3. በችግር ጊዜ ተማሪው እንደ ክርስቲያን እንዴት መኖር እንደሚችል ሊረዳ

ይችላል።

4. ተማሪው እግዚአብሔር ከሁሉም ነገር በላይ መሆኑን ይረዳልን ማለት፦ በሕይወቱ ውስጥ በችግርም ጊዜ፥ በዓለም መሪዎችና ሕይወት እንዲሁም በመላው ዓለም መንግሥታትም ላይ ሁሉ የበላይ ነው።

አንድ ሰው ረጅም መንገድ ከመሄዱ በፊት ስለጉዞው አንዳንድ ነገሮችን ይረዳል። ብዙ መረጃ ሲያገኝ ጉዞውን ያለምንም አደጋ ወይም ችግር ያከናውናል። የእግዚአብሔር ቃልም እንዲሁ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ጉዞ ከማድረጋችን በፊት ጉዞው ምን ዓይነት እንደሚሆን ማረጋገጥ አለብን። ስለ ዳንኤልና ስለነበረበት ዘመን ብዙ ባወቅን ቁጥር አተረጓጐማችንም እንዲሁ በይበልጥ ትክክለኛ ይሆናል።

የመጀመሪያዎቹ ሦስት ትምህርቶች ስለ ዳንኤል መጽሐፍ መግቢያ ሐሳብ ይሰጡሃል። በትምህርት አንድ ዳንኤል በነበረበት ዘመን ስለነበረው የዓለም ሁኔታና ታሪክ እንመለከታለን። በትምህርት ሁለት በመጠኑም ቢሆን አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን እናጠናለን። ትንቢቶችን እንዴት እንደምንረዳ የተለያየ ሐሳብ ቀርቦአልን እነዚህንም አመለካከቶች እናያለን። በትምህርት ሦስት ደግሞ እያንዳንዱን ምዕራፍ ለማጥናት ከመጀመራችን በፊት ስለ ዳንኤል መጽሐፍ ሰፋ ባለ ሁኔታ እናጠናለን። ይህም ዳንኤልን ለማጥናት ጠንካራ መሠረት ይሆንልናል። ዳንኤል ለመረዳት የሚያስቸግር መጽሐፍ ነው። ስለዚህም እነዚህን ሦስት ምዕራፎች በጸንብ ማወቁ ይጠቅምሃል።

## ትምህርት አንድ

### ዳንኤል የነበረበት ዘመን ታሪክ

ስለምንኖርበት ዓለም ለማጥናት ስንፈልግ ስለ ዓለም መንግሥታት በተለይም ከሀገራችን ጋር ስለሚቀራረቡት መንግሥታት እናጠናለን። ስለዚህም በትምህርት ቤታችን ስለ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ስለ ሩስያ፥ አሜሪካ፥ ካናዳ፥ ጣሊያን፥ ወዘተ እናጠናለን። የኢትዮጵያ ታሪክ ከሌሎች አገሮች ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። የዳንኤል መጽሐፍም እንዲሁ ነው። የመጽሐፉን ትምህርት ከመረዳታችን በፊት በዳንኤል ዘመን ስለነበሩት ኃያላን መንግሥታት መረዳት አለብን። በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ምርጥ ስለሆኑት ሕዝብ ማለትም እስራኤላውያን እናጠናለን። እስራኤል ለምን በምርኮ እንደተወሰዱ እንመለከታለን። ከዚያ በኋላ በዳንኤል ጊዜ ኃያላን ስለነበሩ ጥቂት መንግሥታት በመጠኑ እንመለከታለን። የትንቢተ ዳንኤል ታሪክ ከጥንቱ ዓለም ታሪክ ጋር የተሳሰረ ነው።

## ክፍል አንድ:- የእስረኤል ሕዝብ ታሪክ

1ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 1:1-4 አንብብ።
ሀ. የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ምን ሆነ?
ለ. ከእግዚአብሔር ሕዝቦች አንዳንዶቹ ወዴት አገር ተወሰዱ?

የዳንኤልን መጽሐፍ ስንገልጥ:- ኢዮአቄም የተባለውን የአይሁድ ንጉሥ የባቢሎኑ ንጉሥ ናቡከደነፆር እንዳማረከው እናነባለን። የአይሁድን ንጉሥ በናቡከደነፆር እጅ አሳልፎ የሰጠውም እግዚአብሔር ራሱ እንደነበር እናነባለን። ከእምልኮ ዕቃዎች ጥቂቶቹ ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተወስደው በባቢሎናውያን የጣዖት ቤተ መቅደስ ውስጥ እንደተቀመጡ እናነባለን።

ለመሆኑ ኢዮአቄም ማነው? ይሁዳ የምንለው ምንድነው? ባቢሎንስ የምንለው ምንድነው? ናቡከደነፆርስ ማነው? ለምንድነው እግዚአብሔር በቀጣ አይሁድን ለናቡከደነፆር አሳልፎ የሰጠው? የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንዲፈርስ÷ በውስጡ የነበረውም ሀብት ተወስዶ በአሕዛብ ጣዖት ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገበት ምክንያት ምንድነው? የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ እስካላወቅን አብዛኛው የዳንኤል መጽሐፍም ሆነ አብዛኛው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ምስጢር ይሆንብናል። ስለዚህም የዳንኤል ጥናታችንን የምንጀምረው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ በማጥናት ይሆናል። እነዚህም የእስረኤል ሕዝብ÷ የአብርሃም ዘሮች ናቸው።

2ኛ ጥያቄ:- ዘፍ.11:27-12:9 አንብብ።
ሀ. በመጀመሪያ የአብራም ቤተሰቦች የሚኖሩት የት ነበር?
ለ. ከዚያስ ወዴት ሄዱ?
ሐ. ቤተሰቦቹን ትቶ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲሄድ ለአብራም የነገረው ማነው?
መ. ከታዘዘ ምን እንደሚሆን ተስፋ ተሰጠው?

አብዛኛው ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ማለትም የእስረኤላውያን ታሪክ ነው። እስረኤላውያን የዘር ሐረጋቸው ከአብርሃም የሚጀምር እንደሆነ ይናገራሉ። አብርሃም ታራ ከሚባል አባቱ ጋር በዑር ይኖር ነበር። እግዚአብሔር አብርሃምንና ታራን ከነዓን ወደምትባል ክፉ ወደሆነችና ወደላደገቾ ምድር እንዲሄዱ ነገራቸው። ከዑር ተነሥቶ ከነዓን ለመድረስ ብዙ ወር ይፈጅ ነበር። ትንሽ ጊዜ ግን በካራን ተቀመጡ። ካራን በከነዓን መንገድ ላይ ያለች ከተማ ነች። ታራ ከሞተ በኋላ ከነበረበት ሥፍራ ተነሥቶ እንዲሄድ እግዚአብሔር እንዳገና ለአብርሃም ተናገረው፤ ወዴት መሄድ እንዳለበት ግን አልነገረውም። እግዚአብሔር ለአብርሃም ሦስት ዋና ዋና ተስፋዎችን ሰጥቶታል።

1. በግል ሕይወቱ እንደሚባርከው ተስፋ ሰጠው።
2. የአብርሃምን ዘር ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጠው።
3. በአብርሃም አማካይነት ዓለምን ሁሉ እንደሚባርክ እግዚአብሔር ቃል ገብቶለታል። አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ካለበት ተነሥቶ ሄደ። አብርሃም በከነዓን ቢኖርም ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ይዘዋወር ነበር፤ ቤትም አልነበረውም።

ይህ ከሆነ ብዙ ዓመት አለፈ። አብርሃም ይስሐቅን፥ ይስሐቅ ያዕቆብን፥ በኋላ እስራኤል የተባለው ያዕቆብ ደግሞ አሥራ ሁለት ልጆችን በመውለዱ የአብርሃም ዘሮች መባዛት ጀመሩ። የያዕቆብ አሥራ ሁለት ልጆች በግብፅ ለመኖር ሄዱ። ከ400 ዓመት በኋላ የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሆነ። ችግራቸው የግብፃውያን ባሪያ መሆናቸው ነበር። በሙሴ መሪነት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባርነት አውጥቶ የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ሰጣቸው።

3ኛ ጥያቄ:- ዘፀ.19:3-6 እና ኢሳ.49:1-7 አንብብ።
ሀ. እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የመረጠው ለምንድነው?
ለ. እግዚአብሔር የሚያስበው ለእስራኤላውያን ብቻ ነበር ወይስ ለሌላውም ሕዝብ ጭምር?

4ኛ ጥያቄ:- 1ጴጥ.2:9-10 አንብብ።
ሀ. ጴጥሮስ ምን በማለት ይጠራናል?
ለ. ከእስራኤላውያን ጋር የምንመሳሰለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ልዩ ሕዝብ እንዲሆኑ ጠራቸው። እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ቃል ኪዳን ያደረገው በሲና ተራራ ነበር። ቃል ኪዳኑ እውነተኛውን አምላክ እንዲከተሉ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት በመረመድ ልዩ በረከትን ከእርሱ እንደሚያገኙ ነገራቸው። እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው በጨለማው ዓለም ውስጥ ብርሃን ሆነው አሕዛብን ወደ እውነተኛው አምላክ እንዲያመጡ ነበር። እስራኤላውያንን:- «የካህናት መንግና ቅዱስ ሕዝብ» በማለት የጠራቸውም ለዚህ ነበር፤ እስራኤላውያን የቃል ኪዳን ሕዝብ ነበሩ። ይሁን እንጂ ለቃል ኪዳኑ ካልታዘዙ እንደሚቀጣቸው አስጠንቅቆአቸው ነበር። ለቃል ኪዳኑ መታዘዝ በረከትን ሲያመጣ፥ ለቃል ኪዳኑ አለመታዘዝ ደግሞ ቅጣትን ያመጣል።

እኛም ለዓለም ብርሃን መሆን አለብን። እኛም ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ የምንጠራ ካህናት መሆን አለብን። ቅዱሳንም መሆን አለብን። በእርግጥ ነን? ለእግዚአብሔር የምንታዘዝ ከሆነ ይባርከናል። የማንታዘዝ ከሆነ ግን እንቀጣለን።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን ሰጣቸው።

እነርሱ ግን ለእግዚአብሔር አልታዘዙም። በከነዓን የነበሩትን መጥፎ ሕዝቦች አላጠፉዋቸውም፤ (መሳፍንት 2:1-23)። ወደያውኑ ሌሎችን አማልክት አመለኩ፥ ከከነዓናውያንም ጋር ተጋቡ። ስለዚህም «ቅዱስ ሕዝብ» መሆናቸው ቀረ።

ያለመሪ ብዙ የመከራ ዓመታት ካሳለፉ በኋላ ሳዖል የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን ተመረጠ። እርሱም ቢሆን እግዚአብሔርን አልተከተለም፤ (1ሳሙ.13:13-14)። እግዚአብሔር እርሱን ከተወው በኋላ ዳዊትን መረጠ፤ ዳዊት እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው ነበር። ዳዊት በፍጹም ልቡ እግዚአብሔርን ተከተለ፤ (1ሳሙ.16:6-13)። የእስራኤልን ሕዝብ በመምራት ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ አደረገ። እርሱና ልጁ ሰሎሞን ግዛታቸውን ከግብፅ ወንዝ እንሥቶ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ አስፋፉ።

5ኛ ጥያቄ:- በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን የእስራኤል ድንበር ምን ያህል ሰፊ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ ያለውን ካርታ ተመልከት።

በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን እስራኤላውያን ዝነኞች ሆኑ። እግዚአብሔርን ተከተሉ፥ በኢየሩሳሌምም ትልቅ ቤተ መቅደስ ሠሩለት። በጣም ባለጸጎች ሆኑ፤ ሌሎች መንግሥታት ሁሉ ያከብሩዋቸው ነበር። እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ቅዱስ ሕዝብ ሆኑ። ስለ ሰሎሞን አምላክ ክብር ለማየት/ለማወቅ/ ንግሥት ሳባ እንኳ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ነበር።

ይሁን እንጂ የእስራኤላውያን ታላቅነት ለረጅም ጊዜ አልቆየም። በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ሰሎሞን ብዙ የማያምኑ ሴቶችን አገባ። ልቡን ከእግዚአብሔር እንዲርቅ አደረጉት። እንደገናም በይሁዳ የጣዖት አምልኮ ተጀመረ። (1ነገ.11:1-6፤ 26-40፥ 12:1-33።) ከዚያም በኋላ ሕዝቡ በሰሎሞን ላይ ማመፅ ጀመረ። እግዚአብሔርም ቅዱስ የነበረው ሕዝብ እንደሚከፋፈል ተነበየ። ከአሥረ ሁለቱ ነገድ አሥሩ ኢዮርብዓም የሚባለውን ሰው ተከተሉ። የእስራኤል ሕዝብ/ብሔረሰብ/ የተባሉትም ያን ጊዜ ነበር። ሁለት ነገድ ማለትም ይሁዳና ብንያም ብቻ ሮብዓም የተባለውን የሰሎሞን ልጅ ተከተሉ። እነርሱ ደግሞ የይሁዳ ሕዝብ /ብሔረሰብ/ ተባሉ። በመጀመሪያ የእስራኤልን ሕዝብ በቁጥጥሩ ሥር ካዋለ በኋላ ኢዮርብዓም ጣዖት እንዲያመልኩ አደረጋቸው። በእስራኤል ውስጥ እውነተኛውን አምላክ ማምለክ ወደያውኑ ተረሳ።

ሰሎሞን ከሞተ በኋላ በእስራኤል ላይ 20 ነገሥታት ነገሡ። የእያንዳንዱን ሕይወት ብናጠና ከእነርሱ አንዱም እንኳ እግዚአብሔርን እንዳልተከተለ እንረዳለን። በምትኩ ሕዝቡ ጣዖትን እንዲያመልኩ ያበረታቱ ነበር። ሕዝቡ ከእግዚአብሔር እየራቁ እየራቁ ሄዱ። ከእርሱ

በመረፋቸውም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ቀጣቸው። ወደ እርሱ እንዲመለሱ ብዙ ነቢያቶችን ቢልክባቸውም እነርሱ አልሰሙዋቸውም። ስለዚህም እግዚአብሔር በ722 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሰሜናዊውን የእስራኤል ሕዝብ ለአሦራውያን አሳልፎ ሰጠ። አሦራውያን በምርኮኝነት ወሰዱዋቸው። በዓለም ውስጥ በሚገኙ በበዙ አገሮች ውስጥ በታተኗቸው። ሰሜናዊው የእስራኤል ሕዝብ ከዚያ ወዲህ ወደ አገረቸው አልተመለሱም።

## ሁለተኛ ቀን

የእስራኤል ሕዝብ ከሁለት ወገን መከፈላቸውን ትናንትና ተመልክተናል። ሰሜናዊው ግዛት እስራኤል ሲባል፥ ዋና ከተማውም ሰማርያ ነበር። በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ሰሜናዊው ግዛት ሰማርያ በመባል የሚታወቀውም በዚህ ምክንያት ነው። ዋና ከተማው በኢየሩሳሌም የሆነው ደቡባዊው መንግሥት የሚመረው በይሁዳ ነገድ በመሆኑ ይሁዳ ተባለ።

የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ አሥራ ዘጠኝ የዳዊት ዘሮች በይሁዳ ገዝተዋል። ብዙዎቹ እንደ ዳዊት ጌታን የሚወዱ አልነበሩም። አንዳንዶቹም የጣዖትን አምልኮ በይሁዳ አስፋፉ። ንስሐ እንዲገቡ እግዚአብሔር ነቢያትን ላከባቸው፤ እነርሱ ግን ከበደላቸው አልተመለሱም። በመጨረሻም በ586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ይሁዳ በባቢሎናውያን ተደመሰሰች። በምርኮኝነት የተወሰዱት ለ70 ዓመት ነበር። ከ70 ዓመት በኋላ ግን ፈቃደኛ የሆኑት ወደ ይሁዳ እንዲመለሱ ተደረገ።

6ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር ለምን ሕዝቡን ለምርኮ አሳልፎ እንደሰጣቸው ለመረዳት የሚከተሉትን ክፍሎች አንብብ። ኢሳ.24:1-6፤ ኤር.34:12-22፤ 2ዜና 28:2-5 እና ኤር. 44:20-23። ይሁዳ ለምን እንደተማረከች አንዳንድ ነጥቦችን ዘርዝር።

ይህ ምርኮ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚቀጣበት/ለጸቀ መዛሙርትነት የሚያጣረበት/ መንገድ ነበር። እስራኤላውያን የበደሉት በሦስት ዋና ዋና መንገዶች ነበር። በመጀመሪያ በሲና ተራራ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አፈረሱ። ይህን በማድረጋቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አቃለለዋል። ሁለተኛ ሰንበትን ወይም የኢዮቤልዩ ዓመትን አላከበሩም። ሦስተኛ የሐሰት አማልክትን አመለኩ። እግዚአብሔር ይሁዳውያንን ጣዖት አምላኪና በዓለም ካሉት አገሮች ሁሉ እጅግ ዓመፀኛ ወደ ሆነችው አገር ወደ ባቢሎን እንዲጋዙ አደረገ። ከባቢሎን ከወጡ በኋላ ግን ጣዖታትን አላመለኩም።

ዳንኤል የተወለደው በታላቁ የይሁዳ ንጉሥ በኢዮስያስ ዘመን ነበር።

ንጉሥ ኢዮስያስ የነገሠው የ8 ዓመት ልጅ እያለ ነበር። ከነገሠ በኋላ ሕዝቡ ከጣዖት አምልኮ ርቀው እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልኩ አደረገ። የሙሴ መጽሐፍ እንኳን ተገኝቶ ለሕዝቡ እንዲነበብለት ተደርጓል። (2ዜና 34:8-18)

ታላቁ መንፈሳዊ መነቃቃት በምድሪቱ ውስጥ በመስፋፋት ላይ እያለ ሕዝቡ ፖለቲካን በሚመለከት ነፃ መሆንን ፈለገ። ስለዚህም አሦራውያን የሚኑባቸውን ቀንበር ሁሉ ሰባብረው ጣሉ። ብዙ ጣዖታት ተሰባበሩ፤ የጣዖት አምልኮም እንደ ወንጀል ተቆጠረ።

በኢዮስያስ ዘመን ኤርምያስ ትንቢት መናገር ጀመረ። በምድሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ተስፋፋ። ለወደፊትም ሁሉ ነገር ተስፋ ያለው መስሎ ታየ። ነገር ግን በሞኝነት ተነሣስቶ ኢዮስያስ ግብፃውያንን ተዋጋ፤ በጦርነቱም ከቆሰለ በኋላ በኢየሩሳሌም ሞተ፤ (2ነገ.23:29-30)። እግዚአብሔርን በጣም የሚወድ ንጉሥ በመሞቱ ዳንኤል፥ ኤርምያስና ሌሎቹም የእግዚአብሔር ሰዎች የተሰማቸውን ሐዘን ልትገምት ትችላለህ።

ኢዮስያስ ከሞተ በኋላ ወዲያውኑ ሁኔታዎች ሁሉ መባባስ ጀመሩ። ቀጥሎ የተነሣው ንጉሥ ኢዮአክስ በምርኮኝነት ወደ ግብፅ ተወሰደ፤ በእርሱም ፈንታ ኢዮአቄም ነገሠ። የተጀመረው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ተቋረጠ፤ ሕዝቡ ወደ ቀድሞ መንገዳቸው ተመለሱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ባቢሎናውያን ከተማውን ወረሩ። ዳንኤልና ሌሎች የነገሥታት ዘሮች ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። ዳንኤል በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል እየተማረ በማደጉ እግዚአብሔር የተወውና የረሳው ሊመስለው ይችል ነበር። አሁን ያለው ጣዖታትን በሚያመልኩበት አገር ውስጥ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምረው አላገኘም። ለዳንኤል፥ ለጓደኞቹና ለጠቅላላው ለይሁዳ ሰዎች ምን ዓይነት የጨለማ ዘመን እንደነበር መገመት አያዳግትም።

እንደ እስራኤላውያን ቅዱስ እንድትሆን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ጠርቶአል። ክርስቲያኖች በምድር ላይ እርሱን የሚወክሉ ሕዝቦች ናቸው። ከማያምኑ ሰዎች ጋር ትልቅ ልዩነት ሊኖራቸው ይገባል። ይህም ልዩነት የማያምኑትን ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እስኪስባቸው ድረስ ሊሆን ይገባል። ብዙ ጊዜ ግን እንደ እስራኤላውያን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ንፁህ አይደለችም። በኃጢአት በመኖረችንና ከዓለም ጋር በመመሳሰላችን እግዚአብሔር እንደሚገባ ሊጠቀምብን አልቻለም። ስለዚህም ወደ እርሱ እንድንመለስ በማለት ብዙ ጊዜ በእኛ ላይ ይፈርድብናል።

7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሕይወትህ ከእስራኤላውያን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ለ/ ቤተ ክርስቲያንህ ከእስራኤላውያን ጋር የምትመሳሰለው

እንዴት ነው?
ሐ/ «ቅዱስ ሕዝብ» ለመሆን የቀረበላትን ጥሪ አሟልታለችን?

## ክፍል ሁለት:- በእስራኤል ዙሪያ የነበሩ አገሮች

### ሦስተኛ ቀን

እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር በሚጓዙበት ጊዜ አገሪቱን ድል ለማድረግ ከተለያዩ መንግሥታት ጋር መዋጋት ነበረባቸው። ከእነዚህም መንግሥታት ጥቂቶቹን አጠፋዋቸው። ሌሎች ደግሞ ከእስራኤላውያን ጋር ጎን ለጎን ሆነው ይኖሩ ነበር። ከታሪካቸው ለመረዳት እንደሚቻለው ከእነዚህ መንግሥታት የተነሳ እስራኤል የተለያየ ችግር ደርሶባታል። ፍልስጥኤማውያን፥ ኤዶማውያን፥ ሞዓባውያንና አሞናውያን ከእነዚህ መንግሥታት ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህ መንግሥታት ለረጅም ጊዜ ከእስራኤል ጋር ሲዋጉ ነበር፤ የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ጣዖት አምልኮ የመሩዋቸውም እነርሱ ነበሩ።

8ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉት አገሮች የት እንደነበሩ ለማየት በስተጀርባው ከሚገኘው ካርታ ላይ ተመልከት። ግብፅ፥ አሦር፥ ባቢሎን፥ ሜዶንና ፋርስ።

በመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት የእስራኤል ሕዝብ (ይኸውም ሰሜናዊውን የእስራኤልን ግዛትና ደቡባዊውን የይሁዳን ግዛት ያካተተ) ዋነኛውን ሥፍራ ይይዛል። ይህም ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር የሚያመጡ ካህናትና የተመረጡ ሕዝቦች በመሆናቸው ነው። በዓለም ታሪክ ውስጥ አብዛኛው ጊዜ እስራኤል ተራ መንግሥት ነበረች። እስራኤል በጥንት ዘመን ከነበሩት ኃያላን መንግሥታት እንዷ አልነበረችም። በጊዜው የነበሩት ታላላቅ መንግሥታት ግብፅ፥ አሦርና ባቢሎን ነበሩ። በኋላም የፋርስና የሜዶን፥ የግሪክና የሮም መንግሥታት ኃያላን መንግሥታት ሆነዋል።

<u>ግብፅ</u> በጊዜው ከነበሩት ታላላቅ መንግሥታት አንድዋ ነበረች። አብርሃምና ይስሐቅ በነበሩበት ዘመን እንኳ የግብፅ ሥልጣኔ ዝነኛ ነበረ። ግብፃውያን ከሀገራቸው እንሥቶ እስከ ኤፍሬጥስ ወንዝ ድረስ ያሉትን አገሮች ይቆጣጠሩ ነበር። እስራኤላውያን በመንግሥት ደረጃ ከተቋቋሙ በኋላ እንኳ በግብፃውያን ቁጥጥር ሥር ነበሩ።

9ኛ ጥያቄ:- 2ነገ.23:29-30። ሀ/ የይሁዳ ንጉሥ ምን ሆነ?
ለ/ ከማን ጋር ነበር የሚዋጋው?

ከ2000 እስከ 722 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ግብፅ
መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ከፍተኛ ኃይል ነበረት። ምንም እንኳ
ይላቸው ሽልር አልር ዝቅ ወይም ከፍ ቢልም ሌሎችንም መንግሥታት ሁሉ
ቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ነበር። አሦራውያን ግን ግብፅን ድል
ደረጉና ለ75 ዓመት ያህል በዓለም ላይ ገናና መንግሥት ሆኑ።

አሦራውያን በዓለም መንግሥታት ታሪክ ውስጥ ሁለተኛውን ሥፍራ
ዘዋል። የአሦር ኃይል እጅግ ገንና የነበረው ከስምንተኛው እስከ ሰባተኛው
'ዐተ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። አሦራውያንም ሰሜናዊውን
እስራኤል መንግሥት ደመሰሱ። በእስራኤልና ይሁዳ የሚገኙ ብዙ አይሁዶች
ወሰደው በዓለም ሁሉ ተበተኑ። አሦር እጅግ ጨቋኝና ጨካኝ መንግሥት
ለነበረች፥ የእግዚአብሔር ነቢያት አሦርን በመቃወም ትንቢት ተናገረዋል።
ኢሳ.10:5-12፤ ሚክ.5:4-6።)

ባቢሎን ሦስተኛዋ ታላቅ መንግሥት ነበረች። ባቢሎን በጣም ጥንታዊ
'ንግሥት ብትሆንም (ዘፍ.10:10) እስከ 626 ዓመት ከክርስቶስ ልደት
ፊት በከፍተኛ ደረጃ አልተጠናከረችም ነበር። የአሦራውያን ኃይል በደከመ
ጥር ባቢሎናውያን ኃይል እያገኙ መጡ። ባቢሎንን ታላቅ ያደረጋት
ቡከደነፆር የተባለው ንጉሥ ነው። ደካማ የነበረውን መንግሥታቸውን
ጥቂት ዓመታት ውስጥ በዓለም ውስጥ ታላቅ እንዲሆን አድርጓል። በ609
መት ከክርስቶስ ልደት በፊት ባቢሎን አሦርን ድል አደረገችና ተቆጣጠረው
ነበረውን ግዛት በሙሉ ነጠቀቻት። ንጉሥ ናቡከደነፆር ይሁዳንም በቁጥጥሩ
'ር በማድረግ ግዛቱን አስፋፋ። ሦስት ጊዜ ከፍተኛ ጦርነት አድርገው
ይሁዳውያን ተሸነፉ፤ በኋላም በምርኮኝነት ተወሰዱ። በ605 ዓመት
ክርስቶስ ልደት በፊት በተደረገው የመጀመሪያው ጦርነት ነበር ዳንኤልና
ደኞቹ በምርኮ የተወሰዱት። ከሁለተኛው ጦርነት በኋላ ማለትም ከ597
መት ከክርስቶስ ልደት በፊት ንጉሥ ኢዮአኪንና ሌሎች ምሁራን (ሕዝቅኤልን
መሳሰሉ) ወደ ምርኮ ተወሰዱ። በመጨረሻ ማለትም በ586 ዓመት
ክርስቶስ ልደት በፊት የአይሁድ ሕዝብ ተደመሰሱ፤ በሺህ የሚቆጠሩ
ዎችም በምርኮኝነት ተወሰዱ። በሕዝቡ ላይ ስላሳዩት ጭካኔ ባቢሎናውያንን
ንደሚቀጣ እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ተናገረ። (ኢሳ.14:1-23፤
21:1-10፤ 46:1-2፤ ኤር.50-51።) ምንም እንኳ እጅግ ጠንካሬ
ሆኑም ከ70 ዓመት በኋላ ባቢሎናውያን በሜዶንና በፋርስ መንግሥታት
ደመሰሱ። ይህ የሆነው በ539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

ሜዶንና ፋርስ አራተኛው ታላቅ መንግሥት ነበር። በ539 ዓመት
ክርስቶስ ልደት በፊት ባቢሎናውያንን ድል አደረጉ። ከእነርሱ በፊት
ነበሩት አሦራውያንና ባቢሎናውያን ይልቅ የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት
ሕዝቡን በመልካም ሁኔታ ያስተዳድሩ ነበር። በአሦርና በባቢሎን የነበሩትን
ምርኮኞች ወደየሀገራቸው እንዲመለሱና የየግል ሃይማኖታቸውን እንዲከተሉ
ፈቀዱላቸው። በዚህ ጊዜ ነበር አይሁዳውያን ወደ ሀገራቸው ተመልሰው

የፈረሰውን ቤተ መቅደሳቸውን እንደገና የሠሩት። ብሉይ ኪዳን በነህምያና በሚልካይስ መጽሐፍ በተፈፀመ ጊዜ የፋርስ መንግስት በፍልስጥኤም ቁጥጥር ሥር ነበር። በ331 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በታላቁ እስክንድር በሚመራው የግሪክ ሠራዊት ሚደንና ፋርስ ድል ሆኑ።

ዳንኤል የሚኖረው መንግሥታት የበላይነትን ለመያዝ እርስ በርስ ይታገሉ በነበረበት ዘመን ነበር። በስተደቡብ ግብፅ፥ በስተሰሚን ደግሞ አሦር ባቢሎንና ሌሎች መንግሥታት ነበሩ። ፓለስቲና ምን ጊዜም ቢሆን የጦርነት አውድማ ነበረች። እነዚህ መንግሥታት በየጊዜው ትንሽና ደካማ የነበረቸውን እስረኤልን ያጠቁ ነበር። በሰሎሞን ዘመን ለእግዚአብሔር ትታዘዝ ስለነበር በመካከለኛው ምሥረቅ ውስጥ ታላቅ መንግሥት ለመሆን በቃች።

ዳንኤል በቁጥር በጣም ጥቂት ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ይከተሉ በነበሩበት ዘመን ነበር የኖረው። ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን እንደሚከተሉ ቢናገሩም የአሕዛብ ጣዖታትን የማምለክ ፍላጎት ነበረቸው። በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን አይከተሉትም ነበር።

ለብዙ ምዕተ ዓመታት ያህል እግዚአብሔር እስረኤልን ሲጠብቃት ነበር። ብዙ ታገሳቸው። ወደ እርሱ መንገድ እንዲመለሱ በማለትም ነቢያትን ላከላቸው። እነርሱ ግን አልሰሙም። በመጨረሻም እስረኤላውያን በምርኮ እንዲወሰዱ አደረገ። ይሁዳ በእስረኤል ላይ ከደረሰው ቅጣት አልተማረችም፤ ስለዚህም እርሷ ረሷም በምርኮ ተወሰደች።

ዳንኤል እግዚአብሔርን የሚያመልከው ብቻውን ነበር። በንጉሥ ኢዮስያስ ዘመን በትልቅ ደስታ፥ በትልቅ ነፃነት ነበር፤ አሁን ግን ሕዝቡ በግብፅና በባቢሎን ተሸንፈዋል። ባቢሎን ከተማውን በያዘች ጊዜ እርሱ ግን ለከንቱ ተገቶ ጸለየ። እርሱ ረሱም ቢሆን በምርኮኝነት ወደ ሩቅ አገር ተወሰደ። አገሩንና ቤተሰቡን እንደገና የማየት ዕድል ይገጥመው ይሆን? በሚሄድበት አገር እግዚአብሔርን የማምለክ ነፃነት ይኖረው ይሆን? እንዲረዳውስ እግዚአብሔር እዛው ይገኝ ይሆን? ከልጅነቱ ጀምሮ የተማረውን እውነት በምርኮው ምድር ተግባረዊነቱን ይረዳ ይሆን? ዳንኤል እነዚህን ጥያቄዎች እንደሚጠይቅ አያጠረጥርም

10ኛ ጥያቄ:- ሀ/ አሁን የምናየው ዓለምና የዳንኤል ጊዜ በምን ይመሳሰላሉ?
ለ/ የአንተስ ሁኔታ ከዳንኤል ታሪክ ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

ዋና ዋናዎቹን አይሁዳውያን ነቢያት፥ በዳንኤል ትንቢት የተጠቀሱትን ዋና ዋናዎቹን የአሕዛብ መንግሥታት፥ በእነዚህ መንግሥታት ሥልጣን ያገኙትን አንዳንድ ዋና ዋና የአሕዛብ ነገሥታትን ለመመልከት የሚከተለውን ሠንጠረዥ እጥና።

ስእል. 1

| ቀን | የአይሁድ ነብያት/መሪ | የአሕዛብ መንግሥት | የአሕዛብ ንጉሥ |
|---|---|---|---|
| 600 ዓክልበ | ዳንኤል (605-537 ዓክልበ) ሕዝቅኤል (593-571 ዓክልበ) | ባቢሎን (606-539 ዓክልበ) | ናቡከደነፆር |
| | ዘሩባቤል (538 ዓክልበ) | ሜዶንና ፋርስ (539-331 ዓክልበ) | ብልጣሶር (ናቦኒደስ) |
| 500 ዓክልበ | እስቴር (460 ዓክልበ) ዕዝራ (458 ዓክልበ) ነህምያ (444 ዓክልበ) ሚልክያስ (433 ዓክልበ) | | ቂሮስ (ዳርዮስ) አርጤክስስ (አሕሻዊሮስ) |
| 400 ዓክልበ | | | |
| 300 ዓክልበ | | ግሪክ (331-64 ዓክልበ) | ታላቁ እስክንድር |
| 200 ዓክልበ | | | አንጦኪዮስ ኢፒፋንዩስ |
| 100 ዓክልበ | የአይሁዶች ዓመፅ 167-64 ዓክልበ | | |
| 0 ዓክልበ | | ሮም (64-400 ዓ.ም.) | |

አራተኛ ቀን:-

የሳምንቱን ትምህርት ክለሳ አድርግ። ከዛም በየሳምንቱ ስብሰባ ላይ የተነሡትን ጥያቄዎች እንደገና አስተውላቸው። ቡድኑ ሲሰበሰብ የሬስህን መልስ ለመስጠት ተዘጋጅ።

አምስተኛ ቀን:- ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ:- መሪው በዚህ ሳምንት ከተነሡት ጥቅሶች ውስጥ ለሌሎች ተማሪዎች የሚያካፍለው የ5 ወይም የ10 ደቂቃ ውይይት ያድርግ።

2. ጸሎት:- በአንድነት የጸሎት ጊዜ እርስ በርሳችሁ አንዱ ለሌላው የሚጸልይበትና ስለ ቤተ ክርስቲያን የምታስቡበት የ10 ደቂቃ የጸሎት ጊዜ ይኑራችሁ።

3. ክለሳ:- በዚህ ሳምንት የተማርከውን ትምህርት ለ15 ደቂቃ ያህል እንደገና ተመልከተው። መምህር:- ትምህርቱ በደንብ እንዲጠናቀቀና ግብቶት እንዲሆነ ለመረዳት የእያንዳንዱን ተማሪ መልስ ያርሙ። ተማሪዎቹ ከዚህ ትምህርት የተማሩትን ይዘርዝሩ። የቡድን መሪ:- በዚህ ጊዜ በዚህ ሳምንት ትምህርት ላይ አጭር ፈተና ልትሰጣቸው ትችላለህ።

4. ውይይት:- በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ የ25 ደቂቃ ውይይት አድርጉ። እያንዳንዱ ሰው ሐሳቡን በትክክል እንዲያካፍል አድርግ። በጥያቄዎቹ ላይ አስፈላጊ ምሳሌ መስጠትህን እርግጠኛ ሁን።

ሀ/ የእስራኤልን መጠራት ከቤተ ክርስቲያን መጠራት ጋር አነጻፀር።
1. የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
2. ልዩነታቸውስ እንዴት ነው?
3. እስራኤል የተመረጠችው ለምንድነው?
4. እኛስ የተመረጥነው ለምንድነው?

ለ/ የእስራኤልን ታሪክ ክርስቲያኑ ከሚያደርገው መንፈሳዊ ጉዞ ጋር አነጻፀር።
1. የምንመሳሰለው በምን መንገድ ነው?
2. የምንለየውስ በምን መንገድ ነው?

ሐ/ የዳንኤልን ዘመን ከዘመናችን ጋር አነጻፀር።
1. የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
2. ልዩነታቸውስ እንዴት ነው?

5. ጸሎት:- ስብሰባውን በጸሎት ዝጋ። የተማርከውን በተግባር ለማዋል እንዲረዳህ እግዚአብሔርን ጠይቀው።

## ትምህርት ሁለት

## የዳንኤል ትንቢት መሠረት

### የመጀመሪያ ቀን:-

### መግቢያ:- ነቢይ ማለት ምን ማለት ነው?

በዚህ ትምህርት ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን እንመለከታለን። በመጀመሪያ «ነቢይ ምንድነው?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንሞክራለን። እውነተኛውን ነቢይ ከሐሰተኛው ነቢይ እንዴት መለየት እንደምንችልም እንመለከታለን። በሁለተኛ ደረጃ:- ስለ ትንቢት ክርስቲያኖች ያላቸውን የተለያየ አመለካከት እናያለን። የዳንኤልም መጽሐፍ ትርጉም የሚወሰነው በትንቢቶች ላይ ባለን አመለካከት ነው።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ነቢይ ምንድነው?
ለ/ «ነቢይ» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት።
ሐ/ በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ነቢያት ዘርዝር።

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ አምስተኛው የወደፊቱን የሚናገር ትንቢት እንደሆነ ይገመታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘ በመሆኑ ትንቢትን ማጥናት በጣም አስፈላጊ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉት ትንቢቶች ብዙዎቹ በመፈጸማቸው መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ለመሆኑ ክርስቲያኑ የሚያቀርበው ከፍተኛ ማስረጃ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች የተለየ መጽሐፍ ነው፤ ትንቢቶቹም ሌሎች «ትንቢት» እያሉ ከሚጠሩት በፍጹም የተለየ ነው። ሌሎች የተናገሩት ትንቢት አልተፈጸመም። ክርስቶስ በመጀመሪያ ወደዚህ ምድር በመጣበት ጊዜ ከ300 የሚበልጡ ትንቢቶች ተፈጽመዋል። ሌሎቹ ደግሞ ወደ ፊት እንደሚፈጸሙ ይጠበቃል።

2ኛ ጥያቄ:- በብሉይ ኪዳን ተነገረው በአዲስ ኪዳን የተፈጸሙ ጥቂት ትንቢቶችን ዘርዝር። (ማቴ.2:5፤ 3:3፤ ወዘተ።)

ዳንኤል ከብሉይ ኪዳን ታላላቅ ነቢያት አንዱ ነው። ከነበረበት ዘመን አንሥቶ ጌታ ኢየሱስ ዳግመኛ ወደዚህ ምድር እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ የሚኖረውን የዓለም ሁኔታ እግዚአብሔር የገለጸው በዳንኤል አማካይነት ነው። የመጽሐፉ ትንቢቶች እንደሚገባ ተፈጽመዋል፤ የማያምኑ ሰዎች ግን ይህን ከመቀበል ይልቅ «ትንቢቱ የተጻፈው ሁኔታዎቹ ከተፈጸሙ በኋላ ነበር»

እንዲሉ ተገጸዋል። ለዚህም ምክንያታቸው:- የወደፊቱን ሁኔታ እግዚአብሔር ለሰዎች መግለጽ መቻሉን ባለማመናቸው ነው። እኛ ግን አምላካችን ያለፉ ነገሮች አምላክ ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚሆኑትም ነገሮች አምላክ መሆኑን እናውቃለን። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እንኳ ቢሆን በእያንዳንዳችን ሕይወትና በዓለም ላይ የሚሆነውን ሁሉ አስቀድሞ ያውቃል።

ለመሆኑ ነቢይ ምንድነው? ነቢይ:- ከእግዚአብሔር በቀጥታ መልእክትን ተቀብሎ ለሰዎች የሚያስተላልፍ ሰው ነው። በዘመናቸው ላሉ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል አቀባዮች ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለሰዎች ይናገራሉ። ይህም እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። የማስጠንቀቂያ÷ የፍርድና የመጽናናት ቃል ሊሆን ይችላል። ከነቢዩ ትምህርት ውስጥ ስለመጪው ጊዜ የሚያመለክተው ከፊሉ ብቻ ነበር።

3ኛ ጥያቄ:- ከብሉይ ኪዳንና ከአዲስ ኪዳን ነቢያት ጥቂቶቹን ግለጽ። ዘፍ.20:7፤ 1ነገ. 18:36፤ ማቴ. 21:11፤ የሐዋ. 20:10 ተመልከት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዓይነት ነቢያት ተጠቅሰዋል። የመጀመሪያዎቹ÷ ለዘመናቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩ ሲሆኑ÷መልእክታቸውን ግን በጽሑፍ አላሰፈሩም። ምናልባትም ብዙዎቹ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ነቢያት ከዚህ ምድብ ሳይሆኑ አይቀሩም። ነቢያት እንደነበሩ እናነባለን÷ አብዛኛው የተናገሩት ትንቢት ግን በጽሑፍ አልተመዘገበም።

በሁለተኛው ምድብ ያሉት ነቢያት ግን መልእክታቸውን በጽሑፍ ያስተላለፉ ነቢያት ናቸው። ሙሴና ሳሙኤል የረሳቸውን ትንቢት ባይጽፉም መጻሕፍትን ጽፈዋል፤ እስከ ሰሎሞን ሞት ድረስ ግን የሚጽፉ ነቢያት አልተነሡም ነበር። ትንቢቱን በጽሑፍ ያስተላለፈ የመጀመሪያው ነቢይ ኢዩኤል ሲሆን÷ ትንቢት የተናገረውም ከ810-750 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደነበር ይገመታል። በብሉይ ኪዳን መጨረሻ ክፍል ላይ ያሉት ነቢያት የተነሡት ከእርሱ በኋላ ነበር።

4ኛ ጥያቄ:- ከኢሳይያስ ጀምሮ ትንቢታቸውን በጽሑፍ ያሰፈሩ ነቢያትን በዝርዝር ጻፋቸው።

ትንቢታቸውን በጽሑፍ ያስተላለፉ ነቢያት በሦስት ይከፈላሉ። የመጀመሪያዎቹ:- ከምርኮው በፊት ትንቢት የተናገሩ ናቸው። ኢሳይያስ÷ ኤርምያስ÷ ሆሴዕ÷ ኢዩኤልና ሌሎች ነቢያት ከዚህ ምድብ ይገኙበታል። አንዳንዶቹ በእስራኤል ሌሎቹ ደግሞ በይሁዳ ውስጥ ሆነው ነበር የሚተነብዩት። ሁለተኛዎቹ:- በምርኮው ዘመን ትንቢት የተናገሩ ነቢያት ናቸው። እነዚህም:- ዳንኤልና ሕዝቅኤል ናቸው። ሦስተኛዎቹ ደግሞ:- ጥቂት እስራኤላውያን ከምርኮ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ትንቢት

የተናገሩ ነቢያት ናቸው። እነዚህም:- ሐጌ፥ ዘካርያስና ሚልክያስ ናቸው።

5ኛ ጥያቄ:- እውነተኛውን ነቢይና ሐሰተኛውን ነቢይ እንዴት እንለያለን? ዘዳ.13:1-5፤ 18:14-22፤ ሕዝ. 12:21-14:11 ተመልከት።

ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ እውነተኛ ነቢያት ቢኖሩም፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከእውነት ያሳቱ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትም ነበሩ። ስለዚህም እግዚአብሔር ሕዝቡ ሐሰተኛውንና እውነተኛውን ነቢይ ለይተው እንዲያውቁ ጥቂት መመዘኛዎችን ሰጥቶአቸዋል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሐሰተኛ ነቢይ በድንጋይ ተወግሮ ይገደል ነበር።

በመጀመሪያ ደረጃ ነቢዩ የተናገረው ትንቢት በትክክል መፈጸም ነበረበት። እግዚአብሔር እንደማይዋሽ ሁሉ የእርሱን መልእክት የሚናገሩ ነቢያትም ሊዋሹ አይችሉም። የእግዚአብሔርን መልእክት ሲናገሩ ትንቢታቸው በትክክል ይፈጸማል። የሐሰት ነቢያት ግን ምንም እንኳ ጥቂት ትንቢቶቻቸው ቢፈጸሙላቸውም ሙሉ በሙሉ አይፈጸምም። ይህም ከእግዚአብሔር አለመሆናቸውን ያረጋግጣል።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ሐሰተኛ ነቢያት አሉን?
ለ/ ጥቂቶቹን ጥቀስ።
ሐ/ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማሳሳት የሞከሩት እንዴት ነው?

ሰይጣን ለአንዳንድ ሰዎች የወደፊቱን እንዲያውቁ የተወሰነ ችሎታ ይሰጣቸዋል። ትንቢታቸውን በጥንቃቄ ብንከተል ግን ሙሉ በሙሉ እውነት እንዳልሆኑ እናረጋግጣለን።

በሁለተኛ ደረጃ:- ነቢዩ የሚናገረው ትንቢት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት አለበት። እግዚአብሔር ራሱን አይቃረንም። ለአንድ ሰው የሚናገረው ቃል ለሌላው ከሚናገረው ጋር አይጋጭም። የእውነተኛ ነቢይ ቃል እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ከተናገረው ሐሳብ ጋር ይስማማል።

በሦስተኛ ደረጃ:- የነቢዩ ሕይወት ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን መሆን አለበት። የተቀደሰ ሕይወት ሊኖረው ይገባል። እግዚአብሔር በኃጢአት በሚኖር ሰው አማካይነት አይጠቀምም። እውነተኛ ነቢያት በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና ይመላለሳሉ።

7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ቤተ ክርስቲያንህ ስለ ነቢያት ምን ታስተምራለች?
ለ/ በዘመናችን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ ወይስ ትንቢት መናገር በድሮ ዘመን ብቻ የነበረ ነገር ነው?

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትንቢት የሚናገሩ ሰዎች ስለ መኖረቸው ወይም ስላለመኖረቸው ክርስቲያኖች የተለያየ ሐሳብ አላቸው። አንዳንዶች ዛሬም ቢሆን ነቢያት እንዳሉ ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ከተረጸመ ወይም የረሰይ መጽሐፍ ከተጻፈ ወዲህ የትንቢት ስጦታ አቋርጦአል ይላሉ። በዘመናችን ነቢያት ላለመኖረቸውም አንዳንድ ማስረጃ ያቀርባሉ። በመጀመሪያ የሚያቀርቡት ማስረጃ፥ ነቢያትና ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነበሩ የሚል ነው። (ኤፌ.4:11 እና 1ቆሮ.12:28 ተመልከት።) የቤተ ክርስቲያንን መሠረት ተክለው ከሞቱ በኋላ ግን የሚተካቸው አልተነሣም። የረሰይ መጽሐፍ ከተጻፈ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ተፈጽሞአል ይላሉ። በተጻፈው ቃል ላይ መጨመር አስፈላጊ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ልታውቅ የሚገባት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎአል። ለዚህም አባባላቸው፥ 1ቆሮ.13:8-10 እንደማስረጃ ያቀርባሉ። የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅም ቢሆን የብሉይና የአዲስ ኪዳን ነቢያትን የሚመስሉ ነቢያት በዘመናችን ሊኖሩ እንደማይችሉ ያምናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚወዳደር መገለጥን ሊጽፉልን የሚችሉ ነቢያት የሉንም። በእርግጥ አንዳንድ ከእግዚአብሔር ምሪትን በዘመናቸው ላለው ትውልድ የሚሰጡ ነቢያት ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ይህ ምሪት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት አለበት።

8ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ እነርሱ የጻፏቸውን መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እኩል ናቸው የሚሉ ጥቂቶች የሐሰት መምህረንን ጥሪ።
ለ/ የእግዚአብሔር ቃል የተሟላ መሆኑንና ምንም መጨመር እንደሌለብን የምታስረዳቸው እንዴት ነው?

ሁለተኛ ቀን:-

## ክፍል ሁለት:- ትንቢታዊ አመለካከት

የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢቶች ማጥናት ረጅምና በጣም የተወሳሰበ ጥናት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች እንዴት እንደሚረጸሙ ክርስቲያኖች የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንድ ሰው የዳንኤልን ትንቢት ሊረዳ የሚችለውም ካለው አመለካከት አንጻር ነው። ይሁን እንጂ፥ ሁሉም አማኞች የሚስማሙባቸው ቁልፍ ወይም መሠረታዊ ሐሳቦች አሉ።

1. ሰዎች ለዘላለም የሚኖሩባቸው መንግሥተ ሰማያት ወይም ገሃነም የሚባሉ ሥፍራዎች አሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይሄዳሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ግን ወደ ገሃነም ይሄዳሉ። (ማቴ.25:41፤ 46፤ 2ቆሮ.5:1።)

2. በሚያምኑትም ሆነ በማያምኑት፥ ሰዎች ሁሉና እንዲሁም በሰይጣን ላይ ለወደፊት መለኮታዊ የፍርድ ጊዜ ይኖረል።

9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:: ማቴ. 25:41፥ 1ቆሮ.3:13-15 እና ራዕይ 20:11-15::
ለ/ በአማኞች፥ በማያምኑትና በሰይጣን ላይ ስለሚኖረው ፍርድ እነዚህ ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል?

3. የሞቱ ሰዎች ሁሉ ከሞት ይነሣሉ::

10ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ኢዮብ 19:25-27፤ ዳንኤል 12:2 እና ዮሐ. 5:28-29 ተመልከት::
ለ/ ከሞት ስለመነሣት እነዚህ ጥቅሶች ምን ያስተምረሉ?

4. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ይመለሳል::

11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሐዋ/ሥራ 1:11 እና ማቴ.24:21-31 ተመልከት::
ለ/ እነዚህ ጥቅሶች ስለ ኢየሱስ መመለስ ምን ያስተምረሉ?

ምንም እንኳ ክርስቲያኖች ሁሉ ከላይ በተሰጡት ነጥቦች በሙሉ ቢስማሙም፥ እንዴት እንደሚፈጸሙ ግን የተለያየ አመለካከት አላቸው:: በቅደም ተከተላቸውም ላይ የተለያየ ሐሳብ አላቸው::

ትንቢትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ክርስቲያኖች ለምን የተለያየ ሐሳብ እንዳላቸው ከመመልከታችን በፊት፥ ትንቢትን የሚመለከቱ አንዳንድ ገለጻዎችን እንመለከታለን::

1. የታላቁ መከራ ዘመን:- ይህ ዘመን የተገለጸው በራዕይ 7:14 ላይ ነው:: ከዚህ በፊት በዓለም ላይ ታይቶ ስለማይታወቀው የመከራ ዘመን ይናገራል:: ይህ ዘመን የክርስቶስ ተቃዋሚ የሚነሣበትና የሚገዛበት ዘመን ነው:: የእግዚአብሔር ቁጣ በምድር ላይ የሚወርድበት ዘመን ነው:: (ዳንኤል 7:24-25፤ 9:26-27::)

12ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 2ተሰ. 2:1-4 እና ራዕይ 13:1-18 ተመልከት::
ለ/ በዚህ ታላቅ የመከራ ዘመን ስለሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች ዘርዝረህ ጻፍ::

2. የኢየሱስ የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት:- ይህ አጠራር የተገኘው በራዕይ 20:1-10 ውስጥ ነው:: ሰይጣን ስለሚታሠርበት፥ ሙታን ስለሚነሡበትና ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር በምድር ላይ ስለሚነግሡበት አንድ ሺህ ዓመትን ያመለክታል::

3. መነጠቅ:- ይህም አጠራር በ1ኛ ተሰ.4:15-17 ውስጥ የተገኘ ነው:: ለክርስቲያኖች ቢሞቱ እንኳን ኢየሡስ ክርስቶች ሚመለስ ከሞት

እንደሚነሡ የተሠጠ የተስፋ ቃል ነው። በሕይወት ያሉትም ክርስቲያኖች ለዘላለም ከእርሱ ጋር ለመሆን ወደ ክርስቶስ ይነጠቃሉ።

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ መነጠቅ ለክርስቲያኖች የተሰጠ ትልቅ የተስፋ ቃል ኪዳን የሆነው እንዴት ነው?
ለ/ በዚህ ትንቢት እንዴት ልንጽናና እንችላለን?

ስለወደፊቱ ጉዳይ ክርስቲያኖች የተለያየ ሐሳብ የሚያቀርቡበት አንድ ዋና ምክንያት አለ። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ በተለይም በትንቢቶች ላይ ያላቸው የአተረጓጎም ዘዴ ነው። እንደሚታውቀው አብዛኛው የትንቢት ክፍል የተነገረው በምሳሌያዊ አገላለጽ ነው። በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ስለ አንበሳ፥ ድብ፥ ነብር እና ይህ ነው ተብሎ ሊነገር ስለማይቻል አስፈሪ አውሬ ራዕይ ተሰጥቶአል። እነዚህ ወደፊት ስለሚነሡት መንግሥታት የሚያመለክቱ ምሳሌያዊ ገለጻዎች ናቸው። አንዳንድ ክርስቲያኖች አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በተጻፉበት ሁኔታ ሊፈጸሙ እንደማይችሉ ይናገራሉ። ትንቢትን መረዳት ያለብን በምሳሌያዊ ገለጻነቱ ስለሆነ ስውር በሆኑ ትርጓሜዎች ላይ ማተኮር እንደሚኖርብን ያመለክታሉ።

አንዳንዶች ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በቃል መተርጐም እንዳለብንም ይናገራሉ። ስለዚህም ምሳሌያዊ አነጋገር ላይ ማተኮር የለብንም ይላሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እንዲገዛ የዳዊትን ዘሩን እንደሚመሠርት ከተናገረ ያንን ማመን አለብን እንጂ ድብቅ ወይም ስውር ትርጉሙን መመርመር የለብንም።

እነዚህ ሁለት የአመለካከት ዘዴዎች:- የወደፊቱን በሚመለከት ጉዳይ ላይ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ የተለያየ መረዳት እንዲኖር አድርገዋል። ክርስቲያኖች የማይስማሙባቸው ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች አሉ።

አንደኛ:- ክርስቲያኖች እስራኤልና ቤተ ክርስቲያን ስላላቸው ኅብረትና አንድነት አይስማሙም። አንዳንዶች በእስራኤልና በቤተ ክርስቲያን መካከል ምንም ልዩነት አለመኖሩንና ሁለቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሆኑ ይናገራሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል ተብሎ ሲጠራ በአዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን ተብለዋል። ለእስራኤል የተሰጡ ያልተፈጸሙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ሁሉ በመንፈሳዊ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ላይ ይፈጸማሉ። አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔር ሁለት የተለያዩ ግን የተጣመሩ ሕዝብ እንዳሉት ይናገራሉ። በሥጋ ከአይሁድ ዘር የሆኑት እስራኤላውያን ብዙ ገና ያልተፈጸሙ ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተሰጥተዋቸዋል። እነዚህ ትንቢቶች ወደፊት በእስራኤል ላይ ይፈጸማሉ። ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ወደፊት የሚፈጸሙ ትንቢቶች አሉዋት። ለእስራኤል የተሰጡትን ትንቢቶች ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጡዋት ትንቢቶች እንዴት እንደምንለይ አንዳንድ አከራካሪ ሐሳብ ይሰነዘረል።

ሁለተኛ:- ክርስቲያኖች በሺሁ ዓመት የክርስቶስ መንግሥት አተረጓጎም ላይ አይስማሙም።

14ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ራዕይ 20:1-10 አንብብ።
ለ/ ሰይጣን የሚታሠረው ለምን ያህል ጊዜ ነው?
ሐ/ ሺሕ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ምን ይሆናል?
መ/ ይህ ቃል በቃል የሚወሰድ ሺህ ዓመት ነው ወይስ የተለያየ የአተረጓጎም መንገድ ያለ ይመስልሃል?

አንዳንድ ክርስቲያኖች የሺሁን ዓመት ጊዜ እንደ ምሳሌያዊ የጊዜ መለኪያ አድርገው ይቆጥሩታል። ሌሎች ደግሞ ትንቢቶችን እንደ ምሳሌያዊ አነጋገር መውሰድ እንደሌለብን ይገምታሉ። ስለዚህም እግዚአብሔር አንድ ሺህ ዓመት ካለ አንድ ሺህ ነው ይላሉ፤ በተጨማሪም በዚህ በአንድ ሺህ ዓመት ጊዜ ስለ እስራኤል በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተነገሩ ትንቢቶች በሙሉ እንደሚፈጸሙ ያምናሉ።

ሦስተኛ:- የሞቱ ክርስቲያኖች ከሞት ስለሚነሡበትና ወደ ሰማይ ስለሚነጠቁበት ጊዜ የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶች ይህ የሚሆነው ከታላቁ መከራ ዘመን በፊት ነው ይላሉ። አንዳንዶች ይህ የሚሆነው ከታላቁ መከራ ዘመን በኋላ ነው ይላሉ። አንዳንዶች በታላቁ መከራ ዘመን ውስጥ ነው ይላሉ።

15ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 1ተሰ.4:15-17 ተመልከት።
ለ/ ስለ ክርስቲያኖች የተነገሩት ትንቢቶች ምንድናቸው?

እውነተኛ ክርስቲያኖች በንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ የተለያየ አመለካከት ሊኖረቸው እንደሚችል መረዳት አለብን። አንዳንዶች ከእነርሱ የተለየ አመለካከት ካላቸው ክርስቲያኖች ጋር ይከራከራሉ፤ በዚህም ምክንያት እውነተኛ ክርስቲያን መሆናቸውን እንኳ ይጠራጠራሉ። ይህ ግን የእውነተኛ ክርስቲያን ተግባር አይደለም። ጳውሎስ እንደተናገረው ሁሉ:- «ዛሬ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን» (1ቆር. 13:12)። በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ዕውቀታችን የተሟላ አይደለም። ከሌሎች ጋር በማንስማማባቸው ነጥቦች ላይ ሳይሆን በምንስማማባቸው ጉዳዮች ላይ እናተኩር።

## ሦስተኛ ቀን

16ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ትንቢትን በሚመለከት ጉዳይ ላይ የተለያየ ሐሳብ ያላቸውን ቤተ ክርስቲያኖች ወይም ክርስቲያኖች ታውቃለህን?
ለ/ ከየትኛው ቤተ ክርስቲያን ናቸው?

ሐ/ የሚለያዩባቸው ነጥቦች ምንድናቸው?
መ/ ስለ ትንቢት ምን አመለካከት እንዳላቸው የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን አነጋግር።

ትንቢትን በሚመለከት ሁኔታ ክርስቲያኖች ሦስት የተለያየ አመለካከት አላቸው።

1. ክርስቶስ የሚመጣው የሺሁ ዓመት ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ ነው የሚል አመለካከት ነው። ይህ አመለካከት እግዚአብሔር አንድ ሕዝብ ብቻ እንዳለው ነው የሚያሳየው። እነዚህ ሕዝቦች በብሉይ ኪዳን እስራኤል ሲባሉ፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ተብለዋል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጣቸው ተስፋ፥ በመንፈሳዊ ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ላይ ተፈጽመዋል። ስለዚህም ቃል በቃል ለእስራኤል የሚፈጸም ምንም ትንቢት የለም። ወንጌል በዓለም ሁሉ ሲስፋፋ፥ ዓለም በክርስትና ትምህርት ትሞላለች። ክርስቶስ በመጀመሪያ በመጣ ጊዜ የተከላት የእግዚ አብሔር መንግሥት ዓለምን ሁሉ እስከታቅፍ ድረስ ታድጋለች። ለረጅም ጊዜ ሰላም ይኖራል፤ ከዚያ በኋላም ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ይመለሳል። ሁሉም ሰዎች ከሞት ከተነሡና ከተፈረደባቸው በኋላ በፍርዳቸው መሠረት ወደ ገሃነም ወይም ወደ መንግሥተ ሰማያት ይሄዳሉ። ሺህ ዓመት የተባለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን ከዚህ ምድር ካረገበት ጊዜ አንሥቶ ለዘላለም ለመንገሥ እስከሚመለስበት ያለውን ጊዜ ያመለክታል። ከአንደኛውና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት ይህ አመለካከት በጣም የተለመደ ነበር። በፍጥነት በማደግ ላይ የነበረው ክርስትና ለዓለም ሁሉ ስለሚደረስ ሰላም ይሆናል የሚል እምነት ነበረቸው። ከጦርነቱ በኋላ ግን ይህ አስተሳሰብ እንደበፊቱ ብዙ ተቀባይነት የለውም።

17ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ወንጌል ለዓለም ሁሉ የሚደረስበት መንገድ አለን? (ማቴ.24:14 ተመልከት።)
ለ/ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ክርስቲያን ይሆናል ብለህ ታስባለህ?

ቀጥሎ ከላይ የተሰጡትን አስተያየቶች በሠንጠረዥ ትመለከታቸዋለህ። ወደ ጐን የተሰመረው መስመር ጊዜን ወይም ታሪክን እንደሚያመለክት አስተውል። ከፍጥረት ጀምሮ ዘመናት እስከሚፈጸሙበት ድረስ ያለውን ጊዜ ያሳያል።

ስእል 2




2. ቃል በቃል የሚወሰድ የሺህ ዓመት መንግሥት በዚህ ምድር ላይ ሊኖር እንደማይችል የሚሰነዝር አመለካከት። እስከ መጨረሻው ድረስ መልካምም ሆነ ክፉ ሰዎች በዚህ ምድር ሊኖሩ እንደሚችሉ እነዚህ ክርስቲያኖች ያምናሉ። ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ መጥቶ የሚገዛበት የሺህ ዓመት መንግሥት አይኖርም። የሺሁን ዓመት ጊዜ በምሳሌያዊነቱ ነው መረዳት ያለብን። ዛሬም ቢሆን ክርስቶስ የእርሱ በሆኑት ሰዎች ልብና፥ ከዚህ ምድር በሞት ተለይተው ከጌታ ጋር በመንግሥተ ሰማያት ካሉት ቅዱሳን ጋር እየገዛ ነው። በመጨረሻው ዘመን የዚህ ምድር ሁኔታ ይባባሳል። የሐሰት ትምህርት ይስፋፋል። ከዚያ በኋላ ኢየሱስ በታላቅ ክብሩ ይመጣና ጠላቶቹን ይደመስሳቸዋል። ሙታን ይነሣሉ፤ ሁሉም እንደ ሥራው ይፈረድበታል። ከዚያ በኋላ ለዘላለም በመንግሥተ ሰማያት ወይም በገሃነም ለመሆን ይሄዳሉ። እስረኤልና ቤተ ክርስቲያን አንድ በመሆናቸው በብሉይ ኪዳን ለእስረኤል የተሰጣት ተስፋ ሁሉ በመንፈሳዊ ሁኔታ ለቤተ ክርስቲያን ይፈጸማል። ይህ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች አሁንም የሚከተሉት አመለካከት ነው።

ስእል 3



3. ክርስቶስ የሚመለሰው ከሺህ ዓመት መንግሥት በፊት ነው። በምድር ላይ ቃል በቃል የሚወሰድ 1000 ዓመት ይነግሣል የሚል አመለካከ ነው። ይህን አመለካከት የሚከተሉ በፊት እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊ የሰጠውን የተስፋ ቃል እንዳለ ይወስዱታል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ወደፊት ያለምንም ቅድመ ሁኔታዎች የሚፈጸሙ ቃል ኪዳኖችን ሰጥቶአቸዋል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው እቅድ ለቤተ ክርስቲያን ካለው እቅድ በፍጹ የተለየ ነው። እነዚህ ክርስቲያኖች በዚህ ዘመን መጨረሻ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ይመጣላታል ብለው ያምናሉ። ከእርሱ ጋር ለመሆን ክርስቲያኖች ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወሰዱና በእርሱ ይፈረድባቸዋል። በምድር ላይ ግን ታላቅ መከራ ይሆናል፤ በሁሉም ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይወርዳል። ከሰባት ዓመት በኋላ ክርስቶስ ወደ ምድር ይመለሳል፤ የክፋት ኃይላትን ከደመሰሰ በኋላ በምድር ለሺህ ዓመት ይነግሣል። ይህም ጊዜ የታላቅ ሰላምና ብልጽግና ዘመን ይሆናል። በአዳም ምክንያት የደረሰው እርግማን ከተፈጥሮ ሁሉ ላይ ይወገዳል። ክፋት በክርስቶስ ይታገዳል። በሺሑ ዓመት ጊዜ እስራኤል የምትጫወተው ትልቅ ሚና ይኖረታል። ነገር ግን የምትጫወተው ሚና ምን ዓይነት እንደሆነ አከራካሪ ነው። በዚህ ጊዜ ለእስራኤል የተነገረው ተስፋ በአንዳንድ ሁኔታ ይፈጸማል። ከሺሁ ዓመት መንግሥት በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ የተቃውሞ ጦርነት ይደረጋል። ክርስቶስ ግን የክፋትን ኃይሎች ይደመስሳቸዋል። በመጨረሻ ፍርድ ያልዳኑት ሰዎች ወደ ገሃነም ይጣላሉ። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይፈጠራሉ፤ ዘላለማዊነትም ይጀምራል።




በዚህ በመጨረሻው አመለካከት ላይ ሦስት ጥቃቅን ልዩነቶች አሉ። አንዳንዶች ክርስቲያኖች የሚነጠቁት ከታላቁ የመከራ ዘመን በፊት እንደሆ ይናገራሉ። አንዳንዶች ክርስቲያኖች የሚነጠቁት በታላቁ መከራ ዘመን አጋ እንደሆነ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ ክርስቲያኖች በታላቁ መከራ ዘመን ውስ እንደሚያልፉ፥ ከዚያም ወደ ሰማይ እንደሚነጠቁና ከክርስቶስ ጋር በምድ ላይ ለመግዛት እንደሚመለሱ ያመለክታሉ።

በአተረጓጎም ረገድ ሲታይ በሁሉም አመለካከት ችግር የማይረጥር አንድም የለም። ጸሐፊው የቪሁን ዓመት የነገስና ጊዜ እንደተጻፈው አድርጎ ነው የወሰደው። ይህን ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሁሉም ግልጽ ሆና የተዓረ ነገር እንደሆነ ነው የሚያምነው። ስለዚህም እኔ ለዳኔል መጽሐፍ የምሠጠው አተረጓገም ይህን ሦስተኛውን አመለካከት የሚያንፀባርቅ ይሆናል። በምታጠኑበት ጊዜ የኔ አንድ የአተረጓገም ዘዴ እንደሆነ አስተውሉ። ሌሎች ኮሚንታሪዎች (ማብረሪያዎች) ወይም ሠዎች የትንቢተ ዳንኤልን መጽሐፍ በተለየ መልክኩ ማጤንን ይረልት ይሆናል።

ስለ ትንቢት ልናስታውሠው የሚገባን አንድ ሌላ ሀቅ አለ። ብዙ ትንቢቶች ተረዓሚነት አላቸው። በሌላ አነጋገር በቅርብ ጊዜ ከፊላዊ ተረዓሚነት ሊኖር ይችላል። ሙሉ ተረዓሚነቱ ግን ከብዙ አመት በኋላ የሚሆን። ለምሣሌ:- አንጠዮክስ ኢጲፋነስ ስለሚባለው ክፉ መሪ ትንቢት እንደተናገረ በጥናታችን ጊዜ እናያለን። ቢሆንም ይህ ትንቢት ተረዓሚነት የሚኖረው በመጨረሻው ዘመን በሚነሳው አንቲክረይስት በሚባለው ክፉ መሪ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢት ስታጠና ዋናው ጉዳይ:- ለወደፊት እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠረ ስላለህ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ለማብረረት አይደለም። እነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን እንድንረዳ ያስችሉን ይሆናI ይሁን እንጂ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ልናስተውል የሚገባን ጉዳይ አለ። በየትኛውም ሥፍረ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ የወደፊቱን በሚመለከት ጉዳይ ግልጽ የሆነ ሀሳብ አልሰጠም። ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ እንድናውቅ እግዚአብሔር አልፈለገም። ትንቢት የተሰጠው ግን እኛን ዛሬ እንዲያበረታታንና እንዲያጽናናን ነው። ብዙ ጊዜ ትንቢት የተሰጠው በአስቸጋሪ ወቅት ነበር። ዳንኤልና እስራኤላውያን ጓደኞቹ በምርኮ ውስጥ ነበሩ። እግዚአብሔር ለዳንኤል ትንቢትን የሰጠበት ዋናው ምክንያት ሁሉም ነገር በእርሱ ቁጥጥር ሥር እንደሆነ ለዳንኤልና ለእኛ ሊያሳየን ነበር። ምንም እንኳ መሪዎቹ ባያምኑም አሕዛብ በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው። በምድር ላይ ያሉ ኃያላን መንግሥታት በእግዚአብሔር ምሪትና ቁጥጥር ሥር ናቸው። እግዚአብሔር የታሪክ ተቆጣጣሪ ነው። መሪዎችን የሚያነሣም ሆነ የሚጥል እርሱ ነው። የእርሱ በሆኑት ሕዝቦች ላይ የሚደርሰው ነገር ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነው። ስለዚህም ክርስቲያኖች ሆይ ተጽናኑ። ጊዜው ምንም ያህል የጨለመ ሁኔታዎችም እጅግ የከፋ ቢሆኑም እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ መሆኑን አትርሱ።

18ኛ ጥያቄ:- ሀ/ መዝ.2:1-6 እና ዳን.2:20-22 ተመልከት።
ለ/ እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ስላለው ቁጥጥር ምን እንደሆነ ይናገራሉ?
ሐ/ በግል ሕይወትህ ወይም በሀገርህ ላይ እግዚአብሔር

### በሁሉም ሁኔታ ተቆጣጣሪ መሆኑን ያረጋገጥከው እንዴት ነው?

አሁን እግዚአብሔር የሁሉ ነገር የበላይ ተቆጣጣሪ ስለመሆኑና በተለይም ደግሞ የሕይወት ተቆጣጣሪ ስለሆነ ላንድ አፍታ አመስግነው።

<u>አረተኛ ቀን፡-</u>

በዚህ ትምህርት ላይ ክለሳ አድርገህ በሳምንታዊው ስብሰባ ላይ ለሚኖረው ውይይት ዝግጅት አድርግ።

<u>አምስተኛ ቀን፡-</u> <u>ሳምንታዊ ስብሰባ</u>

የቡድኑ መሪ፡- ከትምህርት አንድ ላይ ለሳምንቱ ስብሰባ የተሰጠውን መመሪያ በትክክል መከተልህን አረጋግጥ። ለእያንዳንዱ ክፍል የተወሰነውን ጊዜ መስጠትህን አረጋግጥ።

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ/ 1. ነቢይ ምንድነው?
2. በዘመናችን ነቢያት አሉን?
3. ካሉ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት የሚለዩት እንዴት ነው?
4. የሚመሳሰሉትስ እንዴት ነው?

ለ/ 1. የሐሰት ነቢይ ምንድነው?
2. በዘመናችን የሐሰት ነቢያት አሉን?
3. ምን ዓይነቶች ናቸው?
4. ትንቢታቸው ይፈጸማልን?
5. ሙሉ በሙሉ ትንቢታቸው ሁሌ ይፈጸማልን?
6. እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ነቢይ የምንለየው እንዴት ነው?

ሐ/ 1. የወደፊቱን በሚመለከት ሁኔታ ላይ በቀረቡት ሦስት አስተሳሰቦች ላይ ተወያዩ።
2. አስተሳሰቦቹ የተለያዩ የሆኑት ለምንድነው?
3. የተለያዩት እንዴት ነው?
4. የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
5. አንተ የምትስማማው ከየትኛው አመለካከት ነው?
6. የእንዳንዶቹ አመለካከቶች አደገኛነት እንዴት ነው?
7. ቤተ ክርስቲያንህ የምትከተለው የትኛውን አመለካከት ነው?

መ/ 1. ከትንቢት የምንማረው ዋናውና ጠቃሚው ነገር ምንድነው?

2. ይህ በዘመናችን እንዴት ሊያበረታታን ወይም ሊያጽናናን ይችላል?
3. መጪውን ጊዜ ለመጋረጥ የሚያስችለንን እምነት እንዴት ነው የምናገኘው?

5. ጸሎት።

## ትምህርት ሦስት

## ዳንኤልን መመርመር

### የመጀመሪያ ቀን

በዚህ ሳምንት የዳንኤልን መጽሐፍ በአጠቃላይ እንመለከታለን። ስለ መጽሐፉ ጸሐፊ፥ ስለ ዳንኤል እናጠናለን። ዳንኤል የተጻፈው መቼ እንደሆነም እናጠናለን። በመጨረሻም ጠቅለል ባለ መልኩ መጽሐፉን ከተመለከትን በኋላ የመጽሐፉ ዋና ዋና ትምህርቶች ምን እንደሆኑ ለማየት እንሞክረለን።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ጠቅላላ የዳንኤልን መጽሐፍ አንብብ።
ለ/ በእያንዳንዱ ምዕረፍ ውስጥ ያለው ዋና ትምህርት ምን እንደሆነ አጠር አድርገህ ጻፍ።

### ሁለተኛ ቀን

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ዳንኤል የሚገኘው በየትኛዎቹ ሁለት መጽሐፍቶች መካከል ነው?
ለ/ በነቢያት መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ ተቀምጦአልን?

በአማርኛውም ሆነ በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ዳንኤል የሚገኘው በነቢያት መጻሕፍት መካከል ነው። የሚገኘውም በሕዝቅኤልና በሆሴዕ ትንቢቶች መካከል ነው። ይሁን እንጂ ሁልጊዜ በዚህ ቦታ አልነበረም የሚገኘው። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአንድነት በቅደም ተከተል በተጠረዘበት ዘመን፥ አይሁዳውያን ዳንኤልን ያስቀመጡት ከሌሎች መጽሐሮች ጋር ነበር። እነዚህ መጻሕፍት በነቢያት ተጽፈዋል ተብለው የማይገመቱና ከሙሴ መጻሕፍት ምድብ ያልነበሩ ናቸው። ይሁን እንጂ «በጠቢባን» እንደተጻፉ ስለሚታመን ከመዝሙሮች፥ ከምሳሌዎችና ወዘተ ጋር ተመድቦ ነበር። ምንም እንኳን በዳንኤል ነቢይነት ጥርጥር ባይኖረቸውም እንደ «ጥበበኛ» ቢቆጥሩት መርጠው ነበር።

## ዳንኤል፡- ጸሐፊው

3ኛ ጥያቄ፡- ሀ/ ዳን. 1፡1-6 አንብብ። ዳንኤል ከየትኛው የሕዝብ ወገን ነበር?

ለ/ ወደ ባቢሎን የተወሰደው ለምንድነው?

ሐ/ የዳንኤልን ቤተሰቦች ከተረው ሕዝብ ልዩ የሚያደርጋቸው ነገር ነበርን?

መ/ ዳንኤል በባቢሎን በነበረበት ጊዜ ለልዩ ትምህርት እንዲመርጥ ያደረገው ግላዊ ባሕርያት ምን ነበር?

በ605 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ከአይሁዳውያን ጋር ተዋግቶ ድል አደረጋቸው። ይሁዳን ማሸነፉን ለማሳየት ናቡከደነፆር ሁለት ነገሮችን ወሰደ። በመጀመሪያ፡- የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች ወስዶ፥ በሚያመልካቸው ጣዖታት መቅደስ አኖረቸው። በሁለተኛ ደረጃ ምርጥ ምርጥ ወጣቶችንና አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን ወደ ባቢሎን ይዞአቸው ሄደ። በዚህ ጊዜ ወደ ባቢሎን የተወሰዱት ሰዎች ምን ያህል እንደሆኑ እርግጠኛ አይደለንም። ነገር ግን ከተወሰዱት ወጣቶች አንዱ ዳንኤል ይባል እንደነበር እናውቃለን። ዳንኤል ከአይሁድ ወገን ነበር። ከዚህም በላይ

5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሕዝ.14:14፥ 20፥ 28:3 አንብብ::
ለ/ ዳንኤል ይታወቅባቸው የነበሩት ልዩ ልዩ ባሕርያት ምን ነበሩ?

ሕዝቅኤልና ዳንኤል የኖሩትና የሠሩት በአንድ ዘመን ውስጥ ነበር:: ሁለቱም በባቢሎን የነበሩ ምርኮኛ ነቢያት ናቸው:: ሕዝቅኤል ትንቢቱን ሲጽፍ ዳንኤል በሀገሩ ውስጥ የታወቀ ዝነኛ ሰው ነበር:: በምርኮ ምድር እያለ እንኳ የእግዚአብሔርን ሕግ ይከተል ነበር፤ በጸድቅነቱና በጥበበኛነቱ ይታወቅ ነበር::

የትንቢተ ዳንኤል ጸሐፊ ራሱ ዳንኤል ነው:: (ዳን. 9:2 እና ዳን.10:2):: የትንቢተ ዳንኤል ጸሐፊ ዳንኤል መሆኑንም ክርስቶስ ተናግሮአል፤ (ማቴ.24:15):: አብዛኛውን የመጽሐፉን ክፍል የጻፈው ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም:: መጽሐፉ የተፈጸመው በ537 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው:: ለብዙ ዘመናት ክርስቲያኖችም ሆኑ አይሁዳውያን ዳንኤል በባቢሎናውያን ዘመን የነበረ እውነተኛ ሰውና ጸሐፊ መሆኑን ስያምኑ ኖረዋል:: ሆኖም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ዳንኤል መጽሐፉን እንዳልጻፈው አድርገው ይስባሉ:: ነገር ግን ራሱን ዳንኤል ብሎ የሚጠራ ሌላ ሰው ትንቢቶቹ ከተፈጸሙ በኋላ መጽሐፉን እንደጻፈ ይናገራሉ:: እንደ እነርሱ አነጋገር ይህ ሰው መጽሐፉን የጻፈው ከብዙ መቶ ዓመታት ቀደም ብሎ እንደነበር አድርጐ ነው ያቀረበው ይላሉ:: እነዚህ ሰዎች እንደዚህ በማለት የሚናገሩት ማንም ቢሆን በእንደዚህ ዓይነት ትክክለኛነት የወደፊቱን ትንቢት ለመናገር ይችላል ብለው ባለማመናቸው ነው:: ለእኛ ለክርስቲያኖች ግን ዳንኤል በእርግጥ በሕይወት የነበረ ሰው እንደሆነና ይህንንም ታላቅ ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንደጻፈው የምንጠራጠርበት ምንም ምክንያት የለም::

ዳንኤል:- የትንቢት መጽሐፍ
----

የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት እያጠናን ወደ ዳንኤል ስንመጣ መጽሐፉ ከሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በጣም የተለየ እንደሆነ እንረዳለን:: በውስጡ ታሪክ ቢኖርበትም እንደ 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል የታሪክ መጽሐፍ አይደለም:: መጽሐፉ የትንቢት መጽሐፍ ነው፤ ይሁን እንጂ ትንቢቱን የሚያቀርብበት ሁኔታ ከኢሳይያስና ከኤርምያስ የተለየ ነው:: አንዳንድ ምሁራን ትንቢተ ዳንኤል «አፖካሊፕቲክ ሊትሬቸር» /የወደፊቱን የሚያመለክቱ መጻሕፍት/ ውስጥ የሚመደብ ልዩ መጽሐፍ ነው በማለት ይናገራሉ:: «አፖካሊፕቲክ» ማለት «እውነትን መግለጥ» ማለት ነው:: ይህ ዓይነቱ ሥነ ጽሑፍ ብዙ ጊዜ የሚይዘው እግዚአብሔር በመላእክት በኩል መጪውን ጊዜ የሚገልጽበት ራዕዮችን ነው:: የዚህ ዓይነቱ ሥነ ጽሑፍ እግዚአብሔር ለወደፊቱ በታላላቅ ተአምራቶች በኩል ፍርዶችን እንዴት እንደሚያከናውን ከማሳየቱ ሌላ አንድ ታላቅ የሰላም ዘመን እንደሚመጣም

ይተነብያል። በዘመናት መጨረሻ ዓለም በሙሉ ይለወጣል።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዘካ.8:20-23 እና 14:9-16 አንብብ።
ለ/ እነዚህ ጥቅሶች ከዳንኤል ራዕዮች ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ዘካርያስ በብዙ ሁኔታ ከዳንኤል ጋር ይመሳሰላል። ሁለቱም ስለሚ መጣው ፍርድና ጥፋት ያመለክታሉ። ከዚያ በኋላ ለሰው ልጆች በሙሉ ሰላም ይሆናል። የዮሐንስ ራዕይ እንደ ምሳሌነት ከእንደነዚህ ዓይነት ጽሑፎች ጋር ሊጠቀስ ይችላል። በእርግጥም ዳንኤል፥ ዘካርያስና የዮሐንስ ራዕይ በብዙ ሁኔታ ተመሳሳይ ናቸው። ሦስቱም ስለ ታሪካዊ ክንዋኔዎች ይጀምሩና እግዚአብሔር ስለ ወደፊቱ ያለውን ዕቅድ በረዕይ መልክ ይገልጻሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የዚህ ዓይነቱን የአጻጻፍ ስልት ተከትለው የተጻፉ ብዙ መጻሕፍት ይገኛሉ።

7ኛ ጥያቄ:- አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በምን ቋንቋ ነው?

የዳንኤልን መጽሐፍ ልዩ የሚያደርገው ሌላው ምክንያት በሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች መጻፉ ነው። አብዛኛው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የአይሁድ ቋንቋ በሆነው በዕብራይስጥ ለመጻፉ ያለጥርጣሬ ታውቃላችሁ። ዳንኤል ምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 8-12 በዚህ ቋንቋ ነበር የተጻፉት። ይሁን እንጂ ዳንኤል 2-7 የተጻፈው በአረማይክ ቋንቋ ነው፥ (በሌላም አጠራሩ ካልዲ ይባላል።) ካልዲ ወይም አረማይክ በዳንኤል ዘመን በባቢሎንና በአብዛኛው የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ይጠቀሙበት የነበረ ቋንቋ ነው።

8ኛ ጥያቄ:- የትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 4 ጸሐፊን ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?

ትንቢተ ዳንኤልን ምዕራፍ 4 ልዩ የሚያደርገው በናቡከደነፆር መጻፉ ነው። ናቡከደነፆር ከአሕዛብ ወገን ነው። በእርግጥ በእግዚአብሔር ያመነ ሰው ለመሆኑ እንኳ እርግጠኛ አይደለንም። ይሁን እንጂ በምድር ሁሉ የታወቀ ታላቅ ንጉሥ እንኳ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ያለውን አድናቆት እንዲናገር እግዚአብሔር ይህን ምዕራፍ እንዲጽፍ አድርጎታል።

ሦስተኛ ቀን:- የዳንኤል ዋና ዋና ሐሳቦች

9ኛ ጥያቄ:- የትንቢተ ዳንኤልን ዋና ዋና ሐሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት።

የዳንኤል መጽሐፍ ኀጽረ ሐሳቦችን በተለያየ መንገድ ማስቀመጥ ይቻላል:: ቀጥሎ የምንመለከተው ግን ካሉት የተለያዩ መንገዶች አንዳኛውን ነው::

## ክፍል አንድ:- ታሪካዊ ክንዋኔዎች

1. የዳንኤል መረተንና ወጣቶቹ በት/ቤቱ ውስጥ፤ ዳንኤል 1::
2. ናቡከደነፆር ስለ ታላቁ ምስል ያየው ሕልም፤ ዳንኤል 2::
3. የዳንኤል ጓደኞች በእቶኑ እሳት መረተን፤ ዳንኤል 3::
4. ናቡከደነፆር ስለ ረዥሙ ዛፍ ያየው ሕልም፤ ዳንኤል 4::
5. የብልጣሶር ግብዣና የእግዚአብሔር በግድግዳው መጻፍ፤ ዳንኤል 5::
6. የዳንኤል መረተን÷ የሸማግሌው በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ መጣል፤ ዳንኤል 6::

## ክፍል ሁለት:- ራዕዮች

7. ዳንኤል ስለ አረቱ አረዊት ያየው ራዕይ:: ዳንኤል 7
8. ዳንኤል ስለ አውረው በግ÷ አውረው ፍየልና ታናሹ ቀንድ ያየው ራዕይ:: ዳንኤል 8
9. ዳንኤል ስለ «ሰብዓ ሱባኤ» ያየው ራዕይ:: ዳንኤል 9
10. ዳንኤል ስለ ሰሜን ንጉሥና ስለ ደቡብ ንጉሥ ያየው ራዕይ:: ዳንኤል 10-12

የዳንኤል ጥናታችንን በጥልቀት በቀጠልን ቁጥር እያንዳንዱ ራዕይ ከመጀመሪያው ይልቅ እየተብረረ መምጣቱን እንመለከታለን:: እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር በሰጠው የመጀመሪያው ራዕይ (ምዕረፍ 2) ከዳንኤል ዘመን አንሥቶ የእግዚአብሔር መንግሥት እስከሚመሠረትበት ድረስ በምድር ላይ የሚነሡትን ዋና ዋና መንግሥታት ገልጾለታል:: ዳንኤል ምዕረፍ 7 ደግሞ አረት ዋና ዋና መንግሥታት እንደሚነሱ ይናገረል:: ከአንዱ መንግሥት ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት የሚሻ አንድ ክፉ ሰው እንደሚመጣ ጨምሮ ይናገረል:: በመጨረሻም ምዕረፉ የሚደመደመው በእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት መመሥረት ነው:: ምዕረፍ 8 በሁለቱ መንግሥታት መካከል በሚደረገው ውጊያ ላይ ያተኩረል፤ ወደፊት ስለሚነሣውም ክፉ መሪ ገለጻ ይሰጣል:: ምዕረፍ 9 የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች የጀርባ አጥንት ሊባል ይችላል:: ከእስረኤል ልጆች መመለስ አንሥቶ ክርስቶስ እስከሚመጣበት ዘመን ድረስ ያለውን ትክክለኛ ጊዜ ይገልጻል:: በተጨማሪም ስለሚመጣው ክፉ መሪ ይናገረል:: ምዕረፍ አሥረ አንድ ከሚነሡት መንግሥታት ስለ አንዱ ያብረረል፤ ስለሚያደርጉት ጦርነት ከገለጸ በኋላ ስለሚመጣው ክፉ መሪም ጨምሮ ይናገረል::

## የትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ መሪ ሐሳብ

10ኛ ጥያቄ:- ሀ/ እነዚህን ጥቅሶች ተመልከት ዳንኤል 4:25፥ 32፥ 5:21
ለ/ የጥቅሶቹ ዋና ትምህርት ምንድነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ከሚገኙት የተለያዩ መጻህፍት፥ የዳንኤል መጽሐፍ ከሁሉም በበለጠ ሁኔታ እግዚአብሔር በሰዎችም ሆነ በመንግሥታት ላይ ያለውን የበላይነት ምናልባት በግልጽ ያሳይ ይሆናል:: ከእግዚአብሔር የሚበልጥ አንድ መንግሥት የለም:: እንደ ሐሳቡና ፍላጎቱ እግዚአብሔር መሪዎችን ያስነሣል፥ ሲፈልግም ያዋርዳቸዋል::

11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 4:34-35ን ተመልከት::
እነዚህ ጥቅሶች ክርስቲያኖችን በምን ዓይነት መንገድ ሊያበረታቱ ይችላሉ?
ለ/ እነዚህን ጥቅሶች በቃልህ አጥናቸው::

## የትንቢተ ዳንኤል ዐቢይ ትምህርቶች

ከዳንኤል መጽሐፍ የምናገኛቸው ብዙ ትምህርቶች አሉ:: ከእነዚህም ጥቂቶቹ ቀጥሎ ተዘርዝረውልሃል::

1. ምን ጊዜም ቢሆን በእግዚአብሔር ሕዝብና በማያምኑት መካከል ትግል ይኖረል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ግን በእምነታቸው ጸንተው ለመቆምና የቅድስና ኑሮን ለመኖር መወሰን አለባቸው:: (ዳን.1:1-20፤ 6፤ 11:31-35::)

2. ምንም እንኳ የአሕዛብ መንግሥታት በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ቢነሡም እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ ይጠነቀቃል:: (ዳን.3:16-18፤ 6:16፤ 20-23::)

3. እግዚአብሔር ኃያል አምላክ ነው:: አሕዛብን፥ መሪዎቻቸውንና የዓለም ታሪክን ወዘተ ይቆጣጠረል:: (ዳን.2:20-22፤ 4:17፤ 25፤ 32፤ 34-35፤ 5:18-30፤ 6:26-27::)

4. እግዚአብሔር የማያምኑ መንግሥታትን እንኳ ኃይሉን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል:: (ዳን.2:47፤ 4:34-37፤ 6:26-27::)

5. ከማያምኑት መካከል ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር የሚከተሉትን

ያከብረቸዋል። (ዳን.2:48-49፤ 3:30።)

6. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት የሚሞክር ክፉ መሪ ይነሣል። (ዳን.7:24-26፤ 11:36-45።)

7. የዓለምን መንግሥት ሁሉ የሚደመስስ ዘላለማዊ መንግሥት ይመጣል። ይህ መንግሥት ሊጠፋ አይችልም፤ ለዘላለም ይኖራል። (ዳን.2:44፤ 7:9-14)

12ኛ ጥያቄ:- እነዚህ ዐቢይ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖች በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሊያበረታቱ ይችላሉ?

አምላካችን ነግሦአል፤ በሰማያት ላይ ይገዛል፤ በምድርም ላይ ይገዛል። ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ይህን ለመቀበል ቢያስቸግረንም እውነት መሆኑን በእምነት ልንቀበለው እንችላለን። እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ዘላለማዊ መንግሥቱን ይመሠርታል። በጽድቅ ይገዛል። ሁሉም በሰላም ይኖረል።

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ራዕይ 21-22:6 አንብብ።
ለ/ የዚያ ዘላለማዊ መንግሥት አንዳንድ ባሕርዮች ምንድን ናቸው?
ሐ/ እኛ ክርስቲያኖችስ በዚህ እንዴት ነው የምንበረታታው?

14ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት እስቲ ላንድ አፍታ ረጋ ብለህ አስብ።
ለ/ በሕይወታችን ያለውን ችግር ጨምሮ ሁሉም ነገር በእርሱ ቁጥጥር ሥር በመሆኑ እግዚአብሔርን አመስግን።
ሐ/ ለዚያ መንግሥት ተዘጋጅተሃል?
መ/ በእግዚአብሔር ፊት በቅድስና እየተመላለስክ ነው?

<u>አረተኛ ቀን:-</u>

የዚህን ሳምንት ትምህርት ክለሳ አድርግ። የመወያያ ጥያቄዎችንም እንደገና ተመልከታቸው።

<u>አምስተኛ ቀን:-</u> <u>ሳምንታዊ ስብሰባ</u>

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት
3. ትምህርቶቹን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ
   ሀ/ ከዳንኤል ሕይወት የምንማረቸው ትምህርቶች ምንድን ናቸው?
   ለ/ 1. የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ ምንድነው?
      2. በመከራ ውስጥ ስናልፍ ይህ እውነት ሊያጽናናን የሚችለው እንዴት ነው?
   ሐ/ 1. የዳንኤልን ዋና ዋና ትምህርቶች ዘርዝር።
      2. ከእያንዳንዱ ዋና ዋና ትምህርት ምን እንማራለን?
      3. እነዚህን ዋና ዋና ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያንህ በምን ዓይነት መንገድ ማስተማር እንደሚቻል ተወያዩበት።

5. ጸሎት።

## ትምህርት አራት

## ዳንኤል 1

### የመጀመሪያ ቀን

«ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ በልቡ አሰበ።» (ዳን.1:8)

ዳንኤልና ሦስት ጓደኞቹ ማለትም:- አናንያ፥ ሚሳኤልና አዛርያ ተወልደው ያደጉት በእስራኤል አገር ነበር። ከልጅነታቸው ጀምረው የእግዚአብሔርን ቃል ተምረዋል። በጽንገት ግን በማያምኑና አመፀኛ በሆኑት በባቢሎናውያን ተማረኩ። እነርሱ በግልጽ የሚያመልኩት አንዱን እውነተኛ አምላክ ነው። አሁን ግን ጣዖታትን በሚያመልኩ ሰዎች መካከል ናቸው። እንደ ፈለጉ አምላካቸውን ለማምለክ ነፃነት አልነበረቸውም። ዳንኤልና ጓደኞቹ ወደ ባቢሎናውያን ትምህርት ቤት ገቡ፤ የባቢሎናውያንንም የሐሰት ሃይማኖት አስተማሩዋቸው። እግዚአብሔር በየጊዜው የሚቀርብላቸውን እንዳይበሉ የከለከላቸው የምግብ ዓይነት ነበር። ምርጫ ነበረቸው። እውነተኛውን አምላክ ይከተሉ ወይስ እውነተኛውን አምላክ ትተው የባቢሎናውያንን ጣዖታት ይከተሉ?

በዳንኤልና በሦስት ጓደኞቹ ፊት የተደቀነው ውሳኔ በጣም ከባድ ነበር። በባዕድ ምድር በእምነታቸው ጸንተው ይቆማሉ ወይስ የሀገሩን እምነት ይቀበላሉ? ለእምነታቸው ለመሞት ተዘጋጅተዋል ወይስ ከዘላለማዊው ሕይወት ይልቅ ለዚህ ዓለም ጊዜያዊ ደስታ ይሸነፋሉ?

እንደ ዳንኤል ሁሉ እኛም የምንኖረው በማያምኑ ሰዎች መካከል ነው። ምንም እንኳ የተወለድነው በኢትዮጵያ ምድር ቢሆንም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን ከሆነ የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች ነን። (ፊልጵ.3:20 ተመልከት።) በዚህ ምድር ብዙ ጊዜ ብቻችንን ነው የምንቆመው። ብዙ ሰዎችም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አያምኑም። እግዚአብሔርን የሚከተሉትንም ያሳድዷቸዋል። ምዕመናን እውነተኛውን አምላክ እንዳይከተሉ የሐሰት ሃይማኖታቸውንና ትምህርታቸውን ያቀርባሉ። ታዲያ፥ በዚህ መሐከል ጸንተን ለመቆም የምንችለው እንዴት ነው? ምንም እንኳ ብዙዎች ተቃዋሚ ቢሆኑም በእምነታችን እንዴት ጸንተን ለመቆም እንደምንችል ለመረዳት ዳንኤል ምዕራፍ 1 እንመልከት።

አንደኛ:- ዳንኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን ወሰነ። በባዕድ ምድር በቀላሉ እግዚአብሔርን መርሳት እንደሚቻል ዳንኤል አሳምሮ ያውቃል። ለእግዚአብሔር ጸንቶ ለመቆም ከፈለገ ከሌሎች እንደሚለይ ያውቃል። እግዚአብሔርን ከተከተለ በእምነቱ ሊገደል እንደሚችል እንኳ ያውቃል። የንጉሡን ምግብ አልበላም በማለቱ እንኳ ዳንኤል ስለ እምነቱ ሊገደል ይችል ነበር። ዳንኤል ግን ዓይናቸን በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ ሳይሆን በዘላለማዊው ሕይወት ላይ ነበር ያኖረው።

ሁለተኛ:- ዳንኤል ሕይወቱን በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ አኖረ። የአከባቢውን ገጠመኞቹን ሁኔታ በራሱ ጥበብ ለማሻሻል ከመሞከር ይልቅ በእግዚአብሔር ተማመነ። ስለዚህም ዳንኤል በሙሴ ሕግ መጻሕፍት የተፈቀዱትን ምግቦች ብቻ እንዲበላ ፈቃድ ጠየቀ። በእምነቱ ጸፋር ከሆነ እግዚአብሔር እንደሚያከብረው ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር በሕይወቱ ተአምር እንዲያደርግ በድፍረት ለመጠየቅ ደፈረ። ስለዚህም የተቀሩት በሙሉ ሥጋ ሲመገቡ፥ የወይን ጠጅም ሲጠጡ ዳንኤልና ጓደኞቹ ግን ጥረጥሬና ውሃ ነበር የሚመገቡት።

ሦስተኛ:- እግዚአብሔር የዳንኤልን እምነት እንዳከበረ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በሕይወታቸው ተአምር በማድረጉ የንጉሡን ምግብ ከሚመገቡት ይልቅ ጤነኛ ሆነው ተገኙ። በባለሥልጣኖች ፊት ሞገስ ሰጣቸው። «ለእነዚህም ለአራቱ ብላቴኖች እግዚአብሔር በትምህርትና በጥበብ ሁሉ ዕውቀትንና ማስተዋልን ሰጣቸው» (ዳን.1:17)። በከፍተኛ ሥልጣን ላይም አስቀመጣቸው።

በዓለም ላይ ክፋት በበዛበት ዘመን ውስጥ ነው የምንኖረው። ቀላሉ መንገድ ብዙዎች የሚጓዙበትን መንገድ መከተል ነው። ብዙዎችን መከተል ምን ጊዜም ቢሆን ቀላል ነው። ጥሩ ክርስቲያኖች ከሆንን በሌሎች ዘንድ ታዋቂነትን ላናገኝ እንችል ይሆናል። ምንም እንኳ ሕይወታችንን መሥዋዕት እስከማድረግ ደረጃ ቢያደርሰንም እግዚአብሔር በሕይወታችን የመጀመሪያውን ሥፍራ መያዝ አለበት። እኛም ብንሆን ሕይወታችንን እንዳኖረክስ መወሰን አለብን።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 1ጴጥ.3:8-17 አንብብ:: በዚህ ክፍል ጴጥሮስ የሚሰጠን ምክር ከዳንኤል ሕይወት ልምምድ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
ለ/ ክርስቶስ የሕይወታችን ጌታ መሆኑን የምናሳየው እንዴት ነው?
ሐ/ ክርስቲያኖች ዛሬ በምን ዓይነት መንገድ ነው ዳንኤል የደረሰበት ዓይነት ፈተና የሚደርስባቸው?
መ/ ከዳንኤል ሕይወት የምትማሩት ምንድነው?

2ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ምዕራፍ 1ን አንብብ::
ሀ/ ዳንኤል በምርኮኝነት ወደ ባቢሎን በተወሰደበት ዘመን በይሁዳ ይገዛ የነበረው ማነው?
ለ/ ዳንኤልና ጓደኞቹ በትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩት ለምን ያህል ጊዜ ነው?
ሐ/ ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ዳንኤልና ጓደኞቹ ከተቀሩት ተማሪዎች ጋር ሲወዳደሩ እንዴት ሆነው ተገኙ?

<u>ሁለተኛ ቀን</u> <u>ክፍል አንድ:- ዳንኤል 1:1-5</u>

ዳንኤል 1:1-5 በጥንቃቄ ካነበብክ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ:: መልሶቹም ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ:: ይህንን መጽሐፍ ስታጠና በእያንዳንዱ ምዕራፍና ክፍል እንዲሁ አድርግ::

<u>ጥያቄዎች</u>

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል ወደ ምርኮ ሲወሰድ የይሁዳ ንጉሥ የነበረው ማነው?
ለ/ ለምን ያህል ጊዜ ነገሠ?

4ኛ ጥያቄ:- ዳንኤልን ወደ ምርኮ የወሰደው የባቢሎን ንጉሥ ማን ይባላል?

5ኛ ጥያቄ:- የይሁዳን ንጉሥ ለባቢሎን አሳልፎ የሰጠ ማነው?

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን የተወሰደው ሌላ ነገር ምንድነው?
ለ/ እነዚህ ዕቃዎች በባቢሎን ውስጥ የት ነበር የተቀመጡት?
ሐ/ የባቢሎን ንጉሥ ዕቃዎቹን እዚያ ያስቀመጠበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

7ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ዳንኤልን ወደ ትምህርት ቤት ያስገባው ለምን ይመስልሃል?

8ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ከየትኛው ነገድ ነበሩ?

ለ/ ቤተሰባቸውን ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?

9ኛ ጥያቄ:- ዳንኤልና ጓደኞቹ በትምህርት ቤቱ ለመማር እንዲመረጡ ያበቃቸው ልዩ ስጦታቸው ምንድነው?

10ኛ ጥያቄ:- ዳንኤልና ጓደኞቹ በትምህርት ቤት በነበሩበት ጊዜ ይማሩ የነበረው ምንድነው?

11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤልና ጓደኞቹ ለምን ያህል ጊዜ ነው በት/ቤት የቆዩት?

ለ/ ትምህርቱን ከጨረሱ በኋላ ምን ሆኑ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ (ኮሚንታሪ)

ስለዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ማለትም ስለ ዳንኤል ሰፋ ያለ ገለጻ የሚሰጠን በመሆኑ ምዕራፍ አንድ በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው:: ዳንኤል ማነው? ከየት መጣ? ወደ ባቢሎን እንዴት ሄደ? ምን ዓይነት ሰው ነበር? ለእነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የምናገኘው ከምዕራፍ አንድ ነው::

ዳንኤል መጽሐፉን የሚጀምረው እንዴት ወደ ሰናዖር ወይም ወደ ባቢሎን እንደመጣ በመግለጽ ነው:: ሰናዖር የባቢሎን ጥንታዊ ስም ነው:: በዘፍጥረት 11:1-9 እንደምንመለከተው ሰናዖር በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ነገር የሚደረግባት ቦታ ነበረች:: ስለዚህም እግዚአብሔር የሕዝቡን ቋንቋ ደበላለቀው:: ምናልባትም ዳንኤል በዚህ ስም የተጠቀመው የባቢሎንን ምድር ክፋት ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም:: ዳንኤል ወደ ባቢሎን የተወሰደው በ605 ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር:: የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም ይባል ነበር:: በዚያ ዘመን በቅርቡ በባቢሎን ላይ የሚነግሠው ናቡከደነፆር ለውጊያ ወደ ግብፅ እየተጓዘ ነበር:: ወደ ግብፅ በመጓዝ ላይ እያለ ወይም ከግብፅ ሲመለስ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ኢዮአቄምን በቁጥጥሩ ሥር አደረገው:: ናቡከደነፆር በመጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመጣበት ሁኔታ ብዙ የምናውቀው ባይኖረንም ዳንኤል ግን ከተማይቱን እንደከበበ ይናገራል::

12ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 2ነገ.23:24-25:21 አንብብ::

ለ/ በእነዚህ ምዕራፎች የተጠቀሱትን የይሁዳ ነገሥታት ስም ዘርዝር::

ሐ/ እነዚህ ነገሥታት ምን ሆኑ?

መ/ ስንት ጊዜ ነው ባቢሎን ይሁዳን ለመውጋት የመጣችው?

2ነገ.23:24-25:21 ስለ መጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ይናገራል:: በሪርሃ እግዚአብሔር የሚታወቀው የመጨረሻው ንጉሥ ኢዮስያስ ከግብፃውያን ጋር ሲዋጋ ሞተ:: ይህ የሆነው በ609 ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር:: ልጁ ኢዮአካስ በግብፃውያን ተማርኮ ከመወሰዱ በፊት

የነገሠው ለሦስት ወር ብቻ ነው። ኢዮአቄም የሚባል ሌላው የኢዮስያስ ልጅ ነግሦና አሥራ አንድ ዓመት ገዛ። ንጉሥ ይሁን እንጂ በግዛቱ ዘመነ መንግሥት የናቡከደነፆር አሽከር ነበር። ይህም የሆነው ባቢሎንና ግብፅ በተዋጉበት ዘመን በ605 ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደሆነ አያጠራጥርም። ይህም ዳንኤልና ጓደኞቹ ወደ ባቢሎን የተወሰዱበት ጊዜ ሲሆን፥ ኢዮአቄምም ከነገሠ ገና ሦስተኛ ዓመቱ ነበር። በብዙ ሁኔታ የአይሁዳውያን ምርኮ የተጀመረበት ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ በይሁዳና በባቢሎን መካከል ስለተደረገው ትልቅ ጦርነት አልተጠቀሰም። የሚቀጥለው ንጉሥ ዮአኪን በ597 ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት በባቢሎን ላይ አመፀ፤ ጽል ከተደረገ በኋላ ከሌሎች የሀገሪቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ምርኮኛ ሆኖ ወደ ባቢሎን ተወሰደ። የዮአኪን አጐት ሴዴቅያስ የመጨረሻ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። እርሱም በ586 ዓመተ ከክርስቶስ ልደት በፊት በባቢሎን ላይ ስላመፀ ባቢሎናውያን የይሁዳን ከተማ ደመሰሱዋት።

ናቡከደነፆር ይሁዳን ድል እንዳደረገ ዳንኤል አለመናገሩን ማስተዋል አለብን። ዳንኤል:- «ጌታም የይሁዳን ንጉሥ ኢዮአቄምን ... በእጁ (በባቢሎን ንጉሥ) አሳልፎ ሰጠው» ይላል፤ (ዳንኤል 1:2)። ይሁዳ የተሸነፈችው ባቢሎን ኃይለኛ መንግሥት በመሆኑዋ ብቻ ሳይሆን እርሱንና ሕጉን ስለናቁ እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ፈልጎ ነው። ስለዚህም ይሁዳ ስለ ኃጢአትዋ እንድትቀጣ ለባቢሎናውያን አሳልፎ ሰጣት። ይህ እኛ ክርስቲያኖች በጣም ልናስተውለው የሚገባ እውነት ነው። እግዚአብሔር የዓለም ክንዋኔዎችን ሁሉ ይቆጣጠራል። እግዚአብሔር በሕዝቡ የሚደርሰውን ሁሉ ይቆጣጠራል። ዓለም ሊያሸንፈን አይችልም። በእግዚአብሔር ላይ የምናምፅ ከሆነ ግን እንድንቀጣ ለዓለም አሳልፎ ይሰጠናል።

ናቡከደነፆር ወደ ባቢሎን የወሰደው የይሁዳን ታላላቅ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም መቅደስ የነበሩትን የአምልኮ ዕቃዎችንም ጭምር ነበር። ናቡከደነፆር እነዚህን ዕቃዎች ወስዶ በአምልኮ ቤተ መቅደስ ውስጥ አኖራቸው። ናቡከደነፆር ይህን ያደረገበት ምክንያት ነበረው። ይህም ይሁዳንና አምላካቸውን ድል እንዲያደርግ የረዳው የእርሱ አምላክ እንደነበር በማመኑ ነው። ከይሁዳ አምላክ ይልቅ የእርሱ አምላክ ኃያል እንደሆነ አሰበ። ስለዚህም ከይሁዳ አምላክ ቤተ መቅደስ የዘረፋቸውን ዕቃዎች በረሱ ጣዖት በተ መቅደስ ውስጥ አኖረቸው። በጣም የሚያሳዝነው ነገር የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት ሲያደርጉ የእግዚአብሔር ስም መሰደቡ ነው። በኃጢአት ስንወድቅ ወይም ዓለም ያሸነፈን መስሎ ሲታይ የክርስቶስም ስም ይነቀፋል። ይሁዳ በኃጢአቷ መቀጣቷ ብቻ ሳይሆን፥ በመላው ባቢሎን ምድር የእግዚአብሔር ስም ተነቀፏል።

ናቡከደነፆር አንድ እቅድ ነበረው። ከማረካቸው አገሮች የሰበሰባቸውን ዋና ዋና ሰዎች የባቢሎናውያንን ትምህርት እንዲማሩለት ይፈልጋል። ይህም ቋንቋንና የባቢሎናውያን ሥነ ጽሑፍን ይጨምራል።

ከዚህም በተረፈ የባቢሎናውያንንም ሃይማኖት ይማሩ ነበር። የባቢሎናውያንን ትምህርትና ሃይማኖት ካወቁ በኋላ በአማካሪነት ንጉሡን ያገለግሉት ነበር።

«ከለድ» የሚለው ቃል ሁለት ትርጉም አለው። የመጀመሪያው ትርጓሜ የባቢሎንን ሕዝብ ያመለክታል። ከለዳውያን በባቢሎን ውስጥ ሥልጣን የያዙ ነገድ ናቸው። ናቡከደነፆር ራሱ ከለዳዊ ነበር። ከዚህም በተረፈ ይህ ቃል ጠቢባን፥ አስማተኞችና መተተኞች ወዘተ የሚጠሩበት ቃል ነበር። እነዚህ ሰዎች የንጉሥ አማካሪ ነበሩ። (ዳን.2፡2 ተመልከት)። ዳንኤልና ጓደኞቹ የከለዳውያንን ሕዝብ ሃይማኖትና የጠቢባንን ዕውቀት ሁሉ ተማሩ። ከይሁዳ ወደ ባቢሎን የተወሰዱት ብዙ ወጣቶች ቢሆኑም እግዚአብሔር ግን በእነዚህ አራት ወጣቶች ላይ ብቻ ትኩረት እንዲሰጡ አደረገ። እነርሱም ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ነበሩ።

ዳንኤልና ጓደኞቹ ከይሁዳ ነገድ ናቸው። የዳዊት ዘሮችም ናቸው። ይህም ማለት የንጉሥ ወገን ነበሩ ማለት ነው። ስለዚህም በሀገራቸው በነበሩበት ጊዜ ከሁሉ የሚበልጠውን ትምህርት እንደሚማሩ ግልጽ ነው። ይህም ትምህርት የሙሴን ሕግጋትንም ማጥናት ይጨምራል። በተጨማሪም የነበሩትን ሌሎች ትምህርቶችንም ያጠቃልል ነበር። ዳንኤልና ጓደኞቹ «ነውር (ጉድለት) የሌለባቸው» እንደነበሩ ተገልጾአል። ይህም ማለት አካላቸው ሙሉ ነበር ማለት ነው። እንከኖች ወይም ጸንቆሮች አልነበሩም። በአስተሳሰባቸውም ንቁዎች ነበሩ። ማንኛውንም አዲስ ትምህርት ቶሎ የመቀሰም ችሎታ ከእግዚአብሔር ተሰጥቷቸው ነበር። በሀገራቸው በነበሩበት ጊዜ እንደሚገባ ተምረው ነበር። ንጉሡንም ለማገልገል ብቃት ነበረቻው። በአስተዳደር ሥራ ችሎታ፥ ምክር በመስጠት ረገድም ጥበብ ነበረቸው። እግዚአብሔርም ዋናው ባለሥልጣን አስፋኔስ እንዲመርጣቸው አደረገ። አስፋኔስ ጃንደረባ እንደነበር ተገልጾአል። ይህም ማለት «ስልብ» ነበር ወይም የተከበረ «ጨዋ» ሰው ነበር ለማለትም ሊሆን ይችላል። በዚህም ሆነ በዚያ አስፋኔስ በጣም የተከበረ የንጉሥ አማካሪ ነበር። ስለዚህም ተማሪዎችን የመምረጥና ትምህርታቸውንም የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠው ለዚህ ሰው ነበር።

ዳንኤልና ሦስት ጓደኞቹ ለልዩ ትምህርት መመረጣቸውን ተመልክተናል። ስለ ሃይማኖታቸውም ሆነ ስለ ተለያየ ትምህርታቸው ጠቢባኑ የሚሰጧቸውን ሁሉ መማር ነበረባቸው። ሦስት ዓመት ከተማሩ በኋላ በንጉሡ ፊተና ይቀርብላቸዋል። ፊተናውን እንደሚገባ ካለፉ በልዩ አማካሪነት በንጉሡ አደባባይ ያገለግላሉ ማለት ነው።

ኃጢአት በይሁዳ ሰዎች ላይ ቅጣት አመጣባቸው። ምንም እንኳ ዳንኤልና ጓደኞቹ ገና በይሁዳ እያሉ በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን የተከተሉ ቢሆኑም ከሌላው የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መቀጣት ነበረባቸው። ይሁን እንጂ ቅጣቱን የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ነበር። ለቅጣት

ሕዝቡን ለአረማዊ ንጉስ አሳልፎ ሰጠ። የቅጣቱም ዘመን ሰባ ዓመት እንዲሆን ወሰነ። ዳንኤልና ሦስት ጓደኞቹ እንዲማረኩ ቢያደርግም በባቢሎን መንግሥት ውስጥ ለአስተዳደር ሥራ እንዲመረጡ አደረገ። የሚደረገውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይቆጣጠረው ነበር። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በቁጥጥር ላይ ነው። በሕዝቡ ላይ የተለያዩ ችግሮች እንዲደርሱ ይፈቅድ ይሆናል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ለመታነጽ ይሆንላቸዋል። ይህን የሚያደርገው ክርስቲያኖችን ለአቅዱና ለዓላማው ለማዘጋጀት ይሆናል፤ ወይም እምነታቸውን ለመፈተንና ለማጽናትም ነው። ነገር ግን የመከራና የችግራችንን ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ ይወስነዋል፤ ሁኔታዎችን ለጥቅማችንና ለመንግሥቱ የምንበቃ እንድንሆን እንዲያደርጉን ያደርጋቸዋል። የምናመልከው አምላክ ምንኛ አስደናቂ ነው!

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ዕብ.12:5-11፤ ያዕ.1:2-4፤ 1ጴጥ.1:6-7 እና 1ቆሮ.10:13።
ለ/ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚቀጣበት ምክንያት ምን እንደሚናገሩ ዘርዝረህ ጻፍ።
ሐ/ ከዚህ የምንማረው ትምህርት ምንድነው?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 1:6-16

## ጥያቄዎች

14ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከይሁዳ የመጡት አራት ተማሪዎች ስም ማን ማን ይባላል?
ለ/ ለእያንዳንዳቸው የተሰጣቸው አዲስ ስም ምን ነበር?
ሐ/ አዲስ ስም የተሰጣቸው ለምን ይመስልሃል?
15ኛ ጥያቄ:- ራሱን እንዳያረክስ ዳንኤል የወሰዳቸው እርምጃዎች ምንድናቸው?
16ኛ ጥያቄ:- ዳንኤልን ራሱን እንዳያረክስ እግዚአብሔር በምን መንገድ ጠበቀው?
17ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል ለዘበኞቹ አለቃ ያቀረበው ፈተና ምን ነበር?
ለ/ ዳንኤልና ጓደኞቹ ፈተናውን ያለፉት እንዴት ነበር?
ሐ/ ይህ ተአምር ሊሆን የቻለው በምን መልኩ ነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ዳንኤልና ጓደኞቹ ወደ ባቢሎን ትምህርት ቤት በገቡበት ወቅት ነገሮች ሁሉ አዲስ ነበሩ። አዲስ ባሕል መማር ነበረባቸው። አዲስ ቋንቋ

ሃይማኖት ወዘተ መማር ነበረባቸው። ሁኔታዎቹ ሁሉ አዲስና ልዩ መሆናቸውን ለማሳየት ዋናው ሹም ለተማሪዎቹ አዲስ ስም አወጣላቸው።

በአዲስ ወይም በተለየ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ለሰዎች አዲስ ስም መስጠት በብሉይ ኪዳን ዘመን የተለመደ ነበር።

18ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ዘፍ.17:5፤ 41:45፤ አስቴር 2:7።
ለ/ የእነማን ስም እንደተለወጠና አዲስ ስማቸውም ማን እንደተባለ በዝርዝር ጻፍ።

የዳንኤልና የሦስት ጓደኞቹ ስም ራሱን የቻለ ትርጉም ነበረው። ዳንኤልና ጓደኞቹ ከሃይማኖተኛ ቤተሰብ መገኘታቸው የማያጠራጥር ነው። ለልጆቻቸውም እግዚአብሔርን የሚያስከብር ስም የሰጡዋቸው በዚህ ምክንያት ነበር። ዳንኤል ማለት:- እግዚአብሔር ፈረጅ ነው ማለት ነው። ሐናንያ ማለት:- እግዚአብሔር በጸጋ የተሞላ (ባለጸጋ) ነው ማለት ነው። ሚሳኤል ማለት:- እግዚአብሔር የሆነው እርሱ ማነው? ማለት ነው። አዛርያ ማለት:- እግዚአብሔር ይረዳል፤ ማለት ነው።

ዋናው ባለሥልጣን የእነዚህን አራት ወጣቶች ስም የለወጠው እውነተኛውን አምላክ እንዳያከብር ሳይሆን የእርሱን ጣዖታት ስም እንዲያከብር ነበር። የእነዚህን ስሞች ትርጉም እንደሚገባ ማወቅ ባይቻልም ከዋላ ጉዳል እንደሚከተለው ነው። ዳንኤልን ብልጣሶር አለው። ብልጣሶር ማለትም:- ቤል ሕይወቱን ይጠብቀው ማለት ነው። ቤል ከባቢሎናውያን ጣዖታት አንዱ ነው። ሐናንያን ሲድራቅ አለው። ሲድራቅ ማለት:- በአኩ ትእዛዝ ማለት ነው። አኩ:- ባቢሎናውያን የጨረቃ አምላክ የሚሉት ጣዖት ነው። ሚሳኤልን ሚሳቅ አለው። ትርጉሙም:- አኩ ማነው? ማለት ነው። አዛርያንም አብደናጎ አለው። ትርጉሙም:- የኔቦ ባሪያ ማለት ነው። ኔቦ የቤል ልጅ እንደሆነ የሚታመንለት የሌላ ጣዖት ስም ነው።

ዳንኤልና ጓደኞቹ ትምህርት ቤት ከገቡ በኋላ ወዲያውኑ ችግር ገጠማቸው። አመፀ በበዛበት ምድር ሕይወታቸውን እንዴት በቅድስና ለመጠበቅ ይችላሉ? በእውነተኛው አምላክ ላይ ያላቸውን እምነት ይደብቁ ወይስ ለእርሱ በመታዘዛቸው እምነታቸውን ያሳዩ? ብዙዎቻችን ብንሆን ግን እምነታችንን ከመግለጽ ይልቅ የረከሰ ሕይወትን መኖር እንመርጥ ነበር። ዳንኤል ግን ራሱን እንዳያረክስ ወሰነ።

ዳንኤል የሚቀርብለትን ምግብ ላለመመገብ ወሰነ። የሚቀርብለት ንጉሡ የሚበላው ምግብ ነበር። ስለሆነም በጣም ጣፋጭና የሚያስጐመጅ መሆኑ አያጠራጥርም። ታዲያ ዳንኤል ምግቡን እንዳይበላ የወይን ጠጁንም እንዳይጠጣ ለምን ወሰነ? ለዚህ የተለያየ ገለጸ መስጠት ይቻላል።

1. የንጉሡን ምግብ መመገብ ማለት ተመጋቢው በማንኛውም ሁኔታ ለንጉሡ ታማኝ መሆን አለበት ማለት ነው። ይህም:- ንጉሡ የሚያመልከውን ጣዖት ማምለክን ያጠቃልላል። ዳንኤል ግን በመጀመሪያ ደረጃ ታማኝ የሆነው ለእግዚአብሔር ነው እንጂ ለንጉሡ አልነበረም። ምስክርነቱን ስለሚያንጸፍበት አስመስሎ መኖርንም አልፈለገም።

2. ባቢሎናውያን የሚመገቡት አብዛኛው የምግብ ዓይነት በብሉይ ኪዳን ሕግ የተከለከለ በመሆኑ እስራኤላውያን እንደ እርኩስ ይቆጥሩታል።

19ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዘሌዋውያን 11 አንብብ።
ለ/ እስራኤላውያን እንዳይበሉ የተከለከሉት ምግብ ምን ምን እንደነበር ግለጽ።
ሐ/ እነዚህ ሕግጋት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከምታስተምረው ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ በማመፀዋ እስራኤል በምርኮ ተወስዳ ተቀጣች። ይህንን ዳንኤል ያውቃል። ስለዚህም ከሕዝቡ አመፅ ጋር መተባበር አልፈለገም። ንጹሕ ያልሆነውን ምግብ ላለመመገብ ወሰነ።

3. ብዙ ጊዜ ከሥጋው ወይም ከወይን ጠጁ በከፊል ለጣዖት ይሰዉ ነበር። ስለዚህም ሕዝቡ መብሉንና መጠጡን የሰጡን ጣዖቶቹ ናቸው የሚል እምነት ነበረው። ዳንኤል ይህን አይቀበልም። እርሱ ክብርን ሁሉ የሚሰጠው ለእግዚአብሔር እንጂ ለጣዖታት አይደለም። ለጣዖት የተሠዋውን ምግብ ላለመብላት የወሰነውም በዚህ ምክንያት ነበር።

በባዕድ ምድር እንኳ ዳንኤል በእምነቱ ጸንቶ ቆመ። ስለዚህም በምግቡና በወይን ጠጁ ራሱን እንዳያረክስ ይፈቅድለት ዘንድ ባለሥልጣኑን አነጋገረው። ይህ ንጉሡን መናቅ ወይም ማንቋሸሽ ሊመስል ይችላል፤ ይህም ቢሆን ግን ዳንኤል የወሰደው እርምጃ በእምነት የተሞላ ነበር። እግዚአብሔርም ለዳንኤል ሁኔታዎቹን ሁሉ አመቻችቶለት ነበር። በባለሥልጣኑ ፊት ሞገስ እንዲያገኝ እግዚአብሔር ዳንኤልን ረዳው። ቢሆንም ባለሥልጣኑ ዳንኤልና ጓደኞቹ መልካሙን ምግብ እንዳይመገቡ ፈቃድ ለመስጠት ፈርቷል። ለምን? የእነዚህ ወጣቶች መልክ ከሌሎች ይልቅ ከስቶ ወይም ገርጥቶ ከታየ ንጉሡ እንደሚቀጣው ያውቅ ስለነበር ነው።

ስለዚህም ዳንኤል የአረቱን ወጣቶች ትምህርት እንዲከታተል የተሾመውን ሜልዳር የሚባለውን ባለሥልጣን አነጋገረው። ንጉሡን ፊት ለፊት ከመቃወም ይልቅ ዳንኤል አማራጭ ያለውን ሐሳብ አቀረበ። በመጀመሪያ ቀለል ያለ ፈተና እንዲደረግ ጠየቀው። ይኸውም:- እርሱና ጓደኞቹ ለአሥር ቀን ያህል ጥረጥሬና ውሃ ብቻ እንዲመገቡ ነበር። ከአሥር ቀን በኋላ ባለሥልጣኑ የእነዚህን አረት ወጣቶች ፊት ከሌሎች ወጣቶች ጋር ማወዳደር

ነበረበት። ባለሥልጣኑም ይህን ለማድረግ ተስማማ። ከአሥር ቀን በኋላ የእነዚህ አራት ወጣቶች ሁኔታ መልካሙን ምግብ ሲመገቡ ከነበሩት ሌሎች ወጣቶች ይልቅ አምሮ ተገኘ።

ይህ የአሥር ቀን ሙከራ መልካም ውጤት ካላስገኘ የሚያረክስ ምግብ ላለመብላት ያደረገውን ውሳኔ ዳንኤል መተው ነበረበት። ዳንኤል በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆኖ መገኘትን ከልቡ መርጧል። ስለዚህም እንዲያከብረውና ተአምረትን እንዲያደርግለት እግዚአብሔርን ጠየቀ። እግዚአብሔር የተፈጥሮን ሕግ መለወጥ ነበረበት። ከባቢሎናውያን ምርጥ ምግብ ይልቅ አትክልትና ጥረጥሬ የተሻለ ምግብነት እንዲኖረው አደረገ። ስለዚህም እግዚአብሔር የዳንኤልን እምነት አከበረ። ዳንኤልና ጓደኞቹ ከሌሎች ይልቅ ተሻለው የተገኙት በሥጋዊ አቋማቸው ብቻ ሳይሆን በዕውቀትና ችሎታቸውም ጭምር ነበር።

በዚህ ጨለማ ዓለም ስንኖር ራሳችንን እንዳናረክስ አርምጃ የምንወስድበት ሁኔታ ይገጥመናል። በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆነን ለመገኘት መወሰን አለብን። እንደ እነዚህ ዓይነት ውሳኔዎች ግን ሊከብዱን ይችላሉ። ከሌሎች መለየትና ለብቻችን መቆምን ሊጠይቅ ይችላል። ይሁን እንጂ ዳንኤል እንዳደረገው ሁሉ በፍጹም ልባችን በእግዚአብሔር ታምነን፥ በእምነታችን ጸንተን የምንቆምበትን ብርታትና ጥበብ እንዲሰጠን ልንጠይቀው ይገባል።

20ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዛሬ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ሊያረክሱ የሚችሉባቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?
ለ/ ይህንን የሚያደርጉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉን?
ሐ/ ራሳችንን እንዳናረክስ ልናስወግዳቸው የሚገቡን ነገሮች ምንድናቸው?

<u>አራተኛ ቀን:-</u> <u>ክፍል ሦስት:- ዳንኤል 1:17-21</u>

## <u>ጥያቄዎች</u>

21ኛ ጥያቄ:- ሀ/ እግዚአብሔር ለአራቱ ወጣቶች ምን ሰጣቸው?
ለ/ ለዳንኤል የሰጠው ልዩ ስጦታ ምንድነው?

22ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከሦስተኛው ዓመት ፍጻሜ በኋላ አራቱ ወጣቶች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደሩ እንዴት ነበር?
ለ/ ከባቢሎን ጥበበኞች ጋር ሲወዳደሩስ እንዴት ሆነው ተገኙ?

23ኛ ጥያቄ:- ንጉሥ ናቡከደነፆር ከፈተናቸው በኋላ እነዚህ አራት ወጣቶች ምን ሆኑ?

24ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል በመንግሥት ሥራ የቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነበር?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ከዓለም ጋር ተመሳስሎ ከመኖር ይልቅ ዳንኤልና ጓደኞቹ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ለመስጠት ያደረጉትን ውሳኔ ከትናንትናው ትምህርት ተመልክተናል:: እግዚአብሔርም እምነታቸውን አከበረላቸው:: ምንም እንኳን ጥረጥሬና አትክልት ብቻ ቢመገቡም ሙሉ ጤነኛ እንዲሆኑ ረዳቸው:: ልዩ የማስተዋል ችሎታንም ሰጣቸው:: እግዚአብሔር የተለያዩ ዕውቀትና የሥነ ጽሑፍ ችሎታ እንደሰጣቸው እናነባለን:: እነዚህ አራት ወጣቶች የተፈጥሮ ችሎታ እንደነበራቸው አስቀድመን ተመልክተናል:: እንዲመረጡ የማስተዋል (ዳን.1:4):: ችሎታን ማሳየት ነበባቸው፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እምነታቸውን በማክበር በተፈጥሮ ሊኖራቸው ከሚገባው በላይ የሆነ ችሎታ ሰጣቸው:: ለእነዚህ አራት ወጣቶች እግዚአብሔር ልዩ የአእምሮ ችሎታና የአስተዳደር ዕውቀት ሰጥቶአቸው ነበር:: ይህ ባቢሎናውያን ከሚሰጧቸው ዕውቀት በላይ ነበር:: ይህም ደግሞ የሚማሩትን የመረዳትና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማገናዘብ ችሎታ ሁሉ ነበራቸው:: በተለይ ለዳንኤል ልዩ የሆነ ችሎታን ሰጥቶት ነበር፤ ይህም ሕልምንና ራዕይን የመተርጐም ችሎታ ነው:: በዚህ ችሎታው እግዚአብሔር እንዴት እንደተጠቀመበት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንመለከታለን::

25ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:: 1ቆሮ.12:1-11፤ 27-31፤ ኤፌ.4:11-13::
ለ/ በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን የተለያዩ ስጦታዎች ዘርዝር::
ሐ/ እነዚህ ስጦታዎች እንዲሁ የተፈጥሮ ችሎታዎች ናቸው ውይስ በተለይ እግዚአብሔር የሰጠን ልዩ ስጦታዎች?
መ/ እግዚአብሔር የሰጠህ ስጦታ ምን ይመስልሃል?
ሠ/ ይህንን ስጦታህን እንዴት ትጠቀምበታለህ?

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለልጆቹ የተለያዩ ስጦታዎችን እንደሰጣቸው እንመለከታለን:: ምንም እንኳ የተፈጥሮ ችሎታ ቢኖረንም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እግዚአብሔር የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎችንም ይሰጠናል:: እነዚህ ስጦታዎች ማኅበረ ምዕመናንን ለማነጽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንጠቀምባቸው ናቸው:: (ሮሜ 12:6-8፤ 1ጴጥ.4፤10-11 ተመልከት::)

የባቢሎናውያንንና የዓለምን ጥበብ ለሦስት ዓመት ያህል ከተማሩ በኋላ ተማሪዎቹ በሙሉ ለፈተና በናቡከደነፆር ፊት ቀረቡ:: ከሁሉም ተማሪዎች ዳንኤል፥ ሐናንያ፥ ሚሳኤልና አዛርያ በልጠው ተገኙ:: ዳንኤል እንደጻፈልን እነዚህ ወጣቶች ከባቢሎናውያን ጠቢባን፥ አስማተኞችና ሚርተኞች ይልቅ

አሥር እጅ የሚበልጡ ነበሩ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ጸሐፊዎቹ ቁጥርን ለምሳሌያዊ አተረጓጎሙ ይጠቀሙበታል። ብዙዎች እንደሚያምኑበት <አሥር> የፍጹምነት ወይም የሙሉነት ምልክት ነው። ስለዚህም አሥር እጅ በልጠው ተገኙ ሲል፦ ጥበባቸው ፍጹም ወይም የተሟላ ነበር ማለት ነው። ከተቀረው ከባቢሎን ሕዝብ ይልቅ በጥበብ የላቁ ነበሩ።

ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ዳንኤልና ጓደኞቹ ንጉሡን ማገልገል ጀመሩ። አማካሪዎችና አስተዳዳሪዎችም ሆኑ። ሦስቱ ወጣቶች የባቢሎንን መንግሥት ለምን ያህል ጊዜ እንዳገለገሉ እርግጠኛ ባንሆንም ዳንኤል ግን እስከ ንጉሥ ቂሮስ ዘመን ድረስ እንዳገለገለ እናውቃለን። ንጉሥ ቂሮስም የሚዳንና ፋርስ የመጀመሪያ ንጉሥ ነበር። ስለዚህም ዳንኤል ያገለገለው ከ605 - 539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ነበር ማለት ነው። ይህም ለ66 ዓመታት መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ዳንኤል ከዚህ የሚበልጥ ዘመን በሕይወት ኖሮአል፤ (ዳን.10፡1 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ለሁላችንም የአገልግሎት ሥፍራ አለው። ለአንዳንዶች በጣም የተለየ ስጦታ ይሰጣቸውና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ይሆናሉ። በመንግሥት ባለሥልጣኖች መካከል እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር የሪሱ ምርጥ ሰዎች አሉት። እርሱን የምናገለግልበት ልዩ ችሎታንም እግዚአብሔር ሰጥቶናል። ይህን ስጦታ ማኅበረ ምዕመናንን ለማነጽ ልንጠቀምበት ይገባል። እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ በእነዚህ ስጦታዎች በታማኝነት ማገልገል አለብን። እግዚአብሔር የሚጠቀምብን የቅድስና ሕይወት ሲኖረን ብቻ ነው። የዓለምን መንገድ እንዳንከተልና እንዳንረክስ ውሳኔ ማድረግ አለብን። ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጠው እርሱ ለክብሩ ሊጠቀምበት ይችላል።

አምስተኛ ቀን፦

የሳምንቱን ትምህርት ከልስ፤ የመወያያ ጥያቄዎችንም እንደገና ተመልከት።

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ አምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

   ሀ. 1/ በኢትዮጵያ ያሉ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ሊያረክሱ የሚችሉባቸው መንገዶች ምንድናቸው?

   2/ ራሳቸውን ከርኩሰት እንዴት ሊጠብቁ ይችላሉ?

   3/ በጣም የታወቁ ሆነው ግን ራሳቸውን ያረከሱ ክርስቲያኖች

ምሳሌ ስጥ።
4/ ከፍተኛ ኃላፊነት ያላቸው ሬሳቸውን ግን ለማርከስ ያልፈቀዱ ክርስቲያኖችን ጥቀስ።

ለ. 1/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረጉት ሁኔታዎች ሁሉ እግዚአብሔር የበላይ ተቆጣጣሪ መሆኑን የሚያመለክቱህ ምን ምንድን ናቸው?
2/ መንግሥትን፥ ቤተ ክርስቲያንን፥ የተፈጥሮ ኃይላትንና ወዘተ የሚቆጣጠረው እንዴት ነው?

ሐ. ታማኝ ከሆኑለት እግዚአብሔር ሕዝቡን ያከብረቸዋል። በትዮጵያውያ ክርስቲያኖች ታማኝ ስለሆኑለት እግዚአብሔር እንዴት እንዳከበረቸው አንዳንድ ነጥቦችን ጥቀስ።

መ. 1/ እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች የተለያዩ ስጦታዎች ሰጥቶአቸዋል። የምታውቃቸውን ስጦታዎች ሁሉ ዘርዝረህ ጻፍ።
2/ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ስጦታ የሰጠህ ይመስልሃል?
3/ ስጦታዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ትጠቀምባቸዋለህ?
4/ ያሉንን መንፈሳዊ ስጦታዎች የምናውቀው እንዴት ነው?

5. ጸሎት።

## ትምህርት አምስት

## ዳንኤል 2፡1-23

### የመጀመሪያ ቀን

ጥበብና ኃይል ለእርሱ ነውና የእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፤ ጊዜያትንና ዘመናትን ይለውጣል፤ ነገሥታትን ያፈልሣል፤ ነገሥታትንም ያስነሣል፤ ጥበብ ለጠቢባን እውቀትንም ለአስተዋዮች ይሰጣል። የጠለቀውንና የተሰወረውን ይገልጣል፤ በጨለማ ያለውን ያውቃል፤ ብርሃን ከእርሱ ጋር ነው፤ (ዳን.2፡20-22)።

ጸሎት ለክርስትና ሕይወታችን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ብዙ ጊዜ ስንጸልይ አብዛኛውን ጊዜ የምናሳልፈው የተለያዩ ነገሮችን እንዲሰጠን በመለመን ነው። ስለ ጤንነት፥ ስለ ብርታት፥ ስለ ምግብ፥ ስለ ልብስና ስለተለያዩ ነገሮች እንጠይቀዋለን። አንዳንድ ጊዜ ጸሎታችንን ስለመለሰልን እናመሰግነዋለን። ስላደረገልን መልካም ነገር ሁሉ እናመሰግነዋለን። ይሁን እንጂ ስለ ታላቅነቱ እግዚአብሔርን የምናመሰግነው አልፎ አልፎ ነው። ብዙ ጊዜ ጸሎታችን በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ይመስላል። ብዙው ጸሎታችን ልመና ሲሆን ለምስጋና ያለን ጊዜ ግን በጣም ጥቂት ነው። የምናመሰግን

ብንሆን እንኳ የምናመሰግነው ስላደረገልን መልካም ነገር ብቻ ነው። ስለተለያዩ ነገሮች እግዚአብሔርን መጠየቅ መልካም ነው፤ ስለሰጠን ነገር ማመስገን ግን በጣም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ስለ ባሕርዩና ስለማንነቱ እግዚአብሔርን ማመስገን በይበልጥ ያስፈልጋል። በጸሎት ጊዜያችን እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን።

እንዴት መጸለይ እንዳለብን ከዳንኤል ሕይወት ብዙ ነገር ልንማር እንችላለን። በመጀመሪያ:- ዳንኤል ሕይወቱ በአደጋ ውስጥ ሆና ሲጸልይ እናያለን። በባቢሎን የነበሩ ጥበበኞች ሁሉ እንዲገደሉ መታዘዙን ሲሰማ ዳንኤል ፊቱን ለጸሎት ወደ እግዚአብሔር አዞረ። በዚሁ ምስጢራዊ ጉዳዩ ስለተሸበሩ እርሱና ጓደኞቹ ከሰማይ አምላክ ምሕረትን ለመኑ፤ (ዳን.2:18)። ይህ ዓይነቱ ጸሎት «የልመና» ጸሎት ይባላል።

ሁለተኛ:- ጸሎቱ ከተመለሰለት በኋላ ዳንኤል እግዚአብሔርን ሲያመሰግን እንመለከታለን። እግዚአብሔርን ያመሰገነው ጸሎቱን ስለሰማውና የናቡከደነፆርን ሕልም ስለገለጠለት ብቻ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ጭምር ነበር። እግዚአብሔርን ስለ ባሕርዩና ስለ ማንነቱ አመሰገነ። ይህ ዓይነቱ ጸሎት የምስጋና ወይም የአምልኮ ጸሎት ይባላል። እስቲ ዳንኤል እግዚአብሔርን ስላመሰገነባቸው አንዳንድ ነገሮች እንመልከት።

1. ዳንኤል ስለ ጥበቡና ስለ ኃይሉ እግዚአብሔርን አመሰገነ። እግዚአብሔር ሁሉንም ያውቃል። የወደፊቱንም ሆነ ያለፈውን ያውቃል። ጥበቡ ከሰው ጥበብ ይልቅ እጅግ ይበልጣል። ለሰው የተሰወረ ለእግዚአብሔር የተገለጠ ነው።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ቁጥሮች ተመልከት። ኢር.10:12፤ ሮሜ 11:33፤ 1ቆሮ.1:18-30።
ለ/ እነዚህ ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር ጥበብ ምን ያስረዳሉ?

እግዚአብሔር ሁሉን የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን ሁሉን የሚችልም አምላክ ነው። የፈቀደውን ሁሉ ማድረግ ይችላል። በፍጥረታቱ ታላቅነት በመጠኑም ቢሆን የእግዚአብሔርን ኃያልነት እንመለከታለን። በምድር ላይ የሚፈረረቁትን ወቅቶችንና ጊዜዎችን ለመቆጣጠር በመቻሉ ታላቅነቱን መመልከት ይቻላል። ነገሥታትን ያስነሳል፥ ነገሥታትንም ይጥላል፤ ይህም ታላቅነቱን ያሳያል።

2. ዳንኤል እግዚአብሔርን ያመሰገነው ለሚፈልጉ ሁሉ ጥበብን ለመስጠት በመቻሉ ነበር። ለማያምኑ ሰዎች የተሰወሩትን ነገሮች እንኳ እግዚአብሔር ለልጆቹ ይገልጽላቸዋል።

2ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔርን እንድናመሰግን የሚያደርጉን ሌሎች ባሕርያቱ ምንድናቸው? እግዚአብሔርን እንድናመሰግን የሚያደርጉንን ነገሮች ዘርዝረህ በእነርሱ አመስግነው።

ሦስተኛ:- ዳንኤል በየጊዜው ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ይገናኝ እንደነበር እንመለከታለን፤ (ዳን.6:10)። ምንም እንኳ የሀገሩ ሕግ ጸሎትን የሚቃወም ቢሆንም ዳንኤል ግን በቀን ሦስት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር። ሰዎችን በመፍራት ጸሎቱን አላቋረጠም። በምዕራፍ 9:20-27 ያለው ታላቅ ራዕይ የተገለጸለት ዳንኤል በመጾሙና በመጸለዩ ነው።

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳን.9:1-19 አንብብ።
ለ/ ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ ጸሎት ለመማር የምንችለውን አንዳንድ ነጥቦች ግለጽ።
ሐ/ ከዚህ ክፍል የምንመለከታቸው ሌሎች የጸሎት ዓይነቶች ምንድናቸው?

ጸሎት በዳንኤል ሕይወት ከፍተኛ ሥፍራ ነበረው። በችግር ውስጥ እያለ ይጸልይ ነበር። ጸስተኛ ሲሆን ይጸልይ ነበር። እግዚአብሔርን የሚጠይቀው ጥያቄ ሲኖረው ይጸልይ ነበር። መሪዎች ቢቃወሙትም ይጸልይ ነበር። ዳንኤል ታላቅ ኃይል የነበረው ሰው ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር በታላቅ ሁኔታ ተጠቀመበት። ይህን ኃይል ከየት ያገኘው ይመስልሃል? ይህን ኃይል ሊያገኝ የቻለው በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት በመቆየቱ ነው።

4ኛ ጥያቄ:- ሀ/ እግዚአብሔር በሕይወታችን ሲሠራ እንመለከታለን?
ለ/ በየዕለቱ በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት እንቀርባለን?
ሐ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከትና የተለያዩ የጸሎት ዓይነቶችን ዘርዝር። ኤፌ.6:18፤ ፊልጵ.4:6፤ 1ጢሞ.2:1።
መ/ በዚህ ክፍል ያልተጠቀሱ ሌሎች የጸሎት ዓይነቶች ምንድናቸው?
ሠ/ ስለ ትናንትናውና ስለ ዛሬው ጸሎትህ አስብ።
ረ/ የትኞቹን የጸሎት ዓይነቶች ነበር የተጠቀምክባቸው?
ሰ/ በአመዛኙ የተጠቀምከው በየትኛው ጸሎት ነበር?
5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 2:1-23 አንብብ።
ለ/ ናቡከደነፆር በጣም የተረበሸው ለምን ነበር?
ሐ/ ጠቢባኑ እንዲገደሉ ያዘዘው ለምን ነበር?

## ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 2:1-13

### ጥያቄዎች

6ኛ ጥያቄ:- ናቡከደነፆር ይህን ሕልም ያለመው በነገሠ በስንተኛው

ዓመቱ ነበር?

7ኛ ጥያቄ:- ሕልሙን እንዲተረጉሙለት የተጠሩት አራት የተለያዩ ባለሙያዎች ምን ነበሩ?

8ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ባቀረበው ጥያቄ ጠቢባኑ የተናደዱት ለምንድነው?

9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሕልሙን ካልነገሩት ናቡከደነፆር ጠቢባኑን ምን ሊያደርጋቸው ነበር?

ለ/ ሕልሙን ለሚተረጉሙለትስ ምን ዓይነት ሽልማት ነው እሰጣለሁ ያለው?

10ኛ ጥያቄ:- ጠቢባኑ ሕልሙን መተርጐም ይችላል ያሉት ማንን ነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ዳንኤል ምዕራፍ 2 የመጀመሪያውን ታላቅ ትንቢት የያዘ ምዕረፍ ነው። እግዚአብሔር በምድር ላይ ቀጥለው ስለሚነሡት አራት ታላላቅ መንግሥታት በሕልም ለናቡከደነፆር ገለጸለት። በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር በሰዎች መንግሥታት ላይ ያለውን ሥልጣን የበላይነት ያሳያል። አንዱን መንግሥት ኃያል የሚያደርግና ሌላውንም የሚጥል እርሱ ነው።

በ603 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለናቡከደነፆር በጣም ከባድ ዓመት ነበር። ከእርሱ ሥልጣን ሥር ለመሆን አሻፈረኝ ካሉት የተለያዩ መንግሥታት ጋር ሲዋጋ ብዙ ችግር ገጥሞታል። ስለዚህም ከሠራዊቱ ጋር ሆኖ ከተለያዩ መንግሥታት ጋር ለመዋጋት ከወጣ ብዙ ወራቶች አልፈዋል። ናቡከደነፆር ይህን ሕልም ያየው በጣም አስቸጋሪ በነበረ ወቅትና በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ነበር።

ምሁራን የዳንኤል ምዕራፍ 2 ክንውኖች መቼ እንደተፈጸመ ትክክለኛውን ጊዜ ለማስቀመጥ አልቻሉም። ይህም የጥንት ሰዎች ንጉሦቻቸው የነገሡበትን ዘመን የሚቆጥሩበት ሁለት የተለያዩ የጊዜ መቁጠሪያ ስለነበረቸው ነው። ናቡከደነፆር የነገሠው በ605 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። አይሁዳውያንም እንደዳንኤል ማንኛውንም የዓመቱን ክፍል የንግሥና ዓመት አድርገው ይቆጥሩት ነበር። እንግዲህ ዳንኤል የተከተለው የአይሁዳውያንን አቆጣጠር ከሆነ፥ ናቡከደነፆር ሕልሙን ያየበት ዘመን በ604 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር ማለት ነው። ይህም ማለት 605 የመጀመሪያው፥ 604 ሁለተኛው፥ 603 ደግሞ ሦስተኛው የንግሥናው ዓመት መሆኑ ነው። ዳንኤል የተከተለው የባቢሎናውያንን የጊዜ አቆጣጠር ከሆነ:- ናቡከደነፆር የነገሠበትን ዓመት አይቆጥሩትም። ስለዚህም 604 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የመጀመሪያው የነገሠበት ዓመት፥ 603 ሁለተኛው የነገሠበት ዓመት ይሆን ነበር። ዳንኤል የአይሁዶችን የጊዜ አቆጣጠር ከተጠቀመ እሱና ጓደኞቹ ገና በትምህርት ቤት ነበሩ ማለት ነው፥ (ዳንኤል ምዕራፍ 1:5 ተመልከት)።

የተከተለው የባቢሎናውያንን አቆጣጠር ከሆነ ግን ልክ ትምህርታቸውን የጨረሱበት ጊዜ ይሆን ነበር ማለት ነው።

ሌላው ስለ ዳንኤል ምዕራፍ 2 መረዳት የሚኖርብን ደግሞ ከቁጥር አራት እስከ ዳንኤል 7:28 ድረስ ያሉት ምዕራፎች በጊዜው የባቢሎናውያን ቋንቋ በነበረው በአረማይክ እንደተጻፉ ነው። የተቀረው የመጽሐፉ ክፍል የተጻፈው ግን በዕብረይስጥ ነበር። ዳንኤል የጽሁፉን ቋንቋ ወደ አረማይክ የለወጠው ታሪኩ ሌላውን ዓለም እንጂ እስራኤልን የማይመለከት በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም። ዳንኤል ምዕራፍ 1 እና ከምዕራፍ 8-12 ያሉት ምዕራፎች እስራኤልን የሚመለከቱ በመሆናቸው በዕብረይስጥ ተጽፈዋል።

ንጉሥ ናቡከደነፆር ከውጊያ ተመልሶ አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ስለ ወደፊቱ እያሰበ ይሆናል፥(ዳኔል 2:29 ተመልከት)። ግዛቱ ምን ያህል ሰፊ እንደሆነ፥ የንጉሥነት ሥልጣኑም ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ሳያስብም አይቀርም። ይህን በማሰብ ላይ እያለ ነበር እንቅልፍ ወስዶት አስደናቂውን ሕልም ያለመው። ያለመውም ተከታታይ የሆኑ ሕልሞችን ነው። በዚህ ሕልም ነበር እግዚአብሔር የወደፊቱን ክንውኖች የገለጸለት። ሕልሙ ከዚህ በፊት ካለመው ሁሉ የተለየ ስለነበር ደንግጦ ከእንቅልፉ ነቃ፤ እንቅልፍ ሊወስደውም አልቻለም። ሕልሙ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ቢያውቅም ትርጉሙን ለመረዳት ባለመቻሉ በጣም ተረበሸ።

ባቢሎናውያን ለሕልም ከፍተኛ ግምት ይሰጣሉ። ሕልምን መተርጎም እንዴት እንደሚቻል የሚያስረዱ ብዙ ትላልቅ መጻሕፍት አሏቸው። ብዙ የተለያዩ የሕልም ዓይነቶች በመጽሐፎቹ ሠፍረዋል፤ ስለዚህም ምሁራን የሕልሙን ትርጉም ለመረዳት እነዚህን መጻሕፍት ይመለከታሉ።

ናቡከደነፆር ሕልሙን ለመተርጎም ይችላሉ የሚላቸውን ምሁራንን ሁሉ አስጠራ። በባቢሎን ውስጥ አራት የምሁራንና የሃይማኖት መሪዎች ክፍል ነበሩ። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ ሁሉም «ጠቢባን» በመባል ይታወቃሉ፤ (ዳን.2:12)። የመጀመሪያዎቹ ጠቢባን:- «አስማተኞች» ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ግን ጸሐፊዎችም አስማተኞች ይባሉ ነበር። እነዚህ ሰዎች ነበሩ የሰውን ጥበብ በመጽሐፍ ሰብስበው የሚጽፉ። ሁለተኛዎቹ:- «ቃላተኞች» የሚባሉ የሃይማኖት መሪዎች ሲሆኑ፥ እነርሱም ከሙታን ጋር መነጋገር እንደሚችሉ ይነገርላቸዋል። ስለዚህም ከሞት ባሻገር ስላለው ሁኔታ እነኪ እንደሚያውቁ ይገመታል። ሦስተኛዎቹ:- «መተተኞች» ሲሆኑ እንደ ጠንቋዮች ሁሉ ልዩ መንፈሳዊ ኃይል አላቸው። ከአማልክት ጋር ለመገናኘትና ሐሳባቸውን ለመረዳት እንደሚችሉ ይገመታል። አራተኛዎቹ:- «ከለዳውያን» ኮከብ ቆጣሪዎች ናቸው። እነርሱም ከዋክብትን በመመልከት የወደፊቱን ለማወቅ እንደሚችሉ ይናገራሉ። በአጠቃላይ እነዚህ ጠቢባን በመንፈሳዊ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ዕውቀት አላቸው። ሕልሙ መንፈሳዊ ይዘት ስለነበረው ትርጓሜውን እንዲነግሩት ተጠሩ።

መላውን ዓለም የሚመለከተውን ትንቢታዊ ሕልም እግዚአብሔር በእርሱ ለማያምነው የአሕዛብ ንጉሥ ለናቡከደነፆር መግለጹ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ይህን ሕልም ለዳንኤል ከመግለጽ ይልቅ ለናቡከደነፆር ሊገልጽለት ፈቀደ። (ዘፍጥረት 20:3፤ 41:1-8ን አሕዛብ ታላቅ ሕልም እንደሚያልሙ ለሌላ ተጨማሪ ምሳሌዎች ተመልከት)። በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ሁሉ የሚበልጥ የወደፊቱን የሚገልጽ ይህን ትንቢታዊ ሕልም ለናቡከደነፆር ገለጸለት።

ጠቢባኑ ተጠርተው ከመጡ በኋላ አተረጓጐማቸው ትክክል መሆኑን ለማወቅ ንጉሥ ናቡከደነፆር ፈተና አቀረበላቸው። እነርሱ ራሳቸው የፍጥረተ ዓለምን ምስጢር ጠንቅቀው እንደሚያውቁና ከአማልክት ጋር ለመነጋገር እንደሚችሉ ሲናገሩ ነበር። ስለዚህም ሕልሙን መተርጐም ብቻ ሳይሆን ያየው ሕልም ምን እንደሆነ መግለጽ አለባቸው። አንዳንድ ሰዎች ናቡከደነፆር ሕልሙን እንደረሳው ይናገራሉ፥ (ዳኔል 2:5 ተመልከቱ)። ይሁን እንጂ «ነገሩ ከእኔ ዘንድ ርቆአል» የሚለው አባባል «ትእዛዜ ጽኑ ነው» ተብሎ ሊተረጐም ይቻላል። በሌላ አነጋገር ሕልሙን ሊነግራቸው ፈቃደኛ አልነበረም ማለት ነው። ሕልሙ:- እንቅልፍ እስኪነሣው ድረስ አስደንጋጭ ከነበረ:- ሊረሳው እንደማይችል እስባለሁ። ይህን ያደረገው የጠቢባኑን ፈጠራ ሳይሆን የሕልሙን ትክክለኛ ትርጉም እንዲነግሩት ለማወቅ ሳይሆን አይቀርም። ስለዚህም ሕልሙን እስከ ትርጉሙ እንዲነግሩት ጠየቃቸው። ይህ በጣም አስቸጋሪ ነው። ሕልሙን ነግሮአቸው ቢሆን ኖሮ የፈለጋቸውን ትርጉም በሰጡት ነበር። ወይም ደግሞ ከሕልም መፍቻው መጽሐፍ ትርጉም ለመመልከት በቻሉም ነበር ነገር ግን የንጉሡን ሕልም ሊነግሩት አልቻሉም። ሕልሙን እንዲነግረቸው የተለያየ ሙከራ ቢያደርጉም እርሱ ግን ሊነግራቸው አልፈለገም። ሕልሙን ካልነገሩት እነርሱንና ቤተሰባቸውን ሁሉ እንደሚገድል ቢነግረቸውም መልስ ሊሰጡት አልቻሉም። ሕልሙን ለሚነግረው ከፍተኛ ሽልማት እንደሚያደርግም ቃል ገብቶ ነበር።

በመጨረሻም ጠቢባኑ ናቡከደነፆር ሕልሙን እንዲነግረቸው ለማድረግ ብዙ ከጣሩ በኋላ እንደማይችሉ ገለጹለት። ንጉሡ የጠየቃቸውን ለማሟላት በፍጹም እንደማይቻል ገለጹለት። ከተርጓሚው በፊት ሕልሙን እንዲነግሩት ማንም ንጉሥ ጠቢባንን ጠይቆ አያውቅም። የተሰወረውን ማወቅ ለሰው አይቻልም። ጠቢባኑ «የተሰወረውን ማወቅ የሚቻለው ለአማልክት ብቻ ሲሆን፥ እነዚህ አማልክት ደግሞ ከሰው ጋር አይኖሩም። ወይም ደግሞ የተደበቀውን አይነግሩትም» አሉ። ይህንንም በማለታቸው የእነርሱም ሆነ የሌሎች ሐሰተኛ ሃይማኖት ሁሉ የተመሠረተው በሰው ጥበብ ላይ መሆኑን አመልክተዋል። ምንም እንኳ የሰይጣን ባሪያዎች በመሆናቸው ከፍተኛ ኃይል እንዳላቸው ቢታወቅም ሕልሙን ሊነግሩት ግን አልቻሉም። ለሰው የማይቻለው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይቻለዋል። ከእውነተኛ ፈጣሪ ይልቅ ያመልኩት የነበረው የእርሱን ፍጡር በመሆኑ ለንጉሡ ሊመልሱለት አልቻሉም። ዳንኤል ግን የሚያመልከው የሰውን ሁሉ ምስጢር የሚያውቀውን እውነተኛ አምላክ

በመሆኑ ሕልሙን ገለጸለት። እውነተኛ አምላክ ከሰው ጋር በቤትም ሆነ በቤተ መቅደስ ውስጥ አይኖርም። ከሰው ሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ቢሆንም÷ እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃዱን ለአገልጋዮቹ ይገልጽላቸዋል።

11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕልምን የመተርጐም ችሎታ እንዳላቸው የሚናገሩ ሰዎችን ታውቃለህ?
ለ/ ሁልጊዜ ሕልሙን በትክክል ይተረጉሙታልን?
ሐ/ ሕልሙ ሳይነገረቸው ትርጓሜውን ሊናገሩ ይችላሉን?
መ/ እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖች ናቸውን?
ሠ/ ክርስቲያኖች ሕልምን መተርጐም ይችላሉን?
ረ/ ትክክለኛውን አተረጓጐም እንዴት እናውቃለን?

ሕልሙን ሊነግሩት ባለመቻላቸው ንጉሥ ናቡከደነፆር በባቢሎን የሚገኙ ጠቢባን ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ። ዳንኤል ናቡከደነፆር ሕልሙን እንዲተረጉሙለት ከጠየቃቸው ጠቢባን መካከል ለምን እንዳልነበረ አናውቅም። ምናልባትም ገና በትምህርት ቤት ስለነበረ ስለ ንጉሡ ሕልም አልሰማም ይሆናል። ይሁን እንጂ ከጠቢባን እንዱ ስለነበር እርሱንና ጓደኞቹን ለመግደል ወታደሮች መጡ።

አንዳንድ ሰዎች ለውስጣዊ ችግረቸው ከሌሎች ሰዎች መፍትሔ ለማግኘት ይፈልጋሉ። ከምሁረን÷ ከባለጸጐችና ኃያላን መስለው ከሚታዩ ሁሉ መፍትሔ የሚያገኙ ይመስላቸዋል። የተለያዩ የሃይማኖት መሪዎችን ያነጋግራሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከመናፍስት ጋር ለመገናኘት እንደሚችሉ ወደሚናገሩ ጠንቋዮች እንኳ ይሄዳሉ። የፈለጉትን ያህል ሙከራ ቢያደርጉም ለውስጣዊ ጥያቄዎቻቸው መልስ ሊያገኙ አይችሉም። ችግረቸውን (ኃጢአትን) ሆነ መፍትሔውን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ልንነግረቸው የምንችል እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ነን። እኛ የእግዚአብሔርን ሐሳብና ፈቃድ እናውቃለን÷ (1ቆሮ.2:16)።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሰዎች ውስጣዊ ችግረቸውን በግልጽ እንዲያወያዩን ዕድል እንሰጣቸዋለን?
ለ/ ከአንዳንዶች ጋር ስለ ኃጢአታቸውና የኃጢአታቸው መፍትሔ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደነገርካቸው ግለጽ።

<u>ሦስተኛ ቀን</u> <u>ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 2:14-23</u>

<u>ጥያቄዎች</u>

13ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ሊገድሉት ለመጡት ወታደሮች በምን ዓይነት አነጋገር

ነበር የተናገረቸው?

14ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ንጉሡን ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው የጠየቀው ለምን ነበር?

15ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ሦስት ጓደኞቹን ምን እንዲያደርጉ ጠየቃቸው?

16ኛ ጥያቄ:- በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 2:18 እንደምንመለከተው ዳንኤል እግዚአብሔርን ምን ብሎ ጠረው? ለምን?

17ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የጸሎቱ መልስ የተሰጠው ለማን ነበር?
ለ/ በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር የተሰጠው?

18ኛ ጥያቄ:- ሕልሙ ከተገለጸላቸው በኋላ ዳንኤልና ጓደኞቹ ምን አደረጉ?

19ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከዘላለም እስከ ዘላለም ምስጋና የሚገባው ማነው?
ለ/ ለምን?

20ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል እግዚአብሔርን ያመሰገነበት አንዳንድ ነጥቦችን ዘርዝረህ ጻፍ::

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ጠቢባንን ሁሉ እንዲገድል ሥልጣን የተሰጠው አርዮክ የሚባል ሹም ዳንኤልንና ጓደኞቹንም ለመግደል መጣ:: ዳንኤል ለምን እንደሚገደሉና ንጉሡ ስላደረገው አዋጅ አልሰማም ነበር:: ዳንኤል ለምን እንደሚገደል ቶሎ ብሎ አልጠየቀም:: መጽሐፍ ቅዱስ ዳንኤል «በተፈጥሮ ማስተዋል» እንደተናገረው ነው የሚገልጸው:: ዳንኤል በእንዴት ዓይነት ድምፀና ቃል ተጠቅሞ እውነቱን መረዳት እንደሚችል ያውቅ ነበር:: ብዙ ጊዜ ግን ክርስቲያኖች የተለያየ ችግር ሲገጥማቸው የሚናገሩት «በጥበብና በፈሊጥ» አይደለም:: ዝም ለማለትም ሆነ ለመናገር ፈሊጥና ጊዜ አለው:: ዳንኤል በንጉሡ አለቃ ፊት ሞገስ እንዲያገኝ በትክክለኛ አነጋገር መቅረብ አለበት::

21ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት «በፈሊጥና በማስተዋል» መናገር እንደሚገባ ምሳሌዎችን ስጥ::
ለ/ ያለ ፈሊጥና ማስተዋል በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እንደምንናገር ምሳሌዎችን ስጥ::

ለምን እንደሚገደሉ ዳንኤል የዘበኞቹን አለቃ አልጠየቀውም:: እንዲገደል ያዘዘውን ንጉሥ ሥልጣኑም አልተቃወመም:: ትክክለኛ ፍትሕና ፍርድ እንዲደረግለትም አልተሟገተም:: ከዚህ ይልቅ ግን:- «የንጉሡ ትእዛዝ ስለምን ቸኰለ?» በማለት ጠየቀ:: ንጉሡ ሕልሙን እንዲተረጉሙለት እርሱንና ጓደኞቹን አልጠየቃቸውም ነበር:: ንጉሡ የተቆጣበትን ምክንያት ለማወቅ ፈለገ:: የጠየቀው በጥበብ ስለነበር አርዮክ ስለ ንጉሡና ስላለመው ሕልም አጫወተው:: በዚህ ጊዜ ሕልሙን ለመተርጐም እንደሚችል ዳንኤል ለአርዮክ ሳይነግረው አልቀረም:: ከዚያ በኋላ ወደ ንጉሡ ለመቅረብ ፈቃድ ጠየቀው:: ንጉሡ ተቆጥቶ እንዲገደል የተፈረደበትን ሰው ንጉሡ ፊት

ማቅረቡ የተለመደ አልነበረም። ይሁን እንጂ አርዮክ በሰጠው ምክር ዳንኤል በንጉሥ ፊት መቅረብና ሕልሙን ለመተርጐም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ቻለ። ሕልሙን ለመተርጐም እግዚአብሔር ጥበብ እንደሚሰጠው ያምን ነበር። ንጉሡም ተጨማሪ ጊዜ ሰጠው።

ወደ ቤቱ ከተመለሰ በኋላ ዳንኤል ሦስቱ ጓደኞቹ በጸሎት እንዲተባበሩት ጠየቃቸው፤ ከእግዚአብሔር ምሕረትን መለመን ነበረባቸው። ሕልሙንና ትርጓሚውን መንገር ካልቻሉ እንደሚገደሉ ያውቃሉ። ዳንኤል እግዚአብሔርን:- «የሰማይ አምላክ» በሚል ስም መጥራቱ የሚያስደስት ነው። ይህ አጠራር የተለመደው ከምርኮው በኋላ ነበር፥ (ዕዝራ 1:2፤ 6:10፤ 7:12፥ 21፤ ነህ. 1:5፤ 2:4)። ዳንኤል በዚህ አጠራር የተጠቀመው በእውነተኛው አምላክና በሰዎች የሐሰት አማልክት መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት ሳይሆን አይቀርም። ባቢሎናውያን ብዙ ምድራዊ አማልክት ነበሯቸው። ይሁን እንጂ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ ነው ያለው። ከሰማይ ሆኖ ምድርን ይገዛል። ፈጣሪ እርሱ ነው፤ እርሱ የሰማይ አምላክ ነው። የሰው አማልክት ደካሞች ናቸው፤ ሰማያዊው አምላክ እጅግ ብርቱ ነው። ምድራውያን አማልክት ሕልሙን መግለጽ ባይችሉም ሰማያዊው አምላክ ሊገልጸው ይችላል።

ዳንኤል የጸሎቱን መልስ ካገኘ በኋላ ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር አቀረበ። ዳንኤል የእግዚአብሔርን ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም አመሰገነ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች የእግዚአብሔርን ወይም የኢየሱስን ስም ሲያመሰግኑ ስሙን ማምለካቸው አይደለም። «ኢየሱስ» ወይም «እግዚአብሔር» የሚለው ቃል ብቻ ምንም የተለየ ኃይል የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ኢየሱስ ስም ሲናገር የእግዚአብሔርን ወይም የኢየሱስን ባሕርይ መግለጹ ነው። ስለዚህም ዳንኤል የእግዚአብሔርን ስም ሲያመሰግን:- ፍቅሩን፥ ምሕረቱንና ኃይሉን እንዲሁም ጠቅላላ ባሕርዩን ማመስገኑ እንደሆነ መታወቅ አለበት።

22ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በኢየሱስ ስም ስንጸልይ ምን ማለታችን ነው?
ለ/ ለምን በስሙ እንጸልያለን?
ሐ/ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ጸሎታቸውን በኢየሱስ ስም ሲጸልዩ ሳያስቡበት አስበውበት ነውን?

በኢየሱስ ስም ስንጸልይ:- በኃይሉ በሥልጣኑና በእግዚአብሔር ልጅነቱ መጸለያችን ነው። በኢየሱስ ስም ስንጸልይ ጸሎታችን ሁሉ የተመሠረተው በእኛ ሥልጣን ወይም ኃይል እንዳልሆነ ያሳያል። እንዲያውም ለእግዚአብሔር ስንጸልይ ምልጃችንን ወደ እርሱ የማቅረቡን ሥልጣን ማግኘታችንና መልስ መጠበቃችን በሁለት ምክንያት ነው። የመጀመሪያው:- ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመልን ሥራ ምክንያት ነው። ኢየሱስ ለኃጢአታችን በመስቀል ላይ ሞተ፤ በእግዚአብሔር ፊትም ጻድቃን አደረገን። በኢየሱስ

ክርስቶስ ባለን እምነት ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ንጹሖን ስለሆንን ለመጸለይ እንችላለን። በሁለተኛ ደረጃ:- በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበትን ሥልጣን ሰጥቶናል። በኢየሱስ ስም መጸለይ ማለት ጸሎታችንን የምናቀርበው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ያሳያል ማለት ነው። ጸሎታችን መልስ የሚያገኘው እንደፈሳችን ምኞት ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን ነው፤ (1ዮሐ. 5:14-15)። ጸሎታችን እንዲሰማልን ስንጸልይ ለእግዚአብሔር የሚታዘዝ ሕይወት ሊኖረን ይገባል፤ (1ዮሐ.3:21-22)።

ዳንኤል እግዚአብሔርን ስለ ጥበቡና ስለ ኃይሉ ማመስገኑን ቀጠለ። በጥበቡ ለሰው የተሰወረውን ሁሉ ማወቅ ይችላል። በኃይሉ ጊዜንና ዘመናትን፥ መንግሥታትንና መሪዎቻቸውን ሁሉ መቆጣጠር ይችላል። ይህም ባቢሎናውያን ወቅቶችን፥ ፀሐይን፥ ጨረቃን፥ ከዋክብትን ይቆጣጠራሉ ብለው ከሚያስተምሯቸው አማልክት ጋር ሲነፃፀር የተቃረነ ነው። እቅዱን፥ ማንነቱንና ለሰዎች የተሰወረውን ሁሉ ስለገለጠለት እግዚአብሔርን አመሰገነ። የናቡከደነፆርን ሕልም ለዳንኤል ገለጠለት። ለዚህም የሚያበቃ ጥበብና ኃይል ሰጠው።

ዳንኤል እግዚአብሔርን «የሰማይ አምላክ» ብቻ ሳይሆን «የአባቶቼ አምላክ» በማለትም ጠርቶታል። ይህንንም ሲናገር እግዚአብሔር በሙሴ፥ በኢያሱና በሌሎችም አማካይነት ስላደረገው ተአምራት በይሁዳ ምድር እያለ የተናገረውን ታሪክ እያሰበ እንደሆነ ግልጽ ነው። ለእነርሱ ተአምር ያደረገላቸው አምላክ፥ በእርሱም ሕይወት ተአምር መሥራት ጀምሯል።

ዛሬ እኛ የምናመልከው ዳንኤል ሊያመልከው የነበረውን አምላክ ነው። እርሱ እጅግ ጠቢብ ነው። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ዘመናትን፥ ጊዜያትን፥ ሕዝቦችንና ገዢዎቻቸውን ይቆጣጠረል። ዛሬም ቢሆን የተሰወረውን ለልጆቹ ይገልጽላቸዋል። እግዚአብሔር አይለወጥም። ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት በአባቶቻችን ዘመን ተአምራት ያደረገው አምላክ ዛሬም ቢሆን ተአምር ይሠረል።

23ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔርን ስለ ማንነቱ አመስግነው። እግዚአብሔርን እንድታመሰግን የሚያደርጉህን ባሕርያቱን አስብ። ስለዚህም እግዚአብሔርን አመስግነው።

አረተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ፤ የውይይቱን ጥያቄዎች እንደገና ተመልከት።

## እምስተኛ ቀን:-  የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን ከልስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ የተለያዩ የጸሎት ዓይነቶችን ግለጽ:: ኤፌ.6:18፤ ፊልጵ.4:6፤ 1ጢሞ.2:1 ተመልከት::
2/ አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች የሚጸልዩት የትኛውን የጸሎት ዓይነት ነው?
3/ እግዚአብሔርን ስለምናመሰግንበት ባሕርያት ግለጽ::
4/ ስለምትጸልይባቸው የተለያዩ ነገሮች ግለጽ::
5/ አንተ አብዛኛውን ጊዜ የምትጸልየው የትኛውን የጸሎት ዓይነት ነው?
6/ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስትጸልይ የምትጠቀመው የትኛውን የጸሎት ዓይነት ነው?

ለ. 1/ ሰዎች ለችግሬችን መፍትሔ ይሰጡናል ብለው ስለሚገምቷቸው ሰዎች ግለጽ::
2/ በችግሬቸው የሚረዷቸው ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
3/ ክርስቲያን ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ሊሰጥ ይችላልን?
4/ እንዴት?
5/ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ የሚሰጥባቸው የሰዎች ውስጣዊ ችግሮች ምን ምንድናቸው?

ሐ. 1/ ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በሕልምና በራዕይ ለሰዎች ይናገራልን?
2/ ከሆነ:- ራዕዩ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንዴት እናውቃለን?
3/ አተረጓጎሙ ትክክል መሆኑን እንዴት እናውቃለን?
4/ ራዕይን የሚንረጸበት አንዳንድ መመዘኛዎች ምንድናቸው?
5/ እነዚህ ሕልሞች የእግዚአብሔርን ቃል ያህል አስፈላጊ ናቸውን?
6/ እምነታችንና ጽርጊታችን በሕልም ላይ ብቻ መመሥረቱ የሚያስከትለው ችግር አለን?

5. ጸሎት

# ትምህርት ስድስት

## ዳንኤል 2:24-29

### የመጀመሪያ ቀን

«በእነዚያም ነገሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ፥ ለዘለዓለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች፥ ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች» ዳንኤል 2:44::

ዛሬ የዓለማችንን ሁኔታ ስንመለከት:- የሰዎች መንግሥት ዘላለማዊ መስሎ ይታያል:: ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክን ስንመረምር ግን በዓለም ውስጥ ታላላቅ መንግሥታት ተነሥተው እንደነበር እንረዳለን:: በሙሴ አማካይነት ነፃ እስኪወጡ ድረስ እስራኤል በግብፅ አገር ስደተኛ ነበረች:: ከዚያ በኋላ ደግሞ አሦራውያን እስራኤልን /የሰሜኑን ክፍል/ በምርኮኝነት ወሰዷት:: በኋላም ደግሞ ባቢሎን ይሁዳን /የደቡቡን ክፍል/ በምርኮኝነት ወሰደች:: ከዚያ በኋላ የሚደንና ፋርስ መንግሥት፥ የግሪክ መንግሥት፥ የሮም መንግሥት፥ የእንግሊዝ መንግሥት፥ የቱርክ መንግሥት ወዘተ ተነሡ:: ምን ጊዜም ቢሆን ታላላቅ መንግሥታት ከዓለም ተለይተው አያውቁም:: ዛሬ አሜሪካ፥ ሩሲያና ቻይና የጊዜው ታላላቅ መንግሥታት ናቸው ማለት ይቻላል::

እኛ ክርስቲያኖች በእነዚህ ኃያላን መንግሥታት የተነሣ እንጨነቃለን:: የኒውክሌር ጦርነት እንዳይነሣ እንሰጋለን:: በተለያዩ አገሮች ስለሚደረጉት ድርጊቶች እናስባለን:: አንዳንድ ጊዜ እነዚህ መንግሥታት ዘላለማዊና ሁልጊዜ ሥልጣኑን እንደያዙ የሚቆዩ መስለው ይታዩናል:: ብዙ ጊዜ እነዚህ ኃያላን መንግሥታት ክርስቲያኖችን ያሳድዳሉ፤ ክርስቶስ መጥቶ ከዚህ ሁሉ እስኪገላግለን ድረስ ምን ያህል ጊዜ እንቆይ ይሆን እንላለን::

በዳንኤል ምዕራፍ 2 ስለ አራቱ ዋና ዋና መንግሥታት እናነባለን:: እያንዳንዱ መንግሥት እኔ ኃይለኛ ነኝ ብሎ ያስብ ነበር:: ለዘላለም ጸንተው የሚኖሩ ይመስላቸዋል:: እግዚአብሔር ግን ለዳንኤልና ለናቡከደነፆር የሰዎችን መንግሥት የሚመለከት በጣም ጠቃሚ እውነቶችን ገልጾላቸዋል::

በመጀመሪያ:- ሁለት የተለያዩ መንግሥታት መኖራቸውን አሳያቸው:: አንደኛው የሰው መንግሥት ሲሆን፥ ሁለተኛው ግን መለኮታዊ መንግሥት ነው:: የሰው መንግሥት የተጀመረው በሰው ሲሆን መለኮታዊ መንግሥት የሚመሠረተው ግን በራሱ በእግዚአብሔር ነው::

ሁለተኛ:- እነዚህ ሁለት መንግሥታት የተለያየ የጊዜ ገደብ እንደሚ ኖረቸው ገለጸላቸው። ምን ያህል ታላቅ ቢሆንም የሰው መንግሥት ጊዜያዊ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ዘላለማዊ ነው።

ሦስተኛ:- እነዚህ ሁለት መንግሥታት የተለያየ ኃይል እንደሚኖረቸው ገለጸላቸው። የሰው መንግሥታት ኃይላቸው ውሱን ነው። አንድ ቀን በሌላው መሸነፋቸው አይቀርም። የእግዚአብሔር መንግሥት ግን በማንም አይሸነፍም። አንድ ጊዜ ከተመሠረተ ማንም የእግዚአብሔርን መንግሥት መገልበጥ አይችልም።

ዛሬ የምንኖረው የተለያዩ መንግሥታት ኃያላን ሆነው ለመገኘት በሚሞክሩበት ዓለም ነው። አንዱ መንግሥት ከሌላኛው መንግሥት ጋር ይዋጋል። የእኛ የክርስቲያኖች ዓይን ግን በዚያ ዘላለማዊ መንግሥት ላይ መሆን አለበት (ዕብ.11:8-16 ተመልከት)። አንድ ቀን የሰዎች መንግሥት በሙሉ ይደመሰሳል። ያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻውን ይገዛል። ይህንንም መንግሥት ማንም ሊደመስሰው አይችልም። እኛም ከክርስቶስ ጋር እንገዛለን። በሁሉም ስፍረ ፍትሕና ፍቅር ይሰፍናል። ለዚያ መንግሥት ተዘጋጅተናል? የእርሱ መንግሥት ሲገለጽ ዝግጁ ሆነን እንድንገኝ ዛሬ ቅድስና በተሞላ ሕይወት እግዚአብሔርን እየተከተልን ነው?

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ስለሚመጣው ታላቅ የእግዚአብሔር መንግሥት አስብ። ምን ይመስል ይሆን?
ለ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከተህ ከእግዚአብሔር መንግሥት የምናገኛቸውን አንዳንድ በረከቶች ዘርዝር። ኢሳ.65: 17-25፤ ሪዕ.19:20-21:8።

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 2:24-49 አንብብ።
ለ/ ናቡከደነፆር ስላየው ምስል የምትችለውን ገለጸ ስጥ።
ሐ/ ያ ምስል የተደመሰሰው እንዴት ነው?
መ/ ሕልሙን በመፍታቱ ዳንኤል ያገኘው ሽልማት ምን ነበር?

<u>ሁለተኛ ቀን</u> <u>ክፍል አንድ:- ዳንኤል 2:24-35</u>

ባለፈው ሳምንት ንጉሡ ናቡከደነፆር ስላለመው ሕልም ተመልከተን ነበር። ሕልሙንና ትርጓሚውን እንዲነግሩት በባቢሎን የነበሩትን ጠቢባን ሁሉ ጠይቆአቸው ነበር። ማንም ሕልሙን ሊነግረው ስላልቻለ ጠቢባኑ ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ። ዳንኤል ግን እግዚአብሔር ሕልሙን እንዲገልጽለት ጠየቀ። እግዚአብሔር የዳንኤልን ጸሎት መለሰለት፤ ሕልሙንም ገለጸለት። በዚህ ሳምንት ይህንን ሕልምና አተረጓጐሙን እንመለከታለን።

ይህን ሕልም እንደሚገባ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ዳንኤል ምዕራፍ 2 ከ600 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንሥቶ ክርስቶስ እንደገናም እስከሚመጣ ድረስ የሚሆነውን የወደፊቱን ዓለም ሁኔታ ይገልጻል። ይህም ሁሉ የተካተተው በጣም መጠነኛ በሆነ ገለጻ ነው። ምዕራፍ 7፤ 8፤ 9 እና 11 የሚያብራሩትም በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተውን ሐሳብ ነው።

## ጥያቄዎች

3ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ለአርዮክ ምን ስለነገረው ነው ወደ ንጉሡ የወሰደው?

4ኛ ጥያቄ:- አርዮክ ለንጉሥ ናቡከደነፆር ምን ነገረው?

5ኛ ጥያቄ:- ልሙን ለመተርጐም ይችል እንደሆነ ናቡከደነፆር በጠየቀው ጊዜ ዳንኤል የሰጠው መልስ ምንድነው?

6ኛ ጥያቄ:- ለንጉሡ መልስ በሰጠው ጊዜ ዳንኤል ምስጋና የሰጠው ለማን ነበር?

7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ስለ ምስሉ ገለፃ ስጥ።
ለ/ ምን ይመስላል?
ሐ/ እያንዳንዱ የምስሉ ክፍል የተሠረው ከምንና ከምን ነበር?

8ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ምስሉ ምን ሆነ?
ለ/ ስለ ድንጋዩ ገለፃ ስጥ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ (ኮሚንታሪ)

ባለፈው ሳምንት አርዮክ የንጉሡ ዘበኞች አለቃ መሆኑን ተመልክተን ነበር። ጠቢባኑን ሁሉ የመግደል ትእዛዝ የተሰጠው ለእርሱ ነበር። ወደ ዳንኤል ሲመጣ ወደ ንጉሡ እንዲወስደውና ሕልሙን ለመተርጐም ጊዜ እንዲሰጠው አደረገ። እግዚአብሔር የናቡከደነፆርን ሕልምና ትርጓሜውን ለዳንኤል ገለጸለት።

ዳንኤል ወደ አርዮክ ተመለሰና እንደታዘዘው ጠቢባኑን እንዳይገድል ነገረው። ወደ ንጉሡ ቢወስደው ሕልሙን ሊተረጉምለት እንደሚችል አጫወተው። አርዮክ ዳንኤልን ወደ ንጉሡ ወሰደው፤ ይሁን እንጂ አርዮክ ከዳንኤል ይልቅ ራሱን ለማክበር ፈለገ። ሕልሙን ለመተርጐም የሚችለውን ዳንኤልን እንዳገኘ ለንጉሡ ተናገረ። አርዮክ ከሚገባ በላይ ራሱን ከፍ አድርጐ ማቅረቡ ከብዙዎቻችን ጋር ያመሳስለዋል።

9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ክርስቲያኖች ለሌላው የሚገባውን ክብር ለረሳቸው ያጸርጋሉን?
ለ/ አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።
ሐ/ አንተስ እንደዚህ ያደረግህበት ጊዜ አለን?
መ/ ክርስቲያኖች ይህን ማድረጋቸው ትክክል ነውን?

ሕልሙን ለመተርጐም ይችል እንደሆነ ናቡከደነፆር ዳንኤልን ጠየቀው። ዳንኤል ሕልሙን ለመተርጐም ይችላል ብሎ ማመኑ ለንጉሡ ሳይከብደው አልቀረም። ዳንኤል የሰጠው መልስ ግን በጣም ደስ የሚል ነበር። ምንም ጠቢብ ቢሆን ሰው ይህን ሕልም መተርጐም እንደማይችል ለንጉሡ ነገረው። ዳንኤል «ቃላተኞች» ስለሚባሉ ሰዎች ይናገራል። እነዚህ ሰዎች በሃይማኖት ክፍል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ የእንስሳትን አንጀት በማየት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እንደሚችሉ ይናገራሉ። የፍጥረተ ዓለምን ምስጢር መግለጥ የሚቻለው እውነተኛው አምላክ ብቻ እንደሆነ ለንጉሡ አስረገጠለት። እንደ አርዮክ ወደ ራሱ ከማመልከት ይልቅ ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር አመለከተ። ምስጢርን ሁሉ መግለጽ የሚቻለው አምላክ በሰማይ እንዳለ ዳንኤል ለንጉሡ አስረዳው። ዳንኤል የሕልሙን ትርጓሜ ከእግዚአብሔር ያገኘው ከሌሎች ስለበለጠ ወይም ከሌሎች ይልቅ ጥበበኛ ስለሆነ አለመሆኑን ገልጾ ሕልሙን ለመተርጐም እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት እንደተጠቀመ ለንጉሡ አመልክቷል። እዚህ ላይ «ምስጢር» የሚለው ቃል ለሌሎች የማይነገር ወይም የተሰወረ ማለት አይደለም። ደሩ ግን እዚህ ላይ "ምስጢር" ሲል እግዚአብሔርበቀጥታ ካልገለጸለት በቀር ሰው ሊያቀው ወይም ሊገባው የማይችል ሐቅ ማለቱ ነው። ወደፊት የሚሆነውን ለናቡከደነፆር መግለጹ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር።

ዳንኤል:- ሕልሙና ራዕዩ እንዴት እንደጀመረ ለንጉሡ አመለከተው። ወደፊት በመንግሥቱ ላይ ምን እንደሚሆንና ስለወደፊቱ ሁኔታዎች እያሰበ ናቡከደነፆር በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር። እግዚአብሔርም በዘመናት ሁሉ የሚሆነውን ዕቅዱን ለናቡከደነፆር ገለጸለት። ዳንኤል:- ንጉሡ ያየው ሕልም:- «በኋለኛው ዘመን» የሚሆን እንደሆነ ነገረው።

10ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ብሉይ ኪዳን:- «በመጨረሻው ቀን» የሚለውን ሐረግ እንዴት እንደሚጠቀምበት የሚከተሉትን ቁጥሮች ወይም ተመሳሳይ ቁጥሮችን ተመልከት። ሕዝ.38:6፤ ሆሴዕ 3:5፤ ሚክ.4:1።
ለ/ ይህ ሐረግ በታሪክ ውስጥ የትኛውን ጊዜ ያመለክታል?

ብዙውን ጊዜ ነቢያት «በመጨረሻው ቀን» የሚለውን ሐረግ የሚጠቀሙበት ትንቢታዊ ራዕያቸው የሚፈጸምበትን ጊዜ ለማመልከት ነው። ብዙ ጊዜ ስለ መሢሑ ጊዜ ያመለክታል። መሢሑ ስለሚመጣበት ጊዜና እርሱ ስለሚመሠርተውም መንግሥት ያመለክታል። ከዚህም በተረፈ መሢሑ

ከመምጣቱ በፊት ስለሚሆነው ታላቅ የመከረ ጊዜ ያመለክታል።

11ኛ ጥያቄ፦ ሀ/ ይህንኑ ሐረግ አዲስ ኪዳን እንዴት እንደሚጠቀምበት የሚከተሉትን ቁጥሮች ተመልከት፦ ዮሐ.6:39-44፤ 2ጢሞ.3:1-5፤ ዕብ.1:2።
ለ/ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ይህን ሐረግ የተጠቀሙበት በታሪክ ውስጥ የትኛውን ጊዜ ለማመልከት ነው?

የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች «በመጨረሻዎቹ ቀናት» ውስጥ እንደምንኖር ደጋግመው ያመለክታሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶአል። ቤተ ክርስቲያኑን በመመሥረቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ተጀምሮአል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ገና ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ለመግዛት ስለሚመለስበት ጊዜ ነው የሚያመለክተው።

በዳንኤል 2:31-35 ዳንኤል ናቡከደነፆር ስላየው ሪዕይ ይገልጻል። ናቡከደነፆር ታላቅ ምስል አየ። በጥንት ዘመን፥ የአማልክትን ወይም የታላቅ መሪ ምስልን የሚመስል ምስል መሥራት የተለመደ ነበር። ምስል ከድንጋይ ወይም ከእንጨት ይሠራ ነበር። በጣም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በተለያዩ የብረትነት ባሕርይ ባላቸው ነገሮች ይሸፈን ነበር። ናቡከደነፆር ያየው ይህን የሚመስል ነው። በጣም ትልቅ ነበር። ከተለያዩ ብረትነት ካላቸው ነገሮች በመሠራቱ ፀሐይ ሲነካው ያብረቀርቅ ነበር። በጣም ያስፈራ ነበር። ምስሉን መመልከት ብቻ ናቡከደነፆርን አስፈራው።

ምስሉ ሰው ይመስል ነበር። ራስ፥ አካል፥ ክንዶች፥ ጭኖችና እግሮች ነበሩት። ምስሉ ከአንድ ዕቃ የተሠራ ሳይሆን ከተለያዩ ማዕድኖች የተሠራ ነበር። ራሱ ከወርቅ የተሠራ ነበር፤ ደረቱና ክንዶቹ ከብር የተሠሩ ነበሩ፤ ሆዱና ጭኖቹ ከነሐስ የተሠሩ ነበሩ፤ ቅልጥሞቹ ከብረት የተሠሩ ነበሩ፤ እግሮቹ ከብረትና ከሸክላ ድብልቅ የተሠሩ ስለ ነበሩ በጣም ልዩ ነበሩ።

ምስሉ፦ ታላቅና ማንም ሊነቀንቀው እንደማይችል ሆኖ ቆሞ ነበር። በድንገት ግን አንድ ድንጋይ ሲወድቅ ታየ። ምስሉን ከታች በኃይል መታው፤ ምስሉም ፍርክስክሱ ወጣ። ምስሉ መሰባበር ብቻ ሳይሆን አመድ ሆነ። ነፋስም ምስሉ የነበረበትን ቦታ እስኪጠፋ ድረስ አመዱን አቦነነው። ምስሉን የመታው ድንጋይ ምድርን ሁሉ እስኪሞላ ድረስ ታላቅ ተራራ ሆነ።

ዳንኤል የናቡከደነፆርን ሪዕይ ለመረዳት በመቻሉ ክብርን ለራሱ ለመውሰድ አልፈለገም። ወደ እውነተኛው አምላክ አመለከተና ይህን ሁሉ ምስጢር የገለጠለት እግዚአብሔር መሆኑን ለናቡከደነፆር ነገረው። ብዙ ጊዜ ግን እኛ ክርስቲያኖች የሚገባንን ያህል ለእግዚአብሔር ክብርን አንሰጥም። ለሰዎች ትልቅ መስለን ለመታየት እንፈልጋለን። ወደ ጌታ ስላመጣናቸው ሰዎች

ወይም ስለሠረነው ትልቅ ሥራ እናወረለን። ይህን በማጽረጋችን ክብርን ከእግዚአብሔር እንቀማለን። እኛ ያለን ወይም የሠረነው ሁሉ የእግዚአ ብሔር ስጦታ ነው። ምንም ምስጋና አይገባንም።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ኢሳ.42:8 እና 48:11 ተመልከት።
ለ/ ክብር ሁሉ የሚገባው ለማን ነው?
ሐ/ ራሳችንን ለማክበር ስንል ክብርን ከእግዚአብሔር ስለምንቀማበት መንገዶች ዘርዝር።
መ/ አንዳንድ ጊዜ ከሰዎች ምስጋና ለማግኘት ስትል የእግዚአብሔርን ክብር ትቀማለህን?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 2:36-49

ጥያቄዎች

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የወርቁ ራስ የማን መንግሥት ነበር?
ለ/ ለንጉሡ በሰዎችና በአረዊት ላይ ሥልጣንን የሰጠው ማነው?
14ኛ ጥያቄ:- ሁለተኛውና ሦስተኛው መንግሥታት ምን ዓይነት መንግሥታት ናቸው?
15ኛ ጥያቄ:- የአረተኛው መንግሥት ባሕርይ ምን ይመስላል?
ሀ/ የብረትና የሸክላ መንግሥት ምን ባሕርይ አለው?
ለ/ ብረትና ሸክላ ምን ይወክላሉ?
16ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ድንጋዩ የሚያመለክተው ምንድነው?
ለ/ ድንጋዩ ከመንግሥታቱ ጋር የሚወዳደረው እንዴት ነው?
ሐ/ የሚበልጠው የትኛው ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ማብሪሪያ (ኮሜንታሪ)

ይህ ረጅም ትምህርት ነው። ይህን ትምህርት በሁለት ቀን ልትጨርስና በአምስተኛ ቀን ክለሳ ልታደርግ ትችላለህ።

ዳንኤል 2:36-45 የናቡከደነፆርን ሕልም ትርጓሜ ይዘአል። ዳንኤል የሕልሙን ዝርዝር ትርጉም አይሰጥም። ከዚህ ይልቅ ግን እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር የሰጠውን ዋና ዋና ትምህርት ያሳያል። ጠቅላላ የራዕዩ መሠረታዊ ትርጉም እንደሚከተለው ነው:- የሰዎች መንግሥት፥ በተለይም የአሕዛብ መንግሥታት አንዱ በሌላው እየተተካ ለረጅም ዘመን ይቀጥላሉ።

አንድ ቀን ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ይመጣል። ምንም ፍንጭ እስከማይገኝላቸው ድረስ የሰውን መንግሥታት ያጠፋቸዋል። የእግዚአብሔር መንግሥት መላውን ምድር ይሸፍናል እንጂ እንደሰዎች መንግሥታት ምድርን በከፊል ብቻ አይሸፍንም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑረን በዚህ ዳንኤል በሰጠው አተረጓጐም ላይ በሚጪምሩት ሐሳብ ይለያያሉ። ትንቢትን በሚመለከት ጉዳይ የተለያየ ሐሳብ የቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው። ትንቢትን በሚመለከት ጉዳይ የተለያየ ሐሳብ መቅረቡን ለመመልከት ምዕራፍ ሁለትን እንደገና ልትከልስ ትችላለህ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ሕልሞችና ራዕዮች (በዳንኤልና በዮሐንስ ራዕይ ያሉትን ዓይነት) ስንተረጉም ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ጥቃቅን ዝርዝሩን ሁሉ መተርጐም በጣም ቀላል ነው። ሕልሞች ግን እንደዚህ መተርጐም የለባቸውም። ጥቃቅን ዝርዝሮችን ስንመለከት የዋናውን ትምህርት ሐሳብ እንዘነጋለን። የምስሉን ጥቃቅን አተረጓጐም ከመመልከታችን በፊት ስለዚህ ምስል አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮችን እንመልከት።

1. ወደ ዝቅተኛው የሰውነት ክፍል በሄደ መጠን፥ የምስሉ ዋጋ እየቀነሰ ይመጣል። ወርቅ ከብር ይልቅ በጣም የከበረ ነው። ብር ከነሐስ ይልቅ የከበረ ነው፤ ነሐስ ደግሞ ከብረት ይልቅ የከበረ ነው። ይህም ማለት እያንዳንዱ መንግሥት አስቀድሞ ከነበረው ይልቅ ያነሰ ነው ማለት ነው። ይህም መንግሥታቱ የነበረቸውን ግዛት ስፋት የሚያመለክት አይደለም። አስቀድሞ የነበሩት መንግሥታት በኋላ ከሚነሡት ይልቅ ሰፊ ግዛት ነበረቸው። ይህም ማለት በፊት የነበሩት መንግሥታት በኋላ ከተነሡት ይልቅ የሚበልጥ ሥልጣን ነበረቸው። ናቡከደነፆር በመንግሥታቱ ፍጹም ሥልጣን ነበረው። ይሁን እንጂ በሜዶንና ፋርስ መንግሥት ሕግ ከንጉሥ በላይ ነበር። (ለዚህ ምሳሌ እንዲሆንህ ዳንኤል ምዕራፍ 6 ተመልከት።)

2. ምስሉ የተሠረበትን ማዕድን ከራስ ጀምረን እስከ እግሩ ድረስ ብንሄድ ይበልጥ እየጠነከረ ይመጣል። ብር ከወርቅ ይልቅ ጠንካራ ነው። መዳብ ከብር ይልቅ ጠንካራ ነው፤ ብረት ደግሞ ከሁሉም የበለጠ ጠንካራ ነው። ይህም ማለት እያንዳንዱ መንግሥት ከእርሱ በፊት ከነበሩት ይልቅ ኃይሉ ይጠነክረል ማለት ሊሆን ይችላል። የሮም መንግሥት (በብረት የተመሰለው) ሁሉንም የሚያደቅና የሚረጭ መሆኑ ተነግሮለታል።

3. ምስሉ ጠንካራ ቢመስልም እንኳ ደካማ ነበር። ምስሉ የተሠረው ከወርቅ፥ ከብርና ከነሐስ ሲሆን መሠረቱ ግን ብረትና ሸክላ ነበር። ሸክላ ጠንካራ መስሎ ቢታይም እንኳ በቀላሉ የሚሰበር ነው። የሰው መንግሥት ከውጪ ሲታይ ጠንካራ መስሎ ይታያል። ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ሲነፃፀር ግን በቀላሉ ተሰባሪ ነው።

የምስሉ ራስ የተሠረው ከወርቅ ነበር። ዳንኤል የምስሉ ራስ

ናቡከጸነፆርን እንደሚወክል ተናገረ:: ናቡከጸነፆር የባቢሎን መንግሥት ገዢ ነበር:: በመሠረቱ የምስሉ ራስ የሚያመለክተው የባቢሎንን መንግሥት ቢሆንም ናቡከጸነፆርን የሚወክል መሪ ስለነበረ እርሱን ይመለከተዋል::

ናቡከጸነፆር «ንጉሠ ነገሥት» ነበር:: ብዙ ሀገሮችን የሚገዛና ብዙ ንጉሦችንም የሚቆጣጠር ስለነበር ይህ የክብር መጠሪያ ለናቡከጸነፆር ተሰጥቶታል:: ይሁን እንጂ የመግዛት ችሎታው ከእርሱ አልነበረም:: ግዛትን፥ ኃይልንና ክብርን የሰጠው፥ ሁሉንም ነገር ከቁጥጥሩ በታች ያደረገው የሰማይ አምላክ ራሱ ነበር::

ይህ ለእኛ ለክርስቲያኖች ትልቅ መጽናኛ ነው:: ምንም ዓይነት ታላቅና ክፉ መሪ በሥልጣን ላይ ቢሆንም፥ በሥልጣን ላይ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው:: ግዛትንና ኃይልን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም:: የመግዛት ኃይል የእግዚአብሔር እንጂ የሰው አይደለም::

የናቡከጸነፆር ሥልጣን «በሰዎች፥ በዱር አረዊትና በሰማይ ወፎችም» ላይ እንደነበር ዳንኤል ይናገራል:: ዳንኤል ይህን የተናገረው ናቡከጸነፆር የነበረውን የገዢነት ሥልጣን ለማመልከት ነበር:: ሁሉም ከቁጥጥሩ ሥር ነበር::

ሁለተኛውና ሦስተኛው የዓለም መንግሥታት በዚህ ሥፍረ የተጠቀሱት በጣም በአጭሩ ነው:: በዳንኤል 7፤ 8 እና 10 በሰፊው ይገለጻሉ:: በብር የተመሰለው ሁለተኛው መንግሥት የሜዶንንና የፋርስን መንግሥት እንደሚገልጽ እንመለከታለን:: ከበፊቱ ያነሰ እንደሚሆን ተገልጾአል:: የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ከባቢሎን የሚበልጥ ግዛት ነበረው፤ ስለዚህም ከመጀመሪያው ያነሰ ነው ስንል በሚያስተዳድረው ግዛት ያንሳል ማለታችን አይደለም:: ታናሽ የተባለበት ምክንያት:- የሜዶንና የፋርስ ነገሥታት እንደባቢሎን ነገሥታት ሁሉ ፍጹም ሥልጣን ስላልነበረቸውና መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ሕብረት ስላልነበረው ሊሆን ይችላል::

በነሐስ የተመሰለው ሦስተኛው መንግሥት የግሪክ መንግሥት ነው:: በዚህ ሥፍረ የተጠቀሰው ይህ መንግሥት «ዓለምን ሁሉ» እንደሚገዛ ብቻ ነው:: ዳንኤል ይህን ሲል በልዩ አገላለጽ መጠቀሙ እንጂ ዓለም በሙሉ በግሪኮች መንግሥት ቁጥጥር ሥር ይሆናል ማለቱ አይደለም፤ የግሪኮች መንግሥት በጣም ሰፊና በብዙ መንግሥታት ላይ የበላይ ይሆናል ማለት ነው:: በነሐስ የተሸፈነው ክፍል ሁለት ጭኖች ስለነበሩት አንዳንድ ተርጓሚዎች የግሪክ መንግሥት ሁለት ክፍሎች እንደሚኖሩት ያመለክታል ይላሉ:: ስለ እነዚህ ሁለት ክፍሎች በዳንኤል 8 እና 11 እንመለከታለን::

አራተኛው መንግሥት የሮምን መንግሥት ያመለክታል:: በጣም ኃይለኛና እንደ ብረት ጠንካራ መሆኑ ተገልጾአል:: ሌሎችን መንግሥታት ሁሉ ይገዛል::

የዓለምን ታሪክ ብታነብ የሮም መንግሥት በምዕረቡ ዓለም እጅግ ጠንካረና ብርቱ እንደነበር ትረዳለህ:: ከእንግሊዝ እስከ ሕንድ ከዚያም አልፎ እስከ ሰሜን አፍሪካ ድረስ ይቆጣጠር ነበር:: ሁሉም ሕዝብና መሪዎቻቸው በሮማውያን ድል ተመቱ:: ሮማውያን በጣም ጨካኝ ነበሩ:: በኃይላቸው ሌሎች መንግሥታትን ሁሉ አስገበሩ:: ስለዳንኤል 2:41-43 የተለያየ ሐሳብ ተሰንዝሮአል:: እግሮቹ ምን እንደሚያመለክቱ ዳንኤል በግልጽ አይነግረንም:: እግሮቹ የብረትና የሸክላ ድብልቅ ነበሩ:: ስለዚህም በአንድ ወገኑ እንደ ብረት ጠንካረ በሌላ ወገኑ ደግሞ እንደ ሸክላ ደካማ በቀላሉ የሚሰባበር ነው ማለት ነው:: ከሌሎች የምስሉ አካሎች ይልቅ በዚህኛው ላይ ዳንኤል ሰፋ ያለ ገለጸ ይሰጣል:: ስለዚህም ለእርሱ ይህ ክፍል በጣም አስፈላጊ ነበር ማለት ነው:: የብረቱና የሸክላው እግሮች መንግሥቱ እንደሚከፋፈል የሚያመለክቱ መሆናቸውን ዳንኤል ይናገረል:: በመከፋፈሉም ደካማ ይሆናል:: ይህም መከፋፈል የመጣው መንግሥቱ የተለያየ ባሕል ባላቸው ሕዝብ በመተዳደሩ ሊሆን ይችላል:: ምናልባትም ለመከፋፈሉ ምክንያት የሆነው የተለያየ ፖለቲካዊ ፍልስፍና ማለትም በዲሞክረሲና በአምባ-ገነንነት በመመረቱ ሊሆን ይችላል:: የመከፋፈሉ ምክንያት ምንም ይሁን ምን ሕብረት ስለሌለው ከሌሎች መንግሥታት ይልቅ ደካማ መሆኑ ግልጽ ነው::

ዋናው ጥያቄ እነዚህ የብረትና የሸክላ ድብልቅ መንግሥታት የሚነሡት በብረት ጭን የተመሰለው መንግሥት በሚነሣበት ጊዜ ነው ወይ? የሚል ነበር:: አንዳንድ ምሑረን በብረትና በሸክላ የተመሰለው እግር÷ ያው ራሱ በብረት የተመሰለው ጭን ነው ይላሉ:: ይህ ለረሱ ለሮም መንግሥት የተሰጠ ገለጸ እንደሆነ ያምናሉ:: ሁለቱ እግሮች የሮም መንግሥት በምሥረቅና በምዕረብ የነበሩትን የግዛት ክፍፍል ያመለክታል:: ይሁን እንጂ ታሪክን ስንመለከት በምዕረብ የነበረው የሮም መንግሥት ከምሥረቁ ቀደም ብሎ የወደቀ በመሆኑ ይህ ትክክለኛ አተረጓጐም ሊሆን አይችልም:: እነዚህ ምሑረን ምስሉን ያፈረረሰው ታጋይ የሮምን መንግሥት ያፈረረሰችው የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ እንደሆነ ያስባሉ:: የሮም መንግሥት የወደቀው ቀስ በቀስ እንጂ ከረዕዩ እንደምንረዳው በቅጽበት አልነበረም:: ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት ከሆነች ታዲያ ለምንድነው ኃይልና ያልሆነችው? በረዕዩ እንደተገለጸው ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ድል ያደረገችበት ጊዜ የለም::

17ኛ ጥያቄ:- ትምህርት ሁለትን ተመልከት:: ከላይ የተጠቀሰው አመለካከት አስቀድሞ ካየናቸው ሦስት አመለካከቶች የትኛውን የሚያመለክት ይመስልሃል?

አንዳንድ ምሑረን ከፊሉ ብረት ከፊሉ ሸክላ የሆነ መንግሥት ወደፊት ይነሣል ብለው ያምናሉ:: ይህ መንግሥት ከጽሮው የሮም መንግሥት ግዛት የሚነሣ በመሆኑ ከሮም መንግሥት ጋር ይመሳሰላል:: እንደ ሮም መንግሥት ብረት ይሆናል:: ይሁን እንጂ ከፊሉ ሸክላ በመሆኑ ጠንካረ ወይም ለረጅም ዘመን የሚቆይ አይሆንም:: ይህም ማለት በጽሮው የሮም መንግሥትና

አንዳንዶች አምስተኛ መንግሥት እያሉ በሚጠሩትና እንዳገና በሚያንሰራሪው የሮም መንግሥት መካከል 1000 ዓመት ይኖራል ማለት ነው:: ይህ የሚቻል ነውን? ትንቢት አንዳንዴ በአማዐት ዓመታት የተለያዩትን ሁለት ክንውኖች አንዱ ሌላውን በመከተል ወዲያውኑ እንደተፈጸሙ አድርጎ ያቀርብ ይሆን?

18ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:: ኢሳ.61:1-2 እና ሉቃ.4:17-21፤ ኢዩ.2:28-32 እና የሐ/ሥራ 2:16-21::
ለ/ እነዚህ ጥቅሶች በአንድ ጊዜ ስለሚፈጸሙ ሁለት የተለያዩና ተመሳሳይ ክንውኖችን ያመለክታሉን?

ከላይ የተሰጡትንና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ ሥፍራን በጥንቃቄ ብንመለከት ነቢያት በረጅም ዘመን ልዩነት የሚፈረቁትን ክንውኖች ጐን ለጐን የማስቀመጥ ልምድ እንደነበረቸው እንረዳለን:: የኢየሱስን የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ምፅዓቱን ጐን ለጐን አስቀምጠዋቸዋል:: በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ የኢሳይያስን ትንቢት ለመፈጸም መምጣቱን ተናግሮአል፤ ይሁን እንጂ «የእግዚአብሔርን የበቀል ቀን» ለማወጅ መምጣቱን ግን አልተናገረም:: ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት ኢዩኤል የተናገረው ትንቢት በሐዋ/ሥራ 2 ተፈጽሞአል:: ይሁን እንጂ በመጨረሻው ዘመን ብቻ የሚፈጸሙ ሌሎች ትንቢቶችንም በዚሁ ክፍል ተናግሮአል::

እነዚህ ወጸፊት ሌላ መንግሥት ይነሣል የሚሉ ሰዎች ዳንኤል ስለ ምስሉ የእግር ጣቶች (ምንም እንኳ ዳንኤል ቁጥረቸውን ባይገልጽም እነርሱ ግን 10 ናቸው ይላሉ) መጥቀሱ ወደፊት ስለሚነሣው መንግሥት ያመለክታል በማለት ይናገራሉ:: ይህ መንግሥት በቀድሞው የሮም መንግሥት መሠረት ላይ ይመሠረታል:: አሥር መሪዎችን ስለሚያቀፍ በአንድ መሪ እንደሚመራ መንግሥት ፍጹም ሕብረት አይኖረውም:: በመከፋፈሉም ምክንያት ከፊሉ ብረት (ጠንካራ) ከፊሉ ደግሞ ሸክላ (ደካማ) ሆኖአል:: ይህ መንግሥት ሥልጣን የሚይዘው በመጨረሻው ዘመን እንደሚሆን ያምናሉ:: በክርስቶስ ተቃዋሚ ሥር ሆኖ ዓለምን ይቆጣጠራል:: ኢየሱስ ይህን የመጨረሻ መንግሥት ከደመሰሰ በኋላ ነው በምድር ላይ የሚነግሠው:: እነዚህ 10 የእግር ጣቶች በዳንኤል ምዕራፍ 7 የተነገረላቸው 10 ቀንዶች እንደሆኑ ይናገራሉ:: ምዕራፍ 7 ላይ ስንደርስ ስለዚህ በሰፊው እንወያይበታለን:: ዳንኤል 2 የሌሎቹ ምዕራፎች ሁሉ መሠረት መሆኑን አስተውል:: የሰው መንግሥት በቅጽበት እንደሚወድም በዮሐንስ ራዕይ 19:11-21 ተገልጾአል::

በመጨረሻ በፍጻሜ ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት ይመጣል:: ይህ መንግሥት የራሱ የሆነ ቁልፍ ባሕርያት ይኖሩታል:: በመጀመሪያ:- በድንገት ይሆናል:: የሰው መንግሥት ዘላቂ ዋስትና ያለው መስሎ ይታያል:: ድንጋዩ ምስሉን በፍጹም እንዳጠፋው ሁሉ የእግዚአብሔርም መንግሥት የሰዎችን መንግሥታት ያጠፋቸዋል:: ሁለተኛ:- ሌሎች መንግሥታትን ሁሉ ያሸንፋል::

እግዚአብሔርና የርሱ መንግሥት በበላይነት ይገዛሉ። ይህን ሥልጣን የሚፎካከር ምንም መንግሥት ወይም ሕዝብ አይኖርም። ከዚያ በኋላ በምድር ላይ ክፋትን የሚያደርግ የሰው መንግሥት አይኖርም። ሦስተኛ:- የዘላለም መንግሥት ይሆናል። የሰው መንግሥት ጊዜያዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ ዘላለማዊ ነው። አራተኛ:- ይህ መንግሥት የእግዚአብሔር ብቻ ይሆናል። እግዚአብሔር ሥልጣኑን ወይም መንግሥቱን ለማንም ሕዝብ አይሰጥም። እርሱ ብቻውን በምድር ላይ ይገዛል።

19ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ይህ ትምህርት እንዴት ያጽናናሃል?
ለ/ በኢትዮጵያ ያሉትን ክርስቲያኖችስ እንዴት ያጽናናቸዋል?

የእግዚአብሔር መንግሥት ኃይል የሚታየው አንድን መንግሥት በማጥፋቱ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም መንግሥታት በማጥፋቱ ጭምር ነው። በዳንኤል 2:44 የተጠቀሱት መንግሥታት:- ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ አሕዛብን የሚገዙ መንግሥታት ናቸው። በምስሉ የተወከሉት መንግሥታት ሁሉ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ድንጋይ ማለትም በመንግሥቱ ይደመሰሳሉ። የዚያ መንግሥት ገዢ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሆናል። ምንም ፍንጭ እስከማይገኝላቸው ድረስ የሰዎችን መንግሥታት በሙሉ ይደመስሳል። ድንጋዩ የወደቀው ምንም እጅ ሳይነካው እንደነበር ሁሉ ይህም መግሥት የሚመሠረተው እንደቶች ሰብዓዊ እርዳታ ሳያስፈልገው በራሱ በእግዚአብሔር ይሆናል። ድንጋዩ ምድርን እስኪሞላ ድረስ ታላቅ ሆነ። ልክ እንደዚህ የእግዚአብሔርም መንግሥት ዓለምን ሁሉ ይቆጣጠረል። ማንም ሕዝብ ወይም መሪ የራሱ ሥልጣን አይኖረውም። ከሕልሙ ውስጥ ይህ ገና አልተፈጸመም። ስለዚህም የዚህ ሕልም ፍጻሜ የሚሆነው ወደፊት ነው ማለት ነው።

ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ምንድነው? በዚህም ጉዳይ ላይ ክርስቲያኖች ያላቸው አመለካከት ይለያያል። አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር መንግሥት የተባለው ቤተ ክርስቲያኒቱ ናት ይላሉ። ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ራሱ ክርስቶስ ስለሆነ የገሃነም ደጆች ሊቋቋሟት እንደማይችሉ ይናገራሉ። ቤተ ክርስቲያን አድጋ ምድርን ሁሉ ትሞላለች። በሕዝቡ ወይም በቤተ ክርስቲያኑ አማካይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ይነግሣል።

20ኛ ጥያቄ:- በዚህ ያምናሉ ብለህ የምታስበውን ትንቢታዊ አመለካከት ግለጽ።
21ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ማቴ.16:17-20፤ ሉቃ.13:18-21፤ 17:20-21።
ለ/ ከላይ የተመለከትነውን ሐሳብ በምን ሁኔታ የሚደግፉ ይመስልሃል?

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደልመጣቸ ቅዱሳት መጻሕፍት

ያመለክታል። የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመሠረተው በሰዎች ሁሉ ላይ ለመንገሥ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ነው።

22ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሬዕይ 19:11-20:6።

ለ/ እነዚህ ጥቅሶች ወደፊት ስለሚነሣው ታላቅ መንግሥት የሚያመለክቱ ይመስልሃልን?

ሐ/ ክርስቶስ ከመምጣቱ አስቀድሞ የሚሆኑ ነገሮች ምንድናቸው?

መ/ ምስሉን የሰበረው ድንጋይና የክርስቶስ መንግሥት መምጣት የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ምንም እንኳ አንዳንድ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ ብቻ እንደሆነች ቢሰማቸውም ይህ አባባል ከሌላው የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ አይደለም። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር መንግሥት በልባችንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈሳዊ ሁኔታ የተረጸመበት መንገድ አለ። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት የእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን አካላዊም ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ ክፉዎቹን የምድር መንግሥታት ያጠፋቸዋል። በመላው ዓለም ሕዝብ ላይ በጽድቅ ይነግሣል።

የሕልሙ ትርጓሜ እውነት መሆኑን ዳንኤል ለንጉሥ ናቡከደነፆር ያረጋግጥለታል። ስለ ወደፊት የተነገረው ጉዳይ ሁሉ ይሆናል። እግዚአብሔር ለዓለም ያለው ዕቅድ ሁሉ ይፈጸማል። የእርሱ መንግሥት ያሸንፋል፤ በሰዎች መንግሥት ሁሉ ላይ ይነግሣል።

የሕልሙን ትርጓሜ ሲሰማ ናቡከደነፆር በጣም ተገረመ። ልቡ ተነካ። በዳንኤል ፊት ወደቀ፤ ይህንንም ያደረገው ሊያመልከው ሳይሆን አምላኩን ለማክበር ነበር። ዳንኤል የታላቁ የሰማይ አምላክ ወኪል መሆኑን ተረዳ። የእህል ቁርባንና እጣን ለዳንኤል እንዲቀርብለት በማዘዙ ያከበረው እግዚአብሔርን ነበር። በባቢሎን ከነበሩት አማልክት ሁሉ ይልቅ የዳንኤል አምላክ እንደሚበልጥ ለመገንዘብ ተገደደ። እርሱ «የአማልክት አምላክ» ነው። እርሱ ከዓለም ነገሥታት የሚበልጥ ታላቅ ነው። እርሱ የንጉሦች ንጉሥ ነው። የዳንኤል አምላክ የወደፊቱን ሁኔታ ይገልጣል። ናቡከደነፆር ለነፍሱ ደህንነት የሚሆን እምነት በእግዚአብሔር ላይ አልነበረውም። ይሁን እንጂ እርሱ ከሚያመልካቸው አማልክት የሚበልጥ አምላክ በሰማይ መኖሩን ለማመን ተገደደ።

ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም። በግላቸው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝና ጌታ በእምነት መቀበል አለባቸው። ናቡከደነፆር እግዚአብሔርን አከበረ እንጂ ሙሉ በሙሉ በእርሱ አላመነም። ራሱን ከእግዚአብሔር ይልቅ የማስቀደም ፍላጐት

እንደነበረው በሚቀጥለው ሳምንት ትምህርት እንመለከታለን:: ዛሬ በዓለም ላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ ሞቱ የሚያውቁ ብዙ ሰዎች አሉ:: አንዳንዶቹም ክርስቲያን መሆናቸውን ይናገራሉ:: በግል ሕይወታቸው ግን በኢየሱስ ላይ የሚታመኑ አይደሉም:: ኃጢአተኛ መሆናቸውን አይገነዘቡም:: ለጸህንነት እንዲሆናቸው ኢየሱስን ብቻ መመልከት አይፈልጉም:: ከዚህ ይልቅ መልካም ነገርን በማድረግ በመልካም ሥራቸው መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ይሞክራሉ:: ስለ ኢየሱስ ሞት በአእምሮ ብቻ የተመሠረተ ዕውቀት ስላላቸው ክርስቲያን የሆኑ ይመስላቸዋል:: በግል ካላመነውና ሕይወታችንም ካልተለወጠ በስተቀር እምነታችን ሐሰትና የሞተ ነው::

23ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ኃጢአተኛ መሆንህንና የኢየሱስ ሞት የኃጢአትህን ዋጋ ለመክፈል እንደሆነ የተገነዘብከው መቼ ነበር?
ለ/ የግልህ አዳኝ ያደረግከው መቼ ነበር?
ሐ/ ያን ውሣኔ ካደረግህ ወዲህ ሕይወትህ በምን ሁኔታ ተለወጠ?

ናቡከደነፆር ዳንኤልን አከበረው:: ከፍተኛ ስጦታ ሰጠው:: በባቢሎን ግዛት ውስጥ ባቢሎን በምትባለው ዋነኛዋ ክፍለ ሀገር ውስጥ ከፍተኛውን ሥልጣን እንዲይዝ አደረገው:: ከጠቢባን ሁሉ በላይና የንጉሡ ዋና አማካሪ አደረገው:: ይሁን እንጂ ዳንኤል ይህን ሁሉ ክብር አልፈለገም:: ሕልሙን የተረጐመው ብቻውን ሳይሆን ከሦስት ጓደኞቹ ጋር መሆኑን ለንጉሡ ገልጿል:: በጸሎታቸው በጣም ረድተውታል:: ስለዚህም ንጉሡ እነርሱንም ደግሞ አከበረቸው፤ ከዳንኤል ሥልጣን በታች ባለሥልጣኖች አደረጋቸው::

እግዚአብሔር የዳንኤልን እምነት አከበረ:: ይህ እምነቱ በመጀመሪያ የታየው በምዕራፍ 1 ራሱን ላለማርከስ ባደረገው ውሣኔ ነበር:: የንጉሡን ሕልም እንደሚገልጽለት በማመኑም እምነቱን አስመሰከረአል:: ዳንኤል እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥፍራ ታማኝ ነበር:: ስለዚህም እግዚአብሔር በምድር ላይ ታላቅ በነበረው ንጉሥ ፊት የእርሱ ወኪል እንዲሆን አደረገው:: እኛስ እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ ታማኞች ነን? እግዚአብሔር ታማኝ የሆኑትን ያከብረቸዋል::

እግዚአብሔር የወደፊቱን ሁኔታ ለናቡከደነፆር እንዴት እንደገለጸለት ተመልክተናል:: ተራ በተራ በምድር ስለሚነሡ አራት የአሕዛብ መንግሥታት ነገረው:: የመጀመሪያው:- የባቢሎን መንግሥት ነው:: እርሱም በወርቅ ራስ ተመስሎአል:: ሁለተኛው:- በብር ደረትና ክንዶች የተመሰለው የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ነው:: ሦስተኛው:- በነሐስ የተመሰለው የግሪክ መንግሥት ነው:: አራተኛውና የመጨረሻው:- በብረት የተመሰለው የሮም መንግሥት ነው:: ቢሆንም ከቀድሞው የሮም መንግሥት ሌላ በብረትና በሸክላ የሚመስል ሌላ አምስተኛ መንግሥት የሚነሣ ይመስላል:: እያንዳንዱ መንግሥት

ከእርሱ በፊት የነበረውን መንግሥት ይቆጣጠረል። በመጨረሻ ግን ምስሉ የአሕዛብ መንግሥታት ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚደመሰሱ ያመለክታል። በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሚቋቋመው የእግዚአብሔር መንግሥት ከዘላለም እስከ ዘላለም ጸረስ ይኖረል። ያ መንግሥት ቶሎ ቢመጣ ምንኛ መልካም ነበር? የዚህን ትንቢት ዋና ዋና ሐሳብ በአጭሩ ለመረዳት ከፈለግህ በትምህርት አሥረ ሦስት መጨረሻ ላይ ያለውን ሠንጠረዥ ተመልከት።

24ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 2ጴጥ.3:10-15 አንብብ።
ለ/ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመጣበትን ጊዜ እናውቃለንን?
ሐ/ የእግዚአብሔር መንግሥት ሲመሠረት የሚሆኑ አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?
መ/ ሌላ መንግሥት መምጽጣቱን ካወቅን ዘንዳ እንዴት ነው መኖር ያለብን?
ሠ/ የዚህን መንግሥት መምጣት እንዴት ልናፋጥነው እንችላለን?

አረተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ክለስ፤ የውይይቱን ጥያቄዎች እንደገና ተመልከት።

አምስተኛ ቀን          ሳምንታዊ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ የእግዚአብሔር መንግሥት የአሕዛብን መንግሥት እንደሚቆጣጠር በተግባር የታየው እንዴት ነው?
2/ ይህ ቁጥጥር ሁልጊዜ የሚታይ ነውን?
3/ ክርስቲያኖች ዘወትር ዓይኖቻቸውን «እግዚአብሔር በሠረተና በፈጠረት ከተማ ላይ» ሊያኖሩ የሚችሉት እንዴት ነው? (ዕብ.11:10)

ለ. 1/ መጽሐፍ ቅዱስ «በመጨረሻው ቀን» እንደምንኖር ይናገረል፤ በእነዚህ ቀኖች ውስጥ መኖረችንን የምናውቀው እንዴት ነው?
2/ እነዚህ ቀኖች ገና ወደፊት የሚመጡትስ እንዴት ነው?

ሐ. 1/ በናቡከደነፆር ሕልም የታየው ምስል የአሕዛብ መንግሥታት ብርቱዎች መሆናቸውን የሚያሳየን እንዴት ነው?
2/ ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ሲነፃፀሩ ደካማ መሆናቸውን የምንረዳው እንዴት ነው?
3/ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘላለማዊና ከአሕዛብ መንግሥታት በላይ መሆኑን የምናየው እንዴት ነው?

መ. 1/ ስለ ብረቱና ሸክላው እግሮች የተነገረው ትንቢት ተፈጽሞአል ብለህ ታስባለህን?
2/ ለምን?
3/ ትንቢቱ ተፈጽሞአል የሚለው አስተሳሰብ ድክመት ምን ይመስልሃል?
4/ ትንቢቱ ስለ ወደፊቱ የሚያመለክት እንጂ ገና አልተፈጸመም የሚለው አመለካከት ድክመትስ ምንድነው?

5. ጸሎት።

## ትምህርት ሰባት

## ዳንኤል 3

### የመጀመሪያ ቀን

«ናቡከደነፆር ሆይ፥ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምከውም ለወርቁ ምስል እንዳን ሰግድለት እወቅ አሉት» (ዳን.3፡16-18)።

ባለፈው ሳምንት በምድር ላይ ስለሚነሡት አራት ታላላቅ መንግሥታት ተመልክተናል። እነዚህም መንግሥታት ታላቅ ኃይል ያላቸው መስለው ይታያሉ። ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ሲነፃፀሩ ግን በጣም ደካማ ናቸው። አንድ ቀንም ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክብሩ ወደዚህ ምድር ይመለሳል። የምድር መንግሥታት ሁሉ ይሸነፋሉ፤ እርሱም በምድር ላይ ይነግሣል።

በአሕዛብ መንግሥታት ሥር ስላሉ ክርስቲያኖችስ ምን እንላለን? በክፉ መንግሥታት ጭቆና ሥር ያሉትን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሊረዳቸው ይችላል ወይስ እስከ ዘመናት መጨረሻ ድረስ ይቆያል? ለዚህ መልስ

በዳንኤል ምዕ.3 እናገኛለን። እዎ፤ በዘመናችን ባለው ክፋት ውስጥ እንኳ እግዚአብሔር የሕዝቡን ሕይወት እንደሚቆጣጠር ምንም ጥርጥር የለንም። ዳንኤል ምዕ.3 በተለያዩ ስደት ውስጥ ላሉ ክርስቲያኖች መመሪያና ችግሩን የሚቋቋሙበትን መንገድ ያመለክታል።

በዚህ ክፉ ዓለም የሚኖሩ ክርስቲያኖች በታላቅ ውጥረት ውስጥ ናቸው። የዚህም ውጥረት ምክንያቱ ክርስቲያን የሁለት ዓለም ዜጋ በመሆኑ ነው። የምድራዊው መንግሥት ዜጋ ነው፤ የሰማያዊውም መንግሥት ዜጋ ነው። ክርስቲያን ለሁለቱም መንግሥታት ኃላፊነት አለበት። ከዚህ ኃላፊነት የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ውጥረት ይፈጠራል።

ክርስቲያን አባል ለሆነበት ምድራዊ መንግሥት ኃላፊነት አለበት። ይህም ኃላፊነት የተለያዩ መልክ ሊኖረው ይችላል።

በመጀመሪያ:- መንግሥታችንን ወይም ሕዝባችንን በጸሎታችን ልናስብ ይገባናል። (ጳውሎስ ስለ ክፋው የሮም መንግሥት በ1ኛ ጢሞ.2:1-2 የሰጠውን ትእዛዝ ተመልከት።) እግዚአብሔር ለአገሪቱን ሰላም እንዲሰጥ መጠየቅ አለብን። ምንም እንኳ በእርሱ ባያምኑም እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣቸው ለሀገሪቱን መሪዎች መጸለይ አለብን።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ስለ ሀገርህና ስለ መሪዎችህ የጸለይከው መቼ ነበር?
ለ/ እግዚአብሔር የሀገርህን መሪ እንዲባርከው፥ ጥበብ እንዲሰጠውና በሀገሪቱ ሰላም እንዲኖር ጊዜ ወስደህ አሁኑኑ ጸልይ። ይህም ክፋት በበዛበት ሕብረተ ሰብ ውስጥ እግዚአብሔርን በማምለክ እንድትኖር ነው።

ሁለተኛ:- ለሀገሪቱን መሪዎች የመታዘዝ ኃላፊነት እንዳለብን ተገልጾአል፤ (ሮሜ 13:1-7)። ጳውሎስ አስተዳዳሪዎች ለመልካም የተሾሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች መሆናቸውን ተናግሮአል። ጳውሎስ የሚናገረው በብረት ስለተመሰለው ስለ ሮም መንግሥት ነበር። የሮም መንግሥት መንግሥታትን የደመሰሰ ጨካኝ ነበር። ይሁን እንጂ ሕዝቡን ለመሪዎቻቸው እንዲታዘዙ ይነግረቸዋል። እኛም በተቻለን መጠን ለመሪዎቻችን መታዘዝ አለብን።

እኛ ክርስቲያኖች ይህን የምናደርገው በአንድ ዋና እውነተኛ ምክንያት ነው። መንግሥታትንም ሆነ መሪዎችን የሚያስነሣ ራሱ እግዚአብሔር ነው። አንድ መሪ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ የሆነ ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም።

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:- ምሳሌ 21:1፤ ኢሳ.40:21-24፤ 41:1-4።

ለ/ በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔር የአሕዛብ መሪዎችን የሚቆጣጠረው እንዴት ነው?

ክርስቲያኖች የሌላ መንግሥት ዜጐችም ናቸው፤ (ፊልጵ.3:20 ተመልከት)። ኢየሱስ ክርስቶስ የንጉሦች ንጉሥ፥ የጌቶችም ጌታ ነው። የሕይወታችን ዋነኛ ንጉሥ እርሱ መሆን አለበት።

የሁለቱ መንግሥታት ትእዛዝ በሚጋጩበት ጊዜ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለበት? ክርስቲያን ከምድራዊ ንጉሥ ይልቅ ለንጉሦች ንጉሥ ትእዛዝ መታዘዝ አለበት። ሰማያዊው ንጉሥ ከምድራዊው ንጉሥ ቅድሚያ ማግኘት አለበት። ምድራዊው ንጉሥ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚጻረር ትእዛዝ ካዘዘን፥ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ አለብን።

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሐዋ/ሥራ 4:1-21ን አንብብ።
ለ/ ከኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ጋር የሚጻረር ነገር እንዲያደርጉ በተነገራቸው ጊዜ ጴጥ መዛሙርቱ የሰጡት መልስ ምንድነው?

ለምድራዊ መሪዎቻችን በማንታዘዝበት ጊዜ ይህን ማድረግ ያለብን በትዕቢት ወይም በጋጠ-ወጥነት መሆን የለበትም። በቁጣ መመለስ የለብንም። ከዚህ ይልቅ የማንታዘዝበትን ምክንያት በትሕትና ልንገልጽላቸው ይገባል። ከዚያም በኋላ ባደረግነው ውሳኔ ምክንያት የሚመጣብንን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለብን። በዚህ ሳምንት ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎ የንጉሡን ምስልና የባቢሎንን ሕዝብ ጣዖት እንዴት አናመልክም እንዳሉ እንመለከታለን። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመተላለፍ ይልቅ ሞትን መረጡ። ለንጉሡ ከሰጡት መልስ (ዳን.3:16-18) ሁለት ነገሮችን ለማየት እንችላለን።

በመጀመሪያ:- ሙሉ በሙሉ እምነታቸውን በእግዚአብሔር ላይ አደረጉ። እርሱ ከምድር ነገሥታት ሁሉ በላይ ነው። ከሚደርስባቸው ቅጣት ሊያድናቸው ኃይል አለው። እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው ተማምነው ነበር። ዳን.3 እንዴት አድርጐ እግዚአብሔር ከእሳት እንዳዳናቸው ይናገራል።

ሁለተኛ:- ከሚደርስባቸው ቅጣት እግዚአብሔር እንደሚታደጋቸው ምንም ዋስትና አልነበራቸውም። ሕዝቡን ማዳን ወይም ቅጣቱን እንዲቀበሉ የሚወስን እግዚአብሔር ብቻ ነው። በሁለቱም ቢሆን እርሱ ይከበራል።

4ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዕብ.11:32-40 አንብብ።
ለ/ እግዚአብሔር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሕዝቡን ከቅጣት እንዳዳነ ግለጽ።
ሐ/ እግዚአብሔር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሕዝቡ ቅጣትን

እንዲቀበሉ እንዳፈቀደ ግለጽ።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ክርስቲያኖች የመሪዎቻቸውን ትእዛዝ ሊቃወሙ የሚችሉት የተሰጣቸው ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር የሚጻረር ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። የምንገዳል ብንሆን እንኳ ለዘላለማዊው ንጉሥ መገዛት አለብን።

5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ እንዲህ ያለ ውጥረት በምን ዓይነት መንገድ በሕይወትህ እንደተከሰተ ግለጽ።
ለ/ መሪዎቹ የተላለፉት የትኛውን ትእዛዝ ነበር?
ሐ/ አንተስ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ መለስክላቸው?
መ/ እግዚአብሔር ከቅጣት አዳነህ ወይስ ቅጣቱን እንድትቀበል በጸጋው ረዳህ?

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳን.3ን አንብብ።
ለ/ ናቡከደነፆር ሕዝቡን ሁሉ ያዘዘው ምን እንዲያደርጉ ነበር?
ሐ/ አይሁዳውያን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑት ለምንድነው?
መ/ ሦስቱ አይሁዳውያን ምን ሆኑ?
ሠ/ ለእግዚአብሔር በመታዘዛቸው እርሱ እንዴት ሊከብር ቻለ?

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 3:1-18

## ጥያቄዎች

7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ናቡከደነፆር ምን ሠራ?
ለ/ ምን ያህል ትልቅ ነበር?
8ኛ ጥያቄ:- በምርቃቱ ሥነ ሥርዓት ላይ እንዲገኙ ናቡከደነፆር እነማንን ጠራ?
9ኛ ጥያቄ:- ናቡከደነፆር ለመሪዎቹ ሁሉ የሰጠው ትእዛዝ ምንድነው?
10ኛ ጥያቄ:- ናቡከደነፆር ለሚያምፁት ምን ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው?
11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ አይሁዳውያኑን ማን ከሰሳቸው?
ለ/ ለምን ነበር የከሰሷቸው?
12ኛ ጥያቄ:- ከዳን.3:15 እንደምንረዳው ናቡከደነፆር የእግዚአብሔርን ኃይል በተመለከተ የተናገረው የድፍረት ቃል ምንድነው?
13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሦስቱ ወጣቶች እንዴት ነበር የመለሱት?
ለ/ በዚህ ጊዜ ዳንኤል የት የነበረ ይመስልሃል?

ዳንኤል 3፥ 4፥ 5 እና 6 ዳንኤል በባቢሎንና በሜዶ-ፋርስ ዘመነ መንግሥት ስለተፈጸሙ የተለያዩ ክንውኖች ይገልጻል። እነዚህ ታሪኮች የተጻፉት በምርኮ የነበሩት አይሁዳውያን በታማኝነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ለማበረታታት ነው። እነዚህ ታሪኮች ሁለት እውነቶችን ያመለክታሉ። በመጀመሪያ:- ለእውነት በመቆማቸው ምክንያት ሲሰደዱ ሕዝቡን ሊጠብቃቸው እንደሚችል ያሳያሉ። ይህንንም በዳንኤል 3 እና 6 እናመለከታለን። ሁለተኛ:- በማያምኑ መሪዎች ሕይወት እንኳ የእግዚአብሔር ኃይል እንዴት እንደሚገለጽ ያመለክታሉ። ዳን.4 እና 5 ይህንኑ ያስተምራሉ።

ባለፈው ሳምንት ናቡከደነፆር በሪዕይ ስላየው ምስል ተመልክተናል። ይህ ሪዕይ ከዳንኤል ዘመን እንሥቶ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚመጣበት ድረስ በምድር ላይ ስለሚነሡት አራት ዋና ዋና መንግሥታት ያመለክታል። የመጀመሪያው መንግሥት ባቢሎን በወርቅ ራስ ተመስሉአል።

ዛሬ ደግሞ ስለ ሌላ ምስል እንመለከታለን። ይህ ናቡከደነፆር በባቢሎን ከተማ አጠገብ ያቆመው ምስል ነው። በዳን.2 እና 3 የስንት ዓመት ልዩነት እንዳለ እርግጠኞች አይደለንም። ምናልባትም ብዙ ዓመታት ሳይኖሩ አይቀሩም።

የዱራ ሜዳ ከባቢሎን ከተማ ጥቂት ኪሎ ሜትር ወጣ ብሎ የሚገኝ ሜዳ ነው። ምስሉ በዚያ ቦታ የቆመው ብዙ ሰዎች እንዲያዩትና እንዲያመልኩት ነው። ምናልባትም ናቡከደነፆር በሪዕይ ያየው ምስል ትዝ ሳይለው አልቀረም። ስለዚህም በእንጨት ተሠርቶ በወርቅ የተሸፈነ ምስል ሠራ። ይህ ምስል 27 ሜትር ርዝመት፥ 2.7 ሜትር ስፋት ነበረው። ይህ ምስል በሰው መልክ የተሠራ ለመሆኑ ምንም አያጠራጥርም። አንዳንድ ሰዎች ይህ ምስል በሪዕይ ያየው ምስል ወይም የራሱ የናቡከደነፆር ምስል እንደነበር ይናገራሉ። ምናልባትም ይህ ምስል ከባቢሎናውያን አማልክት የአንዱ ምስል ሳይሆን አይቀርም።

ናቡከደነፆር ይህን ምስል ያቆመው ለተለያዩ ምክንያት ነበር። በመጀመሪያ:- የመንግሥቱን ፖለቲካዊ አንድነት ለማሳየት ነበር። ስለዚህም ይህን ምስል እንዲያከብሩ ገዢዎች ከተለያዩ አገሮች ተጠሩ። መሪዎቹ ሁሉ እንደሚታዘዙትና እንደሚያከብሩት ለማረጋገጥ ፈለገ። ሁለተኛ:- ምናልባት ምስሉ የጣዖት ከሆነ፥ ይህን ያደረገው ሕዝቡን በአንድ ሃይማኖት ለማስተሳሰር ይሆናል። ሦስተኛ:- በሰው ለመከበር በመፈለጉ ነው። ናቡከደነፆር ታላቅነቱን ለማሳየት ፈለገ። እንደዚህ ዓይነት ትልቅ ምስል በማሠራቱ ሊከበር ፈለገ። ለምስሉ እንዲሰገዱ በማድረግ በሕዝቡ ላይ ያለው ሥልጣንና ኃይል እንዲታወቅለት ፈለገ። ምስሉ የራሱ ከሆነም ለመመለክ የነበረውን ፍላጐት

የመለከታል። በዚያ ዘመን ነገሥታት የአማልክት ተወካዮች እንደሆኑና መመለክ እንዳለባቸው ይታመን ነበር።

ምስሉ ከቆመ በኋላ፥ ለምርቃቱ ናቡከደነፆር ትልቅ ግብዣ አደረገ። በመጀመሪያ በባቢሎን የነበሩትን መሪዎች ሁሉ ጠራ። እነዚህ መሪዎች ከሀገር አስተዳዳሪዎች እንሥቶ እስከ የገምጃ ቤት ሹሞችና የወረዳ ዳኞችን የያዙ ነበሩ። እያንዳንዱ መሪ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ ነበር። ያለ ጥርጥር ናቡከደነፆር ከእርሱ በታች ያሉትን ባለሥልጣናት ተሰብስበው ሲያይ ትዕቢት ሳይሰማው አይቀርም።

ይህ ታላቅ በዓል ሲከበር ናቡከደነፆር የተለያዩ ሙዚቀኞችን እንዲሰበሰቡ አዝዞ ነበር። በበዓሉ ላይ ሙዚቃ እንዲያሰሙና ሕዝቡ መቼ ለምስሉ ወድቀው መስገድ እንዳለባቸው እንዲያስታውቁ ነበር የተጠሩት። የሙዚቃውን ድምፅ ሲሰሙ:- ተሰብስበው የነበሩት መሪዎች ወድቀው ለምስሉ እንዲሰግዱ አዋጅ ነጋሪው በግልጽ አስታውቋል። ለምስሉ ያልሰገዱ ግን በእሳቱ እቶን ውስጥ እንደሚጣሉ ማስጠንቀቂያ ጨምሮ ሰጥቶአቸው ነበር።

እስቲ ራስህን በዚያ ሜዳ ላይ እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሙዚቃው እየተጫወተ ነው። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በምስሉ ፊት ወድቀው እየሰገዱ ነው። እዚያ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር? ለምስሉ ትሰግድ ነበር ወይስ ምስሉን አላከብርም በማለት ቀጥ ብለህ ትቆም ነበር? ሙዚቃው መጫወት ሲጀምር ከሦስት ወጣቶች በቀር ሁሉም መሪዎች ወድቀው ሰገዱ። ምስሉን ለማምለክ ፈቃደኛ ያልሆኑ ወጣቶች:- ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጐ ብቻ ነበሩ።

14ኛ ጥያቄ:- ሦስቱ ወጣቶች ለምስሉ ቢሰግዱ ኖሮ የትኛውን ትእዛዝ ይተላለፉ ነበር? ዘፀ.20:1-6 ተመልከት።

ለጣዖት እንዳይሰግዱ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አዝዞአቸው ነበር። እስራኤልና አይሁዳውያን ወደ ምርኮ የተወሰዱበት ዋነኛው ምክንያት ጣዖት በማምለካቸው ስለነበር ነው። እነዚህ ሦስት ታማኝ ወጣቶች ጣዖት በማምለክ ከአባቶቻቸው ኃጢአት ጋር መተባበር አልፈለጉም። ዳንኤል ይህን እውነተኛ ታሪክ የጻፈው ምንም እንኳ ሕይወታቸውን የሚጠይቅ ቢሆንም ጣዖትን ሳያመልኩ ለእምነታቸው እንዲሞቱ ሌሎች አይሁዳውያንን ለማደፋፈር ነው።

ምንም እንኳ ናቡከደነፆር እነዚህን ሦስት ወጣቶች ባያስታውሳቸውም ከለዳውያኑ ግን አስታውሰዋቸው ነበር። ከለዳውያን የባቢሎን ሃይማኖት መሪዎች መሆናቸውን ታስታውሱ ይሆናል። እነዚህ ከለዳውያን በአይሁዳውያን ላይ፤ በተለይም በዳንኤል፥ ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎን ላይ ከባድ ጥላቻ

እንደነበረቸው አያጠረጥርም። እነዚህ ሰዎች በሀገሩ ውስጥ በጣም የተከበሩ ሰዎች ነበሩ። አሁን ግን ዳንኤልና ጓደኞቹን የመሳሰሉ የባዕድ አገር ሰዎች ስፍረቸውን ወስደውባቸዋል። ለሀገሩ ባዕድ የሆነው የአይሁድ ሃይማኖትም የሀገሩን ሃይማኖት እየተጋፋ ነበር። ምንጊዜም ቢሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእውነት ጸንተው ሲቆሙ የተለያየ ተቃውሞ እንደሚደርስባቸው የታወቀ ነው።

15ኛ ጥያቄ:- ክርስቲያኖች ለእውነት ጸንተው ሲቆሙ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ በሌሎች ሊጠሉ እንደሚችሉ ዘርዝር። ከመሥሪያ ቤት፥ ከትምህርት ቤት፥ ከሃይማኖት ...ወዘተ አንዳንድ ምሳሌዎችን ጥቀስ።

የሃይማኖት መሪዎች የነበሩት ከለዳውያን ሦስቱን ወጣቶች በሁለት መንገድ ከሰሱዋቸው። በመጀመሪያ:- የናቡከደነፆርን ሕግ እንደተቃወሙ አጥብቀው ተናገሩ። እርሱንም ሆነ ያቆመውን ምስል አላከበሩም። ከዚህም ሌላ አልናዘዝም ስላሉት በመንግሥቱ መሪዎች ሁሉ ፊት ተዋረደ። ናቡከደነፆርን በጣም ያስቆጣውም ይህ ነበር። የሁሉ በላይ ገዢ ስለነበረ፥ ከሥሩ ካሉት መሪዎች መካከል አንዱ እንኳ ሳይታዘዝለት ቀርቶ አያውቅም። ሁለተኛ:- ወኪላቸው ናቡከደነፆር የሆነው የባቢሎን መንግሥት አማልዕክት የሆኑትን ባለማገልገላቸው ከለዳውያን ከሰሱዋቸው። ሦስቱ በሃይማኖት የተጣመሩ ባይሆኑ ኖሮ ናቡከደነፆር እንዳሚገባ ሊቆጣጠረቸው ባልቻለም ነበር።

ሲድረቅ ሚሳቅና አብድናጐ በናቡከደነፆር የተወደዱ እንደነበር ጥርጥር የለበትም። ምናልባትም በባቢሎን ግዛት ውስጥ ጥሩ አስተዳዳሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ይሁን እንጂ በሌሎች መሪዎች ፊት መዋረድ የለበትም። ከዚህ ቀደም አንድም መሪ ተቃውሞት አያውቅም። ሦስቱን ሰዎች ወደፊት እንዲመጡ አደረገ። ለእነርሱ ከነበረው አክብሮት የተነሣ ምስሉን እንዲያመልኩ ሌላ ዕድል ሰጣቸው። የሃይማኖት መሪዎቹ የከሰሱዋቸው በምቀኝነት እንደሆነ ቢያውቅም። ካልታዘዙት ወደ እሳቱ እቶን እንደሚጣሉ አስጠንቀቆአቸው ነበር። ከእርሱ ፍርድ የሚያድናቸው የትኛው አምላክ እንደሆነም ጠየቃቸው። ናቡከደነፆር ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ ከእርሱ የተለየ አምላክ እንዳላቸው ያውቅ ነበር። ዳንኤል ሕልሙን በተረጐመለት ጊዜ የእግዚአብሔር ኃይል ምን ያህል ታላቅ እንደነበር ተረድቶአል። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ይልቅ ታላቅ እንደሆነ ራሱን ቆጠረ። አነጋገሩም እግዚአብ ሔርን የሚገዳደር ነበር። እግዚአብሔር ከክፋዎች ነገሥታት እጅ ታማኝ ልጆቹን ሊያድናቸው ይችላልን? ከሞትስ ሊያድናቸው ይችላልን?

በዚህ ታሪክ ውስጥ ዳንኤል ለምን እንዳሌለበት ብዙ ሰዎች ይደነቃሉ። ይሁን እንጂ እንደ ሦስቱ ጓደኞቹ ሁሉ እርሱም ለጣዖቱ እንደማይሰግድ እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ምናልባትም ይህ ታላቅ በዓል በሚደረግበት

ወቅት ለሥራ ጉዳይ ወደ ሩቅ ሥፍረ ሄዶ ሊሆን ይችላል።

ሦስቱ ወጣቶች በእግዚአብሔር በማመናቸው ሞት ቢጠብቃቸውም አልፈሩም። ንጉሡ ይቅርታ እንዲያደርግላቸውም አልለመኑትም። ከዚህ ይልቅ ግን በሦስት አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች መልስ ሰጡት። በመጀመሪያ:- ከንጉሡ ጋር መከራከር አልፈለጉም። ስለ እምነታቸውም ሊያስረዱት አልፈለጉም። ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር እጅ አኖሩ። ሁለተኛ:- ለንጉሡ የአምላካቸውን ኃይል ነገሩት። ምንም እንኳ ናቡከደነፆር እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው ባያስብም እነርሱ ግን ሊያድናቸው እንደሚችል ያውቁ ነበር። እግዚአብሔር ከማንኛውም ንጉሥና ከታላቁ ናቡከደነፆርም እንኳ ቢሆን የላቀ ነው። ሦስተኛ:- እግዚአብሔር ሊያድናቸው ፈቃደኛ ባይሆን እንኳ ለምስሉ እንደማይሰግዱ ነገሩት። የሚያመልኩት እውነተኛውን አምላክ ብቻ ነው። ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር እጅ አኖሩ፤ የንጉሡንም ትእዛዝ ተቃወሙ። ለምን እንዲቀጡ እንደፈቀደ በእግዚአብሔር አሠረር ላይ ጥያቄ አላቀረቡም። እግዚአብሔር ከሁሉም ሁኔታዎች በላይ እንደሆነ ያውቁ ነበር። ስለዚህም ለእርሱ ፈቃድ ተገዙ።

በምድራዊ መንግሥትና በሰማያዊ መንግሥት መካከል በሚደረገው ውጊያ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ታማኝ ልጆች በመካከል ይጠመዳሉ። ያለ ምክንያትም ይከሰሳሉ፥ ይሰደዳሉ። ይሁን እንጂ ከመሸሽ፥ ከመደበቅና የክፉ ነገሥታትን ቃል የተቀበሉ መስለው ከመታየት ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝና ሕይወታቸውን ለእርሱ አደራ መስጠት አለባቸው። በሞትም ይሁን በሕይወት ታማኝና ታዛዥ መሆን አለባቸው።

16ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሲድረቅ፥ ሚሳቅ ወይም አብድናጐን ብትሆን ኖሮ ምን ታደርግ ነበር?
ለ/ እስከሞት ድረስ ታማኝ ትሆን ነበር?
ሐ/ በቅርብ ዓመታት ክርስቲያኖች ተመሳሳይ ውሣኔዎችን እንዴት ነበር የተቋቋሚቸው?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 3:19-30

## ጥያቄዎች

17ኛ ጥያቄ:- ሦስቱ ወጣቶች ለምስሉ ለመስገድ ፈቃደኛ ባልሆኑ ጊዜ ናቡከደነፆር ምን አደረገ?
18ኛ ጥያቄ:- ሦስቱን ወጣቶች ወደ እሳት የወረወሩዋቸው ወታደሮች ምን ሆኑ?
19ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ናቡከደነፆር የተደነቀው ለምንድነው?

ለ/ በእሳት ውስጥ ምን አየ?

20ኛ ጥያቄ:- በተአምር ባይሆን ኖሮ በሦስቱ ወጣቶች ላይ ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል ዘርዝር::

21ኛ ጥያቄ:- ስለ ሦስቱ ሰዎች አምላክ ናቡከደነፆር ለሕዝቡ ምን ዓይነት ትእዛዝ ሰጠ?

22ኛ ጥያቄ:- ናቡከደነፆር እግዚአብሔርን እንዴት አከበረ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ሲድረቅ÷ ሚሳቅና አብድናጎ ለንጉሡ ትእዛዝ ባልታዘዙ ጊዜ ንጉሡ በጣም ተቆጣ:: ከዚህ ቀደም ሌላ ዕድል ሰጥቶአቸው ነበር፤ አሁን ግን እንዲገደሉ ፈለገ:: ንጉሡ ለእርሱ ታማኝ ያልሆነውን ሁሉ አያከብርም:: ስለዚህም የእቶኑ እሳት ሰባት እጥፍ እንዲነድ አዘዘ::

ሦስቱ ወጣቶች የተጣሉበት እሳት ምን ዓይነት እንደነበር እርግጠኛ አይደለንም:: ምናልባትም ሰዎች ትልቅ ድስት÷ ብረት÷ ወዘተ እያቀለጡ የሚሠሩበት የእሳት ፍም የሞላበት ሰፊ ጉድጓድ ሳይሆን አይቀርም:: ወንጀለኞች የሚቀጡት በዚህ እቶን ውስጥ ነበር::

እቶን እንደሚገባ እስኪግል ድረስ ንጉሡ ራሱ ሲጠባበቅ ነበር:: ሦስቱ ወጣቶች ለማምለጥ በማይችሉበት ሁኔታ እንዲታሠሩ ንጉሡ አንዳንድ የታወቁ ወታደሮችን አዘዘ:: ቅጣቱ በሦስቱ ወጣቶች ላይ ሲፈጸም ለማየት በሚያስችለው ሥፍራ ተቀመጠ:: እቶኑ በጣም ከጋለ በኋላ ሦስቱ ወጣቶች ወደ እሳቱ ተጣሉ:: እቶኑ በጣም ግሎ ስለነበር ወጣቶቹን የጣሉዋቸው ወታደሮች በእሳቱ ነበልባል ሞቱ::

ሦስቱ ሰዎችስ ምን ሆኑ? እግዚአብሔር እምነታቸውን አክብሮ ይታደጋቸው ይሆን? ንጉሡ እያየ ሦስቱ ወጣቶች በእሳቱ ውስጥ ወዲያ ወዲህ መመላለስ ጀመሩ:: «የአማልክት ልጅ» የሚመስል አራተኛ ሰው አብሮአቸው ነበር:: ከእሳቱ ለመውጣት በቻሉ ነበር፤ እነርሱ ግን ከአራተኛው ሰው ጋር እያወሩ እዚያው ቆዩ::

ይህ አራተኛ ሰው ማን ይሆን? የሰው መልክ ነበረው:: ይህ ሰው ናቡከደነፆር እንደገመተው መልአክ ይሆን? (ዳን.3:28) ምናልባትም ሦስቱ ሰዎች በእሳት እንዳይጐዱ ለማድረግ ከእግዚአብሔር የተላከ መልአክ ሊሆን ይችላል:: ብዙዎች ግን ይህ አራተኛ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በመልአክ ተመስሎ እንደሆነ ይናገራሉ::

ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ሦስቱ ወጣቶች በእሳቱ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ሲመላለሱ በማየቱ ንጉሡ በጣም ተደንቋል:: በአራተኛው ሰው መልክ

ሳይጸነቅ አይቀርም፡፡ ሦስቱን አይሁዳውያንንም ከእሳቱ እንዲወጡ ነገራቸው፡፡ ልዩ በመሆናቸውም «የልዑል አምላክ ባሪያዎች» በማለት ጠራቸው፡፡ ከእሳቱ ከወጡም በኋላ የንጉሡ ባለሥልጣኖች እንደሚገባ መረመሩዋቸው፡፡ ታሥረውበት የነበረው ገመድ በእሳት ቢቃጠልም እነርሱ ግን አልተቃጠሉም፡፡ ለብሰውት የነበረው ልብስና ፀጉራቸው ምንም አልተለበለበም፥ አልተቃጠለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ጭስ ጭስ አይሸቱም ነበር፡፡ በእርግጥም ይህ ታላቅ ተአምር ነው፡፡

ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጐ በመታዘዛቸው እግዚአብሔርን አስመሰገኑ፡፡ ናቡከደነፆርም በእግዚአብሔር ላይ ስለነበራቸው እምነትና ስለታዛዥነታቸው አመሰገናቸው፡፡ ማንም በአምላካቸው ላይ የስድብን ቃል እንዳይናገርም አዋጅ አስነገረ፡፡ ይህን ትእዛዝ ያፈረሰ ሁሉ በንጉሡ ይቀጣል፡፡ ምንም እንኳ ናቡከደነፆር የጣዖት አምልኮውን ባይተውም የሲድራቅ፥ የሚሳቅና የአብድናጐ አምላክ ከአማልክት ሁሉ እንደሚበልጥ ለማመን ተገደደ፡፡ እርሱ ራሱ እንደተናገረው፡- እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና፡፡ በመጨረሻም ለሦስቱ ከፍተኛ ሥልጣን ሰጣቸው፡፡

ከዚህ በኋላ ስለ ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጐ አናነብም፡፡ ምን ያህል በሥልጣን ላይ እንደቆዩ፥ ወይም በሕይወት እንደኖሩ አናውቅም፡፡ ሦስቱ ወጣቶች ግን እስከ ሞት ድረስ ለእምነታቸው በመቆማቸው ዛሬም ቢሆን ለክርስቲያኖች መልካም ምሳሌነት አላቸው፡፡ በዚህ ክፉ ዓለም እንዴት እንደምንኖር መልካም ምሳሌዎቻችን ናቸው፡፡ በምዕራፍ 1 ላይ የባቢሎናውያንን ትምህርትና አኗኗር ላለመቀበል ከዳንኤል ጋር ስላደረጉት ውሣኔ ተመልክተናል፡፡ በባዕድ ምድር እንኳ ለአምላካቸው ታማኝ ሆነው ተገኙ፡፡ በምዕራፍ 2 ከዳንኤል ጋር ታማኝ የጸሎት ሰዎች ሆነው አይተናቸዋል፡፡ በምዕራፍ 3 ደግሞ በእምነታቸው ላይ የተቃጣውን ከፍተኛ ፈተና ተመልክተናል፡፡ በእምነታቸው ለመሞት ፈቃደኛ ነበሩን? ለመሞት ፈቃደኛ ነበሩ፤ እግዚአብሔር ግን ስሙን ለማስከበር ሲል አዳናቸው፡፡ በዚህ ክፉ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔርን ማስከበር በጣም ከባድ ነው፡፡ የዓለምን መንገድ መከተል ግን በጣም ቀላል ነው፡፡ ለእምነታችን ጸንተን እንድንቆም ከተፈለገ ግን ከዓለም የሚቀርብልንን ማንኛውንም ፈተና መቋቋም አለብን፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆነን ለመገኘት መወሰን አለብን፡፡ ከዓለም መሪዎች ትእዛዝ በላይም አምላካችንን ለማስከበር ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡ እርሱ የንጉሦች ንጉሥ፥ የጌቶችም ጌታ ነው፡፡ የሕይወትህ ጌታ ነውን?

23ኛ ጥያቄ፡- ሀ/ የክርስቶስ ጌትነት በሕይወትህ የሚታየው እንዴት ነው?
ለ/ በአኗኗርህ?
ሐ/ ሕይወትህን ከኃጢአት በመጠበቅህ?
መ/ ሞት እንደሚጠብቅህ ብታውቅም እንኳ ለእግዚአብሔር በመታዘዝህ?

አረተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከለስ፤ የውይይት ጥያቄዎችንም እንደገና ተመልከታቸው::

አምስተኛ ቀን:- የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ ዜጋ የሆንክባቸው ሁለት መንግሥታት ምንድናቸው?
 2/ ለሁለቱም መንግሥታት ያለብህ ኃላፊነት ምንድነው?

ለ. 1/ የሁለቱ መንግሥታት ትእዛዝ ሲጋጭ ምን ይሆናል?
 2/ ክርስቲያን መታዘዝ ያለበት ለየትኛው መንግሥት ነው?
 3/ ይህ ውጥረት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ራሱን እንደሚገልጽና ክርስቲያኖች እንዴት ሊቀበሉት እንደሚገባ ግለጽ::

ሐ. 1/ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣት ትእዛዞች አንዳንድ ጊዜ ከሰዎች መንግሥት ጋር ሊያጋጩዋት ስለሚችሉ አንዳንድ ትእዛዞች ግለጽ::
 2/ በትክክል የእግዚአብሔር ትእዛዛት ናቸውን ወይስ የቤተ ክርስቲያን ባሕል?
 3/ ቀጥተኛውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደምናከብር ሁሉ የሰዎችንም ባሕል ማክበር ይኖርብናል?

5. ጸሎት::

## ትምህርት ስምንት

## ዳንኤል 4

የመጀመሪያ ቀን:-

ልዑልም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሰለጥን ለሚወድደውም እንዲሰጠው እስክታውቅ ድረስ ... ሰባት ዘመናት ያልፉብሃል» (ዳን.4:25)::

ስለ ትንቢት እስጠና ዋናው ትምህርት የወደፊቱን የሚመለከት ብቻ

መሆን የለበትም ከዚህ ይልቅ በሕዝቦች፥ በግለሰቦችና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሆኑት ሁኔታዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር በታች መሆናቸውን ለእግዚአብሔር ልጆች ሊያሳዩዋቸው ይገባል። ይህም የመቆጣጠር ኃይሉ በአሁኑ ጊዜ እንኳ በሕይወታችን እየታየ ቢሆንም ለወደፊቱም ቢሆን ሊቆጣጠረን ይችላል። ይህም በችግርና በመከራ ጊዜ እንኳ በእርሱ ታምነን እንድንኖር ያደርገናል።

በዚህ በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ እንደሆነ ተመልክተናል። በመጀመሪያ:- ዳንኤልና ጓደኞቹ በናቡከደነፆር ትምህርት ቤት እንዲማሩ በተመረጡበት ወቅት ታይቶአል፤ (ዳን.1)። ሁለተኛ:- በናቡከደነፆር ሕልም ውስጥ እግዚአብሔር ከመንግሥታት ሁሉ በላይ እንደሆነ ተመልክተናል። የትኛው መንግሥት በየትኛው ላይ እንደሚገዛና ያ መንግሥት ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ የሚወስነው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ያለፈውን ታሪክ እንዲሁም የመንግሥታቱ የወደፊት ሁኔታ የሚወሰነው በእግዚአብሔር ነው፤ (ዳን.2)። ከዚያ በኋላ ደግሞ በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ የሚሆነውን ሁሉ ሲቆጣጠር እንመለከታለን። ስለ እሳቱ ምድጃ የተነገረው ታሪክ ላይ:- በመከረና በስደት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ እንደሆነ እናያለን። በሞትም ይሁን በሕይወት እግዚአብሔር ካልፈቀደለት በቀር አንዳች ሊነካን የሚችል ነገር የለም፤ (ዳን.3)። በዳንኤል 4 ደግሞ እግዚአብሔር የአሕዛብ ገዢዎችን እንደሚቆጣጠር እንመለከታለን። ምንም ያህል ታላቅ ቢሆን ሊገዛ የሚችለው እግዚአብሔር ስለፈቀደለት ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር ሊበልጥ አይችልም። እንዲገዛ የመረጠው እግዚአብሔር ነው። በፈቀደው ወቅት እግዚአብሔር የገዢነት ዘመኑን ሊያሳጥረው ይችላል።

ናቡከደነፆር በዘመኑ የነበረ ታላቅ መሪ ነው። ብዙ የተለያዩ መንግሥታትን ሲቆጣጠር ነበር። በብረት በትር በጭካኔ ሲገዛቸው ነበር። እንደሌሎች መሪዎች ሁሉ ናቡከደነፆር ትዕቢተኛ ነበር። የፈለገውን ሁሉ ለማድረግ የሚችል መስሎ ይታየው ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለናቡከደነፆርም ሆነ ለእኛ ትምህርት ሊሰጠን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ታላቁን ሰው ወደ እንስሳነት ደረጃ ዝቅ አደረገው። በዚህም ናቡከደነፆር ለማንኛውም ነገር በተለይም ለጤንነቱ በእግዚአብሔር መደገፍ እንዳለበት ተማረ።

ብዙዎቻችን ሕይወታችንን የምንቆጣጠረው እኛ እንደሆንን እናስባለን። እቅድ እናወጣለን። የፈለግነውንም እናደርጋለን። ይሁን እንጂ ጤንነታችንን ጨምሮ ማንኛውንም መሠረታዊ ነገር ለማግኘት በእግዚአብሔር የምንደገፍ መሆናችንን ግን እንዘነጋለን። (ያዕ.4:13-16 ተመልከት።) የምናቅደውንም ሆነ የምናደርገውን የምንፈጽመው እግዚአብሔር ሲፈቅድልን ብቻ ነው። ስለዚህም በኑሮአችን አንዳችም የምንታበይበት ምክንያት አይኖረንም።

ምንም ያህል ክፉ ወይም ታላቅ ቢሆኑም የዚህ ዓለም መሪዎችም ከእግዚአብሔር ቁጥጥር በታች ናቸው። የፈለጉትን ሁሉ የማድረግ ችሎታ እንዳላቸው ሊያስቡ ይችላሉ፤ እቅዳቸውን የሚያጨናግፉ ምንም ነገር ሊመጣ እንደማይችል ያስባሉ። ነገር ግን ሕይወታቸው በእግዚአብሔር እጅ ነው። ለዓላማው ይጠቀምባቸዋል። ከፈቀደም ዝቅ ሊያደርጋቸው ይችላል።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ እግዚአብሔር የሕይወታችን ተቆጣጣሪ መሆኑን የሚያሳዩ ጥቂት ሁኔታዎችን ግለጽ።
ለ/ እግዚአብሔር በሕዝብ መሪዎች ሕይወት ተቆጣጣሪ መሆኑን የሚያሳዩ ሁኔታዎችን ግለጽ።
2ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 4ን አንብብ።
ሀ/ የናቡከደነፆርን ሕልም ግለጽ።
ለ/ የምዕራፉ ዋነኛ ትምህርት ምንድነው?
ሐ/ በመጨረሻ ናቡከደነፆር ምን ሆነ?
መ/ ናቡከደነፆር ስለ እግዚአብሔር የተማረቸውን እውነቶች ግለጽ።

<u>ሁለተኛ ቀን</u>    <u>ክፍል አንድ:- ዳንኤል 4:1-18</u>

## <u>ጥያቄዎች</u>

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 4ን የጻፈው ማነው?
ለ/ ይህ ያልተለመደ የሆነው ለምንድነው?
ሐ/ የምዕራፉ መልእክት ለማን የተጻፈ ነው?
4ኛ ጥያቄ:- በዳንኤል 4:3 ላይ ናቡከደነፆር እግዚአብሔርን ስላመሰገነባቸው የተለያዩ ነገሮች ግለጽ።
5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የናቡከደነፆርን ሕልም ሊተረጉሙ ያልቻሉት እነማን ናቸው?
ለ/ ማን ሕልሙን ሊተረጉም ቻለ?
6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ናቡከደነፆር በሕልሙ ስላየው ዛፍ ግለጽ።
7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዛፉ ምን ሆነ?
ለ/ በዛፉ ላይ ይህ እንዲሆን ያዘዘው ማነው?
ሐ/ ስለ ጉቶው የተሰጠው የመጨረሻ መመሪያ ምን ነበር?
8ኛ ጥያቄ:- የዚህ ሕልምና ፍርድ ዓላማ ምንድነው?

## <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ (ኮሜንታሪ)</u>

ዳንኤል 4 ልዩ ምዕራፍ ነው። ልዩ የሚያደርገውም እሕዛብ በሆነ ሰው መጻፉ ነው። የዚህ ምዕራፍ ዋነኛ ጸሐፊ ናቡከደነፆር ነው። (ቁጥር

1-18፤ 28-37።) እግዚአብሔር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ በሕይወቱ እንዳሠረ ይናገረል። ብዙ ሰዎች የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር በእርግጥ ስለማመኑና ደህንነትን ስለማገኘቱ ይደነቃሉ። በትክክል የምናውቀው ነገር የለንም። የምናውቀው ነገር ቢኖር፥ ይህንን የማያምንና ትዕቢተኛውን ሰው ዝቅ እንዳደረገውና ሕይወቱንም ሊቆጣጠረው እንደሚችል እንዳሳየው ብቻ ነው። በመጨረሻም ናቡከደነፆር የእርሱ መንግሥት ጊዜያዊ መሆኑን ተረዳ። እግዚአብሔር ግን ለዘላለም የሚኖር መንግሥት አለው። ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጻጸር በጣም ታናሽ ነው።

ናቡከደነፆር ይህን ትእዛዝ ነገሥታት ለሕዝባቸው በሚጽፉበት መንገድ ጽፎታል።

በመጀመሪያ:- ይህ ትእዛዝ የራሱ የናቡከደነፆር እንደሆነ ይናገረል።

ሁለተኛ:- ትእዛዙ ለማን እንደተጻፈ ይናገረል። ትእዛዙ የተጻፈው ለዓለም ሕዝብ ነበር። ይህ በብዙ ነገጽ ላይ ከሚገዛ ንጉሥ የተጻፈ ደብዳቤ እንደመሆኑ መጠን በግዛቱ ሁሉ መዳረስ ነበረበት።

ሦስተኛ:- ንጉሡ ሰላምታውን ሲጽፍ ለመላው ሕዝብ ሰላምን እንደ ሚመኝላቸው ይገልጻል።

በአረተኛ ደረጃ:- ስለ አዋጁ ዓላማ ለሕዝቡ ይገልጽላቸዋል። ትእዛዙ ወይም አዋጁ በምስክርነት መልክ ነበር። ዓላማውም የዘላለማዊው አምላክ ኃይል በሕይወቱ እንደተገለጸ ለሕዝቡ ለማስታወቅ ነው።

ናቡከደነፆር በሁለት መንገድ እግዚአብሔርን አከበረ። በመጀመሪያ:- በሕይወቱ ስለተደረገው ነገር እግዚአብሔርን አከበረ። የእግዚአብሔርንም ሥራ:- «ተአምረትና ድንቅ» ብሎታል። ይህም የእግዚአብሔርን ሥራ ለመግለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለመደ የአገላለጽ መንገድ ነው። (ለምሳሌ ያህል ነህምያ 9:10 ተመልከት።) ናቡከደነፆር በሕይወቱ የተደረገው ተራ ሁኔታ እንዳልሆነ አስተዋለ። እግዚአብሔር ልዩ በሆነ መንገድ በሕይወቱ ሠርቶአል። ተአምራዊ ሁኔታዎች ናቸው።

9ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ እንዴት በተአምራዊ ሁኔታ እንዳሠረ ግለጽ። ጊዜ ወስደህ ስላደረገው ነገር እግዚአብሔርን በጸሎት አመስግነው፥ አክብረውም።

ሁለተኛ:- ስለ ታላቅነቱ ናቡከደነፆር እግዚአብሔርን አከበረ። ናቡከደነፆር እግዚአብሔርን «ልዑል እግዚአብሔር» በማለት ጠረው። ይህም ናቡከደነፆር እግዚአብሔር ከማንኛውም አምላክ ወይም መሪ በላይ እንደሆነ መገንዘቡን ያመለክታል። ይህም ታላቅነቱ በዘላለማዊ መንግሥቱ ይታያል።

የሰው መንግሥት ይነሣል ይወድቃል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን (ፈቃዱን፥ ዓላማውንና ግዛቱን ጨምሮ) ዘላለማዊ ነው።

በሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ ናቡከደነፆር የሰላምና የብልጽግና ዘመን ሆኖለታል። ጦርነቶቹ ሁሉ ተፈጸሙ። ተቃዋሚ ወገኖቹም ጽል ተመቱ። ባቢሎንንም ታላቅና አስደናቂ ከተማ አደረጋት። ስለዚህም በሥራውና ባገኘው ውጤት ታበየ።

አንድ ሌሊት አስፈሪ ሕልም አለመ። በአስቸኳይ በምድሩ የነበሩ የሃይማኖት መሪዎችንና አማካሪዎቹን ጠራቸው። እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ከፍተኛ ሕልምን የመተርጐም ችሎታ እንደነበረቸው ከምዕራፍ 2 ተመልክተናል። ናቡከደነፆር ሕልሙን ነገረቸው። ነገር ግን እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ሕልሙን ሊተረጉሙለት አልቻሉም። ዳንኤል ለምን አብሮአቸው እንዳልነበረ አናውቅም፤ በኋላ ግን እንዲመጣ ተደርጐአል።

ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረት እንደነበረው ናቡከደነፆር ለመገንዘብ ችሎአል። ሕይወቱ ከሌሎች የተለየ ነው። እንደሌሎቹ ጠቢባን አልነበረም። «የቅዱሳት አማልክት መንፈስ» በዳንኤል ውስጥ እንደነበር ራሱ ናቡከደነፆር ተናገረ። ናቡከደነፆር በብዙ አማልክት እንጂ በአንድ አምላክ ብቻ የማያምን ሰው እንደሆነ አስተውሉ። ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ በሆነ ሁኔታ እንደሚመላለስ ናቡከደነፆር ተረዳ። ይህንን በመረዳቱም ነው ዳንኤል ሕልሙን ለመተርጐም እንደሚችል እርግጠኛ የሆነው። ዳንኤል (በአሕዛብ ብልጣሶር በመባል የሚታወቀው) የተከበረው በናቡከደነፆር ብቻ ሳይሆን በመላው የሀገሪቱ ሰዎችም የተከበረ ነበር። (የዳንኤል ዝናና ክብር ምን ያህል ሰፊ እንደነበር ለማረጋገጥ ይህ መጽሐፍ በተጻፈበት ዘመን የተጻፈውን የነቢዩ ሕዝቅኤልን መጽሐፍ 28፡3 ተመልከት።)

ናቡከደነፆር ዳንኤልን፡- «የሕልም ተርጓሚዎች አለቃ» በማለት ጠራው። ይህም ናቡከደነፆር ለዳንኤል የነበረውን አክብሮት ያሳያል። ዳንኤል እንደ ባቢሎን አገር ሕልም ተርጓሚዎች በአስማት የሚጠቀም ሰው አልነበረም፤ እንደ እነርሱ አይጠነቁልም ነበር፤ (ዳን.4፡7)። አንዳንዴ «የሕልም ተርጓሚ» «ምሑር» ብለን መተርጐም ይቻላል። ዳንኤል በጣም የታወቀ ዋነኛ የንጉሥ አማካሪ ነበር። ዳንኤል ሥጦታ ስለነበረውና ከእግዚአብሔርም ጋር የተቀረረበ ስለነበር ምስጢሩን የመረዳት ችሎታ እንዳለው ናቡከደነፆር ተረድቶአል።

ናቡከደነፆር ሕልሙን ለዳንኤል ነገረው። በምድር መካከል አንድ ዛፍ ነበረ። ዛፉ በጣም ትልቅ ነበር። ቅርንጫፎቹ ምድርን የሚሞሉና እስከሰማይ የሚደርሱ ይመስሉ ነበር። ዛፉ በጣም ትልቅ ከመሆኑም ሌላ ብዙ ፍሬ ስለነበረው የምድር አራዊትና የሰማይ አእዋፍ በፍሬው ረክተው ነበር። በድንገት አንድ መልአክ ከሰማይ ወረደ። ዛፉ እንዲቆረጥ፥ ቅርንጫፎቹ እንዲመለመሉና ፍሬዎቹም እንዲበተኑ አዘዘ። በሥሩ ተጠልለው የነበሩ

አረዊት ሁሉ መበታተን ነበረባቸው። ይሁን እንጂ ጉቶው እዚያው መሆን አለበት። ጉቶውን የሚመለከት ሌላ ትእዛዝ ተሰጠ። ሥሩ ተቆፍሮ መውጣት አልነበረበትም፤ ከመበስበስ እንዲጠብቀው በናስና በብረት ማሠሪያ ታስሮ መቆየት አለበት። መልአኩ መናገሩን ቢቀጥልም የተናገረው ስለዛፉ አልነበረም። የተናገረው ስለ አንድ ሰው ሲሆን ይህም ሰው በሰማይ ጠል (ዝናብ) መረስረስ ነበረበት። እንደ እንስሳ እንዲሆን የሰውዬው አእምሮ ይለወጣል። ይህም የሚሆነው «ለሰባት ዘመናት» ብቻ ነው።

ሕልሙ በእግዚአብሔርና በመልአኩ የታዘዘ ስለነበር መፈጸሙ የማይቀር ነው። በሕልሙና በትርጓሜው እግዚአብሔር በሰዎች መንግሥት ላይ ሥልጣን እንዳለው ሰዎች ሁሉ ይረዳሉ። እግዚአብሔር በታላላቅ ሰዎች ሕይወት እንኳ ሥልጣን አለው። ለፈቀደው መንግሥትን ይሰጣል። በጣም ዝቅተኛና ተራ ለሆኑ ሰዎች እንኳ እግዚአብሔር መንግሥትን ሊሰጣቸው ይችላል። በእርግጥ እግዚአብሔር ትሑታንን ያከብራል። ይህ ዓረፍተ ነገር ናቡከደነፆር ያሰብ ከነበረው ሀሳብ ጋር ተቃራኒ ነው። ናቡከደነፆር አሕዛብን ድል ያደረገውና ሊገዛቸው የቻለው በራሱ ኃይል እንደሆነ አሰበ። ይህ ትክክል እንዳልሆነ እግዚአብሔር ሊያሳየው ፈለገ።

እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር ስለ ዛፉ ያሳየው ሕልም ትልቅ ምስጢር አለው። በባቢሎን ፍርስራሽ ውስጥ አርኪኦሎጂስቶች አንድ የናቡከደነፆርን መንግሥት የሚወክል የዛፍ ሥዕል የነበረበት ገጽገጸ አግኝተዋል። ዛፍ የባቢሎናውያን ዓርማ ነበር። ከዚህም ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንግሥታት በዛፍ ይመሰላሉ። (ለምሳሌ ያህል ሕዝቅኤል 31ን ተመልከት።)

10ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር በገዢዎችና በግለሰቦች ሕይወት የበላይ መሆኑ በእንዴት ያለ ሁኔታ ሊያጽናናን እንደሚችል አንዳንድ ነጥቦችን ግለጽ።

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- የዳንኤል 4:19-27

## ጥያቄዎች

11ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል የተጨነቀውና «ለአንድ ሰዓት ያህል» ያሰበው ለምን ይመስልሃል?
12ኛ ጥያቄ:- ዛፉ ማንን ያመለክታል?
13ኛ ጥያቄ:- ታላላቅ ቅርንጫፎቹ ማንን ያመለክታሉ?
14ኛ ጥያቄ:- ይህ ፍርድ በናቡከደነፆር ላይ እንዲፈጸም ትእዛዝ የሰጠው ባለሥልጣን ማነው? (ዳንኤል 4:24)
15ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ናቡከደነፆር ምን ሆነ?
ለ/ ይህ የሚሆነው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

16ኛ ጥያቄ:- ጤንነቱ እንዲመለስለት ናቡከደነፆር ምን ማድረግ ነበረበት?
17ኛ ጥያቄ:- ጉቶው በምድር ውስጥ እንዲቀር የተደረገው ለምንድነው?
18ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ለናቡከደነፆር ምን ምክር ሰጠው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ዳንኤል ሕልሙን እንደሰማ ወዲያውኑ ትርጉሙን ተረዳ። ሕልሙ ለናቡከደነፆር አስደንጋጭ እንደሚሆን አወቀ። ስለዚህም እንዴት አድርጎ የሕልሙን ፍቺ እንደሚነግረው «ለአንድ ሰዓት ያህል» አሰበ። ለንጉሦች ክፉ ወሬ የሚነገሩ ሁሉ ይገደሉ እንደነበር አስተውል። ዳንኤል ለጥቂት ጊዜ ያህል አሰበ፤ ይሁን እንጂ ይህ በትክክል አንድ ሰዓት ላይሆን ይችላል።

ንጉሡ ያለአንዳች ፍርሃት ሕልሙን እንዲነግረው ዳንኤልን አደፋፈረው። ምንም እንኳ ትርጓሚው ክፉ ቢሆንም እንደማይገደል ነገረው። ምናልባትም ሕልሙ መጥሮ መልእክት እንዳለው ናቡከደነፆር ራሱ ሳይገምት እንደማይቀር አስባለሁ። ክፉም ይሁን ደግ ለማወቅ ፈለገ።

ዳንኤል ለብዙ ዓመታት ከናቡከደነፆር ጋር አገልግሎአል። ምናልባትም ከንጉሡ ዋነኛ አማካሪዎች አንዱ ሳይሆን አይቀርም። ለንጉሡ ከነበረው ፍቅር የተነሣ ዳንኤል ሕልሙ ለናቡከደነፆር ሳይሆን ለጠላቶቹ እንዲሆን ተመኘ። ነገር ግን ሕልሙ የሚያመለክተው ስለ ናቡከደነፆር ነበር።

እንደ ዛፉ የናቡከደነፆርም መንግሥት በጣም ታላቅ ነበር። አብዛኛውን የጥንት ዓለም ይሸፍን ነበር። እንደ ታላቅ የዛፍ ቅርንጫፎች ሁሉ የናቡከደነፆር መንግሥት ብዙ ሕዝብን ያጠቃልል ነበር። ምናልባት ስለነበረው ኃይል ናቡከደነፆር ትዕቢት ሳያድርበት አልቀረም። መንግሥትን የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ከመቀበል ይልቅ በራሱ ችሎታ እንዳገኘው አሰበ።

19ኛ ጥያቄ:- ሀ/ አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች በተለይም ክርስቲያን መሪዎች ስላከናወኑት ተግባር ይታበያሉን?
ለ/ አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

ዳንኤል «ልዑል አምላክ» እያለ የሚጠራው እግዚአብሔር ናቡከደናፆርን ሊያዋርደው (ዝቅ ሊያደርገው) ፈለገ። ዛፉ እንደተቆረጠ ሁሉ፥ ናቡከደነፆር በባቢሎን ላይ የነበረውም ሥልጣን ከእርሱ ይወሰድበታል። እርሱም ያብዳል። ከሕዝብ ተለይቶ ከአረዊት ጋር ይኖራል። እንደ እንስሳ ሣር ይበላል። ይህ ፍርድ የሚቆየው ለተወሰነ ጊዜ ነው። ሰባቱ ዓመት ከተፈጸመና እግዚአብሔር በእርሱና በሰዎች መንግሥት ላይ ያለውን ሥልጣን ከተረዳ በኋላ ይፈወሳል። «ሰማያዊው መንግሥት እንደሚገዛ» ናቡከደነፆር

መገንዘብ ነበረበት። ይህም በሰማይ የሚኖር እግዚአብሔር በሰዎች እንደሚሰለጥን ለናቡከደነፆር ለማስረዳት የተሰጠ ሌላ የአገላለጽ መንገድ ነው። እውነተኛ ሥልጣን የሚገኘው ከሰማይ እንጂ ከምድር አይደለም። ዳንኤልም መንግሥቱ እርሱን እንደሚጠብቀው ለናቡከደነፆር አረጋገጠለት። ጉቶው ከምድር ተቆፍሮ እንዳልወጣና በብረት ሰንሰለት እንደታሠረ ሁሉ ለናቡከደነፆርም መንግሥቱ ይቆየዋል።

በመጨረሻም ዳንኤል ለናቡከደነፆር አንዳንድ ምክር ሰጠው። ኃጢአቱን እንዲናዘዝ ነገረው። ይህም ንስሐ በጸባዩ መለወጥ መታየት ነበረበት። በኃጢአቱ ከመቀጠል ይልቅ መለወጥ አለበት። የጸባዩ ለውጥ ከሌሎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሁሉ መታየት ይኖርበታል። ሥልጣኑን መከታ አድርጐ ሌሎችን ከመጨቆን ይልቅ (ዳንኤል 5:18-19) ሕዝቡን በርኅራኄ መምረት አለበት። ናቡከደነፆር ይህን አድርጐ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም ባልተፈረደበት ነበር።

ዳንኤል ንስሐ ስለማድረግ መልካም ትምህርት ሰጥቶናል። ንስሐ ስናደርግ ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር መንገር ብቻ በቂ አይደለም። የበደልናቸውን ሰዎች ይቅርታ መጠየቅ ብቻም በቂ አይደለም። ይህን ማድረጋችን በጣም አስፈላጊ ቢሆንም በዚህ ብቻ ካቆመ ግን ያደረግነው ንስሐ እውነተኛ አይደለም ማለት ነው። እውነተኛ ንስሐ የጸባይ መለወጥ ማለት ነው። ስለ ሰረቅነው ነገር ይቅርታ ከጠየቅን በኋላ ከስርቆት ካልተቆጠብን በትክክል ንስሐ አላደረግንም ማለት ነው። ከሰረቅነው ሰው፥ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ይቅርታ መጠየቅና የሰረቅነውንም መመለስ አለብን፤ ጸባያችንም መለወጥ አለበት። ስርቆትን መተው አለብን።

20ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በሀገርህ ባሕል መሠረት «ንስሐ ማድረግ» ምን ማለት ነው?
ለ/ የሀገርህ ባሕል ጸባይህ በፍጹም ሳይለወጥ በአፍህ ብቻ ይቅርታ እንድትጠይቅ ይፈቅድልሃልን?
ሐ/ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለንስሐ የሚያስተምረው ነውን?
መ/ በግል ሕይወትህ ወይም በቤተ ክርስቲያንህ እውነተኛ ንስሐ ሳያደርጉ ንስሐ ያደረጉ መስሎ ለመታየት የሞከሩበትን ጊዜ ታስታውሳለህን? አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

አረተኛ ቀን ክፍል ሦስት:- ዳንኤል 4:28-37

ጥያቄዎች

21ኛ ጥያቄ:- የናቡከደነፆር ሕልም ሳይፈጸም ለምን ያህል ጊዜ ቆየ?

22ኛ ጥያቄ:- ናቡከጾነዖር የተናገረው፥ ትዕቢተኛነትን የሚገልጽ ቃል ምንጽነው?
23ኛ ጥያቄ:- ናቡከጾነዖር በትዕቢት ከተናገረ በኋላ ምን ሆነ?
24ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳን.4:32ን ከዳን.4:25 እና 4:17 ጋር አነጻጽር::
ለ/ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
ሐ/ ተደጋግመው የተነገሩት ለምን ይመስልሃል?
25ኛ ጥያቄ:- የናቡከጾነዖር የቅጣት ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ ምን ሆነ?
26ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳን.4:34-35ን ከዳን.4:2-3 ጋር አነጻጽር::
ለ/ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
27ኛ ጥያቄ:- ናቡከጾነዖር ከተፈወሰ በኋላ ምን ሆነ?
28ኛ ጥያቄ:- ስለምን ነበር ናቡከጾነዖር እግዚአብሔርን ያመሰገነውና ያከበረው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

እንደ አብዛኛዎቻችን ናቡከጾነዖር እግዚአብሔር በሕልሙ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ እንደሚገባ አላሰበበትም:: ወዲያውኑ እግዚአብሔር የነገረውን ረሳው:: አሥራ ሁለት ወር አለፈ:: አንድ ቀን በቤተ መንግሥቱ ሠገነት ላይ ሆኖ የባቢሎንን ከተማ በመመልከት ላይ እያለ በሠራው ሥራ በትዕቢት ተናገረ:: ያች ታላቅ ከተማ ክብሩንና ግርማውን የምታንጸባርቅ ነበረች::

29ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ «ባቢሎን» የሚለውን ቃል ተመልከት::
ለ/ ታላቅነትዋን የሚያመለክቱ አንዳንድ ነገሮችን ግለጽ::

ናቡከጾነዖር ስለ ብዙ ነገሮች ለመታበይ ይችላል:: ስለመሪነቱ የተናገርን እንደሆነ:- የባቢሎን መንግሥት ከአሦራውያን መንግሥት የሚበልጥ ነበር:: እርሱ የሠራት የባቢሎን ከተማ ከማንኛውም ጥንታዊ ዓለም የምትበልጥ ውብና ኃያል መንግሥት ነበረች:: (ኢሳ.13:19 ተመልከት::) በከተማይቱ ዙሪያ ያለው ቅጥር በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ በላዩ ጐን ለጐን ሆነው አራት ሠረገሎች ለማለፍ ይችሉ ነበር:: አማልክት የሚመለኩበት ብዙ ታላላቅ ቤተ መቅደሶች ነበሩዋት፤ (53ቱ ታውቀዋል፤) ቤተ መንግሥቱም በጣም ትልቅና ብዙ ዋጋ የወጣበት ነበር:: ከቤተ መንግሥት አጠገብ የተለያዩ አበቦችና ዛፎች ያሉበት ውብ መናፈሻ ነበር:: ይህ ሁሉ የናቡከጾነዖርን ችሎታ ያመለክታል::

ናቡከጾነዖር በመናገር ላይ እያለ፥ ስለሚጸርስበት ፍርድ ከሰማይ ድምፅ ሰማ:: ሕልሙም ተፈጸመ::

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «ሰባት ዘመናት» የሚለው ቃል ተደጋግሞ

ተጠቅሶአል። «ዘመን» የሚለው ቃል ምን ያህል ጊዜ እንደሚያመለክት አርግጠኛ አይደለንም። ምናልባትም ያልተወሰነ ጊዜን ወይም አንድ ዓመትን የሚያመለክት ይሆናል። አንዳንድ ምሑራን፡- ናቡከደነፆር ያበደው ለሰባት ዓመት እንደሆነ ይናገራሉ። ይህንኑ ቃል እንደገና በዳንኤል 7 እንመለከታለን።

ወዲያውኑ ናቡከደነፆር አበደ። እብደቱ በጣም ያልተለመደ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ዶክተሮችን ያጋጥማቸዋል። ይህ ዓይነት ሕመም ያደረበት ሰው ጸባይ ወደ እንስሳት ይለወጣል። በቤት ውስጥ ከመኖር ይልቅ በውጪ መኖርን ይመርጣል፤ እንደከብት ሣር ይበላል፥ ውኃን ብቻ ይጠጣል። ናቡከደነፆር እንደ እንስሳ ሆኖ «ለሰባት ዘመን» ኖረ። ፀጉሩና ጥፍሩ እንደ እንስሳ ሆነ።

ለሰባት ዓመታት ያህል መንግሥቱ እንዴት እንደተመራ አናውቅም። ናቡከደነፆር በቤተ መንግሥቱ አጠገብ ወይም በመናፈሻው ውስጥ ሳይኖር እንዳልቀረ እንገምታለን። ምናልባትም በዳንኤል የሚመሩት አማካሪዎቹ የአስተዳደሩን ሥራ ሳይሠሩ አልቀሩም። መንግሥቱን ለመውሰድ የተነሣ ሰው አለመኖሩ የሚያስገርም ነው። ምናልባትም ከረጅም ጊዜ በኋላ ናቡከደነፆር ወደ ሥልጣኑ እንደሚመለስ ዳንኤል ለሌሎቹ ነግሮአቸው ይሆናል። በማንኛውም ሁኔታ እንደተናገረው ሁሉ እግዚአብሔር የናቡከደነፆርን መንግሥት ጠበቀለት።

ሰባት ዓመት ተፈጸመ። ናቡከደነፆር ወደ ሕሊናው ተመለሰ፤ ዓይኖቹንም ወደ ሰማይ አንስቶ ለእግዚአብሔር ክብር ሰጠ። ወዲያውኑ ከሕመሙ ዳነ።

ከዚያም በጣም ደስ የሚል የምስጋና ቃል አቀረበ። ናቡከደነፆር ለተለያዩ ነገሮች እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

በመጀመሪያ፡- ስለዘላለማዊነቱ እግዚአብሔርን አመሰገነ። መንግሥቱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው። ግዛቱም ከትውልድ እስከ ትውልድና ዘላለማዊ ነው።

ሁለተኛ፡- እግዚአብሔርን ስለታላቅነቱ አመሰገነ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጻፀሩ ብዛታቸውንና ኃይላቸውን ጨምሮ የምድር ሰዎች ከምንም አይቆጠሩም። (ኢሳ.40:15-17)

ሦስተኛ፡- ከሁሉም በላይ በመሆኑ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ፈቃዱን ማንም ሊቃወም አይችልም። በምድርም ሆነ በሰማይ የፈቀደውን ያደርጋል። ስለሚያደርገው ነገር ማንም ጥያቄ ሊያቀርብለት አይችልም።

ብዙ ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር እነዚህን ሦስት ነገሮች አልተገነዘቡም። ብዙዎች እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚኖር ይመስላቸዋል። ታላቅና ከሁሉም በላይ መሆኑን ይዘነጋሉ። ጊዜው ሲከፋብንና አሕዛብም ሲቆጡ ብንደናገጥ ብዙ ላያስደንቅ ይችላል። (መዝ.2) ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር አሳየው። እንደዚሁም እግዚአብሔር ታላቅነቱን እንድናውቅ ይፈልጋል። እንደ ናቡከደነፆር ሁሉ እኛም እግዚአብሔርን ልናከብር ይገባናል።

30ኛ ጥያቄ:- ሀ/ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ትዘነጋለህን?
ለ/ ታላቅነቱን የሚያሳዩ አንዳንድ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ግለጽ።
ሐ/ ይህን ማወቅ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን ምን ያህል የሚያጽናናቸው ይመስልሃል?
መ/ ጊዜ ወስደህ እግዚአብሔርን ስለታላቅነቱ አመስግነው።

ከእብደቱ ከተፈወሰ በኋላ የናቡከደነፆር አማካሪዎች መጥተው ወሰዱት፤ መንግሥቱንም አስረከቡት። ምናልባትም የሀገሩ መሪዎች ናቡከደነፆርን በጣም ሳይወዱት አይቀሩም። ስለ እግዚአብሔር የነበረው አስተሳሰብ ከተለወጠ በኋላ ናቡከደነፆር እንደገና መግዛት ጀመረ፤ ከበፊቱ የበለጠ ባለጸጋ ሆነ።

ናቡከደነፆር አዋጁን የሚፈጽመው እንደገና እግዚአብሔርን በማመን ነው። እግዚአብሔር የሰማይ አምላክ ነው። ምንም እንኳ በምድር ብዙ አማልክት ቢኖሩም በሰማይ ያለው ግን አንድ አምላክ ብቻ ነው። የዳንኤል አምላክ ከፍጥረታቱ በላይ ሆኖ በሰማይ ይገዛል። ምንም እንኳ ለጊዜው ከባድ መስለው ቢታዩም የዚህ ታላቅ አምላክ ሥራ ምን ጊዜም ጽድቅና ትክክል ነው። አንድን ሰው ዝቅ ሲያደርግ ሌላውንም ከፍ ሲያደርግ ጥያቄ ልናቀርብለት አንችልም። ፍርዱ ትክክል ነው። ችግር በሕይወታችን ቢደርስም እርሱ ምን ጊዜም ትክክል መሆኑን አውቀን ልንቀበለው ይገባል።

ናቡከደነፆር መልእክቱን የሚደመድመው ዋና ዋና መንፈሳዊ መመሪያዎችን በመስጠት ነው። ትዕቢተኞችን እግዚአብሔር ያዋርዳቸዋል። በፊቱ ትሑታን ሆነው የሚታዘዙትን ሁሉ ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል።

31ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ምሳሌ 3:34፤ ያዕ.4:10፤ 1ጴጥ.5:5-6።
ለ/ ክርስቲያኖች ሊታበዩ ስለሚችሉበት መንገድ አንዳንድ ነጥቦችን ግለጽ።

እንደናቡከደነፆር ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖችም ክብርን ለራሳቸው ሊወስዱ ይፈልጋሉ። አንድን ሰው ወደ ጌታ ሲያመጡ ስላደረጉት ሥራ

ለሰዎች ሁሉ ያወረሉ። ብዙ ጊዜ መሪዎች በትዕቢት በጸል ያጸርጋሉ። ስለተጠቀመባቸው እግዚአብሔርን ከማመስገን ይልቅ ስላጸረጉት ታላቅ ሥራ መታበይ ይፈልጋሉ።

በአጭሩ:- ምዕ.4 የሚያስተምረን ዋነኛ ትምህርት ምንም እንኳ የማያምኑ ቢሆኑም እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ሥልጣን ያለው መሆኑን ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዳንኤል ይህን እውነት ሦስት ጊዜ በአንክሮ ይናገረል። (ቁጥር 17፤ 25፤ 32) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ሀሳብ ተጸጋግሞ ከተነገረ፥ እግዚአብሔር ስለዚያ ጉዳይ በጥንቃቄ እንድናስብ ይፈልጋል ማለት ነው። በጣም አስፈላጊ ነው ማለት ነው። ዳንኤል 4:3 እና 34 ተመሳሳይ ሀሳብ አላቸው። አምላካችን ነገሦአል። በሕዝቦች ላይ ይገዛል፤ በግለሰቦችም ላይ ይገዛል። ምንም እንኳ በምድር ላይ በግልጽ ባይታይም መንግሥቱ ዘላለማዊ ነው። ምንም የሚያስጸንቀው የለም። ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነ ምንም ነገር የለም። ክርስቲያን ወገኖቼ:- ያላችሁበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን በዚህ እውነት ተጽናኑ።

አምስተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ጥያቄ ከልሱ፤ የውይይቱን ጥያቄዎችንም እንጸገና ተመልከቷቸው።

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ አምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ በዳንኤል 4 ዋነኛው ትምህርት ምንድነው?
   2/ በኢትዮጵያ ውስጥ እግዚአብሔር በሁሉም ሁኔታ ላይ የበላይ መሆኑን እንዴት ማየት ይቻላል?
   3/ በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት ይታያል?
   4/ በሕይወትህስ እንዴት ይታያል?

ለ. 1/ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ንስሐን እንዴት ይረዳዋል?
   2/ ይህ ክርስቲያን ንስሐን ከሚረዳበት ሁኔታ እንዴት ይለያያል?
   3/ በሕይወታቸው ስላለው ኃጢአት እንጸሚገባ ንስሐ እንዲያጸርጉ ሌሎችን እንዴት ታስተምራቸዋለህ?
   4/ በሕይወቱ ስላለው ኃጢአት አንድ ሰው እንጸሚገባ ንስሐ ማድረጉን እንዴት ለማሳየት እንጸሚችል አንዳንድ ሀሳቦችን ግለጽ።

ሐ. 1/ በዳንኤል 4 የተገለጹ የተለያዩ የእግዚአብሔር ባሕርያትን ግለጽ።
2/ ይህ እውነት እንዴት ሊያጽናናን ይችላል?
3/ ይህን እውነት ለሌሎች ተስፋ የቆረጡ ክርስቲያኖች እንዲጽናኑበት እንዴት ልናስረዳቸው እንችላለን?

መ. 1/ ናቡከደነፆር እንዴት እንደታበየና ብዙ ክርስቲያኖች መሪዎች እንዴት ለመታበይ እንደሚችሉ አነጻጽር።
2/ እግዚአብሔር ትዕቢተኛውን ክርስቲያን የሚያዋርደው እንዴት ነው?
3/ የእግዚአብሔርን ክብር ለራሳችን የምንወስደው በምንና በምን መንገድ ነው?
4/ መሪዎች ትህትናቸውን ለማሳየት ስለሚችሉበት አንዳንድ መንገድ ግለጽ።

5. ጸሎት።

## ትምህርት ዘጠኝ

## ዳንኤል 5

### የመጀመሪያ ቀን

ንጉሥ ሆይ፥ ልዑል አምላክ ለአባትህ ለናቡከደነፆር መንግሥትንና ታላቅነትን፥ ክብርንና ግርማን ሰጠው። ... ብልጣሶር ሆይ፥ አንተ ልጁ ስትሆን ይህን ሁሉ እያወቅህ በሰማይ ጌታ ላይ ኰራህ እንጂ ልብህን አላዋረድህም። ...ትንፋሽህንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ አላከበርከውም። (ዳን.5:18፤ 22-23)

ከብልጣሶር ሕይወት የምንመለከተው መንፈሳዊ መመሪያ አለ። ይህም መመሪያ ሁለት ገጽታዎች አሉት። የመጀመሪያው ምንም እንኳ ልጆች በወላጆቻቸው ጥፋት በተለያዩ ሁኔታ በጸል ሊደርስባቸው ቢችልም፥ እግዚአብሔር ግን የአባቶች ኃጢአት በልጆች ላይ የማይፈርድባቸው መሆኑን ነው። አባቶች ለራሳቸው ኃጢአቶች ኃላፊዎች ይሆናሉ። (ጠቃሚ ገለጻ ለማግኘት ሕዝ.18:1-20 ተመልከት።)

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በወላጆች ኃጢአት ልጆች ይቀጣሉ በማለት የሚያምኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አሉን?

ለ/ ለእንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ምን መልስ ትሰጣለህ?

ሁለተኛ:- የአባት መንፈሳዊነት በምንም ዓይነት ለልጆች አይተላለፍም:: ማንኛውም ሰው ስለራሱ እምነት በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ነው:: አባት ለልጆቹ ሊያምንላቸው አይችልም:: የአባት እምነት ለልጆች አይተላለፍም:: እግዚአብሔርን ለመከተል እያንዳንዱ ልጅ መወሰን አለበት:: አንድ ሰው ከእስላም ቤተሰብ ስለተወለደ እስላም እንደማይሆን ሁሉ ከክርስቲያን ቤተሰብ በመወለዱም ክርስቲያን ሊሆን አይችልም::

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ወላጆቻቸው ስለጸኑ ብቻ እነርሱም የጸኑ የሚመስላቸው ወጣቶች አሉን?
ለ/ ይህ በቅዱሳት መጻሕፍት የተደገፈ ነውን?
ሐ/ እግዚአብሔርን ለመከተል ወይም ላለመከተል ለግላቸው እንዲወስኑ እንዴት ታስተምረቸዋለህ?

ይህ ሁለተኛው መመሪያ በዳንኤል 5 በግልጽ ይታያል:: ብልጣሶር የናቡከደነፆር ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ነው:: እግዚአብሔር ናቡከደነፆርን በምሪነት ሥልጣኑ መታበይ እንደሌለበት አስተምሮት ነበር:: ታላቁን መንግሥት የሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ነበር:: ይህን በመዘንጋቱ እግዚአብሔር ናቡከደነፆርን ወደ እንስሳነት ደረጃ እንዳዋረደው ባለፈው ሳምንት ተምረን ነበር:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ናቡከደነፆርን ማረው፤ እንደገናም ወደ መንግሥቱ መለሰው::

ናቡከደነፆር ከተዋረደ ምናልባት ከሰላሣ ዓመት በኋላ የነገሠው ልጁ ብልጣሶር መንግሥቱ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆኑን ዘነጋ:: በችሎታው በመመካቱ ነገሥታትን ከፍ ወይም ዝቅ የሚያደርጋቸው እግዚአብሔር መሆኑን ረሳ:: ሕይወቱ እንኳ በእግዚአብሔር እጅ መሆኑን ዘነጋ:: በታላቅ ትዕቢት ተነሣሥቶ አባቱ ናቡከደነፆር ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ያመጣቸውን የመቅደስ ዕቃዎች አረከሰ:: (ስለነዚህ የመቅደስ ዕቃዎች ለማንበብ ትምህርት ሦስትን ተመልከት::) ስለዚህም እግዚአብሔር ፈረደበት:: በዚያው ሌሊት መንግሥቱ ከእርሱ ተወሰደ:: ሕይወቱም አለፈ:: የሜዶንና የፋርስ ሕዝቦች መጥተው የባቢሎንን መንግሥት ደመሰሱ፤ ብልጣሶርንም ገደሉ::

ይህን መንፈሳዊ እውነት ዘወትር ማስታወስ አለብን:: በወላጆቻችን ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር በደለኛ አያደርገንም:: ምንም እንኳ በወላጆቻችን ኃጢአት ምክንያት በራሳችንና በቤተሰባችን ላይ የተለያየ ችግር ሊደርስብን ቢችልም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ የምንሆነው ስለራሳችን ኃጢአት ብቻ ነው:: ወላጆቻችን አማኞች ስለሆኑ ብቻ መዳን እንደማንችልም ማስተዋል አለብን:: እኛ ራሳችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና ለእርሱ መታዘዝ አለብን:: ምንም እንኳ የታላላቅ ወንጌላውያንና የቤተ

ክርስቲያን መሪዎች ልጆች ብንሆንም እምነታቸው ለእኛ ሊተርፈን አይችልም።

እስተዋይ ከሆንን እግዚአብሔር ለአባቶቻችንና ለቀድሞ ሰዎች ካስተማረው መንፈሳዊ ትምህርት ብዙ የምንማረው ይኖረናል። እነርሱ የተማሩትን ትምህርት ለመማር እነርሱ ባለፉበት ችግር ማለፍ ላያስፈልገን ይችላል። ከስሕተታቸውና ከመልካምነታቸው ልንማር እንችላለን። ይሁን እንጂ ታሪክ ራሱን ሲደጋገም ይታያል። ወጣቶች ከእነርሱ በፊት ከነበሩት ሰዎች ሕይወት ሲማሩ አይታይም።

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከታላላቆችህ ልትማር ስለምትችለው ትምህርት አንዳንድ ነጥቦችን ግለጽ።
ለ/ አንዳንድ መልካም ትምህርቶች ምንድናቸው?
ሐ/ ከሌሎች ልትማረው የማይገባህ አንዳንድ ስሕተቶች ምንድናቸው?

4ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 5ን አንብብ።
ለ/ ንጉሡ ማን ነበር?
ሐ/ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ምን ነገር አደረገ?
መ/ እግዚአብሔር እንዴት ተናገረው?
ሠ/ እግዚአብሔር ምን አለው? እንዴትስ ተፈጸመ?

በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር ለእርሱ ክብር ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነውን መሪ እንዴት እንዳዋረደው ከምዕራፍ 5 እንመለከታለን። የምድር መሪዎች ሕይወት በሙሉ በጌታችን እጅ ውስጥ ነው። ከ70 ዓመት በፊት በዳንኤል 2 የተነገረውን ትንቢት ፍጻሜ እንመለከታለን።

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 5:1-12

ጥያቄዎች

5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ «ብልጣሶር» የሚለውን ስም በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት።
ለ/ ስለዚህ ሰው ሕይወት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት የተረዳኸውን ሁሉ ግለጽ።

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ እግዚአብሔር በግድግዳው ላይ ሲጽፍ ብልጣሶር ምን እያደረገ ነበር?
ለ/ በግብዣው ላይ እነማን ነበሩ?

7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ብልጣሶር ወይን እንዲጠጣበት ምን እንዲመጣ አዘዘ?
ለ/ እነዚህን ዕቃዎች ከየት አገኛቸው?
ሐ/ ይህን ያደረገው ለምን ይመስልሃል?

መ/ ለምንድነው ይህ እግዚአብሔርን ያስቆጣው?

8ኛ ጥያቄ:- ወይን በመጠጣት ላይ እያለ ብልጣሶር ምን እንደተመለከተ ግለጽ።

9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ስለደረሰበት ችግር ምክር እንዲሰጠው ብልጣሶር በመጀመሪያ ያስጠረው ማንን ነበር?

ለ/ የጠረቸው ሰዎች ለብልጣሶር ምክር ለመስጠት ቻሉ?

10ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ሊረዳው እንደሚችል ለንጉሡ የነገረው ማነው?

11ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ንጉሡን ለመርዳት የሚያበቃ ምን ልዩ ዓይነት ስጦታ ነበረው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

በዳንኤል 1 የተጠቀሰው ሁኔታ ካለፈ 70 ዓመት ሆነው። (ከ606-539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት።) ንጉሥ ናቡከደነፆር፥ ታላቁ የባቢሎን ንጉሥ የሞተው ብዙ ዓመት ቀደም ብሎ በ562 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። ከእርሱ በኋላ ኢብል ሜሮዳክ፥ ኔሪጆሊሰር፥ ሬቦሮ ስርቻድና በመጨረሻም ናቦኒዳስ የተባሉት ልጆቹ ነገሡ። ምንም እንኳ ናቦኒዳስ የመጨረሻው ሕጋዊ የባቢሎን ንጉሥ ቢሆንም በእርሱ ፈንታ ልጁ ብልጣሶር እንዲነግሥ አደረገ። ስለዚህም ናቦኒዳስ ብቻ ሳይሆን ብልጣሶርም ንጉሥ ተብሎ ይጠራ ነበር። ብልጣሶር ዳንኤልን ሦስተኛ ገዥ ያደረገውም በዚህ ምክንያት ነበር። (ዳን.5:7፤ 16፤ 29።)

ብልጣሶር የናቡከደነፆር ልጅ ተብሎ ተጠርቶአል፤ (ዳን.5:11፤18)። ብልጣሶር ከናቡከደነፆር ጋር የነበረውን ትክክለኛ ግንኙነት ማወቅ ያስቸግረል። «አባት» የሚለው ቃል «አያት» ከዚያም አልፎ «ቅድመ አያት» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ምናልባትም ብልጣሶር ከናቡከደነፆር ሚስቶች የአንዲቷ ልጅ ሳይሆን አይቀርም። ወይም ከናቡከደነፆር ሴት ልጆች አንዲቱን ያገባው የናቦኒዳስ ልጅ ሊሆን ይችላል።

ከናቡከደነፆር በኋላ የተነሣው ንጉሥ ናቡከደነፆር የነበረውን ያህል ችሎታ አልነበረውም። ስለዚህም ቀስ በቀስ የባቢሎን መንግሥት ኃይል መዳከም ጀመረ። በዳንኤል 5 ላይ ያለው ታሪክ በሚፈጸምበት ወቀት ከዋናው ከተማ ከባቢሎን በስተቀር የተቀረው አገር ሁሉ በሚደንና ፋርስ ሠረዊት ቁጥጥር ሥር ነበር። ይህ ለባቢሎን መንግሥት የመጨረሻው ጊዜ ነበር፤ በዚህ ምሽት ማለትም በ539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ባቢሎን በጠላቶቸዋ እጅ ወደቀች።

ታሪክ ስለዚህ ምሽት በጣም ደስ የሚያሰኝ ነገር ይነግረናል። ናቦኒዳስ በሚደንና ፋርስ ጦር ላይ ሠረዊቱን ለማዝመት እንዲመቸው ከነበረበት ሥፍረ ወደ ባቢሎን ዋና ከተማ መጥቶ ነበር። ከባቢሎን ውጭ ከፍተኛ ጦርነት

ተጸረገና ናቦኒዳስ ጽል ሆነ። ምናልባትም ሳይሟረክና በኋላም የሜዶንና የፋርስ መሪዎች ከእስር ሳይፈቱት አልቀረም። የተቀረው ሠረዊት አምልጦ ወደ ባቢሎን ከተማ ገባ። የባቢሎን ከተማ በሁለት ግንቦች የተከበበች ነበረች። በስተውጭ ያለው ግንብ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ በላዩ ላይ አረት ሰረገሎች ጐን ለጐን ሆነው ሊያልፉበት ይችሉ ነበር። ውስጠኛ ከተማውንም የሚከላከል ሌላ ግንብ ነበር። ወደ ከተማይቱ የሚያስገባው ትልቁ በር ከነሐስ የተሠረ ሲሆን ከውስጥ ተቆልፎ ነበር። በከተማይቱ ውስጥ ያሉ ለብዙ ዘመናት ያህል ማንም ጽል ያጸርገናል ብለው አላሰቡም ነበር። የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አከማችተው ስለነበር ቢከበቡም እንኳ ለብዙ ዓመት ለመቆየት ይችሉ ነበር። የቂሮስ ወታጸሮች በመጡበት ወቅት በቀላሉ እንሸነፋለን የሚል ግምት አልነበረቸውም። ስለዚህም በባቢሎን ከተማ መካከል የሚያልፈውን የኤፍረጥስ ወንዝ በከፊል አቅጣጫውን አስለወጡት። አዲስ የባሕር በር ከፈቱለት፤ ውኃው ወደ አዲስ አቅጣጫ ሲሄድ አስቀድሞ ተኝቶበት በነበረው ሥፍረ በኩል ወደ ከተማይቱ ገቡ። በዚያ ጊዜ ግን ባቢሎናውያን ታላቅ ግብዣ አድርገው እየበሉ፥ እየጠጡ ነበር። ስለዚህም ከተማይቱ ጽል የተጸረገችው ያለ አንጻች ውጊያ ነበር።

ዳንኤል 5 ስለዚህ ታላቅ ጽግስና የሜዶንና ፋርስ ሠረዊት ወደ ከተማይቱ ሲገባ በባቢሎን ቤተ መንግሥት ውስጥ ምን ይጸረግ እንጸነበር ይነግረናል። የሜዶንና ፋርስ ሠረዊት ጽል ያጸርገኛል ብሎ ያልገመተው ብልጣሶር ለመኳንንቱና ለሚስቶቻቸው ከፍተኛ ግብዣ አዘጋጅቶ ነበር። ምናልባትም በቅርቡ በጸረሰባቸው ሽንፈት ተበሳጭተው ብዙ ወይን ጠጅ በመጠጣት ረሳቸውን ለማጽናናት እየሞከሩ ይሆናል። ከዚህም ሌላ ይህ ግብዣ የወርቅን፥ የብርን፥ የነሐስን፥ የብረትን፥ የእንጨትንና የሸክላ አማልክቶቻቸውን ለማምለክ ያዘጋጁት ጽግስ ሳይሆን አንጸልቀረ ይገመታል። እየበሉ፥ እየጠጡ፥ እነዚህን አማልክቶቻቸውን ያመሰግኑ ነበር። ሰክሮ ስለነበር ንጉሥ ናቡከጸነፆር ከኢየሩሳሌም ያመጣቸውን ዕቃዎች እንጸያመጡና እርሱና ዕቁባቶቹ ለአማልክቶቻቸው ክብር የወይን ጠጅ እንጸጠጡበት አዘዘ። ምናልባትም ንጉሥ ብልጣሶር ባይሰክር ኖሮ ይህን ያህል ጽፍረት ባልኖረውም ነበር።

ንጉሥ ብልጣሶር እነዚህን ዕቃዎች ማርከሱ ክፉ የሆነው ለምን ነበር? በሌላ መንገጽ ጸግሞ በአሕዛብ ቤተ መቅጸስ ውስጥ በመቀመጣቸው ረክሰው ነበር። (ዳን.1:2) በሁለቱም ሁኔታ እነዚህ ዕቃዎች ለባቢሎናውያን አማልክት ክብር ውለዋል። በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ግን ሁኔታው ልዩነት ነበረው። ናቡከጸነፆር ይህን ያጸረገው ባለማወቅ ነበር። የአሕዛብ ንጉሥ ስለነበር እውነተኛውን የእስረኤል አምላክ አላወቀም ነበር። ስለዚህም ኢየሩሳሌምን ጽል ለማጽረግ ስለረዱት አማልክቱን አመሰገነ። ብልጣሶር ግን ስለኢየሩሳሌም ጽል መሆንና ስለ እስረኤል አምላክ ታላቅነት ሳይሰማ አይቀርም። ፈቱን ከእውነት የመለሰው አውቆ ነበር። ከዚህም አልፎ የረሱን ባሕል እንኳ የሚጸረር ነገር አጸረገ። የተቀጸሱ ዕቃዎች ለተረ

አገልግሎት አይውሉም ነበር። በእነዚህ የተቀደሱ ዕቃዎች እርሱና መኳንንቶቹ፥ እንዲሁም ዕቁባቶቹ የወይን ጠጅ የጠጡበት ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ለማፌዝ ነበር። ናቡከደነፆር ግን ዕቃዎቹን በክብር በመቅደሱ ውስጥ ነበር ያስቀመጣቸው። ብልጣሶር ያደረገው ነውር፥ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ቤተ ክርስቲያን መጠጥ ቤት ወይም ዳንስ ቤት ከማድረግ የማያንስ ነው።

ግብዣው ለአማልክቶቻቸው ክብር የተዘጋጀ ነበር። ዳንኤል እንዴት እንደሚገልጸው አስተውል። አማልክቶቹ የወርቅ፥ የብር፥ የመዳብ፥ የብረት፥ የእንጨትና የድንጋይ ሥራዎች ነበሩ። ሕይወት የሌላቸውና በሰው እጅ የተሠሩ ጣዖታት ነበሩ። ዳንኤል የአሕዛብ አማልክት ምን ያህል የማይረቡ መሆናቸውን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለማሳየት ይፈልጋል። ዳንኤል በነበረበት ጊዜ ምስል እየተደረገላቸው ታናናሽ ጣዖታት ይከበሩ ነበር። ምንም እንኳ ዛሬም ቢሆን ሰዎች እንደ ድንጋይና ዛፍ የመሳሰሉትን ሕይወት የለሽ ነገሮች ቢያመልኩም ሌሎች ደግሞ ገንዘባቸውን፥ ትምህርታቸውንና ኃይላቸውን ያመልካሉ። በጣም አስፈላጊ የምናደርጋቸውና የምንደገፍባቸው፥ እንዲሁም በችግራችን ጊዜ ይረዱናል የምንላቸው ነገሮች ሁሉ «ጣዖቶች» ናቸው። ከወርቅና ከብር የተሠሩ ጣዖቶቹ ብልጣሶርን ከሚደንና ፋርስ ሠራዊት እንዳላዳኑት ሁሉ እኛም ትምህርታችን፥ ገንዘባችንና ኃይላችን ከመከራ ሊያድነን አይችልም። እውነተኛው አምላክ የሰማይና የምድር ፈጣሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ሰዎች እንደ አምላካቸው የሚያመልኳቸውን አንዳንድ ነገሮች ግለጽ።
ለ/ ክርስቲያኖችስ እነዚህን ነገሮች እንደ አማልክት ያመልካሉን?
ሐ/ እንዴት? አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

ግብዣው በሚደረግበት ወቅት ብልጣሶር በአዳራሹ ውስጥ ነበር። ወዲያውኑ ከእግዚአብሔር የተላከ የሰው እጅ የሚመስል ነገር አየ። እጅ ብቻ እንጂ ሌላ አካል አልነበረውም። ይህ እጅ በግድግዳ ላይ ለንጉሡ የሚሆን መልእክት ጻፈ። ምን ያህል ሰዎች ይህን እጅ እንዳዩ እርግጠኛ ባንሆንም፥ ንጉሡ ለማየቱ ግን በጣም እርግጠኞች ነን። ይህን እጅ ሲመለከት ደነገጠና ወኔው ረቀውና እጅግ ፈራ። ፊቱ ገረጣ፤ ጉልበቱ ስለተብረከረከ መቆም እንኳ አልቻለም።

ንጉሡ የሃይማኖትና የፖለቲካ አማካሪዎቹን አስጠርቶ ጽሑፉን እንዲተረጉሙለት አዘዘ። ጽሑፉን ለሚተረጉምለት ሰው ሐምራዊ ግምጃ እንደሚያለብሰውና የወርቅ ማርዳ በአንገቱ ላይ እንደሚያደርግለት ቃል ገባ። እነዚህ እገሮች የተለዩ የክብርና የምስጋና ምልክት ነበሩ። በምድሩ ላይ ሦስተኛ ገዥ እንደሚያደርገውም ተናገሮ ነበር። ናቦኒዳስ የመጀመሪያው፥

ብልጣሶር ሁለተኛው ገዢ ሲሆን ጽሑፉን የሚተረጉም ሰው ደግሞ ሦስተኛ መሪ እንዲሆን ተወስኖ ነበር።

የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ በግድግዳው ላይ የታየውን ጽሑፍ ለመተርጎም አልቻሉም። ለምን መተርጎም እንዳልቻሉ አናውቅም። ቋንቋው በራሳቸው ቋንቋ በአረማውያን ነበር። ምናልባትም ሊረዱት በማይችሉት መንገድ ስለተጻፈ ሊሆን ይችላል። በሌላ ወገን ደግሞ ምንም እንኳ ቃላቶቹን ቢያውቁም መልእክቱን ባለመረዳታቸው ሊሆን ይችላል።

በግብዣው አዳራሽ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ሰምታ ንግሥቲቱ ሳትመጣ አትቀርም። አመሠረቱ ግን ንጉሡ ፊት ማንም ሳይፈቀድለት አይገባም ነበር። (የአስቴርን ታሪክ አስተውል። አስቴር 4:9-11) ንግሥቲቱ ወደ ንጉሡ ቀረበችና ልኮ ዳንኤልን እንዲያስጠራ ነገረችው።

ይህች ንግሥት ማን እንደሆነች እርግጠኛ አይደለንም። ሚስቱ ግብዣው ላይ ስለነበረች ይህች ሴት ሚስቱ ለመሆን አትችልም፤ (ዳንኤል 5:2)። የናቦኒዳስ ሚስት ወይም የራሱ የብልጣሶር እናት ሳትሆን አትቀርም። ምናልባትም የንግሥቲቱ እናት ወይም የናቡከደነፆር ሚስት ትሆን ይሆናል። የተናገረችው ቃል ከናቡከደነፆር ጋር ይስማማል፤ ባለፈው ጊዜ ናቡከደነፆር ስለ ዳንኤል የተናገረውን ሳትሰማ አትቀርም። (ዳንኤል 5:11ን ከዳንኤል 4:9 ጋር አነጻጽር።)

ንጉሡ ዳንኤልን እንደሚያውቀው ጥርጥር የለውም። እንደ እርሱ ያለ ታላቅ ሰው መታወቅ አለበት። ምናልባትም በዚህ ጊዜ ዳንኤል ከፖለቲካው ሥራ ጡረታ ወጥቶ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ከሰማንያ ዓመት በላይ ሳይሆነው አይቀርም። ምናልባትም ብልጣሶር ዳንኤልን ስላልወደደው ከፖለቲካው ሥራ ሽሮት ይሆናል።

ንግሥቲቱ ዳንኤል እንዲመጣና ጽሑፉን እንዲተረጉምለት ለንጉሡ መከረችው። «የቅዱሳን አማልክት መንፈስ» ያደረበት ስለነበር ዳንኤል ጥበበኛ ሊሆን እንደሚችል ታውቃለች። (የዚህን ትርጉም ለመረዳት ከፈለግህ ቢያንስ ያለፉት ጥቂት ሳምንታት ትምህርቶችን ተመልከት።) ዳንኤል ልዩ አእምሮ÷ ማስተዋልና እውቀት እንዲሁም ሕልምና እንቆቅልሾችን የመፍታት ችሎታ እንደነበረው በመረዳቱ ናቡከደነፆር የጠቢባን አለቃ አድርጎት ነበር። ዳንኤል በግድግዳው ላይ የነበረውን ጽሑፍ ለመተርጎም እንደሚችል ንግሥቲቱ ጥርጥር አልነበረትም።

የዚህ ዓለም ዕውቀት በከፊልና ጊዜያዊ ለመሆኑ ይህ በቂ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል። ምንም እንኳ የዚህ ዓለም ዕውቀት ለአንዳንድ ችግር መፍትሔ ሊሆነን ቢችልም÷ ከፍተኛ ችግር በሚመጣበት ጊዜ ግን ምንም ሊረዳን አይችልም። የዘላለሙን ነገሮች እንድንገነዘብ የሚረዳን የእግዚአብሔር ሰው ብቻ ነው።

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 1ቆሮ.2:12-15 ተመልከት::
ለ/ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው የማይረዳቸው በመንፈስ ቅዱስ የሚመረ ክርስቲያን ግን የሚረዳቸው አንዳንድ ነገሮችን ግለጽ::

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 5:13-30

## ጥያቄዎች

14ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ስለ ዳንኤል ምን ሰማ?
15ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በግድግዳው ላይ ያለውን ጽሑፍ ከተረጐመለት ንጉሡ ምን እንደሚያደርግለት ነበር ለዳንኤል የነገረው?
ለ/ ዳንኤል ግን ምን መልስ ሰጠው?
ሐ/ ዳንኤል እንዲዚህ የመለሰለት ለምን ይመስልሃል?
16ኛ ጥያቄ:- ለናቡከደነፆር ሥልጣን የሰጠው ማን ነበር?
17ኛ ጥያቄ:- በነበረው ሥልጣን ምክንያት ናቡከደነፆር ማድረግ የሚችላቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?
18ኛ ጥያቄ:- ሥልጣንና ኃይሉ የተወሰነ መሆኑን እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር ያሳየው ለምን ይመስልሃል?
19ኛ ጥያቄ:- በምን ሁኔታ ነበር ብልጣሶር የአባቱን ምሳሌነት ያልተከተለው?
20ኛ ጥያቄ:- በግብዣው ወቅት ስላደረገው ነገር በምን ሁኔታ ነበር ዳንኤል ብልጣሶርን የወቀሰው?
21ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር በብልጣሶር ሕይወት ላይ እንኳ ሥልጣን እንዳለው ዳንኤል የነገረው እንዴት ነበር?
22ኛ ጥያቄ:- በግድግዳው ላይ የተጻፉትን ሦስት የአረማይክ ቋንቋ ትርጉማቸውን ግለጽ::
23ኛ ጥያቄ:- ብልጣሶር ለዳንኤል ምን ሸለመው?
24ኛ ጥያቄ:- በግድግዳው ላይ የተጻፈው ቃል በዚያን ሌሊት እንዴት ተፈጸመ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ለአንዳንድ ችግሮች መፍትሔ እንደሚያገኝ ንጉሥ ብልጣሶር ስለ ዳንኤል የሰማው ከንግሥቲቱ ነበር:: ስለዚህም ዳንኤልን አስመጣው:: ዳንኤል ሲመጣ አብዛኛውን ንግሥቲቱ ስለ እርሱ ያጫወተችውን ሁሉ ነገረው:: ዳንኤል ከአማልክት ጋር የነበረውን የቀረበ ግንኙነት፥ ስለ ዕውቀቱ፥ ስለ ጥበቡ ሰምቶ ነበር:: ስለዚህም ብልጣሶር በግድግዳው ላይ የተጻፈውን ጽሑፍ እንዲተረጉምለት ጠየቀው:: ለሌሎች እንደተናገረው ሁሉ ሐምራዊ

ግምጃ እንደሚያለብሰውና የወርቅ ማርዳ በአንገቱ ላይ እንደሚያደርግለት ለዳንኤል ነገረው። በሀገሪቱ ላይ ሦስተኛ ባለሥልጣን እንደሚያደርገውም ነገረው።

ዳንኤል ግን ድፍረት በተሞላበት ሁኔታ እነዚህን ሁሉ ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ገለጸ። ይህም ሁለት ምክንያት አለው። በመጀመሪያ:- የነቢይነት ሥልጣን በገንዘብ የሚገዛ አለመሆኑን ሊያሳየው ነው። ዓላማው የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝቡ መናገር እንጂ ለገንዘብ ወይም ለሽልማት አልነበረም። ሁለተኛ:- ብልጣሶር እንደሚሰጠው የነገረው ነገር ሁሉ በዚያው ሌሊት እንደሚወሰድ በመረዳቱ ነበር። ባቢሎን በሜዶንና ፋርስ ሠረዊት እጅ ስትወድቅ የነበረው ሥልጣንና ብልጽግና ሁሉ እንደሚወሰድበት ያውቃል። ዳንኤል ግን የጽሑፉን ትርጉም የነገረው በፈቃደኝነት ብቻ ነበር።

ዳንኤል ጽሑፉን ከመተርጐሙ በፊት እግዚአብሔር በናቡከደነፆር ላይ ምን እንዳደረገ ነገረው። ኃይልን ሁሉ ለናቡከደነፆር የሰጠውና መንግሥቱንም ታላቅ ያደረገለት እግዚአብሔር እንደሆነ አስገነዘበው። ናቡከደነፆር በመንግሥቱ ሁሉ ሥልጣን ቢኖረውም እግዚአብሔር ደግሞ በናቡከደነፆር ላይ ሥልጣን አለው። ናቡከደነፆር አንድን ሰው ለመግደልም ሆነ ለማዳን ሥልጣን ነበረው፤ ትዕቢት ባደረበት ጊዜ ግን እግዚአብሔር ይህን ሥልጣን ገፈፈው። ይህንንም ያደረገው ናቡከደነፆርን በማሳበድ እንደሆነ ባለፈው ሳምንት ተመልክተናል። እግዚአብሔር በመንግሥታትና በገዢዎች ሁሉ ላይ ያለውን ሥልጣን ናቡከደነፆር ተማረ። መንግሥታትን የሚያስነሣው እርሱ ነው፤ መንግሥታትን የሚጥለውም እርሱ ነው።

ምንም እንኳ ብልጣሶር ታሪኩን እንደሚገባ ቢያውቅም እርሱ ግን ከናቡከደነፆር ሕይወት አልተማረም። ዳንኤልም ስለሁለት ነገሮች ወቀሰው። አንደኛ:- የሜዶንና ፋርስ ጦር መጥቶ በከተማይቱ ውጪ ሰፍሮአል፤ ይህም በመሆኑ ትሑት መሆን ሲገባው እርሱ ግን ጦሩን ለመመለስ እንደሚችል በራሱ ችሎታ ታበየ። ሁለተኛ:- እውነተኛውን የሰማይ አምላክ አላወቀም። እግዚአብሔርን ናቀ፤ እንደ እርሱ አማልክት ሁሉ እግዚአብሔርም ደካማ እንደሆነ አሰበ። ይህም ትዕቢቱ እግዚአብሔርን እንዲሰድብ አደረገው። ብልጣሶር የቤተ መቅደሱን ዕቃዎች ወደ ግብዣው አዳራሽ አምጥቶ ማርከሱ እውነተኛውን የሰማይ አምላክ መቃወሙን እንደሚያመለክት ዳንኤል ተረድቷል።

ይህም ስድቡ በሁለት አቅጣጫ ምኝነቱን ያሳያል። በመጀመሪያ:- ታላቅ÷ ሕያውና ኃያል ከሆነው ከሰማይ አምላክ እርዳታን መጠየቅ ሲኖርበት እርሱ ግን የማይጠቅሙና የሰው እጅ ሥራ የሆኑትን አማልክት አመለከ። እነዚህ አማልክት በባቢሎን የሚሆነውን የማየትም የመስማትም ችሎታ የላቸውም፤ ብልጣሶር ላቀረበላቸው የጸሎት ጥያቄ ሁሉ መልስ መስጠት አይችሉም። ሁለተኛ:- ብልጣሶር እርሱን ለመግደልም ሆነ ለማዳን

የሚችለውንና ሕይወቱን በእጁ የያዘውን አምላክ አላከበረም። በባቢሎን የሚሆነውን ሁሉ የሚቆጣጠርም እርሱ ነው።

በግድግዳው ላይ የነበሩት ሦስት ቃላት በጊዜው የባቢሎናውያን ቋንቋ በነበረው በአረማይክ የተጻፉ ነበር። የእነዚህ ቃላት ፍቺ ከአንድ በላይ ትርጉም ስለነበረው ትርጉሙም የተወሳሰበ ሆኖአል። ምንም እንኳ ንጉሡ ጽሑፉን መረዳት ቢችልም ትርጉሙን ግን ለመረዳት ባለመቻሉ የዳንኤል እርዳታ አስፈለገው።

ማኔ:- «ተቆጠረ» ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ «ሚና» የሚባለውን አነስተኛ የገንዘብ ክፍልፋይ (ሣንቲም) ያመለክታል። ቃሉ ሁለት ጊዜ አጸጋገሙ እግዚአብሔር የብልጣሶርን የንግሥና ዓመታት እንደቆጠረቸውና ዓመታቱም መፈጸማቸውን የሚያመለክት እንደሆነ ዳንኤል አስተዋለ። የብልጣሶር የንግሥና ጊዜ ተፈጽሚል፤ አልቋል።

ቴቄል:- ይህ ቃል «ተመዘነ» ማለት ሲሆን በሌላ አነጋገር ደግሞ «ስቅል» የሚባለውን ገንዘብ ያመለክታል። ዳንኤል ብልጣሶር በሚዛን መመዘኑን ይናገራል። ይሁን እንጂ ሕይወቱ እግዚአብሔር በሚፈልገው መጠን ሆኖ አልተገኘም።

ፋሬስ:- ይህ ቃል የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። «ግማሽ» ማለት ሊሆን ይችላል፤ በሌላ አነጋገር ደግሞ መከፋፈልን ያሳያል። ቃሉ የሚና ወይም የስቅል ግማሽ ማለት ሊሆን ይችላል። ፋርስ ከሚለው ቃል ስለሚቀረረብ የባቢሎንን በፋርስ መሸነፍ የሚያመለክት ቅኔያዊ አነጋገር ሊሆንም ይችላል። እንደ ዳንኤል አተረጓጎም የባቢሎናውያን መንግሥት ዘመን ተፈጽሚል። መንግሥቱንም ሜዶንና ፋርስ ይከፋፈሉታል።

እንደተናገረው ሁሉ ብልጣሶር ዳንኤልን ሐምራዊ ልብስ አለበሰው፤ በአንገቱም የወርቅ ማርዳ አደረገለት። በባቢሎን መንግሥት ውስጥም ሦስተኛ ገዢ አደረገው። ይሁን እንጂ ይህን በሚነጋገሩበት ሰዓት እንኳ የሜዶንና የፋርስ ሠራዊት ባቢሎን ውስጥ ገብቶ ስለነበር ይህ ሥልጣኑ ምንም ያህል አልቆየም። ከተማይቱ ተማረከች፤ ብልጣሶርም ተገደለ።

በዳንኤል 2 የወርቁ ራስ ባቢሎንን የሚያመለክት እንደሆነ ታስታውሳለህ። የትንቢቱ የመጀመሪያ ክፍል ተፈጸመ። ሁለተኛው መንግሥት፥ ማለትም ደረቱና ክንዶቹ ከብር የተሠሩት የሜዶንና የፋርስ መንግሥትን ያመለክታል። አሁን ይህ መንግሥት ጀምሮአል።

የባቢሎን ከተማ በሜዶንና ፋርስ መንግሥት ተያዘች። የባቢሎንን መንግሥት የወሰደው ዳርዮስ የሚባለው ሜዶናዊ ሰው ነው። ዳርዮስ ባቢሎንን መግዛት ሲጀምር የ62 ዓመት ሰው እንደነበር ዳንኤል ይናገራል።

ይህም ዳንኤል ዳርዮስን በግል ያውቀው እንደነበር ያመለክታል። ስለ እርሱም ሰፋ ባለ መልኩ በሚቀጥለው ሳምንት እናጠናለን።

የባቢሎን ሕዝብ ለአይሁዳውያን ልዩ ምልክት ሆነውላቸዋል። የባቢሎንን መነሣትም ሆነ መውደቅ ነቢዩ ኢሳይያስ በግልጽ ተንብዮአል፤ (ኢሳ. 13-14:23)። ከዚህም ሌላ፥ የባቢሎን ትዕቢትና ውድቀት የዲያብሎስ ትዕቢትና ውድቀት ምሳሌ እንደሆነ ተገልጾአል።

25ኛ ጥያቄ:- ኢሳ.14:12-15 በጥንቃቄ አንብብ። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ይህ ክፍል ሰይጣን እንዴት እንደወደቀ የሚያመለክት መሆኑን ይስማማሉ።

ባቢሎን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለጨቆኑ ሌሎች መንግሥታትም ምልክት ወይም ምሳሌ ሆናለች። የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚጨቁነው የመጨረሻው መንግሥት ምሳሌ ሆናለች፤ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት በሚመለስበት ጊዜ ይህንን መንግሥት ያጠፋዋል፥ (ራዕይ 17-19)።

እግዚአብሔር የብልጣሶርን ዓመታት እንደቆጠረቸው ሁሉ የእኛንም ዓመታት ቆጥሮአቸዋል። ምን ያህል ዘመን እንደምንኖርና መቼ እንደምንሞት እንኳ እግዚአብሔር ያውቃል። እኛ ግን ይህን አናውቅም። እግዚአብሔር ዕድሜያችንን ሁሉ ስለወሰነልን የምንኖርበትን ዘመን በሙሉ እርሱን ለሚያስከብር ነገር ልናውለው ይገባል።

26ኛ ጥያቄ:- ሀ/ መዝ.90:1-12 ተመልከት።
ለ/ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊነት ጋር የሰውን ዕድሜ አወዳድር።
ሐ/ ዘመናችንን መቁጠር ለምን አስፈለገ?

ብልጣሶር በሚዛን እንደተመዘነና ቀልሎ እንደተገኘ ሁሉ አንድ ቀን እግዚአብሔር ሥራችንን ይመዝነዋል /ይፈትነዋል/። በዚያ ቀን ምን ያህል እንደምንመዝን ይታወቃል።

27ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 1ቆሮ.3:10-15 ተመልከት።
ለ/ የእኛን ሥራ የሚያመለክቱ የትኞቹ የሥራ ዓይነቶች ናቸው?
ሐ/ ሥራችን ሁሉ የሚመዘነው ወይም የሚፈተነው በምንድነው?
መ/ ሥራው የሚጸናለት ሰው ምን ያገኛል?

አረተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ፤ የውይይቱን ጥያቄዎችንም እንደገና ተመልከት::

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ የመቅደስ ዕቃዎችን በማርከስ የብልጣሶር ሐሳብ ወይም የልብ ዝንባሌ ምን ነበር?
   2/ ዛሬስ ሰዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ነው የተቀደሱ ነገሮችን የሚያረክሱት?
   3/ ሰዎች የሚያመልኳቸው የተለያዩ አማልክት ምንድናቸው?
   4/ አንዱን አምላክ ብቻ ከማምለክ ይልቅ ክርስቲያኖች የተለያዩ አማልክትን ወደ ማምለክ የሚገፋፉት እንዴት ነው?

ለ. 1/ የዓለምን ጥበብና የእግዚአብሔርን ጥበብ አወዳድር::
   2/ ብልጣሶር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው ዓለማዊ ጥበብን ያሳየው?
   3/ ጸህንነትን፥ ብልጽግናን፥ የሕይወት ዓላማን፥ የተለያየ አመለካከትን፥ ወዘተ በሚመለከት የሰውና የእግዚአብሔር ጥበብ እንዴት እንደሚለያዩ ግለጽ::

ሐ/ 1/ ከብልጣሶር ሕይወት የምትማረቸው ዋና ዋና ነገሮች ምንድናቸው?
   2/ በዚህ ትምህርት ክርስቲያኖችን እንዴት ልታጽናና ወይም ልታበረታታ ትችላለህ?
   3/ ክርስቲያኖች የብልጣሶርን ሕይወት አይተው ሊጠነቀቁ የሚገባቸው እንዴት ነው?

መ/ የብልጣሶር ቀኖች መቆጠረቸውን እግዚአብሔር ይናገረል:: መዝ.90:1-12 ደግሞ የእኛም ቀኖች እንደተቆጠሩ ያመለክታል:: ከዚህ የምንማረው ምንድነው?

ሠ. እግዚአብሔር ብልጣሶርን መዝና ቀላል ሆኖ እንዳገኘው ተናግሯል:: በ1ቆሮ.3:10-15 ላይም ሕይወታችን በእሳት ውስጥ እንደሚፈተን ወይም እንደሚመዘን ይናገረል:: እንዴት ነው ይህ ቃል የቅድስና ኑሮ እንድንኖር ሊያበረታታን የሚችለው?

5. ጸሎት::

## ትምህርት አሥር

## ዳንኤል 6

### የመጀመሪያ ቀን

የዚያን ጊዜም አለቆችና መሳፍንቱ ስለ መንግሥቱ በዳንኤል ላይ ሰበብ ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን የታመነ ነበርና ስሕተትና በደል ያገኙበት ዘንድ አልቻሉም። እነዚያም ሰዎች ከአምላኩ ሕግ በቀር በዚህ በዳንኤል ላይ ሌላ ሰበብ አናገኝበትም አሉ፥ (ዳን.6:4-5)።

ዳንኤል ለሰባ ዓመት ያህል እግዚአብሔርን አገልግሎአል። ገና በወጣትነቱ በምርኮኛነት ወደ ባቢሎን ተወሰደ፤ በባቢሎን ሃይማኖትና ባሕል /አኗኗር/ ራሱን እንዳያረክስ ወሰነ። ብዙ ዓመት የፖለቲካ መሪ ቢሆንም እርሱ ለአምላኩ ታማኝ ነበር። አሁን ግን ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ አካባቢ እንደገና በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት ተፈተነ። ከወጣትነት እስከ እርጅና ዘመናቸው ድረስ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሚሆኑ ሰዎችን ማግኘት አዳጋች ይመስላል። ዳንኤል ግን እስከመጨረሻ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነ።

በብልጽግናና በሥልጣን ዘመናቸው ለእግዚአብሔር ታማኝ የሚሆኑ በጣም ጥቂት ክርስቲያኖች ናቸው። በድህነት ወይም በስደት ጊዜ ግን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ቀላል ነው። በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ለመታመን እንገደዳለን። በብልጽግናና በሥልጣን ዘመን ግን እምነታችን ይደከማል፥ (ዘዳ. 6:10-15 ተመልከት)። ዳንኤል በሕይወቱ ዘመን እንደዚህ ያለ ፈተና ተጋግሞ ደርሶበታል። በባቢሎን መንግሥት በአስተዳዳሪነት በሚያገለግልበት በወጣትነቱ ዘመን ለአምላኩ ታማኝ ሆና መኖርን ተምሮአል። አሁን ደግሞ በሕይወቱ ፍጻሜ እንደዚያ ያለ ፈተና እንደገና ደረሰበት። በመሪዎች ሕይወት እግዚአብሔር ሊያገኝ ለሚፈልገው ባሕርይ ዳንኤል መልካም ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። በጣም የሚያሳዝነው ግን በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ባሕርያት በቤተ ክርስቲያን አለመታየታቸው ነው።

ዳርዮስ በባቢሎን መግዛት እንደጀመረ ወዲያውኑ አዲሱን መንግሥት አቋቋመ። 120 ክፍለ ሀገሮችን የሚገዙ 120 መሪዎችን መረጠ። እነዚህን 120 መሪዎች በበላይነት የሚቆጣጠሩለትን ሦስት ሰዎች ሾመ። ከተሾሙት ሦስት ሰዎች መካከል አንዱ ዳንኤል ነበር። የሦስቱን የሥራ ሁኔታ ሲያወዳድር የዳንኤል ሕይወትና ሥራ የተለየ ሆና በልጦ በመገኘቱ፥ ዳርዮስ፡- ከሁሉም መሪዎች በላይ ዳንኤልን ሊሾመው ፈለገ። ይህም ነገር በመሪዎቹ መካከል ቅንዓትንና ምቀኝነትን አነሣሣ። በዓለምም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ታዋቂና ተወዳጅ መሪዎች መሪ ለመሆን ከሚፈልጉት ሰዎች ተቃውሞ

ይደርስባቸዋል።

እነዚያ መሪዎች ዳንኤልን በንጉሡ ፊት የሚከስሱበት ሰበብ ፈለጉ። በመጀመሪያ ዕለታዊ ተግባሩን መረመሩ። ብዙ በመረመሩ መጠን በጉልህ የሚታይ አንድ ባሕርይ አገኙበት። ይህም ታማኝነቱ ነው። ንጉሡ የሚሰጠውን ሥራ ሁሉ በሙሉ ልቡ ያከናውን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ቸልተኛ አልነበረም። በአጠገቡ ሰዎች ቢኖሩም ባይኖሩም ስንፍና አይታይበትም ነበር። የተጣለበትን ኃላፊነት ሁሉ በታማኝነት ይፈጽማል።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 1ቆሮ.4:1-2 አንብብ።
ለ/ በመሪዎች ሕይወት ሊታይ የሚገባው ዋነኛ ባሕርይ ምንድነው?
ሐ/ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥራቸው ታማኝ ስለሚሆኑበት ጉዳይ ምሳሌ ስጥ።
መ/ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥራቸው ታማኝ ስላልሆኑበት ጉዳይ ምሳሌ ስጥ።

ሁለተኛ:- የግል ሕይወቱን እንደሚገባ መረመሩ። በግል ሕይወቱም ቢሆን ዳንኤል ብልሹ አልነበረም። ሕይወቱ ንጹሕ ነበር። ሥልጣኑን ለግል ጥቅሙ አይጠቀምበትም። ጉቦ አይቀበልም። ለቅርብ ጓደኞቹ ሥልጣን አይሰጥም። በማንኛውም ሁኔታ ሕይወቱን በንጽሕና ይጠብቃል።

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 1ተሰ.5:21-22 አንብብ።
ለ/ ጳውሎስ ሕይወታችንን በንጽሕና ስለመጠበቅ ምን ይናገራል?
ሐ/ መሪዎች ሕይወታቸውን በንጽሕና ስለማይጠብቁበት ሁኔታ አንዳንድ ምሳሌ ስጥ።
መ/ ሕይወትህ ከኃጢአት ሁሉ የነጻ ነውን? ካልሆነ ሕይወትህን ንጹሕ ለማድረግ ኃጢአትህን ሁሉ ለእግዚአብሔር ተናዘዝ።

የዳንኤልን ሕይወት በጥንቃቄ ከመረመሩ በኋላ እርሱን የሚከስሱበት ምንም ሰበብ ማግኘት አልቻሉም። በመጨረሻም÷ ሃይማኖቱንና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ሕብረት መመርመር ጀመሩ። በንጉሡ ፊት ሊከሱትና ሊያሳጡት የሚችሉት እግዚአብሔርን ማምለኩን ሕገ-ወጥ በማድረግ ብቻ ነበር። የግል ሕይወታችን ቢመረመር ምንም ነቀፋ የማይገኝብን በጣም ጥቂቶች ነን።

ዳንኤል ሕይወቱን በንጽሕና መጠበቅ የቻለው እንዴት ነው? በመንገዱ ለገጠመው ፈተና ሳይበገር ሥልጣኑንና ብልጽግናውን እንደጠበቀ ሊቆይ የቻለው እንዴት ነው? ዳንኤል 6 ለዚህ መልስ የሚሆኑንን ሦስት ነጥቦች ይሰጠናል።

በመጀመሪያ:- ሕይወቱን ከማንኛውም ርኩስ ነገር በንጽሕና ጠበቀ። እውነትን ይናገር ነበር፤ በእውነትም ይኖር ነበር። በማንኛውም ነገር በደል አልነበረበትም፥ (ዳን.6:21)።

ሁለተኛ:- ዳንኤል በየጊዜው በጸሎት ሕይወት ከአምላኩ ጋር ይመላለስ ነበር። ምንም እንኳ እንዳይጸልይ ንጉሥ አዋጅ ቢያውጅም እርሱ ግን ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበር። ሥራ ቢበዛበትም፥ ሁኔታዎች አመቺ ባይሆኑለትም፥ በአምላኩ ፊት በጸሎት የሚያሳልፈው ጊዜ እንደሚያስፈልገው ተረድቷል። ጸሎት የዘወትር ልምዱ ነበር። በቀን ሦስት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ይገናኝና ያመሰግነው፥ እርዳታውንም እንዲሰጠው ይጠይቀው ነበር፤ (ዳን.6:10-11)። ጸሎትንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ቸል ስንል እንወድቃለን።

ሦስተኛ:- ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ኅብረት የማያቋርጥ ነበር። በደስታም ይሁን በሐዘን፥ በሰላምና በበረከት ጊዜም ይሁን በስደት ጊዜ ዳንኤል ከአምላኩ ጋር የነበረው ኅብረት አንድ ዓይነት ነበር። ንጉሡ ዳርዮስ እንኳ ሳይቀር:- «ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ እርሱ ያድንህ» በማለት መስክሮለታል፤ (ዳን.6:16፤ 20)። ሁልጊዜ ሳያቋርጥ በእርሱ ላይ መደገፋን እግዚአብሔር አከበረለት፤ ስለዚህም ከአንበሶች አፍ አዳነው፥ (ዳን.6:23)።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ዳንኤሎች ያስፈልጉዋታል። በእግዚአብሔር ፊት ሕይወታቸውን በንጽሕና የሚጠብቁ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ያስፈልጉዋታል። ከሥራቸው፥ ከዚያም አልፎ ከምግባቸው እንኳ አስበልጠው ከእግዚአብሔር ጋር ለሚያሳልፉት ጊዜ ቅድሚያ የሚሰጡ ሰዎች ያስፈልጉዋታል። በማያምኑ ሰዎች ፊት በምስክርነታቸውና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የጸኑ ሰዎች ያስፈልጉዋታል። አንተስ ዳንኤልን ትመስላለህ?

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 6ን አንብብ።
ለ/ ዳንኤልን ለማጥፋት የሞከሩት ሰዎች እነማን ነበሩ?
ሐ/ ለዳንኤል ያቀረቡት ፈተና ምን ነበር?
መ/ የዳንኤልን መታመንና መታዘዝ እግዚአብሔር እንዴት አከበረለት?

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 6:1-16

## ጥያቄዎች

4ኛ ጥያቄ:- ሀ/ «ዳርዮስ» የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ

ቃላት ውስጥ ተመልከት።

ለ/ የምትችለውን ያህል ስለ ዳርዮስ የተረዳኸውን አስፍር።

5ኛ ጥያቄ:- ዳርዮስ የመንግሥቱን አስተዳደር በምን ሁኔታ አዘጋጀ?

6ኛ ጥያቄ:- ምንም ነቀፋ /ክስ/ እንዳይገኝበት ዳንኤል በሥራው ላይ ያሳያቸው አንዳንድ ባሕርያት ምንድናቸው?

7ኛ ጥያቄ:- ጠላቶቹ ዳንኤልን ለመክሰስ የቻሉበት የመጨረሻ ነጥብ ምን ነበር?

8ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል እንዲገደል ጠላቶቹ ያደርጉት ሤራ ምን ነበር?

9ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል የንጉሡን ትእዛዝ በምን ዓይነት መንገድ ተቀበለው?

10ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ሲጸልይ በማግኘታቸው ጠላቶቹ ምን አደረጉ?

11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በሕግ አፍራሽነቱ ዳንኤል ተይዞ አፊቱ ሲቀርብ ዳርዮስ ሁኔታውን በምን ዓይነት ተመለከተው?

ለ/ ዳርዮስ ምን ለማድረግ ፈለገ?

12ኛ ጥያቄ:- ዳርዮስ አዋጁን ወይም ትእዛዙን መለወጥ ያልቻለው ለምንድነው?

13ኛ ጥያቄ:- በመጨረሻ ንጉሡ በዳንኤል ላይ ምን ለማድረግ ተገደደ?

14ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ለዳንኤል የተመኘለት የመጨረሻ ምኞት ምን ነበር?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ባለፈው ሳምንት ትምህርታችን የባቢሎን የመጨረሻ ንጉሥ የነበረውን ብልጣሶርን እግዚአብሔር እንዴት እንዳዋረደው ተመልክተናል። በትዕቢት ተነሣስቶ የቤተ መቅደስን ዕቃዎች አረከሰ። ስለዚህም እግዚአብሔር መንግሥቱን ከእርሱ ወስዶ ለሜዶንና ፋርስ ንጉሥ ለዳርዮስ ሰጠው። በዚህ ሳምንት ዳንኤል 6ን እናጠናለን። ሁኔታዎቹ የተፈጸሙት ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠበት በመጀመሪያ ዓመት ነበር። እንደ ዳንኤል 3 ሁሉ ይህም ታሪክ ለእርሱ ታማኝ የሆኑትን ሰዎች ሕይወት እግዚአብሔር እንደሚጠብቅ ያስተምረናል። ዳንኤል እስከ ሞት ድረስ ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆኑ እግዚአብሔር ታደገው።

ስለ ዳርዮስ ማንነት የዓለም ታሪክ ምሁረን ብዙ ጥያቄዎችን ስንዘረዋል። በዓለም ታሪክ መሠረት ከባቢሎን ውድቀት በኋላ በሜዶንና ፋርስ መንግሥት ላይ ዳርዮስ የሚባል ንጉሥ መንገሡ አይታወቅም። ይሁን እንጂ ዳርዮስ ቀዳማዊ ሐይስታስፐስ የሚባል ንጉሥ ነበር። እርሱም የነገሠው ዘግይቶ ከ522-486 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

ታሪክ የሚያውቀው የመጀመሪያው የሜዶንና የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ መሆኑን ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ቂሮስ የመጀመሪያው የሜዶና ፋርስ ንጉሥ እንደነበር ይናገራል። ከዚህም ሌላ የአይሁዳውያን ነፃ አውጪ እንደሆነም ይታወቃል። አይሁዳውያን ወደ ሀገራቸው ወደ ይሁዳ ሄደው እንዲኖሩ

የተፈቀደላቸው በዚሁ በቂሮስ ዘመን ነበር። ስለዚህም በዘሩባቤል መሪነት በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል።

15ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። 2ዜና መዋዕል 36:22-23፤ ዕዝራ 1:1-8፤ ኢሳ.45:1።
ለ/ እነዚህ ጥቅሶች ስለ ቂሮስ ምን እንደሚናገሩ አንዳንድ ነገሮችን ግለጽ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳርዮስ በሚናገረው ላይ በጣም ግልፅ ነው። ሜደናዊው ንጉሥ ዳርዮስ በማለት ይጠረዋል። ንጉሥ ብልጣሶርን አሸንፎ የባቢሎንን መንግሥት ወሰደአል። ዳንኤል ያውቀው ነበር። ዳርዮስ ሥልጣን ሲይዝ ዕድሜው 62 ዓመት እንደነበር ዳንኤል ይናገረል።

ስለ ዳርዮስ ማንነት ሁለት ሐሳብ ማቅረብ ይቻላል። ምናልባት «ዳርዮስ» የዓለም ታሪክ ጋባሩ እያለ የሚጠረው ንጉሥ ሌላ ስሙ ሳይሆን አይቀርም። ጋባሩ በባቢሎንና በአካባቢው ባሉ አገሮች የነገሠ ንጉሥ ቢሆንም ጠቅላላ መንግሥቱን ይቆጣጠር ከነበረው ከንጉሥ ቂሮስ በታች ነበር። አይሁዳውያን ወደ ሀገሬቸው እንዲመለሱ የፈቀደላቸው ቂሮስ ነበር፤ ጋባሩ ወይም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ዳርዮስ እያለ የሚጠረው ንጉሥ ግን ባቢሎንን ይገዛ ነበር። እንዲህም ከተባለ ዳንኤል 6:28 የሚናገረው በአንድ ወቅት ስለነበሩ ሁለት ገዢዎች ነው ማለት ነው።

ሁለተኛ:- ምናልባትም ዳርዮስ የተባለው ራሱ ቂሮስ ሳይሆን አይቀርም። ብዙ ጊዜ ንጉሥ ሲሾም የመጀመሪያ ስሙ ይለወጥ ነበር። (በሀገሬችን በኢትዮጵያ እንኳ ንጉሦች ሲሾሙ የመጀመሪያ ስማቸው ይለወጥ እንደነበር የታወቀ ነው። ምናልባትም የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ በባቢሎን መንገሥ በጀመረበት ጊዜ ዳርዮስ የሚል ስም ተሰጥቶት ይሆናል። ስለዚህም ዳንኤል 28:- «ዳንኤል አገልግሎቱን የሰጠው ዳርዮስ ተብሎ በተጠረው በፋርሳዊው ቂሮስ ዘመን ነበር» ተብሎ ሊነበብ ወይም ሊተረጐም ይችላል። ምንም እንኳ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆነን መናገር ባንችልም ለጊዜው ትክክለኛ መስሎ የታየን ሐሳብ ይኸው ነው።

ዳርዮስ በባቢሎን ከነገሠ በኋላ አዲሱን መንግሥት እንደገና ማደረጀት ጀመረ። በዚያን ዘመን እንደዚህ ዓይነት ሰፊ ግዛት ያለው መንግሥት በዓለም ላይ ታይቶ አያውቅም። 120 ክፍለ ሀገሮች ነበሩት። በኋላ ደግሞ ወደ 127 ክፍ ብሎአል፥ (አስቴር 1:1 ተመልከት)። (በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለውን የሚያንና የፋርስ ካርታ ተመልከት።)

በ120 ግዛቶች 120 አስተዳዳሪዎች ነበሩ። እነርሱን በበላይነት የሚቆጣጠሩ ደግሞ ሦስት ከፍተኛ ሹማምንት ነበሩ። እነዚህ በ120 ግዛት ላይ የተሾሙ የበላይ አስተዳዳሪዎች የንጉሡ ትእዛዝ በትክክል መፈጸሙንና

የመንግሥቱ ግብር መሰብሰቡን ይቆጣጠራሉ። እነዚህ ሰዎች የተመረጡት በታማኝነታቸውና በአስተዳደር ችሎታቸው ነበር። ዳርዮስ ዳንኤል በባቢሎን መንግሥት ስለሠረው ሥራ ሳይሰማ አልቀረም፤ ስለዚህም ከሦስቱ የበላይ አስተዳዳሪዎች አንዱ እንዲሆን ተመረጠ። ሕይወቱና አገልግሎቱ መልካም ሆኖ በመገኘቱ ዳርዮስ በሦስቱ የበላይ አስተዳዳሪዎች ላይ አለቃ እንኳ ሊያደርገው አስቦ ነበር።

ይህ በአለቆቹና በመሳፍንቱ መካከል ቅንዓትን ፈጠረ። የዳንኤል ስም እንዲጎድፍና ከፍተኛ ሥልጣኑን እንዲያጣ ለማድረግ ሞከሩ። ምናልባትም ዳንኤልን የጠሉት ጉቦ መቀበልን በመቃወሙ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በግል ሕይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ ምንም ነቀፋ ሊያገኙበት አልቻሉም።

ቀጥሎም መንፈሳዊ ሕይወቱን መመርመር ጀመሩ። በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን ጽኑ እምነት አስተዋሉ። ስለዚህም አዲስ አቀድ ይዘው ወደ ንጉሡ ቀረቡ። ለሰላሣ ቀን ያህል በዚያ ግዛት ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ሁሉ ከንጉሡ በቀር ሌላ አምላክ እንዳያመልክ ሐሳብ አቀረቡ።

በጥንት ዘመን ነገሥታት አማልክትን ይወክላሉ ተብሎ ይገመት ነበር። ነገሥታት እንደ አማልክት ይመለኩ ነበር። አስተዳዳሪዎቹ ይህን አቀድ ያወጡት በሁለት ምክንያት ነበር። በመጀመሪያ:- የሀገሩ ሕዝብ በሙሉ ንጉሡን በማክበርና በማምለክ አንድነቱን እንዲያሳይ ፈለጉ። ሁለተኛ:- ሰዎች በሙሉ ሲያከብሩትና ሲያመልኩት በማየቱ ንጉሡ እንዲታበይ ፈለጉ። ይህንንም ያደረጉት ንጉሡ በትዕቢት ተነሣሥቶ አዲስ ሕግ እንዲያወጣና ዳንኤልን የሚያጠምዱበት ሰበብ ለማግኘት ነበር። ምንም እንኳ የሀገሩ ባለሥልጣኖችና መሳፍንት በዚህ ሐሳብ እንደተስማሙ ቢናገሩም ውሸታቸውን ነበር። ምክንያቱም ዳንኤልን አላማከሩትም ነበርና።

አቅዱ ንጉሡን ደስ አሰኘው፤ ስለዚህም በመላው መንግሥት ውስጥ አዋጅ አስነገረ። ለሰላሣ ቀን ያህል ከንጉሡ በቀር ማንኛውንም አምላክ የሚያመልኩትን ወደ አንበሳ ጉድጓድ በመጣል እንዲቀጡ ተስማማ። አንድ ጊዜ ሕግ ከወጣ ሕጉ ሊሻር አይችልም። በሜዶንና ፋርስ ሕግ መሠረት:- አንድ ሕግ ከወጣ ንጉሡ ራሱ እንኳ ለዚያ ሕግ መታዘዝ ነበረበት።

ዳንኤል ስለ አዲሱ ሕግ ሳይሰማ አልቀረም። ይሁን እንጂ በዳንኤል 3 ላይ ታሪካቸው እንደተጠቀሰው ጓደኞቹ ሁሉ እርሱም በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት መጸበቅ አልፈለገም። ዳንኤል የአስተዳዳሪዎቹን ሤራ ያውቃል፤ ስለዚህም ለመሞት እንኳ ተዘጋጅቶአል። በዳንኤል 3 ላይ የተጠቀሰው ፈተና ሦስቱ ወጣቶች እግዚአብሔር የከለከለውን ነገር እንዲያመልኩ ነበር። ለዳንኤል የቀረበለት ፈተና ግን በሕግ በተከለከለበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔርን ማምለኩ ነበር። በሁለቱም ምዕራፍ የተጠቀሰው ታሪክ ምንም እንኳ እውነተኛውን አምላክ እንዳያመልኩ ነገሥታት

ቢከለክሉአቸው የእግዚአብሔር ልጆች ግን ለአምላካቸው መታዘዛቸውን ያመለክታሉ። እንደ ዘወትር ልማዱ ሁሉ ዳንኤል በኢየሩሳሌም ትይዩ የነበረውን መስኮት ከፈተ። ሲጸልዩ ፊታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ማድረግ የአይሁዳውያን ልማድ ነበር። ይህንንም የሚያደርጉት ሰለሞን በ2ኛ ዜና መዋዕል 6:34-39 በተናገረው መሠረት ለመሆኑ ጥርጥር የለንም። በቀን ሦስት ጊዜ የመጸለይ ልማድ በመዝ.55:16-17 ተጠቅሶአል።

ዳንኤል እግዚአብሔርን ማምለኩን እንደማያቋርጥ አስተዳዳሪዎቹ እርግጠኞች ነበሩ። ዳንኤልን ሲጸልይ አገኙት፤ ሄደውም በንጉሡ ፊት ከሰሱት።

ከዚህ ቀደም ያስነገረውን አዋጅ በማስታወስ የሜዶንና ፋርስ ሕግ በረሱ በንጉሡ እንኳ ሊሻር እንደማይችል አሳሰቡት። ጸሎቱን ለንጉሡ ስላላቀረበ ለንጉሡ ያለውን አክብሮት ባለመግለጹ ዳንኤልን ከሰሱት። የመንግሥቱን ሕግ በመተላለፉም አሳጡት።

ወዲያውኑ ዳርዮስ የእቅዳቸው ዓላማ ምን እንደነበረ አስተዋለ። ዳንኤል እንዳይገደል ለማድረግ ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ የተለያየ ሙከራ አደረገ። ይሁን እንጂ ምንም ለማድረግ አልቻለም። ወደ ምሽቱ ገደማ ከሳሾቹ ወደ ንጉሡ መጡ። ዳንኤልም በአንበሶች ጉድጓድ እንዲጣል ተፈረደበት። ንጉሡ:- «ዳንኤል ሆይ÷ ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ያድንህ» ከማለት በቀር ምንም ሊያደርግ አልቻለም። በአመዛኙ ንጉሡ ይህን የተናገረው እግዚአብሔር ሊያድነው እንደሚችል በማመን አልነበረም።

16ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል እምነቱን ከመደበቅ ይልቅ በግልጽ መጸለይ የፈለገበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?
ለ/ እኛስ የዳንኤልን ምሳሌነት እንዴት መከተል እንችላለን?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 6:17-28

ጥያቄዎች

17ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ከአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ መውጣት እንዳይችል ንጉሡና ባለሥልጣኖቹ ምን አደረጉ?
18ኛ ጥያቄ:- በዚያ ሌሊት ንጉሡ ስለነበረበት ሁኔታ ግለጽ።
19ኛ ጥያቄ:- በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ንጉሡ ምን አደረገ?
20ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ዳንኤልን ምን ብሎ ጠየቀው?
21ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ከአንበሶች አፍ ለመዳኑ የተሰጡ ሁለት ምክንያቶች ምንድናቸው? (ዳን.6:22-23)

22ኛ ጥያቄ:- ዳንኤልን ለማጥፋት ተነሥተው የነበሩ ሰዎች ምን ሆኑ?

23ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በመንግሥቱ ላሉ ሰዎች ሁሉ ዳርዮስ የላከው አዋጅ ምን የሚል ነበር?

ለ/ ስለ እግዚአብሔርስ የሰጠው ገለጸ ምንድነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

የሜዶንና ፋርስ ሕግ በራሱ በንጉሡ እንኳ ሊለወጥ የሚችል ባለመሆኑ ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ ተጣለ:: የአንበሶቹ ጉድጓድ እንዴት ዓይነት ሥፍራ እንደነበር እርግጠኞች ባንሆንም÷ ምናልባት በመሬት ውስጥ የነበረ ሰፊ ዋሻ ሳይሆን አይቀርም:: ለአንበሶቹ ምግብ ለመስጠት እንዲያመች በዚህ ዋሻ ውስጥ ክፍት ሥፍረ ነበረበት:: በሜዶንና ፋርስ ዘመን ጥፋተኞችን በዚህ ሁኔታ መግደል የተለመደ ነበር::

ዳንኤል ወደ አንበሶቹ ጉድጓድ ከተጣለ በኋላ÷ የጉድጓዱ ደጃፍ በድንጋይ ታሸገ:: በድንጋዩ ላይ ሰም ካፈሰሱበት በኋላ ንጉሡና ባለሥልጣናቱ ማሕተማቸውን በሰሙ ላይ አተሙ:: ይህም የተደረገው ንጉሡን ጨምሮ ማንም ሰው ዳንኤልን ከአንበሶቹ ጉድጓድ እንዳያወጣው ነበር::

ንጉሡ በዚያ ሌሊት እንቅልፍ አልወሰደውም:: ዳንኤል የቅርብ አማካሪው ሳይሆን አይቀርም፤ ይሁን እንጂ ተታልሎ በአንበሶች ጉድጓድ እንደጣለ [illegible]

ንጉሡ ዳርዮስ ዳንኤልን የከሰሱ ባለሥልጣናትን ሁሉ ሰብስቦ ወደ አንበሶቹ ጉድጓድ እንዲጣሉ አደረገ። እነርሱን ብቻ ሳይሆን ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው እንኳ አብረው እንዲጣሉ አዘዘ። ገና በአየር ላይ እንዳሉ አንበሶች ተቀበሉዋቸው፤ አጥንቶቻቸውን ሰባብረውም ገደሉዋቸው። ያለቁት 120ዎቹ መሪዎችና ቤተሰቦቻቸው በሙሉ ይሁኑ ወይም ዋና ዋናዎቹ መሪዎች ብቻ እርግጠኞች አይደለንም። ሆኖም ሌሎቹ መሪዎች ለክብረቸውና ለሥልጣናቸው መስገብገብ እንደማይገባቸው ይህ መልካም ትምህርት ሊሰጥ እንደሚችል እርግጠኞች ነን።

24ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዘዳግም 32:35ን አንብብ።
ለ/ ጌታ የሰጠው ተስፋ ምንድነው?
ሐ/ ይህ ቃል በሕይወትህ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ተፈጽሞአል?

በዘዳግም ውስጥ መበቀል እንዳሌለብን እግዚአብሔር ያስጠነቅቀናል። ለሕዝቡ ጥንቃቄ ማድረግና ክፉ አድራጊዎችን ወዲያውኑ እንዲቀጣቸው እንመኛለን። ይሁን እንጂ ሁልጊዜ በዚህ ሁኔታ አይቀጣቸውም። የኋላ ኋላ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም መቀጣታቸው የማይቀር ነው። እግዚአብሔር ወዳጆቹን መታደግ ብቻ ሳይሆን እንደሚበቀልላቸውም የዳንኤል ታሪክ ይመሰክራል።

ዳንኤል 6 የሚፈጸመው ለዳንኤል አምላክ በቀረበ የምስጋና ዜማ ነው። በዳንኤል ምስክርነት ምክንያት ክርስቲያን ያልነበረው ንጉሥ እንኳ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ቻለ። ይህ መዝሙር በምዕራፍ 4 ናቡከደነፆር ከጻፈው መዝሙር ጋር ይመሳሰላል።

25ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 6:25-27 ከዳንኤል 4:1-3 አነፃፅር።
የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ናቡከደነፆርና ዳርዮስ አዋጁን ያወጁት በመላው ግዛታቸው ውስጥ ለሚኖረው ሕዝብ ነበር። ሁለቱም ስለታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች እንዲሁም ስላደረገው ተአምራት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ናቡከደነፆር የእግዚአብሔርን ኃይል ያየው በገዛ ሕይወቱ ሲሆን፥ ዳርዮስ የእግዚአብሔርን ኃይል ያየው ደግሞ የተመረጡ ሕዝቡን ሲያድን ነበር። ሁለቱም ስለ ዘላለማዊነቱና ዘላለማዊ ስለሆነው መንግሥቱ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ምንም እንኳ የአሕዛብ መንግሥት ከባቢሎን ወደ ሜዶን ከዚያም ወደ ፋርስ ቢሸጋገርም የእግዚአብሔር መንግሥት ግን አይለወጥም። ግዛቱንም ሆነ መንግሥቱን ማንም ሊደመስሰው አይችልም።

ዳንኤል 6 የእግዚአብሔር ልጆች መጠበቅ ስላለባቸው ጉዳይ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። የእግዚአብሔር ልጆች በታማኝነታቸው ሲጸኑ፥ በተለያየ

ምክንያት ይሰደዳሉ። እግዚአብሔር ከስደቱ ሊያድናቸው ይችላል፤ የእግዚአብሔር ልጆች በስደቱና በመከራው ውስጥ ጸንተው መቆማቸው ግን ዋነኛ ጉዳይ ነው። ይህ ምዕራፍ ሰዎች የሚያዝዙን ትእዛዝ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ እንዳለብን ያመለክታል። ታማኝነታችን መጀመሪያ ለእግዚአብሔር፥ ቀጥሎም ለነገሥታት መሆን አለበት።

<u>አረተኛ ቀን፡-</u> የዚህ ሳምንት ትምህርት ክለሳ

## <u>ሳምንታዊ ስብሰባ</u>

1. የሳምንቱ አምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ ዳንኤል የተቋቋመውን ፈተና ግለጽ።
2/ በዳንኤል 3 ላይ ከተጠቀሰው ፈተና የሚለየው እንዴት ነው?
3/ ዛሬ በሰዎች ላይ የሚደርስ ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ፈተና ምሳሌ ስጥ።

ለ. በመጀመሪያ ቀን ትምህርታችን ከስደት ዘመን ይልቅ በብልጽግናና በሰላም ጊዜ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን አዳጋች መሆኑንም መግለጻችን ይታወሳል።
1/ ከዚህ አባባል ጋር ትስማማለህን?
2/ ከሆነ፥ በብልጽግና ዘመን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን አስቸጋሪ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል?
3/ ሀብታም በመሆናቸው ወይም ሥልጣን በማግኘታቸው ከጌታ የኩበለሉ ክርስቲያኖችን ምሳሌ አቅርብ።
4/ ለምን ይመስልሃል የኩበለሉት?
5/ ብልጽግናን ወይም ሥልጣንን ስናገኝ ከጌታ እንዳንኩበልል ምን ማድረግ አለብን?

ሐ. 1/ ከዳንኤል 1-6 ያገኘኸውን ዋና ዋና ትምህርት ክለስ። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ያለው ዋና ዋና ትምህርት ምን ይመስልሃል?
2/ በእያንዳንዱ ምዕራፍ የተሰጠው ትምህርት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን እንዴት ሊያጽናናቸው እንደሚችል ግለጽ።

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥረ አንድ

## ዳንኤል 7፣1-14

**<u>የመጀመሪያ</u> ቀን**

አውሬይቱ እስክትገደል አካልዋም እስኪጠፋ ድረስ፥ በእሳትም ለመቃጠል እስክትሰጥ ድረስ አየሁ። ... በሌሊት ራዕይ አየሁ፤ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ፤ ወደፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ፥ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፤ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው። (ዳንኤል 7፣11፤ 13-14)።

ታሪክን በተለያየ መንገድ ልንመለከተው እንችላለን። ከእነዚህም ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው፡

የመጀመሪያው:- ሶሻሊስታዊ አመለካከት ነው። ሶሻሊስቶች ታሪክ በባለጸገችና በድሆች መካከል የሚደረግ ግጭት ወይም ትግል ነው ይላሉ። እንደ እነርሱ አመለካከት ከሆነ ታሪክ በጨቋኝና በተጨቋኝ መደብ መካከል የሚደረግ ትግል ነው።

ሁለተኛው:- የካፒታሊስት አመለካከት ነው። ይህ አመለካከት ታሪክ ለተለያየ ጥቅም በመንግሥታት መካከል የሚደረግ ትግል ነው ይላል። ታሪኩ ከግብርና ተነሥተው ለእድገትና ለኢንዱስትሪ ውጤት የሚደረግ ሂደት ነው። የሰው ልጅ የተሻለ ለማገኘትና ለመበልጸግ የሚያደርገው ሙከራ ነው።

ሦስተኛው:- ክርስቲያናዊ አመለካከት ነው። ክርስቲያኖች ታሪክ በሰው ክፋትና በፍቅር፥ ቅዱስና ጻድቅ በሆነው አምላክ መካከል የሚደረግ ግጭት ነው የሚል አቋም አላቸው። ይህ ክፋት የጀመረው በአዳምና ሔዋን ዘመን በኤደን ገነት ውስጥ ነበር፤ ታሪክ የጀመረው ከዚህ ሥፍራ ቢሆንም ክፋት እስከሚወገድበት እስከመጨረሻው ቀን ድረስ ይቀጥላል ይላሉ። ውጊያው የጨለማ ንጉሥ በሆነው ሰይጣንና የብርሃን ንጉሥ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል ነው። እነዚህ ሁለቱ ዋነኛ መንግሥታት ሲሆኑ፥ የሰው ልጅ ደግሞ የጦርነቱ ሜዳ ነው። ሰይጣን ሰዎችን ሊቆጣጠርና ለክፉ ዓላማው ሊጠቀምባቸው ይፈልጋል። እግዚአብሔር ግን ሰዎችን ከኃጢአትና ከሰይጣን ግዛት አውጥቶ ወደ ራሱ የብርሃን መንግሥት ሊያገባቸው ይፈልጋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዲሞት እግዚአብሔር የላከው ለዚህ ነበር። ከሰይጣን ጋር ተዋግቶ ድል ነሣ፤

ኃይሉን ሁሉ ነጠቀው፤ በመጨረሻም ፍጹም ያጠፋዋል። እስከዚያ ድረስ ግን ውጊያው ይቀጥላል።

ትንቢተ ዳንኤል በተለይም 10:10-11:1 ይህንን ውጊያ በሥዕላዊ ሁኔታ ይገልጸዋል። በምዕራፍ 7 ላይ እግዚአብሔር የዓለምን መንግሥትና የእርሱን ዘላለማዊ መንግሥት በማነፃፀር ሲያቀርብ እንመለከታለን።

በመጀመሪያ:- የሰዎች መንግሥታትን ክፋት እናያለን። በዳንኤል 7 አራት የዓለም መንግሥታትን ምስል እናያለን። አራቱም በአራዊት ተመስለዋል፤ አራዊት ደግሞ ዋናው ምኞታቸው ማጥፋት ነው። በየጊዜው ከመሻሻልና ከመሰልጠን ይልቅ እነዚህ መንግሥታት እየባሰባቸው ይሄዳሉ፤ በመጨረሻም የሚነሣው መንግሥት ክፋት ደግሞ በቃል ሊገለጽ ከሚቻለው በላይ ይሆናል።

ሁለተኛ:- እነዚህ መንግሥታት ጊዜያዊ ናቸው። አራዊቶቹ አስፈሪና ብርቱ ብዙ ነገርን ማድረግ የሚችሉ መስለው ቢታዩም በመጨረሻው ግን ለክፋታቸው መታሰቢያ ሊገኝላቸው በማይችል ሁኔታ ይደመሰሳሉ፤ (ዳንኤል 7:11)።

ሦስተኛ:- አንድ ዘላለማዊ መንግሥት ብቻ መኖሩን ያሳያል። ያም መንግሥት የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። እርሱ በሰማይ ዙፋኑ ላይ ነው። የሰው መንግሥት ብርቱ መስሎ ቢታይም የሚያሸንፈው የእርሱ ፈቃድ ነው። መንግሥቱን «ለሰው ልጅ» ማለትም ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሰጠዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ለመግዛት ሥልጣን አለው። ዘላለማዊ መንግሥቱ አይጠፋም። የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን፥ የዚያ መንግሥት ወራሾች ነን፤ (ዳን.7:27)።

ክርስቲያን ወንድሞቼና እህቶቼ የምንኖረው በአውሬዎቹ ዘመን ነው። የሰው መንግሥት የመግዛት ሥልጣኑን የጨበጠ መስሎ ይታያል። ይሁን እንጂ፥ አንድ ቀን ጽድቅና ሰላም በሞላበት መንግሥቱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንነግሣለን። ጌታችንና አዳኛችን ከእኛ ጋር ይነግሣል። ዓይኖቻችን በዚያ መንግሥት ላይ እንጂ በዚህ ዓለም ባለው አራዊት መንግሥት ላይ አይሁኑ።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የዓለም መንግሥታት ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ሲነፃፀር ያለውን ኃይልና የጊዜ ርዝመት ግለጽ።
ለ/ የሚለያዩት እንዴት ነው?
ሐ/ በዚህ ትምህርት እንዴት ልንጽናና እንችላለን?

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 7:1-14 አንብብ።
ለ/ ስለ አራቱ አራዊት ግለጽ።
ሐ/ «በዘመናት ስለ ሸመገለው» ግለጽ።
መ/ በመጨረሻ ስለሚቋቋመው መንግሥት ግለጽ።
ሠ/ የመጨረሻው መንግሥት ለማን ይሰጣል?

ሁለተኛ ቀን    ክፍል አንድ:- ዳንኤል 7:1-6

## ጥያቄዎች

3ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው ታሪክ ማን በሚገዛበት ዘመን ነው የተፈጸመው? በስንተኛው ዓመት?
ለ/ በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው ታሪክ የተፈጸመው በምዕራፍ 4÷ 5÷ እና 6 የተጠቀሰው ታሪክ ከመፈጸሙ በፊት ነው ወይስ በኋላ?

4ኛ ጥያቄ:- አራቱ አራዊት የተነሡት ከየት ነው?
5ኛ ጥያቄ:- ስለመጀመሪያው አውሬ ግለጽ::
6ኛ ጥያቄ:- ስለሁለተኛው አውሬ ግለጽ::
7ኛ ጥያቄ:- ስለ ሦስተኛው አውሬ ግለጽ::
8ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል 2:24-25 አንብብ::
ለ/ በዚህ ምዕራፍ የተማርናቸው አራት መንግሥታት እነማን ናቸው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

የትንቢተ ዳንኤል መሪ ሐሳብ የእግዚአብሔር ከሁሉም በላይ መሆኑን ተመልክተናል:: ይህንንም በግለሰቦችና በአረማውያን ነገሥታት ሕይወት እንኳ የሚሠራውን በማየት አረጋግጠናል::

ትንቢተ ዳንኤል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል:: የመጀመሪያው ክፍል ማለትም ከ1-6 ያለው የእግዚአብሔርን ከሁሉ በላይነትን የሚያሳዩ የተለያዩ ታሪኮች ይዞአል:: ሁለተኛው ክፍል ማለትም ከ7-12 ያለው ደግሞ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ መሆኑንና እግዚአብሔር የወደፊት ሁኔታዎችን ማወቅ ብቻ ሳይሆን እንደሚቆጣጠራቸው የሚያመለክቱ የተለያዩ ራዕዮችን ይዞአል:: እነዚህ ራዕዮች ከዳንኤል ዘመን አንሥቶ እስከፍጻሜ ዘመን ድረስ የሚሆኑትን ሁኔታዎች በግልጽ ያመለክታሉ::

በብዙ መንገድ ዳንኤል 7 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ትንቢቶች ሁሉ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ትንቢት ነው ማለት ይቻላል:: ይህም ከማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ይልቅ ዳንኤል ከነበረበት ዘመን አንሥቶ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ እስከሚገዛበት ዘመን ድረስ የሚሆኑትን ሁኔታዎች ቀጸም ተከተል በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ በማሳየቱ ነው:: ታሪኩ የተጻፈው በ533 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ እስከሚገዛበት ድረስ በዓለም ላይ

ስለሚነሡት ዋና ዋና መንግሥታት ያመለክታል። ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት እንደሚመሠረት ይናገራል። የዚህ ትምህርት ዋነኛ መልእክት እግዚአብሔር በሰማይ ብቻ ሳይሆን በምድርም እንደሚገዛ ማመልከት ነው። የሰዎች መንግሥታት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ይቃወሙ ይሆናል፤ የሚያሸንፉ መስለውም ይታዩ ይሆናል፤ ግን ምን ጊዜም ቢሆን በእግዚአ ብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው። መንግሥታት ታላቅ ስደት በሚያስነሡበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር በቁጥጥር ላይ ነው። በችግር ጊዜ ጠንካራና ታማኝ ሆነው የሚቆሙ ከእግዚአብሔር ጋር ያሸንፋሉ፤ ከእርሱም ጋር በዘላለማዊ መንግሥት ይገዛሉ።

ከመጽሐፉ አጋማሽ የመጨረሻው ክፍል ጀምሮ አተረጓጐሙ በጣም አስቸጋሪና ውስብስብ እየሆነ መጥቶአል። ይህም የሆነው ስለ ወደፊቱ ሁኔታ ለዳንኤል ለመግለጽ እግዚአብሔር በሕልምና በራዕይ በመጠቀሙ ነው። ከራዕዩቹ ውስጥ ብዙው ክፍል እንደ ነብር፥ አንበሳ፥ ድብ ወዘተ ያሉትን እንስሳት እንደ ምልክት ይጠቀምባቸዋል። እንደእነዚህ ዓይነቶቹ ራዕዮችንና መገለጦችን ስንመለከት ፀሐፊው ያየው ነገር በተጨማሪም በምሳሌያዊ አነጋገር የሚታዩ ራዕዮች በመጀመሪያ ልባችንን ሊነኩ ይገባል። በግልጽ አእምሮአችን ውስጥ መቅረፅ ይገባናል። ከዚያን በኋላ ነው ትርጓሜ ልንሰጥ የምንችለው። ራዕዮች የተለያዩ ስለሆኑ አንዳንድ ጊዜ የምንሰጠው ትርጓሜ ትክክል ላይሆን ይችላል። ለዚህም ነው የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ብዙ የተለያዩ ትርጓሜ ለእነዚህ ራዕዮች ያላቸው።

በዳንኤል 7 ውስጥ የተከናወኑት ነገሮች በሙሉ የተፈጸሙት የባቢሎን ንጉሥ ብልጣሶር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ላይ ነው። ናቦኒዳስ እውነተኛ ንጉሥ እንደነበርና ልጁ ብልጣሶር ግን በእርሱ ምትክ ይገዛ እንደነበር ከትምህርት ዘጠኝ ትረዳለህ። ይህም የሆነው በ553 ዓመት ክክርስቶስ ልደት በፊት አካባቢ ሲሆን፥ ታሪኩ የተፈጸመውም በምዕራፍ 4 እና 5 መካከል ነው። በዚያን ጊዜም ቢሆን የባቢሎን መንግሥት ጠንካራ ነበር። በብዙ ሁኔታ ይህ ራዕይ በዳንኤል 2 ከተሰጠው ሕልም ጋር ይመሳሰላል። በምዕራፍ 2 ላይ በምድር ላይ ስለሚነሡት አራት መንግሥታት እግዚአብሔር ለናቡከደነፆር እንደገለጸለት ተመልክተናል። በሰው ዓይን እነዚህ መንግሥታት ጠንካራና ባለግርማ መስለው ይታያሉ። እንደገና እግዚአብሔር ለዳንኤል ስለ እነዚህ መንግሥታት ሰፋ ያለ ገለጻ ሰጠው። እነዚህ መንግሥታት በእግዚአ ብሔር ዓይን ሲታዩ አረዊት ናቸው።

ስለ ወደፊቱ ሁኔታ እግዚአብሔር ራዕይ ሲሰጠው ዳንኤል በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር። ወዲያውኑ ተነሥቶ ራዕዩን መጻፍ ጀመረ። ራዕዩን በስምንት ምስሎች ልንከፍለው እንችላለን።

የመጀመሪያው ምስል:- ባሕር:- ዳንኤል ታላቅ ባሕር አየ። ከምሥራቅ፥ ከምዕራብ፥ ከሰሜንና ከደቡብ ኃይለኛ ነፋስ ተነሥቶ ባሕሩን

አናወጠው። ተራ በተራ አራት የተለያዩ አራዊት ከባሕር ወደ ምድር ወጡ።

እነዚህ ነፋሳት የአራቱን መንግሥታት ንግሥና ለመጀመር እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸውን የሰማይ መላእክትን ያመለክታሉ። (ይህንን የሚመስል ራዕይ በዘካርያስ 6፥1-8 ተመልከት።) ባሕር በጣም የተለመደ የአሕዛብ መንግሥታት ምሳሌ ነው። የባሕሩ መናወጥ በእነዚህ አሕዛብ መንግሥታት መካከል የሚደረገውን ውጊያና ብጥብጥ ያመለክታል።

9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ራዕይ 13፥1ን አንብብ። ይህ ራዕይ ከዳንኤል 7 ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ሁለተኛው ምስል:- የንስር ክንፎች የነበሩት አንበሳ፥ ዳንኤል ያየው የመጀመሪያው አውሬ ታላላቅ ክንፎች የነበሩት አንበሳ ነበር። በድንገት ክንፎቹ ተነቃቀሉ፤ በእግሩ ቆመ። የሰው ልብም ተሰጠው።

አንበሳ የአራዊት ንጉሥ በመባል ሲታወቅ፥ ንስር ደግሞ የአዕዋፋት ንጉሥ ነው። የሁለቱ መጣመር የመንግሥቱን ብርታት ያሳያል። ዛሬም ቢሆን በባቢሎን ጸጆች ላይ ክንፍ ያለው የአንበሳ ምስል እንደተቀረፀ እናያለን። በዳንኤል 2 በተጠቀሰው ምስል ላይ የወርቁ ራስ የባቢሎን መንግሥት እንደነበር ሁሉ፥ አንበሳም የባቢሎንን መንግሥት ያመለክታል።

የክንፎቹ መነቃቀልና የሰው ልብ ለአንበሳው መሰጠቱ በዳንኤል 4 የተጠቀሰውን የናቡከደነፆርን ከክብሩ መዋረድ የሚያሳይ እንደሆነ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይናገራሉ። እግዚአብሔር ልቡን ስለለወጠለት እንደ አውሬ ጨካኝ ሳይሆን በሥልጣኑ ሥር ላሉት ሰዎች መራራት ጀምሮአል።

በምስሉ ላይ ያየነው ወርቅ ከብር እንደሚበልጥ ሁሉ፥ በዚህ ምዕራፍ የምናየው አንበሳ ከድብ ወይም ከነብር ይበልጣል።

ሦስተኛው ምስል:- በአንድ ጐኑ የቆመና በአፉ መካከል ሦስት የጐድን አጥንቶችን የያዘ ድብ ነው። ለዚህ ድብ የሚችለውን ያህል እንዲበላ ትእዛዝ ተሰጠው።

10ኛ ጥያቄ:- ድብ የሚለውን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት።

በፍልስጤና ውስጥ ድብ ከአንበሳ ቀጥሎ በጣም የሚፈራ አውሬ ነው። በብርታቱና በአስፈላጊነቱ የታወቀ ነው። ድብ 250 ኪሎ ያህል ሊመዝን ይችላል። ብዙ ጊዜ የሚመገቡት አትክልት ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ግን ሥጋ ይመገባሉ።

ይህ ጽብ የተባበረውን የሚደንና ፋርስ መንግሥትን ያመለክታል። ሚደንና ፋርስ ከባቢሎን ቀጥሎ ሁለተኛው የዓለም መንግሥት ነበር። አንዳንድ ሰዎች ይህ ድብ በአንድ ጐኑ ቆሞ የታየው ሌላውን መንግሥት ለመውረር ለንጥቂያ መዘጋጀቱን ያመለክታል ይላሉ። ይሁን እንጂ፥ አንደኛው ጐን ከሌላው ከፍ ብሎ መታየቱ በተባበረው መንግሥት ውስጥ የፋርስ መንግሥት ከሚደን መንግሥት ይልቅ ጠንካራ እንደነበር ለማመልከት ነው። በጽቡ አፍ ውስጥ የነበረው ሦስት የጐድን አጥንት ግዛታቸውን ለማስፋፋት ሚደንና ፋርስ ያደረጉትን ሦስት ዋና ዋና ጦርነት ያመለክታል። የትኛው መንግሥት እንደሚነሣ፥ የትኛው መንግሥት እንደሚወድቅ የሚወሰነው በእግዚአብሔር በመሆኑ ጽል እንዲያደርጉ የሚረዳቸው ራሱ እግዚአብሔር ነበር።

አረተኛው ምስል:- አረት ክንፎችና አረት ራሶች የነበሩት ነብር ነው። ለዚህም ነብር ሥልጣን ተሰጠው።

ነብር ምንም እንኳ እንደ አንበሳ አስፈሪ ግርማ ባይኖረውም በጣም ፈጣን ነው። አረቱ ክንፎቹም ፍጥነቱን የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ ነብር በ330 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተነሣውን የግሪክ መንግሥት ያመለክታል። ይህ በታላቁ እስክንድር የሚመራው መንግሥት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከግሪክ እስከ ሕንድ ከዚያም አልፎ እስከ ሰሜን አፍሪካ ድረስ ግዛቱን አሰፋ። <u>አረቱ</u> ክንፎቹና <u>አረቱ</u> ራሶች መንግሥቱን በአረት መከፋፈሉን ያመለክታሉ። በትንቢቱ መሠረት ከታላቁ እስክንድር ሞት በኋላ ግዛቱን አረቱ ጄኔራሎች ተከፋፈሉት።

የታላቁ እስክንድር ኃይል ከራሱ የተገኘ አልነበረም። ግዛቱን የሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ነው።

11ኛ ጥያቄ:- የሰዎችን መንግሥታት እግዚአብሔር በአረዊት የመሰላቸው ለምን ይመስልሃል?
12ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ለሦስቱ መንግሥታት ሥልጣን የሰጣቸው ማን ነው?
ለ/ ይህ በአሁኑ ጊዜ ስላለው የዓለም መንግሥት ምን ያስተምረናል?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 7:7-10

## ጥያቄዎች

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ስለ አረተኛው አውሬ ግለጽ።
ለ/ ከዚህ ቀደም ከምታውቀው አውሬ ጋር ይመሳሰላልን?

14ኛ ጥያቄ:- ቀንደቹ ምን ሆኑ?
15ኛ ጥያቄ:- ስለ ታናሹ ቀንድ ግለጽ።
16ኛ ጥያቄ:- ሀ/ «በዘመናት ስለ ሸመገለው» ግለጽ።
ለ/ ማን ይመስልሃል?
17ኛ ጥያቄ:- በዙፋኑ አካባቢ እነማን ነበሩ?
18ኛ ጥያቄ:- ፍርድ ከመጸረጉ በፊት የተገለጡት ምንድናቸው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ትናንትና ዳንኤል በረዕይ ስላያቸው አራት ምስሎች ተመልክተናል። የመጀመሪያው ምስል:- የባሕር ነበር። ሁለተኛው ምስል:- የባቢሎንን መንግሥት የሚወክለው አንበሳ ነው። ሦስተኛው:- የሜዶንና ፋርስ መንግሥትን የሚወክለው ድብ ነው። አራተኛው ደግሞ:- የግሪክን መንግሥት የሚወክለው የነብር ምስል ነው።

ዛሬ ሁለት ተጨማሪ ምስሎችን እንመለከታለን። ዳንኤል ያየውን አምስተኛ አውሬ ምንነት ለመግለጽ ያዳግታል። እስከ አሁን ድረስ በዚህ ምድር ላይ ካሉት አራዊት አንዱንም ባይመስልም በጣም የሚያስፈሪ ነበር። ታላቅ ኃይል ነበረው። የሚያደቅበትና የሚውጥበት ታላላቅ የብረት ጥርሶች ነበሩት። ለመዋጥ የማይፈልገውን ደግሞ በታላላቅ እግሮቹ ይረጋግጣቸው ነበር። በራሱ ላይ አሥር ቀንዶች ነበሩት። ዳንኤል በእነዚህ ቀንዶች ምንነት በመገረም ላይ እያለ÷ በድንገት ከአሥሩ ቀንዶች መካከል አንድ ታናሽ ቀንድ ወጣ። ቀንዱ አደገ÷ ከአሥሩ ቀንዶች መካከል ሦስቱ ተነቅለው ወደቁ። ይህ ቀንድ ከሌሎች አሥር ቀንዶች የተለየ ነበር፤ እንደ ሰው ዓይኖች የመሰሰሉ ዓይኖችና በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበረው።

ይህ አራተኛ አውሬ የሮምን መንግሥት ያመለክታል። የሮም መንግሥት ጥንት ከነበሩት መንግሥታት ሁሉ ታላቅና ኃይለኛ ነበር። አዳዲስ አገሮችን ሁሉ አሸንፎ በቃኝ የማይል ነበር። ድል ያደረጋቸውን አገሮች በጭካኔ ይገዛቸው ነበር። ስለዚህ አራተኛው አውሬ በምዕራፉ መጨረሻ ላይ በድጋሚ በመጠቀሱ በሚቀጥለው ሳምንት እናጠናዋለን።

ስድስተኛ ምስል:- በሰማይ የተዘረጋውን ዙፋን ያሳያል። እዚህ ላይ ዳንኤል «በዘመናት የሸመገለው» በመባል የሚጠራውን እግዚአብሔር አብን ያመለክታል። ልብሱም ፀጉሩም በጣም ነጭ ነበር። ከነበሩት ብዙ ዙፋኖች በአንደኛው ተቀምጦአል። በመንኰራኩር ላይ ከተቀመጠው ዙፋኑ የእሳት ነበልባል ይወጣል። የእሳት ፈሳሽም ያለማቋረጥ ይመነጫል። በዙፋኑም ዙሪያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍጥረታት ቆመዋል። የተሰበሰቡት በአሕዛብ ለመፍረድ በመሆኑ መጻሕፍት ተገለጡ።

ባለፉት አምስት ምስሎች የዳንኤል አስተሳሰብ ያተኰረው በምድር በሚደረጉ ነገሮች ላይ ነበር። በድንገት ግን በሰማይ የሚደረገውን የሚያሳይ ራዕይ ተሰጠው። ይህ ራዕይ ከምድር መንግሥታት እንሥቶ እስከ ዘመናት ፍጻሜ ያለውን ያመለክታል። በሕዝብ ላይ ፍርድና ቅጣት በሚመጣበት ጊዜ ስለሚሆነው ሁኔታ ያሳያል።

ዳንኤል እግዚአብሔር አብን፦ «በዘመናት የሸመገለው» በማለት ይጠሪዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በዚህ ስም የተጠራው በዚህ ሥፍራ ብቻ ነው። ይህንን ቃል የተጠቀመበት፦ ምንም እንኳ መንግሥታት ቢነሡና ቢወድቁም እግዚአብሔር ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም እንደሚኖር ለማሳየት ነው። ከትውልድ እስከ ትውልድ የማይለወጥ እርሱ ብቻ ነው።

19ኛ ጥያቄ፦ ሀ/ የዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 4ን አንብብ። ዮሐንስ እግዚአብሔርን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ በዙፋኑ ላይ ሆኖ እንዳየው ግለጽ።
ለ/ ዳንኤል ስለ እግዚአብሔር ካየው ራዕይ ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ግለጽ።

ምንም እንኳ ብዙ ዙፋኖች ቢኖሩም፥ እግዚአብሔር አብ ግን በአንዱ ዙፋን ላይ ብቻ ተቀምጦአል። የተቀሩት ዙፋኖች የእነማን እንደሆኑ እርግጠኛ አይደለንም። አንዳንድ ሰዎች የተቀሩት ዙፋኖች የሥላሴ እንደሆኑ ይናገራሉ። ስለ እግዚአብሔር አብ ሁለት ነገሮች ብቻ ተገልጸአል። በመጀመሪያ፦ ልብሶቹ ነጮች ነበሩ። ይህም ንጽሕናንና ቅድስናን ለማሳየት የተለመደ አገላለጽ ነው። (ራዕይ 3፡5፥ 4፡4፥ 7፡9፲ 19፡14።)

ሁለተኛ ጸጉሩ በጣም ነጭ ነበር። ይህ ንጽሕናንና ቅድስናን የሚያሳይ ሳይሆን ዘላለማዊነቱን የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ነበረ፥ አሁንም አለ፥ ወደፊትም ይኖረል። ጅማሬ ወይም ፍጻሜ ሳይኖረው ከዘላለም እስከ ዘላለም ይኖረል።

20ኛ ጥያቄ፦ ራዕይ 1፡13-14 ተመልከት።
ሀ/ ስለማን የተሰጠ ገለጻ ነው?
ለ/ ይህ ዳንኤል ካየው ራዕይ ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

ከዚያ በኋላ ዳንኤል እግዚአብሔር ተቀምጦበት ስለነበረው ዙፋን ይገልጻል። ዙፋኑ ከእንጨት ወይም ከወርቅ የተሠረ ሳይሆን ከእሳት የተሠረ ነበር። ዙፋኑ እንደማንኛውም ዙፋን የተቀመጠው እግር ላይ ሳይሆን በመንኰረኩር ላይ ነበር። (ሕዝ.1፡13-28)

ከዙፋኑ ይወጣ የነበረውና በዙፋኑ ዙሪያ የነበረው እሳት

የእግዚአብሔርን ክብርና ፍርድ ያመለክታል። መንኰረኩሮቹ የሚያመለክቱት እግዚአብሔር በአንድ ሥፍራ የተወሰነ ሳይሆን በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር ብቻውን አልነበረም። ፈቃዱን የሚፈጽሙ በዙሪያው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፍጥረታት ነበሩ። እነዚህ ፍጥረታት መላእክት ይሁኑ ከሙታን የተነሡ ቅዱሳን ወይም ሁለቱም እርግጠኞች አይደለንም። የስብሰባው ዓላማ በአሕዛብና በመንግሥታቸው ለመፍረድ ነው። ፍርዱ የሚደረገው ያለምንም ማስረጃ እንዳልሆነ ለማሳየት መጻሕፍት ተገለጡ። የአሕዛብ ክፉ ሥራዎች ሁሉ በእነዚህ መጻሕፍት ተጽፎአል። ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው አንድ ቀን እንደሚፈረድባቸው ለሕዝቡ ደጋግሞ ገልጾላቸዋል። ሥራዎቻቸው ሁሉ በመጻሕፍት ተጽፈዋል፤ የሚፈረድባቸውም በእነዚህ መጻሕፍት በተጻፈው መሠረት ነው። ክፉም ሆነ በጐ ምግባረችን በእነዚህ መጻሕፍት ይጻፋል፤ (ኢሳ.65:6)።

21ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። ሚል. 3:16፤ ራዕይ 20:12 እና ማቴ.25:31-46። እግዚአብሔር የሚፈርደው በምን መሠረት ነው?

አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት እንደምንቆምና እንደ ሥራችን እንደሚፈረድብን ብዙዎቻችን እንዘነጋለን። ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች ሕይወትና ተግባር ይፈረዳል። ምንም እንኳ ዓላማው የተለየ ቢሆንም፥ በክርስቲያኖች ላይ ይፈረዳል። የሥራችን ጠቃሚነትና ዘለቄታ በእግዚአብሔር ይመዘናል፤ (1ቆሮ.3:12-15 ተመልከት)።

22ኛ ጥያቄ:- አስቲ ቆም ብለህ ሥራህን መዝነው።

ሀ/ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ነው ወይስ አንተን ብቻ የሚያስከብር?

ለ/ «በእንጨት፥ በገለባና በአገዳ» በተሠሩትና «በወርቅና በብር» በተሠሩት ሥራዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

<u>አረተኛ ቀን</u> <u>ክፍል ሦስት:- ዳንኤል 7:11-14</u>

<u>ጥያቄዎች</u>

23ኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ምን ሆነ?
24ኛ ጥያቄ:- የተቀሩት ሦስት አረዊት ምን ሆኑ?
25ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ከሰማይ ደመናት ጋር ሲመጣ ያየው ማንን ነው?
26ኛ ጥያቄ:- በዘመናት የሸመገለው «ለሰው ልጅ» ምን ሰጠው?

27ኛ ጥያቄ:- ዳን.7:14ን ከዳን.4:34 አነፃፀር:: የሚመሳሰሉትስ እንዴት ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ትናንትና ዳንኤል አሥር ቀንዶች ስላሉት ታላቅ አውሬ ያየውን ሪዕይ አጥንተናል:: ከዚያም ወደ ሰማያዊ የፍርድ አደባባይ ቀረበ:: ዛሬ ስለ አውሬው መጨረሻና ስለ አምስተኛው መንግሥት እንመለከታለን::

ሰባተኛው ምስል:- የአሪተኛውን አውሬ መጨረሻ ያመለክታል:: በቀንዱ ላይ ያለው አፍ በትዕቢት ይናገር ነበር:: በድንገት ተገደለ፤ ሥጋውም ለእሳት ተጣለ:: የተቀሩት ሦስት አሪዊት ግን ለጥቂት ጊዜ እንዲቆዩ ተደረገ:: ይሁን እንጂ ሥልጣን አልነበረቸውም::

ዳንኤል በሰማይ የሚደረገውን ፍርድ ካየ በኋላ በምድር የሚሆነውንም ሁኔታ ይመለከታል:: አሪተኛውን አውሬ፥ በተለይም በትዕቢት ይናገር የነበረውን ታላቅ ቀንድ በመመልከት ላይ ነው:: ይህንን በማየት ላይ እያለ ይህ አውሬ ተገደለ:: አውሬውን የገደለው ማን እንደሆነ ግን አልተገለጸም፤ ሥጋውም ለእሳት ተጣለ::

28ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:: ሪዕይ 19:20፤ 20:10፤ 14-15፤ እና 21:8:: በእሳቱ ባሕር ውስጥ የሚጣሉት እነማን ናቸው?

ከዚያ በኋላ ስለቀሩት ሦስት አሪዊት ይነግረናል:: እንደ አሪተኛው አውሬ ወዲያውኑ አልጠፉም:: ሥልጣናቸው ቢወሰድባቸውም፥ ለጥቂት ጊዜ በሕይወት እንዲኖሩ ተደረገ:: ይህ ለመረዳት የሚያዳግት ቀጥር ወይም ጥቅስ ነው:: እንደዚህ ጥቅስ አባባል ከሆነ:- የባቢሎን፥ የሜዶ-ፋርስና የግሪክ መንግሥታት ሥልጣናቸው ከተወሰደባቸው በኋላ እንደገና በሮም መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ይመስላል:: እያንዳንዱ መንግሥት ሥልጣኑን የወሰደው ከእርሱ በፊት ከነበረው መንግሥት ሲሆን አንደኛው መንግሥት በሌላኛው ውስጥ አለ ማለት ነው:: የሮሚ መንግሥት አብዛኛዎች የቀድሞ ሦስት መንግሥታትን የያዘ ነበረ::

ስምንተኛው ምስል:- «የሰው ልጅ» የሚመስለው በዘመናት ከሸመገለው ዘላለማዊ መንግሥትን ሲቀበል ያሳያል::

ዳንኤል እንደገና ወደ ሰማያዊ ሪዕይ ይመልሰናል፤ ምናልባትም ይህ ዙፋን የተዘረጋበት አዳረሽ አስቀድሞ የተገለጸው አዳረሽ ይሆናል:: እርሱ በመመልከት ላይ እያለ ሰው የሚመስል ፍጡር መጣ፤ በዘመናት

ወደ ሸመገለውም ፊት አቀረቡት:: በዘመናት የሸመገለውም ሁሉን የሚያጠቃልልና ዘላለማዊ መንግሥት ሰጠው:: ይህ የጠቅላላ ሪዕዩ መደምደሚያ ነው:: ታሪክ የሚመረኀም ወደዚህ ግብ ነው::

"የሰው ልጅ" የሚለው አባባል ለተለያዩ ምክንያቶች የሚጠቅም አባባል ነው::

አንደኛ:- የመጨረሻውን መንግሥትና የንጉሡን ባሕርይ ከእርሱ በፊት ከነበሩት እንዴት እንደሚለይ ለማሳየት የተሰነዘረ ቃል ነው:: የሰዎች መንግሥት:- ኃጢአተኛ÷ ጨካኝና ክፋትን የተሞላ ስለሆነ በአረዊት ተመስሎአል:: የእግዚአብሔር መንግሥት ግን በመጀመሪያ ለሁልጊዜ አቅዶ ምድርን በፈጠረት ጊዜ እንደነበረው ዓይነት የሚሆን ነው:: ይህም ሰውን ያለ ኃጢአት በፈጠረበት ጊዜ ማለት ነው:: ይህ መንግሥት ጽድቅና ውበት የሞላበት ይሆናል::

ሁለተኛ:- ይህ አገላለጽ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ስለነበረው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰነዘረ አባባል ነው:: ዳንኤል «የሰው ልጅ የሚመስለውን» አለ እንጂ÷ «የሰው ልጅ» አለማለቱን ማስተዋል ይኖርብናል:: ይህንንም «የሰው ልጅ» የሚለውን ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ደጋግሞ ይጠቀምበት ነበር:: ምንም እንኳ ይህ ቃል ሰብዓዊነቱን /ሥጋ መልበሱን) የሚያመለክት ቢሆንም በዳንኤል 7:14 በተገለጸው መሠረት ራሱን:- እንደሚመጣው ንጉሥ አድርጎ ለመግለጽም በዚህ ቃል ተጠቅሞበታል::

29ኛ ጥያቄ:- ኢየሱስ «የሰው ልጅ» በማለት የተናገረውን ለማየት የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:: ማቴ.9:4-8፤ 13:36-43:: እነዚህ ጥቅሶች «የሰው ልጅ» ስላለው ሥልጣን ምን ይናገራሉ?

ዳንኤል 7:13-14 በሁለቱ የሥላሴ አካላት ማለትም በአብና በወልድ መካከል ያለውን ሕብረት ያሳዩናል:: ከዚህም በላይ የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊነት በጉልህ ያመለክታል:: የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውል::

በመጀመሪያ:- «የሰው ልጅ የሚመስለው» የመጣው በሰማይ ደመና ነበር:: ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር በክብር ደመና ይታጀብ ወይም ይከበብ እንደነበር ይታወቃል፤ (ዘፀ.13:21፤ 16:10):: ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው በደመና ታጅቦ ነበር፤ ወደዚህ ምድር የሚመጣውም በደመና ታጅቦ ነው፤ (የሐዋ/ሥራ 1:9 እና ሉቃ.21: 25-28):: እነዚህ ደመናዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮታዊ ክብር ያመለክታሉ::

ሁለተኛ:- እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣንን÷ ክብርን÷

እንደሁም ኃይልን በመጨረሻው መንግሥት ውስጥ ሰጥቶታል፤ (ማቴ.28:19፤ ዮሐ.5:19-23፤ ኤፌ.1:19-23፤ 1ቆሮ.15:24-28)።

ሦስተኛ:- የእግዚአብሔር አብ መንግሥት፥ ከእግዚአብሔር ወልድ መንግሥት ጋር ተመሳሳይ ነው። በዳንኤል 4:34 የእግዚአብሔር መንግሥት ዘላለማዊና ከሌሎች መንግሥታት ሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ተመልክተናል። በዚህ በዳንኤል 7:14 ደግሞ «የሰው ልጅ የሚመስለው» የተባለለት የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ደግሞ ዘላለማዊና ከሁሉ በላይ መሆኑን እናያለን። እንደ አውሬዎቹ መንግሥታት የእርሱ መንግሥት የሚጠፋና የሚያልፍ አይደለም።

አራተኛ:- እንደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስንም የተለያዩ ነገድና ቋንቋ ያላቸው ሰዎች ያመልኩታል፤ (ራእይ.2:9-11)።

ዳንኤል ስለ አምስት የተለያዩ መንግሥታት ራዕይ አየ። የመጀመሪያ አራቶቹ በተለያዩ አራዊት ተመስለዋል። እነዚህ አራዊት ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ በዚህ ዓለም የሚነሡትን አራት መንግሥታት ይወክላሉ። በመጨረሻ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አምስተኛ መንግሥት ይመሠርታል፤ ይህ መንግሥት ዘላለማዊ መንግሥት ነው። መንግሥታትና ሕዝቦቻቸው በሙሉ በዚህ መንግሥት ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ ራዕይ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ መጥቶ ቤተ ክርስቲያንን በመሠረተበት ጊዜ ተፈጽሞአል ይላሉ። ይሁን እንጂ ዳንኤል የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስ በኃይልና በክብር ሲመለስ የታሪክ ፍጻሜ እንደሚሆን ነው።

30ኛ ጥያቄ:- 1ተሰ.4:13-18 አንብብ።
ሀ/ እነዚህ ጥቅሶች ስለምንድነው የሚተነብዩት?
ለ/ ይህና ይህን የመሳሰሉ ትንቢቶች የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዴት ያጽናናሉ?

ምንም እንኳ ይህ ዓለም በተለያዩ ማረኪ ነገሮች የተሞላ ቢሆንም በዚህ ምድር ላይ ብቻ ማተኮር የለብንም። ተስፋችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መጥቶ በሚመሠርተው መንግሥት ላይ ማተኮር አለበት። ዛሬ ቢመጣ ተዘጋጅተናልን? የልባችን መሻት «ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎ ና» የሚል ነውን?

አምስተኛ ቀን:-
---------

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ፤ ለሳምንቱ ስብሰባ ለመዘጋጀት የውይይት ጥያቄዎችን እንደገና ተመልከታቸው።

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን ከልስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ ሦስቱን የታሪክ አመለካከቶች ወይም ፍልስፍናዎች አወዳድር።
 2/ በትምህርት ቤት የተማርከው የትኛውን ፍልስፍና ነው?
 3/ ክርስቲያን ስለ ታሪክ ያለው አመለካከት ወይም ፍልስፍና ምንድነው?
 4/ የታሪኩ መጨረሻ ወይም ግቡ ምን ይመስልሃል?

ለ. 1/ ስለ አረቱ አረዊት ግለጽ።
 2/ እግዚአብሔር ምድረዊ መንግሥታትን በአረዊት የመሰላቸው ለምን ይመስልሃል?
 3/ ለእያንዳንዱ መንግሥት ሥልጣንን የሰጠው ማን ነው?
 4/ ከዚህ ገለጻ በአሁኑ ዘመን ስላሉት ሕዝቦችና መንግሥታት ምን እንማረለን?

ሐ. 1/ ከእነዚህ ምዕራፎች ስለ እግዚአብሔር አብ እና ስለ እግዚአብሔር ወልድ ምን ለመማር እንደምንችል ግለጽ።
 2/ የሚለያዩት እንዴት ነው?
 3/ የሚመሳሰሉትስ እንዴት ነው?
 4/ የክርስቶስ መለኮታዊነት የተገለጸው እንዴት ነው?

መ. 1/ አንድ ቀን በእግዚአብሔር እንደሚፈረድባቸው በመረዳት ክርስቲያኖች እንዴት መኖር ይገባቸዋል?
 2/ 1ቆሮ.3፡12-15 ተመልከት። በእንጨት የተሠረና በወርቅ የተሠረ ሥራ ልዩነቱ ምንድነው?

ሠ. 1/ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅርቡ እንደሚመለስ በማሰብ ክርስቲያኖች እንዴት ሊጽኑ ይገባቸዋል?
 2/ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ በከፍተኛ ናፍቆት የምትጠብቀው ምንድነው?

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥረ ሁለት

## ዳንኤል 7:15-28

የመጀመሪያ ቀን:-

እነሆም፥ ያ ቀንድ ከቅዱሳን ጋር ሲዋጋ አየሁ፤ በዘመናት የሸመገለው እስኪመጣ ድረስ፥ ፍርድም ለልዑሉ ቅዱሳን እስኪሰጥ ድረስ፥ ቅዱሳኑም መንግሥቱን የሚወርሱበት ዘመን እስኪመጣ ድረስ አሸነፋቸውም፤ (ዳን.7:21-22)።

የትንቢት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን ልጆች በተለይም በስደት ላይ ያሉትን ማጽናናት እንደሆነ በሌሎቹ ትምህርቶቻችን ተመልክተናል። እግዚአብሔር ይህን የሚያሳየን የሚደርስብንን መከራ በበላይነት በመቆጣጠር ነው።

ስደት ለእግዚአብሔር ሕዝብ አዲስ አይደለም። ከቃየልና ከአቤል ጀምሮ በተለያየ ሁኔታ ሲደርስባቸው ኖሯል። ከችግሩ ፍጻሜ በኋላ ምን እንደሚሆን እርግጠኛ ካልሆንን፥ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመልካም እንደሚለውጣቸው ካልተረዳን በስተቀር በመከራ ውስጥ ጸንተን መቆም አንችልም። በትንቢት አማካይነት እግዚአብሔር ሁኔታዎችን እንደሚቆጣጠርና ክፋውን አስወግዶ ጽድቅና ዘላለማዊ መንግሥትን እንደሚመሠርት ያሳየናል።

በዛሬው ትምህርታችን ይህንን እውነት በጉልህ ለማየት እንሞክራለን። ዳንኤል በራዕይ አሥር ቀንዶች የነበሩት ታላቅ አውሬ ተመለከተ። ከአሥሩ ቀንዶች መካከል የተነሣ ታናሽ ቀንድ፥ ሦስቱን ቀንዶች ነቃቀላቸው። ይህ ቀንድ ከቅዱሳን ጋር ተዋግቶ አሸነፋአቸው። ምንም እንኳ ይህ ቀንድ ወደፊት ስለሚነሣው በጣም ክፉ መሪ የሚያመለክት ቢሆንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት በታሪክ ውስጥ የተነሡትን መንግሥታት ሁሉ ይወክላል። በየዘመናቱ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የሞከሩ የተለያዩ መሪዎች ነበሩ። በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችም ተሰውተዋል። ዛሬም እንኳ ቢሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ብቻ በየዓመቱ በሺሕ የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ይገደላሉ። በመጨረሻው ዘመን ደግሞ ይህ ሁኔታ እየተባባሰ ይመጣል። ሰይጣን አጭር ጊዜ ብቻ እንደቀረው ያውቃል። በዓለም መሪዎች በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የመጨረሻ ሙከራ ያደርጋል።

1ኛ ጥያቄ:- ራዕይ 12:7-17 አንብብ። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ሰይጣን ስለሚያደርገው የመጨረሻ ሙከራ ግለጽ።

በዚህ ስደት ዘመን ጸንተን የምንቆመው እንዴት ነው? አራት ዋና ዋና እውነቶችን ማስታወስ አለብን። በመጀመሪያ:- ምንጊዜም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን እንደምትሰደድ መረዳት አለብን፤ (ዮሐ. 16:1-2)። ስደት የደረሰብን እኛ ብቻ አይደለንም። በዘመናት ሁሉ ክርስቲያኖች ሲሰደዱ ነበር። ዛሬም ቢሆን በዓለም ዙሪያ ብዙዎች ለእምነታቸው ሲሉ መከራ እየተቀበሉ ነው።

ሁለተኛ:- በስደትም ጊዜ ቢሆን ሕይወታችን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆኑን መረዳት አለብን። የትኛው አውሬ እንደሚነሣ የሚወስነው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የስደቱ ጊዜ ማጠር መርዘሙን የሚወስነውም እርሱ ነው። ጽድቅ የሞላበት ዘላለማዊ መንግሥቱ የሚመሠረትበትን ጊዜ የሚወስነው እግዚአብሔር ነው።

ሦስተኛ:- ስደት እንድናድግና እንድንበረታ ያደርገናል። በስደት ጊዜ እምነታችን ይጠራል፥ ይጠነክራልም። ቤተ ክርስቲያን የምትጠራው በሰላም ጊዜ ሳይሆን በስደት ውስጥ ስታልፍ ነው።

2ኛ ጥያቄ:- ያዕቆብ 1:2-4 አንብብ። መከራ በሕይወታችን የሚያስገኘውን የተለያዩ ነገሮች ዘርዝር።

አራተኛ:- ለማንኛውም ስደት ፍጻሜ እንዳለው ተረዳ። የሰው መንግሥት ጊዜያዊ ነው። ለጊዜው ፈተና የሚያርስባቸው በታማኝነት እግዚአብሔርን ቢከተሉ ዘላለማዊ መንግሥት በጽድቅ የሚገዛው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው፤ እኛም የመንግሥቱ ተሳታፊ እንሆናለን። የሚያሳድዱን ግን በዘላለማዊ እሳት ውስጥ ይጣላሉ። ዘላለማዊው መንግሥት ይጠብቃቸዋል። የዚያ መንግሥት ወራሾች ነን። ያን መንግሥት እንድንቀበል በስደት ጊዜ ታማኝ ሆነን መገኘት ይኖርብናል። ስለዚህ ወንድሞችና እህቶች ትዕግሥት ይኑራችሁ። ያ መንግሥት በቅርቡ ይመጣል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል። ጳውሎስ እንደተናገረው ሁሉ:- «ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት በዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው፤» (2ቆሮ.4:16-18)።

3ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 7:15-28 አንብብ።
ሀ/ አራቱ አራዊት ምንን ይወክላሉ?
ለ/ የዘላለሙ መንግሥት የተሰጠው ለማን ነው?
ሐ/ ታናሹ ቀንድ ቅዱሳኑን ምን አደረጋቸው?
መ/ ታናሹ ቀንድ ምን ሆነ?

ሁለተኛ ቀን　　ክፍል አንድ:- ዳንኤል 7:15-18

## ጥያቄዎች

4ኛ ጥያቄ:- ራዕዩን ካየ በኋላ ዳንኤል ምን እንደሆነ ግለጽ።
5ኛ ጥያቄ:- የሕልሙን ትርጉም ለመረዳት ዳንኤል ወደ ማን ሄደ?
6ኛ ጥያቄ:- አራቱ አራዊት ምንን ይወክላሉ?
7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የመጨረሻው መንግሥት የተሰጠው ለማነው?
ለ/ የመጨረሻው መንግሥት ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ባለፈው ሳምንት በምዕራፍ 7 ያለውን ራዕይ አጥንተናል። ከዳንኤል ዘመን አንሥቶ የሰው ልጅ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚመጣበት ድረስ ያለውን የዓለም መንግሥታት ታሪክ የተረዳው በዚያ ራዕይ ውስጥ ነበር። አምስት ዋና ዋና መንግሥታት እንዳሚኖሩ ተገለጸለት። አራቱ ምድራዊ መንግሥታት ሲሆኑ፥ የመጀመሪያው የባቢሎን፥ ሁለተኛው የሜዶንና ፋርስ፥ ሦስተኛው የግሪክ፥ አራተኛው የሮም መንግሥታት ናቸው። አምስተኛው ግን የራሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ይህንን መንግሥት «የሰው ልጅ ለሚመስለው» ይሰጠዋል። እንደ ሌሎች መንግሥታት ሳይሆን ይህ መንግሥት ዘላለማዊና የማይጠፋ ነው። ይሁን እንጂ ራዕዩን ባየበት ወቅት ዳንኤል ትርጉሙን አልተረዳም ነበር።

በዚህ ሳምንት የራዕዩን ትርጉም እናጠናለን። በተለይም ስለ አራተኛው መንግሥት በአንክሮ ጥናት እናደርጋለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናየው ራዕይ በቀላሉ የሚሰጥ ነገር አይደለም። ነቢያት ራዕይ ሲያዩ በሥጋቸውም ሆነ በስሜታቸው ጉዳት ይደርስባቸው ነበር። (ለምሳሌም ያህል ኢር. 4:19 እና ሕዝ. 3:15ን ተመልከት።) የተለያዩ ራዕዮችን (ከምዕ.7-12) ባየበት በእያንዳንዱ ወቅት ዳንኤል ደካምና ድንጋጤ ይሰማው ነበር። (ዳን.8:27፡ 10:1-2)።

በምዕራፍ 2 የታየውን ራዕይ ለመተርጎም ቢችልም ዳንኤል የራሱን ራዕይ ትርጓሜ ለማግኘት አልቻለም። የሌላ ሰው ዕርዳታ አስፈለገው። ስለዚህም በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ቆመው ከነበሩት መላእክት ወደ አንዱ ቀረበ። ራዕዩን የሚያይ ብቻ ሳይሆን በድንገት በራዕዩ ውስጥ በመሳተፍ የራዕዩ አካል ሆነ። ዳንኤል ለመረዳት የፈለጋቸውን ጥያቄዎች በሚከተለው ሁኔታ አጥር፥ ምጥን አድርገን ልናቀርባቸው እንችላለን። ላቀረባቸውም ጥያቄዎች መልአኩ የተብራራ ትርጉም ሰጥቶታል።

የዳንኤል የመጀመሪያ ጥያቄ:- የራዕዩ ትርጉም ምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ መልስ እንዲሆነው መልአኩ ስለ ራዕዩ ጠቅለል ያለ ትርጉም ሰጠው። አራቱ አራዊት አራት ነገሥታትን ወይም መንግሥታትን ይወክላሉ። እነዚህ የሰማያዊው ተዓረሪ የሆኑ ምድራዊ መንግሥታት ናቸው። መልአኩ እነዚህ መንግሥታት እነማን እንደሆኑ አልነገረውም። ይሁን እንጂ ዳን.2 እና 8ን መሠረት በማድረግና በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙትን ራዕዮች በመመርመር እነዚህ መንግሥታት እነማን እንደሆኑ መረዳት እንችላለን።

የሰዎች መንግሥት ሲያከትም፥ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ይጀመረል። በራዕዩ የመጀመሪያ ክፍል:- መንግሥት «የሰው ልጅ ለሚመስለው» እንደተሰጠ አይተናል፤ በዚህ ክፍል ደግሞ መንግሥት ለቅዱሳን መሰጠቱን እናነባለን። ለምን በራዕዩ ውስጥ ለውጥ እንደተደረገ አናውቅም። ይሁን እንጂ ለእርሱ ታማኞች እግዚአብሔር መንግሥትን መስጠቱ የዚህ ምዕራፍ ዋነኛ ትምህርት ነው። (ዳን.7:18፤ 22፤ 27 ተመልከት።)

እነዚህ መንግሥትን የሚቀበሉ ቅዱሳን እነማን ናቸው? አንዳንድ ሰዎች መላእክትን እንደሚያመለክት ይናገራሉ፤ (በዳንኤል 4:17 መሠረት)። ይሁን እንጂ ይህ የሚያመለክተው በዘመናት ሁሉ ተነሥተው የነበሩትን የእግዚአብሔር ሰዎች ነው። እነዚህ ከአዳምና ከሔዋን ዘመን እንሥቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ እስኪመለስ ድረስ በእግዚአብሔር የታመኑ ቅዱሳን ናቸው። እነዚህ ቅዱሳን የልዑሉ ሕዝብ ናቸው። እርሱ አምላካቸው፥ እነርሱ ደግሞ ሕዝቡ ናቸው። የምድር ነገሥታት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊያጠቁና ሊያሸንፉ እንዲሁም መንግሥታቸውን መቆጣጠር እንደሚችሉ ያስቡ ይሆናል፤ እኛ ግን ሁሉን የሚችል አምላክ ሕዝብ ነን። ለእኛ ያለው እቅድ አንድ ቀን ይፈጸማል።

ቅዱሳን መንግሥትን ለመውሰድ አይዋጉም። እንዲያውም መንግሥቱን የሚሰጣቸው ራሱ እግዚአብሔር ነው። የዚህ መንግሥት ባለቤት እግዚአብሔር ሲሆን፥ ቅዱሳኑ ግን ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መንግሥት በእርሱ ሥልጣንና ኃይል ይገዛሉ። የሰው መንግሥት ምንም ያህል ታላቅና ብርቱ መስሎ ቢታይም ጊዜያዊ ነው። ቅዱሳኑ የሚቀበሉት መንግሥት ግን ዘላለማዊ ነው። ፍጻሜም የለውም።

8ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት። 1ቆሮ. 6:2፤ 2ጢሞ.2:12፤ ራዕይ 20:4። በሚመጣው መንግሥት ክርስቲያን ስለሚኖረው ሥፍራ እነዚህ ጥቅሶች ምን ይላሉ?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 7:19-22

## ጥያቄዎች

9ኛ ጥያቄ:- ዳን.7:19ን ከዳን.7:7 ጋር አነፃፀር። በዳን.7:19 ምን ተጨማሪ ማስረጃ ይሰጣል?
10ኛ ጥያቄ:- በዚህ ክፍል ውስጥ የዳንኤልን አስተሳሰብ በጣም የማረከ ጉዳይ ምንድነው?
11ኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ቅዱሳንን ምን አደረገ?
12ኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ኃይሉን ያሳየው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ስለ ራዕዩ ለመረዳት የፈለገው ዳንኤል ለመልአኩ ጥያቄዎችን ማቅረቡን ቀጠለ። ስለ መጀመሪያዎቹ ሦስት አራዊት ተጨማሪ ማብራሪያ አለመፈለጉ ሳያስደንቀን አይቀርም። ስለ ዘላለማዊ መንግሥትም ተጨማሪ ማብራሪያ አልጠየቀም። ያቀረበው ጥያቄ ስለ አራተኛው መንግሥት ነበር።

የዳንኤል ሁለተኛ ጥያቄ:- ይህ አራተኛ አውሬ ምንን ይወክላል?

ምናልባትም የዳንኤልን አስተሳሰብ የማረከው በዚህ በአራተኛው አውሬ ላይ የሚታየው ልዩ ተፈጥሮ ሳይሆን አይቀርም። ዳንኤል ስለ አራተኛው አውሬ እንደገና ይገልጻል። በጣም የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነበር። ዋና ዓላማው በተቻለው መጠን ያገኘውን ሁሉ በአስቸኳይ ማጥፋትና መደምሰስ ነበር። አንዳንዶቹን በብረት ጥርሶቹ ይቆረጣጥማቸዋል። ሌሎቹን ደግሞ ነሐስ በሚመስሉ እግሮቹ ይረጋግጣቸዋል። ዳን. 7:19 እና 7:7ን ስናነፃፅር ይህ አውሬ የነሐስ ጥፍሮች እንደነበሩት እንረዳለን። ራዕዩን እንደገና ተመልክቶ በፊት ያላየውን ነገር ያስተዋለ ይመስላል።

የዳንኤል ሦስተኛ ጥያቄ:- አሥሩ ቀንዶች ምንን ይወክላሉ?
የዳንኤል አራተኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ምንን ያመለክታል?

ከማንኛውም ነገር ይልቅ የዚህ ታናሽ ቀንድ ጉዳይ የዳንኤልን አስተሳሰብ ስቦአል። እንደገና ከአሥሩ ቀንዶች መካከል ሲነሣ ተመለከተ። ከእርሱ በፊት የነበሩትን ሦስት ቀንዶች ነቃቀላቸው፥ በትዕቢትም መናገር ጀመረ። ወዲያውኑ ዳንኤል አዳዲስ ነገሮችን ተመለከተ። ይህ ታናሽ ቀንድ ከሌሎች ቀንዶች ሁሉ እስኪበልጥ ድረስ ታላቅ ሆነ። ቀንዱ ትልቅ በሆነ መጠን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተዋግቶ ድል አደረጋቸው፤ ብዙዎችንም

ገጸላቸው:: ወደያውኑ ግን ቀንዱ ተሰበረ:: የፍርድ ጊዜ በመምጣቱ «በዘመናት የሸመገለው» ለቅዱሳኑ ፈረደላቸው:: እግዚአብሔር ለቅሶአቸውን ሰማ፤ በታናሹ ቀንድ ፈረደና መንግሥቱን ለቅዱሳኑ ሰጣቸው:: ለዘላለምም ይገዛሉ::

ለዳንኤል ጥያቄ የተሰጠውን መልስ በሚቀጥለው ክፍል እንመለከታለን:: የዳንኤል አስተሳሰብ ያተኮረው በአረተኛው አውሬና በታናሹ ቀንድ ላይ ቢሆንም፥ መልአኩ ያተኮረው በመጨረሻው ዘመንና የእግዚአብሔር መንግሥት በሚመሠረትበት ጊዜ ላይ ነበር:: እኛ ክርስቲያኖችም ምንጊዜም ቢሆን ሁኔታዎችን የምናየው በዚህ መልክ ነው:: አስተሳሰባችን የሚያተኩረው በችግሮቻችን ላይ ነው:: በምድር የሚደርስብን ስደትና መከራ ከብዶብናል:: እግዚአብሔር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ግን ከፋትና ዓመፅ ተወግደው መንግሥቱ ተመሥርቶ ውድ ለሆኑ ልጆቹ ዋጋቸውን የሚሰጥበት ጊዜ ላይ ነው:: ይልቁንስ አሁን የሚያጋጥመንን ችግር ከምናይ ትኩረታችን ወደሚመጣው መንግሥት ቢሆን አይሻልምን?

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚከብዱህን አንዳንድ ችግሮች ዘርዝር::
ለ/ አስተሳሰብህና ትኩረትህ ይበልጥ እግዚአብሔር ወደፊት በሚመሠርተው መንግሥት ላይ ቢሆን አንተንና ሌሎች ክርስቲያኖችን እንዴት የሚያጽናና ይመስልሃል?

አረተኛ ቀን ክፍል ሦስት:- ዳንኤል 7:23-28

## ጥያቄዎች

14ኛ ጥያቄ:- የአረተኛው አውሬ ትርጉም ምንድነው?
15ኛ ጥያቄ:- የአሥሩ ቀንዶች ትርጉም ምንድነው?
16ኛ ጥያቄ:- የታናሹ ቀንድ ትርጉም ምንድነው?
17ኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ያደረጋቸው አረት ነገሮች ምንድናቸው?
18ኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ለስንት ዓመታት ያህል ነው ቅዱሳኑን ሲያጠፋ የቆየው?
19ኛ ጥያቄ:- በፍርዱ አደባባይ ምን ተደረገ?
20ኛ ጥያቄ:- የራዕዩን ትርጉም ከሰማ በኋላ ዳንኤል ምን ሆነ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

በሁለተኛው ክፍል ላይ ዳንኤል ራዕዩን ለሚተረጉምለት መልአክ ብዙ ጥያቄዎችን ሲያቀርብለት እንመለከታለን:: በመጀመሪያ ለቀረበው ጥያቄ

መልስ:- መልአኩ ለዳንኤል ስለ አራቱ አራዊት ሰፋ ያለ ገለጻ ሰጠው:: አሁን ግን ለሁለተኛው፥ ለሦስተኛውና ለአራተኛው ጥያቄ መልስ ሲሰጠው እንመለከታለን::

አራተኛው አውሬ በምድር ላይ የሚመሠረት አራተኛ መንግሥት ነው:: የዚህ አውሬ ተፈጥሮ ከሌሎች አራዊት ሁሉ የተለየ ነው:: ይህ አውሬ የሚታወቀው በግርማው፥ በኃይሉና በፈጣንነቱ ሳይሆን ምድርን ሁሉ ለማጥፋትና ጽል ለማድረግ ባለው ፍላጐት ነው:: ይህ አራተኛ መንግሥት የሮምን መንግሥት የሚወክል እንደሆነ ተመልክተናል:: የሮም መንግሥት የተነሣው ዳንኤል ከሞተ አራት መቶ ዓመታት በኋላ እንደሆነ ታሪክ ይናገራል::

21ኛ ጥያቄ:- በዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ የሮምን መንግሥት ካርታ ተመልከት:: በጥንቱ የሮም መንግሥት ክልል ውስጥ የነበሩትን አንዳንድ የዘመናችን አገሮች ጥቀስ::

ዳንኤል በሦስተኛ ደረጃ ያቀረበው ጥያቄ በአራተኛው አውሬ ራስ ላይ ስለነበሩት አሥር ቀንዶች ነበር:: እነዚህ ቀንዶች፥ ከዚህ መንግሥት ውስጥ የሚነሡ አሥር ነገሥታት እንደሆኑ መልአኩ ይናገራል:: ሁሉም የሚነግሡት በአንድ ወቅት ነው::

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን በዚህ አውሬ ራስ ላይ የነበሩትን አሥር ቀንዶች በዳንኤል 2 ላይ ከተጠቀሰው ምስል የእግር ጣቶች ጋር ያያይዙታል:: እነዚህ አሥር ቀንዶች እነማንን እንደሚያመለክቱ እርግጠኛ ሆነን መናገር አንችልም:: የታሪክ ምሁራንም ቢሆኑ ታሪካዊ በሆነው በሮም መንግሥት ውስጥ አሥር ነገሥታት በአንድ ጊዜ የገዙና የዳንኤል ትንቢትንም የፈጸሙ ሊያገኙ አይችሉም:: ስለዚህም እነዚህ አሥር ነገሥታት የሚነሡት ወደፊት ነው የሚለውን እምነት በብዙ ሰዎች ውስጥ ሊያሳድር ችሎአል:: እነዚህ ሰዎች ዳንኤል ስለ አራተኛው አውሬ ያየው ራዕይ በከፊል በሮም መንግሥት ላይ ተፈጽሞአል ይላሉ:: የተቀረው ግን ወደፊት በጽሮው የሮም ግዛት ውስጥ በሚነሣው መንግሥት ይፈጸማል ብለው ያምናሉ:: ይህም አሥር ነገሥታት ተባብረው የሚገዙት መንግሥት ይሆናል:: በአንድነት ሆነው አዲሱን የሮም መንግሥት ይመሠርታሉ:: በብዙ መልኩ ይህ መንግሥት ጥንታዊውን የሮም መንግሥት ይመስላል::

22ኛ ጥያቄ:- ራዕይ 13:1-8 እና 17:12-14 አንብብ::
ሀ/ የዮሐንስና የዳንኤል ራዕይ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
ለ/ ዮሐንስ በራዕይ ስላየው አውሬ ግለጽ::

ምንም እንኳ ዮሐንስ በነበረበት ዘመን የሮም መንግሥት ሥልጣን ላይ ቢሆንም በመጨረሻ ዘመን ስለሚነሣው አውሬ ያየው ራዕይ ዳንኤል ካየው ራዕይ ጋር ይመሳሰላል:: ምንም እንኳ ዮሐንስ ያያቸው አንዳንድ ራዕዮች

ከዳንኤል ጋር የማይመሳሰሉ ቢሆኑም በአብዛኛው ግን የሁለቱም ራዕይ ይመሳሰላሉ።

ከማንኛውም ነገር የበለጠ ዳንኤል ስለ ታናሹ ቀንድ ለማወቅ ይፈልጋል። መልአኩ ይህ ታላቅ ቀንድ በምድር ላይ የሚነሣ አሥረ አንዳኛ ንጉሥ እንደሆነ ለዳንኤል ነገረው። ይህ በጣም ታናሽና ተረ ንጉሥ ቢመስልም ከእርሱ በፊት የነበሩትን ሦስት ነገሥታት ደምስሶአቸዋል። መንግሥታቸውን እንደወሰደም ጥርጥር የለውም። ይህ መንግሥት በጣም ታላቅ ይሆንና ሌሎቹን መንግሥታት ሁሉ ይቆጣጠረቸዋል።

መልአኩ ስለዚህ ስለሚመጣው ንጉሥ አረት ባሕርያት ይገልጻል። በመጀመሪያ:- ኩሩና እግዚአብሔርን የማያከብር ነው። የሰማይን አምላክ ያለማቋረጥ ይሳደባል።

ሁለተኛ:- የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ባለው ዓላማ ትልቅ ውጊያ ይከፍታል።

ሦስተኛ:- ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያመልኩባቸውን ሃይማኖታዊ በዓላት ያስቀረል። ይህም እንደ ፋሲካ የመሳሰሉ የአይሁድ በዓላትንና እንደ ክርስቶስ ልደትና ትንሣኤ የመሳሰሉ በዓላትን ሁሉ ይጨምረል።

አረተኛ:- የራሱን ሕግና ሞረላዊ ሥነ-ምግባር ለመመሥረት ይፈልጋል። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ላለው ሕግ ወይም ሥነ-ምግባር ደንታ የለውም። ሰዎች እርሱ ላወጣው ሕግ እንዲገዙ ያደርጋል።

23ኛ ጥያቄ:- እነዚህ አረት ባሕርያት በዓለማችን ምን ያህል እየታዩ ናቸው?

ይህ ታናሽ ቀንድ ለጥቂት ጊዜ ይሳካለታል፤ ቅዱሳኑንም ያሸንፋቸዋል። እስከ መጨረሻው የሚያጠፋቸውም መስሎ ይታያል።

24ኛ ጥያቄ:- በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ስለሚመጣው ስደት የሚከተለውን ተመልከት:- ራዕይ 16:4-6፤ 17:6።

ለእግዚአብሔር ልጆች ነገሮች ምንም ያህል የተባባሱ ቢሆኑም እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠረል። ለተወሰነ ጊዜ ሕዝቡን ድል እንዲያደርግ ለታናሹ ቀንድ ሥልጣን ይሰጠዋል። ይህ ጊዜ የሚቆየው «ለዘመን፥ ለዘመናትና ለዘመንም እኩሌታ» ነው። ይህንን አባባል እንደሚገባ ለመረዳት አዳጋች መሆኑን በምዕራፍ 4 ተመልክተናል። ምናልባትም አጭር ጊዜን ለመግለጽ የተሰነዘረ አባባል ይሆናል። በሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር የመከረውን ጊዜ ያሳጥረዋል። (ማቴ.24:22) ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ግን ይህ «ዘመን» የሚለው ቃል አንድ ዓመትን እንደሚያመለክት ይናገራሉ። እንደዚህም ከሆነ በዳንኤል 4 መሠረት

ናቡከደነፆር የታመመው ለሰባት ዓመት ነበር ማለት ነው:: አሁን እንገደህ በዚህ ትንቢት ስለዚህም ይህ ታናሽ ቀንድ ቅዱሳኑን የሚዋጋቸው ለሦስት ዓመት ተኩል ነው በማለት ያስባሉ::

25ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ይህ ሦስት ዓመት ተኩል የተጠቀሰበትን ሥፍረ ለማየት የሚከተሉትን ቁጥሮች ተመልከት:: ዳን.12:7፤ ራዕይ 11:1-3፤ 13:5::
ለ/ 42 ወር ስንት ዓመት ነው?
ሐ/ 1260 ቀን ስንት ዓመት ነው?

ይህ ታናሽ ቀንድ በበረታበትና ቅዱሳኑን በሚዋጋበት ጊዜ በጽንነት ይገዳላል:: የእግዚአብሔር ፍርድ በሰማይ ይጀመራል፤ በአህዛብም ላይ ይፈረድባቸዋል:: ታናሹ ቀንድና ሌሎችም ዓመፀኛ መንግሥታት ሥልጣናቸውን ይገፈፋሉ፥ ፈጽሞም ይጠፋሉ::

በመጨረሻም የእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ አሸናፊ ይሆናል:: ዘላለማዊ መንግሥቱን ይመሠርታል:: እስከ ሞት ጸረስ ታማኝ ለሆኑት ሕዝቦች ሥልጣንን ይሰጣቸዋል፤ (ራዕይ 12:10-11):: ለጥቂት ጊዜ በዚህ ታናሽ ቀንድ ቢሸነፉም ለዘላለም ይነግሣሉ:: የምድር ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔርን ያመልካሉ፤ ለሕጉም ይታዘዛሉ:: ምንም እንኳ የተለያዩ መንግሥታት በምድር ቢኖሩም፥ ሁሉም ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ሥር ይሆናሉ:: ይህ መንግሥት የጽድቅና የሰላም መንግሥት ይሆናል::

የዳንኤል ሕልም እዚህ ላይ ይፈጸማል:: ምንም እንኳ ከራዕዩ የአንዳንዶቹ ትርጉም ቢነገረውም ተረብሾ ነበር:: ገና ያጋባው ራዕዩ እንደሆነ አንጠረጠርም:: ይሁን እንጂ፥ የእግዚአብሔር እቅድ ትክክለኛና የሚሻል መሆኑን በማወቁ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት አጸና:: ራዕዩን በጽሑፍ ከማስፈሩ በቀር ስለ ራዕዩ ለማንም አልተናገረም::

ምንም እንኳ ስለ ዳንኤል ራዕዮች የተለያዩ አተረጓጐም ቢቀርቡም ራዕዮቹን በሚከተለው ሁኔታ ማጠቃለል ይቻላል ብዬ አስባለሁ:: በ70 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በኢየሩሳሌም የነበረው ቤተ መቅደስ ከተደመሰሰ በኋላ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ትኩረቱን ከአይሁዳውያን ላይ አንሥቶ በአሕዛብ ላይ አደረገ:: ስለዚህም ዳንኤል ይኖር የነበረው «በአህዛብ ዘመን ነበር ማለት ነው፤ (ሉቃስ 21:24):: በወገኖቹ አይሁዳውያን ላይ ተፅዕና ስለሚያደርጉት አራት መንግሥታት እግዚአብሔር ለዳንኤል ገለጸለት:: በመጀመሪያ ባቢሎናውያን አይሁዳውያንን በምርኮኝነት ወሰዷቸው:: ቀጥሎ የሚደንና የፋርስ መንግሥት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ፈቀደላቸው:: ሦስተኛ የግሪክ መንግሥት ታላቅ ስደት አስነሣባቸው:: አረተኛ የሮም መንግሥት ደግሞ ጌታ ኢየሱስን ሰቀለው:: ከዚህ በኋላ በታሪክ ውስጥ ወደሚደረገው ታላቁ የፍጻሜ ጦርነት እግዚአብሔር ዳንኤልን ይወስደዋል::

አንድ ቀን የጥንቱን ሮም የሚመስል መንግሥት እንደገና ያንሰራራል፤ የአሥር ነገሥታት ጥምር መንግሥት ያቋቁማሉ። በድንገት ቅዱሳት መጻሕፍት «የክርስቶስ ተቃዋሚ» እና «የዓመፅ ሰው» በማለት የሚጠሩት ሰው ይነሣል፤ (1ተሰ.2:1-12፤ 1ዮሐ.2:18)። ከእርሱ በፊት የነበሩትን ሦስት መንግሥታት ያዋርዳቸዋል፤ የዓለም መሪ ይሆናል። የእግዚአብሔርንም ሰዎች ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል ያሳድዳቸዋል። ክርስቶስ ሲመጣ ግን እርሱና ሌሎች መንግሥታት ሁሉ ይደመሰሳሉ። ክርስቶስና በእርሱ የሚያምኑት ለዘላለም ይነግሣሉ።

26ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ለዚያ ዘላለማዊ መንግሥት ዝግጁ ነህን?
ለ/ ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንድትነግሥ፥ ዛሬ ክርስቶስን በታማኝነት ታገለግለዋለህን?

አምስተኛ ቀን:-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ፤ ለሳምንቱ ስብሰባ ለመዘጋጀት የውይይት ጥያቄዎችን እንደገና ተመልከት።

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. በስደት ያሉትን ክርስቲያኖች የሚረዱ በመጀመሪያ ቀን ትምህርት የተማርካቸውን አራት ዋና ዋና እውነቶችን ተወያይባቸው።
1/ የተማርነው እውነት በስደት ጊዜ ክርስቲያኖች ጸንተው እንዲቆሙ እንዴት ሊረዱዋቸው ይችላሉ?
2/ በስደት ጊዜ ጸንተው እንዲቆሙ እነዚህን እውነቶች ለቤተ ክርስቲያንህ ሰዎች እንዴት ልታካፍላቸው እንደምትችል ተወያዩ።

ለ. በዳንኤል 7 የተጠቀሰውን ራዕይ በዮሐንስ ራዕይ 13:1-18 እና 17:12-14 ከተጠቀሱት ጋር አነጻጽር።
1/ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
2/ የሚለያዩትስ እንዴት ነው?

ሐ. በታናሹ ቀንድ የታየው ባሕርይ በዘመናችን በዓለም ላይ ከሚታዩት ባሕርያት ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

መ. ክርስቲያኖች በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ለሚመጣው መንግሥት ተዘጋጅተው ለመኖር እንደሚችሉ ዘርዝር።

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥረ ሦስት

## ዳንኤል 8

### የመጀመሪያ ቀን

እኔም ዳንኤል ተኛሁ፥ አያሌ ቀንም ታመምሁ፤ ከዚያም በኋላ ተነሥቼ የንጉሡን ሥራ አሠራ ነበር፥ ስለ ራዕዩም አደንቅ ነበር፥ የሚያስተውለው ግን አልነበረም፤ (ዳን.8:27)።

ብዙ ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች ለጥያቄዎቻችን ሁሉ መልስ እንፈልጋለን። ነገሮች ሁሉ ለምን በእንዲዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደሆኑ መረዳት እንሞክራለን። በማያጠራጥር ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ሁሉ ለመረዳት እንፈልጋለን። እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ ለጥያቄዎቻችን ሁሉ መልስ አይሰጠንም። መልስ ቢሰጠንም እንኳ እንደሚገባ አንረዳውም። ለምን እንደምንታመም ወይም ለምን አንዳንድ ወዳጆቻችን በሞት እንደሚለዩን አናውቅም። የእግዚአብሔርን መንገድ እየተከተልን እያለ ለምን ችግርና መከራ እንደሚደርስብን አናውቅም፤ (1ቆሮ.13:12)። የእግዚአብሔርን ዓላማ ማየት የምንችለው በጭላንጭል ነው። የእግዚአብሔር መንገድ ከእኛ መንገድ የተሻለና የተለየ እንደሆነ ማስተዋል ይኖርብናል፤ (ኢሳ.55:8-9 ተመልከት)።

የእግዚአብሔርን መንገድ ለማወቅ ወይም ለመረዳት የማንችልባቸው ሦስት ሥፍራዎች አሉ። በመጀመሪያ:- በግል ሕይወታችን ለምን አንዳንድ ችግሮችና መከራዎች እንደሚደርሱብን አናውቅም። ይህም ሕመም፥ የገንዘብ ችግር ወይም ስደት ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛ:- በዚህ በምንኖርበት ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ አናውቅም። በዓለም ላይ ክፋት የበዛው ለምንድነው? እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ለምን አይፈርድባቸውም? ረሃብና ጦርነት የሚበዛው ለምንድነው? ቤተ ክርስቲያን ለምን ነፃነት አይኖራትም? ለምንድነው ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባት ንጹሕ ሆና የማትገኘው? እነዚህ መልስ ካላገኙ ጥያቄዎቻችን ጥቂቶቹ ናቸው።

ሦስተኛ:- ስለወደፊቱ ሁኔታ አንዳንድ ጥያቄዎች አሉን። ወደፊት በሕይወታችን ምን ያጋጥመን ይሆን? በማለት እንጠይቃለን። በዓለም መጨረሻ ምን ይደረግ ይሆን? በማለት እንጠይቃለን። ዓለም የሚጠፋው በጦርነትና በኒውክሊር ቦምብ ይሆን? ምንም እንኳ የወደፊቱን የሚመለከቱ ትንቢቶች እግዚአብሔር ቢሰጠንም አንዳንድ ጊዜ ትርጉማቸው ግልጽ አይሆንልንም።

ዳንኤል አንዳንድ ሕልሞችን እንዲተረጉም እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሰው ነበር። ይሁን እንጂ ለሁሉም ሕልሞችና ራዕዮች አጥጋቢ ትርጉም እንዳላገኙ እርሱ ራሱ ይናገራል። ትርጉሞቻቸው ከእርሱ እንኳ ተሰውረዋል። እኛ የምንኖረው ከዳንኤል ብዙ ዓመታት ርቀን ነው። እርሱ ከተናገራቸው ትንቢቶች አንዳንዶቹ በመፈጸማቸው የዳንኤልን ትንቢት ከእርሱ ይልቅ ለመረዳት ችለናል ማለት ይቻላል። የዳንኤልን ትንቢት ለመረዳት እንድንችል እግዚአብሔር የወደፊቱን ለማወቅ የሚረዱንን ሌላ ተጨማሪ ትንቢቶችን ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ የወደፊቱ ሁኔታዎችና የአፈጻጸማቸው ቅደም ተከተል ከእኛ የተሰወሩ ናቸው። ምንም እንኳ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት በዚህ ዓለም ስለሚሆኑት ሁኔታዎች ለመረዳት የምናደርገው ሙከራ መልካም ቢሆንም ብዙ ያልተገለጸልን ጉዳይ መኖሩን ማስታወስ ይኖርብናል። ምን ጊዜም ቢሆን ትሑት ሆነን ከእኛ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ለመቀበል መዘጋጀት አለብን።

እነዚህ ጥያቄዎች በውስጣችን ሲመጡ ምን ማድረግ አለብን? በመጀመሪያ፡- የመረዳት ችሎታችን በከፊል መሆኑን መቀበል አለብን። ለሚደርስብን ችግር ሁሉ መልስ የለንም። ሁለተኛ፡- እምነታችን በእግዚአብሔር እንጂ በአካባቢው ሁኔታዎች ላይ አለመሆኑን መገንዘብ አለብን። እግዚአብሔርን በቃሉ በተገለጸው መሠረት ልንረዳው ይገባል፤ ይህን ካደረግን ምንም ዓይነት ችግር ቢገጥመን እንኳ እንደሚወደንና ሁኔታዎችን ሁሉ እንደሚቆጣጠር እናውቃለን።

1ኛ ጥያቄ:- ስለ እግዚአብሔር ዓላማ የምታቀርባቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ምንድናቸው? በኢትዮጵያ ያሉ ክርስቲያኖች የሚጠይቋቸውና መልስ ያላገኙላቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ምንድናቸው?

በዚህ ሳምንት ትምህርታችን በምዕራፍ 8 ያለውን የዳንኤልን ትንቢት እናጠናለን። በዚህ ራዕይ ስለ ሁለት ታላላቅ የዓለም መንግሥታት የተነገረ ትንቢት እንመለከታለን። ይህ ትንቢት በዳንኤል ዘመን አልተፈጸመም፤ ለእኛ ግን ያለፈ ታሪክ ነው። በጣም አስደናቂ በሆነ እርግጠኝነት እግዚአብሔር ስለ እነዚህ ሁለት የዓለም መንግሥታት ለዳንኤል ገለጸለት። ከእነዚህ መንግሥታት አንዱ በአይሁዳውያን ላይ ስለሚያመጣው መከራም ገልጸለታል። ይህ ጨካኝ መሪ ወደፊት ከእኛም ጊዜ በኋላ ለሚነሣው የዓለም መሪ ምሳሌ ነው። ይህ መሪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያሳድዳል። በዳንኤል 11 ስለዚህ መሪ ሰፋ ባለ ሁኔታ እንመለከታለን።

2ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 8ን አንብብ።

ሀ/ ዳንኤል ያያቸው ሁለት እንስሳት ምንድናቸው?

ለ/ የትኞቹን ሁለት መንግሥታት ያመለክታሉ?

ሐ/ ስለ ታናሹ ቀንድ መጠነኛ ገለጻ ስጥ።

## ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 8:1-14

### ጥያቄዎች

3ኛ ጥያቄ:- ዳን.7:1ን እና ዳን.8:1ን አነፃፅር:: በእነዚህ ሁለት ራዕዮች መካከል የስንት ዓመት ልዩነት አለ?

4ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በራዕዩ ዳንኤል ወዴት ተወሰደ?
ለ/ በኋላ ይህች ከተማ የየትኛው መንግሥት ዋና ከተማ ሆነች? ነህ.1:1 እና አስቴር 1:5 ተመልከት::

5ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ያየውን የመጀመሪያ እንስሳ ግለጽ:: ምን ይመስላል? በየትኛው አቅጣጫ ይዋጋ ነበር? የውጊያውስ ውጤት ምን ሆነ?

6ኛ ጥያቄ:- ሁለተኛውን እንስሳ ግለጽ:: ምን ይመስላል? ከየት መጣ ከምን ጋር ተዋጋ? የውጊያውስ ውጤት ምን ሆነ?

7ኛ ጥያቄ:- በፍየሉ ላይ የነበረው ቀንድ ምን ሆነ?

8ኛ ጥያቄ:- የተሰበረውን ቀንድ ምን ተካው?

9ኛ ጥያቄ:- ስለ መጨረሻው ቀንድ ግለጽ:: ከየት መጣ? የት ነው በጸንብ ያደገው? እንዳንድ ለማድረግ የፈለጋቸው ነገሮች ምንድናቸው?

10ኛ ጥያቄ:- ታናሹ ቀንድ ለምን ያህል ጊዜ ነው የመፀው?

### የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ዳንኤል 8 በምሳሌያዊ ሁኔታ የቀረበ የመጨረሻው ትንቢት ነው:: (በዳንኤል ትንቢት ውስጥ) ዳንኤል 2፤ 4፤ 7 እና 8 የወደፊቱን በምሳሌያዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ትንቢቶች ናቸው:: ከምዕራፍ 9ና በኋላ ያሉትን ግን የሚገልጽልን በምሳሌያዊ ሁኔታ አይደለም:: በዳንኤል 2 የዓለም መንግሥታት በታላቅ ምስል ቀርበዋል:: በምዕራፍ 4 የናቡከደነፆር ሕይወት በታላቅ ዛፍ ተመስሎአል:: በምዕራፍ 7 ወደፊት የሚነሡት መንግሥታት በአራት ታላላቅ አራዊት ተመስለዋል:: በምዕራፍ 8 ደግሞ ሁለቱ መንግሥታ[ት] በሁለት እንስሳት ተመስለዋል::

በሌላ መልኩ ስናየው ግን ዳንኤል 8 በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ የሌ[ላ] ክፍል መጀመሪያ ነው:: ከዳን.2:4 - ዳን.7:28 ያለው ክፍል የተጻፈው በአረማይክ ማለትም በባቢሎናውያን ቋንቋ እንደነበር መግለጻችን ይታወሳል:: ከምዕራፍ 8 ጀምሮ ግን የተጻፈው የአይሁድ ቋንቋ በሆነው በዕብራይስጥ በመሆኑ ምዕራፍ 8 የአዲስ ክፍል መጀመሪያ ነው ማለት ይቻላል:: ይህም ዳንኤል የጻፈው ለአይሁዳውያን በመሆኑ ነው፤ ለወደፊት የሚደርሱባቸውን ዋና ዋና ነገሮች ሊያሳያቸው ይፈልጋል::

በዳንኤል 8 ያለው ራዕይ የተሰጠው በምዕራፍ 7 ያለው ራዕይ ከተሰጠ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው። ምንም እንኳ ዋናው ንጉሥ ናቦኒዳስ ቢሆንም ባቢሎንን በመግዛት ላይ የነበረው ልጁ ብልጣሶር እንደነበር ታስታውሳለህ። ብልጣሶር በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ማለትም በ551 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ዳንኤል ራዕይን ተቀበለ። ወደፊት በሜዶንና ፋርስ መንግሥት ላይ የሚነግሠው ቂሮስ በባቢሎን ላይ ያመጸውም በዚሁ ዘመን ነበር። በ551 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የባቢሎን መንግሥት መዳከም ጀመረ፤ ከአሥራ ሁለት ዓመት በኋላም ጨርሶ ወደቀ። ዳንኤል 8 ከባቢሎን በኋላ ስለተነሡት ሁለት መንግሥታት እንጂ ስለ ባቢሎን አይገልጽም።

ዳንኤል 8፡1-14 በአምስት የተለያዩ ክፍሎች ሊከፈል ይቻላል።

ክፍል 1:- ራዕዩን ያየበት ሥፍራ፤ (ዳን.8፡1-2)። እግዚአብሔር በራዕይ ዳንኤልን በኡባል ወንዝ አጠገብ ወደነበረው ወደ ሱሳ ግንብ ወሰደው። ምንም እንኳ ዳንኤል በነበረበት ዘመን ሱሳ አነስተኛ መንደር ብትሆንም÷ እግዚአብሔር ዳንኤልን ወደ ሱሳ የወሰደበት ምክንያት ወደፊት የሜዶንና የፋርስ ዋና ከተማ እንደምትሆን ስላወቀ ነው። በኡባል ወንዝ አጠገብ የተመሠረተችው ሱሳ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ታላቅ ከተማ ትሆናለች። ሱሳ:- የሜዶንና ፋርስ መንግሥታት ከግሪኮች ጋር ትልቅ ውጊያ ያደረጉባት ሥፍራ ናት።

ክፍል 2:- ስለ አውራው በግ የተሰጠ ራዕይ (ዳን.8፡3-4)። በኡባል ወንዝ አጠገብ ቆሞ ዳንኤል ሁለት እንስሳት አየ። የመጀመሪያው እንስሳ አውራ በግ ነበር። በዚህ በግ ራስ ላይ በመጀመሪያ አንድ ቀንድ÷ ከዚያም ሌላ ቀንድ ታየ። ሁለተኛው ቀንድ ከመጀመሪያው ቀንድ የሚበልጥ ሆነ። ይህ አውራ በግ ሌሎቹን እንስሳት ሁሉ እየተዋጋ ድል አደረጋቸው። ውጊያውንም ያደረገው በሦስት አቅጣጫ ማለትም በምዕራብ÷ በሰሜንና በደቡብ ነበር። ይህ አውራ በግ ሌሎችን እንስሳት ሁሉ አሸነፋቸው፤ የወደደውንም ነገር ማድረግ ይችል ነበር።

11ኛ ጥያቄ:- ዳን.8፡20 ተመልከት። ይህ አውራ በግ ማንን ይወክላል?

ይህ አውራ በግ የሜዶንና ፋርስን መንግሥት እንደሚወክል ለዳንኤል ተነገረው። የፋርስ መንግሥት ዓርማ አውራ በግ እንደነበር ታሪክ ራሱ ይመሰክራል። (የኢትዮጵያ ዓርማ አንበሳ እንደሆነ ዓይነት ነው።) ምንም እንኳ በባቢሎን ላይ አስቀድሞ ያመፀው የሜዶን መንግሥት ቢሆንም÷ ከሜዶን መንግሥት ጋር የተጣመረው የፋርስ መንግሥት ጠንካራና የሚበልጥ ሆነ። ታናሹ ቀንድ የሜዶንን መንግሥት ሲያመለክት ትልቁ ቀንድ ደግሞ የፋርስን መንግሥት ያመለክታል። በኋላ ግን ሁለቱ በአንድነት ተጣመሩና

የሜዶንና ፋርስ መንግሥት አቋቋሙ። ይህ ጥምር መንግሥት ከ200 ዓመት በላይ ገዝቶአል። አውራው በግ የተዋጋው በምዕራብ፥ በሰሜንና በደቡብ እንጂ በምሥራቅ አቅጣጫ አልተዋጋም። ይህም የሜዶንና ፋርስ መንግሥት ግዛቱን ያስፋፋው በምዕራብ (በታናሹ እስያ) በሰሜን (በባቢሎን፥ ሜዲያ፥ ፋርስ) እና በደቡብ (በግብፅና ፓለስታይን) በኩል እንደነበር ለማመልከት ነው።

ክፍል 3:- ስለ አውራ ፍየል የተሰጠ ሪዕይ፤ (ዳን.8:5-8)። ዳንኤል ስለ አውራው በግ በማሰብ ላይ እያለ በድንገት ሌላ እንስሳ ማለትም አውራ ፍየል ተመለከተ። ይህ ፍየል በዓይኖቹ መካከል አንድ ትልቅ ቀንድ ብቻ ስለነበረው ከሌሎች እንስሳት የተለየ ነበር። የመጣው ከምዕራብ አቅጣጫ ሲሆን፥ በጣም እየሮጠ ወደፊት ይገሰግስ ነበር፤ በጣም ከመፍጠኑ የተነሣ ምድርን የሚረግጥ እንኳ አይመስልም ነበር። በታላቅ ኃይል ከአውራው በግ ጋር ተዋጋ፤ የበጉን ሁለት ቀንዶች ሰበረ፤ በመጨረሻም ገደለው። ይህ ቀንድ በጣም ማደግ ጀመረ፤ በድንገት ግን የነበረው አንድ ቀንድ ተሰበረ፤ በእርሱም ምትክ አራት ቀንዶች በቀሉ።

12ኛ ጥያቄ:- ዳን.8:21ን ተመልከት። አውራው ፍየል የትኛውን መንግሥት ይወክላል?

ይህ አውራ ፍየል የሜዶንና የፋርስን መንግሥት የሚያጠፋው የግሪክ መንግሥት ምሳሌ ነው። የግሪኮች በተለይም የሴሌዩሲድ ግሪኮች መለያ ዓርማ አውራ ፍየል እንደነበር በታሪክ የተረጋገጠ ነው። በዓይኖቹ መካከል የነበረው ታላቅ ቀንድ ታላቁ እስክንድርን ያመለክታል። እስክንድር ታላቅ የግሪክ ንጉሥ ነበር። አውራው ፍየል ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ሲገሰግሥ እንደታየ ሁሉ፥ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ትልቁ እስክንድርም ከግሪክ (ከባቢሎን በስተምዕራብ) እስከ ሕንድ (ከባቢሎን በስተምሥራቅ) እና እስከ ግብፅ ድረስ ግዛቱን አስፋፋ። ትልቁ እስክንድር ግን ራሱን የሚቆጣጠር ሰው አልነበረም። በመጠጥ ብዛት በ33 ዓመቱ ሞተ። ታላቁ ቀንድ ተሰበረ። ሃያ ዓመት ተዋግቶ ያገኘው መንግሥት ለአራት ተከፈለ። ከጄኔራሎቹ አንዱ ካሳንደር ይባላል፤ እርሱም ግሪክንና ሜቄዶንያን ወሰደ። ሊሲማኩስ የሚባለው ጄኔራል ታናሹ እስያን ወሰደ። ሲሊውከስ የሚባለው ሦስተኛው ጄኔራል ሦርያንና ባቢሎንን ወሰደ። ቶሎሚ የሚባለው ጄኔራል ግብፅንና ፓለስታይንን ወሰደ። በዚህ ሁኔታ ከ220 ዓመታት በኋላ ዳንኤል የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ።

13ኛ ጥያቄ:- በዚህ መጽሐፍ በስተጀርባ ያለውን የግሪክ መንግሥት ካርታ ተመልከት።

ክፍል 4:- ታናሹ ቀንድ፤ (ዳን.8:9-12)። በአውራው ፍየል ራስ ላይ ከበቀሉት አራት ቀንዶች አንዱ ላይ ሌላ ታናሽ ቀንድ በቀለ።

ይህ ቀንድ በሬዕዩ ውስጥ ትልቁንና አስፈላጊውን ሥፍራ ይዞአል። የዳንኤል ገለጻ ሰፋ ያለውን ሥፍራ የሰጠውም ለዚሁ ቀንድ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ፥ የዚህን ታናሽ ቀንድ ማንነት መረዳት በጣም አዳጋች ነው። በመንግሥታት መካከል የሚደረገው ውጊያ አከትሞ፥ በአንድ መሪና በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚደረገው ውጊያ የሚጀምረው ከዚህ ሥፍራ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። ስለዚህ ታናሽ ቀንድ ማንነት በነገው ጥናታችን እንመለከታለን። ዛሬ ግን ስለዚህ ታናሽ ቀንድ አንዳንድ ነጥቦችን እንመልከት።

1. ይህ ቀንድ ትንሽ ነበር፤ በኋላ ግን በጣም አደገ፤ ወደ ደቡብ፥ ወደ ምሥራቅና ወደ መልካሚቱ ምድር ተስፋፋ። ወደ ደቡብ ሲል ግብፅን ያመለክታል። ወደ ምሥራቅ ሲል በሦርያ አካባቢ ያሉትን አገሮችና መልካሚቱን ምድር ያመለክታል። መልካሚቱ ምድር የተባለችው የአይሁዳውያን አገር ፓለስታይን ናት።

2. ታናሹ ቀንድ እስከ ሰማይ ድረስ አደገ። ከከዋክብትም ጥቂቶችን ወደ ምድር ጣላቸው፤ በእግሩም ረጋገጣቸው። ይህ የዚህን መሪ ትዕቢት ያሳያል። እንደ ሰማይ አምላክ ሁሉ፥ እርሱም አምላክ እንደሆነ አሰበ። በከዋክብት የተመሰሉትን የእግዚአብሔር ሕዝብ አዋረዳቸው፤ ጨርሶ ሊያጠፋቸውም የተቻለውን ሁሉ አደረገ። ለጊዜው ሥልጣን ስለተሰጠው ከቅዱሳኑ ጥቂቶችን ያሳድዳል፥ ይገድላቸውማል።

3. «እስከ ሠረዊት አለቃ ድረስ» ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ። «የሠረዊት አለቃ» የተባለው እግዚአብሔር ነው። ይህ መሪ ራሱን እንደ እግዚአብሔር እንደሚያይ፥ ሰዎች እንዲያከብሩትና እንዲያመልኩት እንደ ሚፈልግ ይህ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

4. ታናሹ ቀንድ ወደ ቤተ መቅደስ የሚሄደውን የዘወትሩን መሥዋዕት ያስቀረል። ይህ መሪ ከሚያደርሰው በደል አንዱ አይሁዳውያን ቤተ መቅደስ ውስጥ መሥዋዕት እንዳያቀርቡ መከልከል ነው።

5. ቤተ መቅደሱን ያረክሳል። አይሁዳውያን የሚያመልኩበትንም ሥፍራ ያፈርሳል።

6. ይህ ቀንድ እውነትን ወደ ምድር ይጥላል፤ በእግሩም ይረግጣታል። ይህ አባባል፦ ይህ ክፉ መሪ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል እንዳይታዘዙና እውነተኛውን አምላክ እንዳያመልኩ የሚያደርገውን ሙከራ ያመለክታል።

ዳንኤል 8፡12 ለመረዳት የሚያዳግት ቁጥር ነው። የዚህን ታናሽ ቀንድ ክፉ ሥራ በአጭር የሚያቀርብ ይመስላል። ይህ ታናሽ ቀንድ

የሚነሣው የአይሁድና ሌሎች ሕግ ተላላፊዎች በጣም ከፍ ከፍ ባሉበት ዘመን ነው። በአይሁዳውያን ላይ ሥልጣን ይኖረዋል፤ የመቅደሱንም አምልኮ ያስቀራል። ለጊዜውም ቢሆን እቅዱና ውጊያው ይሳካለታል።

ክፍል 5. የሁለቱ መላእክት ውይይት፤ (ዳን.8:13-14)።
ዳንኤል፥ ሁለቱ መላእክት እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ በጽንነት ሰማ። አንደኛው መልአክ ሌላኛውን:- ይህ ታናሽ ቀንድ የቤተ መቅደሱን አምልኮ የሚያስቀረውና ቅዱሳንን የሚያሳድደው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ጠየቀ። ሌላው መልአክ ደግሞ:- ይህ ዓመፅ የሚቀጥለው 2300 (ለሁለት ሺህ ሦስት መቶ) የማታና የጥዋት መሥዋዕት ብቻ እንደሚሆን ነገረው።

2300 የጥዋትና የማታ መሥዋዕት የሚለውን ቃል እንደሚገባ ለመረዳት ያዳግታል። ይሁን እንጂ ሁለት አመለካከቶች ቀርበዋል። አንዳንዶች የቤተ መቅደሱ መሥዋዕት የሚቋረጠው ለ2300 ቀን እንደሆነ ይናገራሉ። ከ2300 ቀን በኋላ ግን መስዋዕቱ ይጀመራል። ሌሎች ደግሞ ጸሐፊው ይህን ሲል ስለ 1150 የጥዋትና 1150 የማታ መሥዋዕት መናገሩ ነው፤ ሁለቱም ሲደመር 2300 ይሆናል ይላሉ። ስለዚህም መሥዋዕቱ የሚቋረጠው ለ1150 ቀን ብቻ ነው ይላሉ።

ይህ ታናሽ ቀንድ ስለማን ያመለክታል? ነገ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንሞክራለን። እስከዚያ ድረስ ግን ስለሚመጣው ጥፋት በማወቃቸው አይሁዳውያን ሊያገኙ የሚችሉት መጽናናት ምንድነው? በማለት ጥያቄ ልናቀርብ እንችላለን። ለዚህ ጥያቄ የምናቀርበው መልስ የሚያጽናናቸው ስለሚመጣው ጥፋት አስቀድሞ ማወቃቸው ሳይሆን የዚህ ጥፋት ጊዜ በእግዚአብሔር የተወሰነ መሆኑን መረዳታቸው ነው የሚል ይሆናል። እግዚአብሔር ይህን ያቀደው ትንቢቱ ከመፈጸሙ 400 ዓመት አስቀድሞ ነበር። ለምን ያህል ጊዜም እንደሚቆይ ወስኗል። እንደዚሁም በእኛ ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ችግር በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ነው፤ ችግሩ ምን ያህል ጊዜ እንደሚቀጥልም የሚወስነው እርሱ ብቻ ነው።

14ኛ ጥያቄ:- ዮሐ.15:18-16:4 አንብብ።
ሀ/ ክርስቶስ ለአማኞች የገባው ቃል ኪዳን ምንድነው?
ለ/ ችግር እንደሚደርስብህ አስቀድሞ ማወቁ አስፈላጊነቱ ለምን ይመስልሃል?

ሦስተኛ ቀን    ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 8:15-27

## ጥያቄዎች

15ኛ ጥያቄ:- የራዕዩን ትርጉም ለዳንኤል እንዲነግር የታዘዘው ማነው?
16ኛ ጥያቄ:- መልአኩ ሲቀርበው ዳንኤል ምን ሆነ?
17ኛ ጥያቄ:- ራዕዩ የትኛውን ጊዜ እንደሚያመለክት ነው መልአኩ የተናገረው?
18ኛ ጥያቄ:- ሁለቱ እንስሶች የሚወክሉዋቸው ሁለት መንግሥታት ምንና ምን ናቸው?
19ኛ ጥያቄ:- ትንሹ ቀንድ ማንን ያመለክታል?
20ኛ ጥያቄ:- ትንሹ ቀንድ ስለሚያደርጋቸው ጥቂት ክፉ ነገሮች ግለጽ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ሁለቱ መላእክት ውይይታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ዳንኤል ብቻውን ሆነ። ትርጉሙን ለማወቅ ካለው ፍላጐት የተነሣ ራዕዩን እየተከታተለ ነበር። ወዲያውኑ የሰው ድምፅ የሚመስል ድምፅ ሰማ። ይህ ድምፅ የእግዚአብሔር ድምፅ ነበር። እግዚአብሔር የራዕዩን ትርጉም ለዳንኤል እንዲነግረው ሰውን መሳይ ሌላ መልአክን አዘዘ፤ መልአኩም ገብርኤል ነበረ። ልክ በዳንኤል 7 እንደተመለከትነው ሁሉ ዳንኤል በሚያየው ራዕይ ውስጥ መሳተፍ ጀመረ።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱት ሁለት መላእክት ብቻ ናቸው። አንደኛው ገብርኤል ይባላል። ገብርኤል ማለት «እግዚአብሔር ብርታቱን አሳይቶአል» ማለት ነው። ሌላው ሚካኤል ይባላል። ስለዚህ መልአክ በዳንኤል 10:13፤ 21 ሰፋ አድርገን እንመለከታለን። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው የሌሎች መላእክት ስም በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሰም።

መልአኩ ገብርኤል ወደ ዳንኤል ሲቀርብ ከፍርሃት የተነሣ ሕሊናውን ስቶ ዳንኤል ወደ ምድር ወደቀ። ገብርኤል ግን አነቃውና በእግሩ አቆመው። የመጣበትም ምክንያት የራዕዩን ትርጉም ሊገልጽለት እንደሆነ ነገረው።

ገብርኤል ራዕዩ ስለመቅሰፍት ጊዜ እንደሚያመለክት ይናገረል። ይህም በመጨረሻ ዘመን የሚፈጸም ነው። የመቅሰፍት ጊዜ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስለወሰነው የቁጣና የፍርድ ጊዜን ያመለክታል፤ (ኢሳ. 10:24-25

ተመልከት)። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ስደት እንዲደርስባቸው የሚያደርገው ሊያስተካክላቸውና ሊያጠራቸው ሲፈልግ ነው።

«የፍጻሜ ዘመን» የሚለውን ቃል፤ (ዳን.8:19፤ 26) ሰዎች በተለያየ ሁኔታ ይረዱታል። ለዚህም ስለ ታናሹ ቀንድ ያለን አተረጓጐም ወሳኝነት አለው።

ታናሹ ቀንድ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ተነሥቶ የነበረውን ግለሰብ የሚወክል ከሆነ፥ «የፍጻሜ ዘመን» የሚለው ቃል የሚያመለክተው የራዕዩን ፍጻሜ ነው ማለት ነው። ይህም የሆነው በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ባለው ጊዜ ነው። ይህ ሁኔታ የሚፈጸመው ዳንኤል ራዕዩን ካየ ከረጅም ጊዜ ማለትም ከ400 ዓመት በኋላ ነበር። ነገር ግን ታናሹ ቀንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመንገሥ ከመምጣቱ በፊት በታሪክ ውስጥ ስለሚነሣው ክፉ መሪ የሚያመለክት ከሆነ ራዕዩ የሚያሳየው የታሪክን መጨረሻ ነው ማለት ነው።

ሁለቱ እንስሳት ሁለት መንግሥታትን እንደሚያመለክቱ አይተናል። አውራው በግ ከባቢሎን መውደቅ በኋላ የተነሣውን የሜዶንና የፋርስ መንግሥትን ያመለክታል። አውራው ፍየል የሜዶንና ፋርስ መንግሥትን የደመሰሰውን የግሪክ መንግሥትን ያመለክታል። ታላቁ እስክንድር የመጀመሪያው የግሪክ መንግሥት ንጉሥ ሲሆን፥ ከእርሱ በኋላ ሌሎች አነስተኛ መሪዎች ይነሣሉ። የግሪክ መንግሥት ወደ ማክተሚያው አካባቢ ሲደረስ ታላቅ ችግር የሚፈጥር ሌላ መንግሥት ይነሣል።

እዚህ ላይ የተጠቀሰው «ታናሽ ቀንድ» ባለፈው ሳምንት ከዳንኤል 7 ላይ ከተመለከትነው «ታናሽ ቀንድ» የተለየ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። በዳንኤል 7 የተመለከትነው «ታናሽ ቀንድ» የሚወጣው ከአራተኛው አውሬ ማለትም ከሮም መንግሥት ነበር። በምዕራፍ 8 የምንመለከተው «ታናሽ ቀንድ» የሚነሣው ግን ከአውሬው ፍየል ማለትም ከግሪክ መንግሥት ነው። ስለዚህም ሁለቱ ምዕራፎች የሚገልጹት ስለተለያዩ ሰዎች ነው ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች በዳንኤል 8 የተጠቀሰው «ታናሽ ቀንድ» አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ በሚባል ሰው ተፈጽሞአል ይላሉ። ይሁን እንጂ በሁለቱም ምዕራፎች የተጠቀሱት ሰዎች ተመሳሳይ ባሕርይ ስላላቸው በዳንኤል 8 የተጠቀሰው ትንቢት በአንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ ዘመን ቢፈጸምም በተጨማሪ በዳንኤል 7 የተጠቀሰውን በመጨረሻ ዘመን የሚነሳውን ክፉ መሪ ያመለክታል የሚል ግምት አላቸው።

ስለ ታናሹ ቀንድ ሰፋ ባለ ሁኔታ ከመመልከታችን በፊት የዚህን ክፍል ፍጻሜ ለመረዳት ታሪክን መመርመር ይኖርብናል። ከባቢሎን ውድቀት በኋላ የሜዶንና ፋርስ መንግሥት መግዛት ጀመረ። አይሁዳውያንንም ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀዱላቸው። በፖለቲካ መሪው በዘሩባቤል፥ በካህኑ

ዕዝሬ÷ በነቢያቱ በሐጌና በዘካርያስ መሪነት ቤተ መቅደሳቸውን ሠሩ። በኋላም በነህምያ መሪነት የከተማይቱ ቅጥር ተሠራ። ፋርሳውያን ከአይሁዳውያን ጋር መልካም መቀራረብ ነበራቸው። በኋላ ግን በ331 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የፋርስ መንግሥት በተልቁ እስክንድር በሚመራው የግሪክ መንግሥት ድል ሆነ። ትልቁ እስክንድር ኢየሩሳሌምን ለመደምሰስ በመጣበት ጊዜ ሊቀ ካህኑ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግሪኮች መምጣት እንደሚናገር ለትልቁ እስክንድር ነገረው። በዚህም ምክንያት ከተማይቱን አልነካትም። ምንም እንኳ በግሪክ መንግሥት ሥር ቢሆኑም አንጦኪዮስ ኤጲፋንዮስ እስከተነሣበት ዘመን ድረስ አይሁዳውያን በሰላም ኖሩ።

የግሪክ መንግሥት በአራት ክፍል መከፋፈሉን ታስታውስ ይሆናል። ከእነዚህ ግዛቶች አንዱን የሚገዛው ሴሌውከስ የሚባለው ነበር። ሴሌውሳውያን ሥርወ መንግሥት አቋቁመው በተከታታይ ከገዙ በኋላ በ175 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አንጦኪዮስ ኤጲፋንዮስ እነርሱ ይገዙ በነበረበት ክፍል ላይ ንጉሥ ሆነ። ቶሎሚ ከሚባሉ የግብፅ ነገሥታት ጋር መዋጋት ጀመረ። (ምዕራፍ 11 ይህን ጦርነት ሰፋ ባለ ሁኔታ ይገልጸዋል)። አንጦኪዮስ ኤጲፋንዮስ በግዛቱ በነበሩ አገሮች ሁሉ የግሪክን ባሕልና ሃይማኖት ሊያስፋፋ ፈለገ። ሕዝቡንም እንደ አምላክ እንዲያመልኩት አደረገ። ራሱ የጨመረው «ኤጲፋንዮስ» የሚባለው ስሙ «የአማልክት መገለጥ» ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት እንዲቋረጥና በዚያ ምትክ የግሪኮች አማልክት እንዲመለኩ÷ የግሪክም ባሕል እንዲስፋፋ አደረገ። በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በነበረው መሠዊያ ላይ እሪያ ሠዋበትና አረከሰው። በኋላም የግሪክ አማልክት የሚመለኩበት መሠዊያ አደረገው። በዚህም ምክንያት አይሁዳውያን አመፁና ከአንጦኪዮስ ጋር መዋጋት ጀመሩ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን ተገደሉ። በመጨረሻ ግን በ164 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የሦርያ ሠራዊት ድል ተደረገ÷ መቅደሱም እንደገና ነጸ፤ የአምልኮ ሥርዓቱም እንደገና ተቋቋመ። ወዲያውኑ አንጦኪዮስ ባልታወቀ ሕመም ምክንያት ሞተ፤ አይሁዳውያንም ነፃነታቸውን አወጁ።

ዳንኤል በ551 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ይህን ክፍል ሲጽፍ በአንጦኪዮስ ዘመን ስለሚፈጸመው የሃይማኖት ተጽዕኖ መናገሩ ነው። ይህም ከ167-164 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ተፈጽሞአል። ዳንኤል 8፡9-12፤ 19-25 ስለ አንጦኪዮስ ዘመንና ባሕርይ የሚያመለክት ነው። የሚከተሉት ስለዚያ ዘመን ከተነገሩት ዋና ዋና ትንቢቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

1. አንጦኪዮስ አቅሙ ደካማ ቢመስልም÷ በጣም ያድጋል። በየጊዜውም አዳዲስ ግዛት ይጨምራል።

2. አንጦኪዮስ ሥልጣኑን የሚይዝበት ቀን÷ ጨለማና ክፉ ቀን ነው። በእግዚአብሔርና በሕጉ ላይ ብዙ ዓመፅና ክፋት ያደርጋል።

አንጦኪዮስ ሥልጣንን በያዘበት ዘመን ብዙ አይሁዳውያን እምነታቸውን ቸላ እንዲሉና እግዚአብሔርን እንዲተዉ አድርጎ ነበር።

3. አንጦኪዮስ የሚያሳስት ሰው ነው። መንግሥቱንም የመሠረተው ሌሎቹን በማሳሳትና በማጭበርበር ነበር። «እንቆቅልሽን የሚያውቅ» የሚለውም ቃል የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው። የማሳሳት ተግባሩንም በብዙ አገሮች በተለይም በኢየሩሳሌም ላይ በግልፅ አሳይቶአል። ብዙ አይሁዶች እምነታቸውን ትተው የግሪክን አማልክት አምልኮ በአገሪቸው እንዲለመድ አድርገዋል።

4. አንጦኪዮስ እንደ አምላክ ራሱን ከፍ ከፍ ያደርጋል። ራሱን እንደ አምላክ በመቁጠሩና የመቅደሱ አምልኮ እንዲቋረጥ በማድረጉ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን ተቃውሞ መግለጹ ነበር።

5. ቅዱስና ታማኝ የሆኑትን አይሁዳውያንን ይወጋቸዋል፤ ለተወሰነ ጊዜም ያሸንፋቸዋል። እምነታችንን ትተን የሐሰት አማልክትን አናመልክም በማለታቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን ለእምነታቸው ተሠውተዋል።

6. አንጦኮዮስ የጥዋትና የማታው መሥዋዕት ለ2300 ቀን እንዲቋረጥ ያደርጋል። ይህም የረከሰው መቅደስ እስከሚነጻበትና እግዚአብሔር እንደገና እስከሚመለክበት ያለውን 1150 ቀን ያመለክታል። ወይም ደግሞ አንጦኪዮስ ለግል ጥቅሙ ለማዋል ከመቅደስ ገንዘብ ከወሰደበት ጊዜ አንሥቶ በ164 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከሞተበትና መቅደሱ እስከነጻበት ድረስ 2300 ቀን የሚያመለክት ይሆናል።

7. አንጦኪዮስ የሚገደለው በሰው እጅ አይደለም። የሞተው ባልታወቀ ድንገተኛ ሕመም ነበር። ይህም በእርግጥ የእግዚአብሔር ፍርድ ነበር።

ምንም እንኳ እነዚህ ትንቢቶች ግልጽ በሆነ ሁኔታ በአንጦኪዮስ ኤጲፋንዮስ የተፈጸሙ ቢሆኑም፥ በመጨረሻ ዘመን ስለሚነሣው ዓመፀኛና ክፉ መሪ እንደሚያመለክቱም መዘንጋት የለብንም። እንደገና እስራኤል መከራ ይደርስባታል፤ ብዙ አማኞች ግን ስለ እምነታቸው ይገደላሉ። በዳንኤል 8 መጀመሪያ ላይ የተፈጸመው ትንቢት ሌላውን በመጨረሻ የሚፈጸመውን የዳንኤልን ትንቢት ያመለክታል።

ዳንኤል ይህንን የጻፈው በዚያ ስደት ዘመን የሚኖሩ ወገኖቹን ለማጽናናት ነበር። በራሳቸው ኃይል አንጢዮኮስን ሊቋቋሙት አይችሉም። ይሁን እንጂ እስከሞት ድረስ ታማኝ መሆን አለባቸው። ውጊያው የእግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህም እርሱ በወሰነው ጊዜ ጠላታቸውን አስወግዶ ሕዝቡን ያከብረቸዋል። ራዕዩን እንዳየም ለዳንኤል የተነገረው ለዚህ ነበር።

ዓላማው  የመጽሐፉን መልእክት ለመደበቅ  ሳይሆን÷ በስደቱ ጊዜ ሕዝቡ ከእምነታቸው እንዳይዘናጉ ለማበረታታት ነበር።  እኛም ብንሆን ለእምነታችን በስደትም ጊዜ ቢሆን ታማኞች መሆን አለብን።  አንድ ቀን የዓመፅ ኃይል ሲያከትም÷ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓመፀኛ መንግሥታትን ይደመስሳቸዋል፤ የጽድቅ መንግሥትም ይመሠረታል።

21ኛ ጥያቄ:- በዚህ ምዕራፍ የተሰጠው ትምህርት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የቤተ ክርስቲያኑን ሰዎች ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን እንደሚረዳቸው ገለጽ።

ዳንኤልን ስናጠና ስለ አንዳንድ አስደናቂ ትንቢቶች ተመልክተናል። በባቢሎን ምርኮ በነበረበት ጊዜ ከ500 ዓመታት በኋላ በሮም መንግሥት ላይ የሚፈጸመውን ሁኔታ እግዚአብሔር ለዳንኤል ገለጸለት። የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ስለምትገዛበት የመጨረሻው ጊዜም ገልጾለታል። የሚከተለው ሠንጠረዥ በዳንኤል 2÷ 7 እና 8 ያሉትን ትንቢቶች በአጭሩ ያመለክታል።

| ምዕራፍ ሁለት | ምዕራፍ ሰባት | ምዕራፍ ስምንት | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| ምስሉ | አውሬው | እንስሳቶች | |
| የወርቁ ራስ | አንበሳ | | ባቢሎን |
| የብር ደረትና ክንዶች | ድብ | ወጠጤ | ሜዶንና ፋርስ |
| የናስ ሆድና ወገብ | ነብር | ትንሽ ቀንድ ያለው ፍየል | ግሪክ (አንጦኪዮክስ ኢጲፋንዩስ) |
| የብረት ጭኖች | አስፈሪው አውሬ | | ሮም |
| የብረትና የሸክላ እግሮች | 10 ቀንዶችና አንድ ትንሽ ቀንድ | | የአንሰራራው የሮም መንግስትና የክርስቶስ ተቃዋሚ |
| የድንጋዩ ታላቅ ተራራ መሆን | የጥንት ዘመንና የሰው ልጅ | | የእግዚአብሔር የዘላለም መንግስት |

<u>አረተኛ ቀን፡-</u> የዚህን ሳምንት ትምህርት መከለስ

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ክርስቲያኖች ጥያቄ ስለሚያቀርቡበት አንዳንድ ሁኔታዎች ወይም ገጠመኞችን ዘርዝር።
2/ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ ሰዎች የምትሰጣቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ምክር ምንድነው?

ለ. ዮሐ.15፡18-16፡4 ተመልከት።
1/ ስለሚመጣው ስደት ኢየሱስ ማስጠንቀቂያ የሰጠን ለምን ይመስልሃል?
2/ ችግር እንደሚደርስበት እግዚአብሔር ለክርስቲያን ሲነግረው ምን ያህል የሚያጽናናው ይመስልሃል?
3/ እግዚአብሔር ስለሚመጣው ስደት እስራኤላውያንን ያስጠነቀቃቸው ለምን ይመስልሃል?

ሐ. 1/ የአንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ ዘመን ከዘመናችን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
2/ የቤተ ክርስቲያናችንን ሰዎች ለማጽናናት በዳንኤል 8 ያለውን ትምህርት እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥራ አረት

## ዳንኤል 9፡1-19

<u>የመጀመሪያ ቀን</u>

አምላኬ ሆይ፥ በፊትህ የምንለምን ስለ ብዙ ምሕረትህ ነው እንጂ ስለ ጽድቃችን አይደለምና (ዳን.9፡18)።

የእግዚአብሔር ሰዎች ብርታትን የሚያገኙት ከየት ይመስልሃል? ከሌሎች ይልቅ ልዩ የሚያደርጋቸው ምን ይመስልሃል? ችሎታቸው ነውን? ትምህርታቸው ነውን? ወይስ ብዙ በመሥረታቸው? አብርሃም፡- የእግዚአብሔር ወዳጅ የተባለው፥ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር «ፊት ለፊት» መነጋገር የቻለው፥ ለዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር «እንደ ልቤ የሚሆንልኝ» በማለት የመሰከረለት ለምን ይመስልሃል?

ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ የሚያደርገው ችሎታው፥ ትምህርቱ፥ ኀብረቱ ወይም ሌላ ውጫዊ ሁኔታው አይደለም። ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ የሚያደርገው ከእርሱ ጋር ያለው መቀረረብ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህን የጠበቀ ኅብረትና መቀረረብ እግዚአብሔርን ማወቅ ይሉታል፤ (ኤር.9፡23-24 ተመልከት)። ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመቀረረብ እንጂ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ሊኖረን ስለሚችለው የአእምሮ እውቀት አይደለም። ዳን.11፡32፡- «አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም» ይላል። ለእግዚአብሔር ትልቅ ሥራ ለመሥራት የምንችለው እርሱን በማወቃችን ከምናገኘው ኃይል ነው።

አንድ ሰው እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚችለው እንዴት ነው? እግዚአብሔርን በጸንብ እንድናውቅ ከተፈለገ ሁለት ነገሮችን ማድረግ አለብን። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አለብን። ከዚያም ምንም ያህል ዋጋ ያስከፍለን ለእግዚአብሔር ቃል በፍጹም ልባችን መታዘዝ አለብን። ዳንኤል ጣዖት ከማምለክ ይልቅ በአንበሳ ጉድጓድ ለመጣል ባደረገው ምርጫ ፍጹም ታዛዥነቱን አሳይቶአል፤ (ዳን.6)። በምዕራፍ 9 ላይ ዳንኤል ያቀረበው ታላቅ ጸሎት፥ በቃሉ እንደተገለጸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመረዳቱ ላይ የተመሠረተ ነበር።

ሁለተኛ፡- በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረን ይገባል። ጸሎት፥ ክርስቲያን ኃይልን የሚያገኝበት ምንጭ ነው። ጸሎት፥ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረት ምን ያህል ጥልቅ መሆኑን የምንለካበት ቴርሞ ሚትር ነው።

ዳንኤል ታላቅ የጸሎት ሰው መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። በምዕራፍ 1 ላይ ሕልሙን የሚረዳበት ችሎታ እንዲሰጠው ሲጸልይ ተመልክተናል። በረሱ የተለያየ ሙከራ ከማድረግ ይልቅ የጥበብ ሁሉ ምንጭ ወደሆነው አምላክ ፊቱን ሲያቀና እንመለከታለን። እንዳይጸልይ በተከለከለበት ጊዜ እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት መገናኘቱን እንዳላቋረጠም ተመልክተናል። ስለዚህም በአንበሶች ጉድጓድ ተጣለ፤ እግዚአብሔር ግን ታደገው። ዛሬ ከዳንኤል ጸሎቶች አንዱን እንመለከታለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ከሠፈሩት ታላላቅ ጸሎቶች አንዱ የሆነው ይህ ጸሎት ዳንኤል በእግዚአብሔር ላይ የነበረው እምነትና እውቀት ምን ያህል ጥልቅ እንደነበር ያመለክታል።

ከዳንኤል 9:1-19 ስለ ጸሎት አምስት ዋና ዋና እውነት እንመለከታለን።

በመጀመሪያ:- ስንጸልይ እግዚአብሔር የጠየቅነውን ሁሉ እንዲሰጠን ግዴታ እንዳሌለበት መረዳት አለብን። ለእግዚአብሔር ስለታዘዝን ብቻ ለጸሎታችን ሁሉ ጊዜ የእሺታን ምላሽ ዋስትና አይደለም። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የጠየቅነውን ላይሰጠን ይችላል። እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚሰማልንና እንደሚመልስልን የምናውቀው በምሕረቱ በመደገፋችንና የማይገባን ብንሆንም እንኳ ሊባርከን ፈቃደኛ መሆኑን በመረዳታችን ነው።

ሁለተኛ:- ጸሎታችን በቅዱሳት መጻሕፍት በተሰጠው ተስፋ መመሥረት አለበት። በነቢዩ ኤርምያስ የተነገረውን የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል በመረዳቱ ዳንኤል እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲጸገና እንዲያቋቁማቸው ለመጸለይ ቻለ። እግዚአብሔር በሺሕ የሚቆጠር የተስፋ ቃል ሰጥቶናል፤ በዚህ የተስፋ ቃል መሠረት ጸሎታችንን እንደሚመልስልን እናውቃለን።

1ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚመልስ የምንተማመንባቸው የተለያዩ የተስፋ ቃሎችን ግለጽ። ለምሳሌ ያህል እንዲሆንህ ኤርምያስ 29:11-13 ተመልከት።

ሦስተኛ:- ስለ ኃጢአታችንና ስለ ሌሎች ክርስቲያን ወገኖቻችን ኃጢአት በጥልቀት ልናስብበት ይገባል። ኃጢአት እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዳይሰማና እንዳይመልስልን የሚያደርግ ትልቅ እንቅፋት ነው። ዳንኤል ከፍተኛ የኃጢአት ጥላቻ ነበረው። የራሱን ኃጢአት ወይም የሌሎችን ኃጢአት አጉል ምክንያት ወይም ሰበብ በመስጠት ሊሸፋፍነው አይፈልግም። ምንም ሳይሸፋፍን በግልጽ ንስሐ ያደርጋል። ኃጢአታችንን እንደሚገባ ካልተናዘዝን በቀር ጸሎታችን ኃይል ሊኖረው አይችልም።

አራተኛ:- በጸሎታችን የምንተማመነው ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ኅብረትና ግንኙነት መጠን ነው። በጸሎት አማካኝነት ዳንኤል እግዚአብሔር ታላቅና ኃያል፥ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ፥ ጸድቅ፥ መሐሪ፥ በኃጢአተኞች የሚቆጣ ትሑታንን ግን ይቅር የሚል ለመሆኑ ዳጋግሞ ማረጋገጫ አገኘቷል። በዚህ ፍጹም መተማመን ነበረው። እግዚአብሔርንና ባሕርዩን ይበልጥ ባወቅነው መጠን የጸሎት ሕይወታችንም ጥልቀት ይኖረዋል። ጸሎት ስለ አንዳንድ ነገሮች እግዚአብሔርን መለመን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ማለት ነው።

አምስተኛ:- ስለ ጸሎት የቀና አመለካከትና ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል። ዳንኤል የልቡን ዝንባሌ በአንዳንድ ውጫዊ ሁኔታዎች አሳየ። ማቅ ለብሶ፥ አመድ ነስንሶ ነበር የጸለየው። ይህ ሁሉ ምን ያህል በእግዚአብሔር እንደሚታመን የሚያሳይ ነበር። ዳንኤል ቅድሚያ የሰጠው ሐሳብ የተሻለ ኑሮ

እንዲኖሩና እግዚአብሔር ልጆቹን እንዲባርክ አልነበረም። ዳንኤል ቅድሚያ የሰጠው ለእግዚአብሔር ክብር ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት ሲያደርጉ፥ በኃጢአታቸውም የተለያየ ቅጣት ሲደርስባቸው በማያምኑት ዘንድ የእግዚአብሔር ስም እንደሚነቀፍ በሚገባ ተረድቶአል። ዳንኤልን በጣም ያሳሰበው እግዚአብሔር የሚገባውን ያህል ክብር አለማግኘቱ ነበር። «አምላኬ ሆይ፥ ስምህ በከተማህና በሕዝብህ ላይ ተጠርቶአልና ስለ ሬስህ አትዘገይ» በማለት የጸለየውም በዚህ ምክንያት ነው፤ (ዳን.9:19)።

2ኛ ጥያቄ:- ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረትና ግንኙነት እንዳላቸው የምታውቃቸውን ሰዎች ጥሬ። ከጸሎታቸው ውስጥ እግዚአብሔርን እንደሚገባ እንደሚያውቁ የሚገልጹ ነገሮች ምንድናቸው?

እኛስ እግዚአብሔርን እናውቀዋለን? ከቃሉ ስለ እርሱ ለማወቅ ጊዜ ወስደን እናጠናዋለን? በዳንኤል ምሳሌነት እየተመረን በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እናደርጋለን?

3ኛ ጥያቄ:- ፊልጵ.3:7-14 አንብብ። ኢየሱስ ክርስቶስን የማወቅ ፍላጐት በሕይወትህ ውስጥ የሚታየው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው?

4ኛ ጥያቄ:- ዳን.9:1-19 አንብብ።
ሀ/ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ከእነዚህ ጥቅሶች የተረዳኸውን ግለጽ።
ለ/ ዳንኤል የሕዝቡን ኃጢአተኛነት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ይገልጻል?

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 9:1-3

## ጥያቄዎች

5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ዳንኤል ስለ ወገኖቹ እንዳገና መቋቋም መጸለይ የጀመረው ማን በሚገዛበት ዘመን ነበር?
ለ/ በዚህ ጊዜ ይህን ጸሎት መጸለይ የጀመረው ለምን ይመስልሃል?

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የዳርዮስ ሌሎች ስሞቹ እነማን ናቸው? መልሱን ለማግኘት አሥረኛውን ትምህርት ተመልከት።
ለ/ ዳንኤል ስለ ዳርዮስ የተናገረቸውን አንዳንድ ነገሮች ግለጽ።

7ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ስለ ሕዝቡ እንደገና መመለስ መጸለይ የጀመረው የማንን መጽሐፍ ካጠና በኋላ ነው?

8ኛ ጥያቄ:- «የኢየሩሳሌም ጥፋት» ለምን ያህል ጊዜ ነበር? ኤር.25: 8-14 አንብብ።

9ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ራሱን ማዋረዱንና የጸሎቱን ጥልቀት ለማሳየት የተጠቀመባቸው ውጫዊ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

የዳንኤል መጽሐፍ:- «የትንቢት መጻሕፍት ቁልፍ» ተብሎ እንደሚጠራ አስቀድመን ተመልክተናል። እንደዚህም የተባለበት ምክንያት ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ሁሉ ትንቢተ ዳንኤል ከዚያን ዘመን አንሥቶ እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ ስለሚናረው ሁኔታ በቅደም ተከተል ስለሚያስረዳ ነው። ዳንኤል 2-8 እና 11 «ስለ አሕዛብ ዘመን» ገለጻ ይሰጣል። ይህ ዘመን አሕዛብ እስራኤልን የተቆጣጠሩበት ዘመን ነው። ዳንኤል ስለ ሜዶንና ፋርስ፥ ስለ ግሪክ፥ ስለ ሮም፥ እንዲሁም ኢየሱስ መጥቶ ዘላለማዊ መንግሥቱን ከመመሥረቱ በፊት ስለሚነሣው የመጨረሻው መንግሥት በትንቢቱ አመልክቶአል።

ዳንኤል 9 ስለ አይሁድ ሕዝብ ቁልፍ ትንቢቶችን የያዘ ምዕራፍ ነው ሊባል ይቻላል። ዳንኤል ለወገኖቹ አይሁዳውያን በጣም ያስብላቸው ስለነበር ወደ ሀገረቸው ስለመመለሳቸው አጥብቆ ይጸልይ ነበር። እግዚአብሔር ግን መሢህ መጥቶ እነርሱን ከመታደጉ በፊት በመጨረሻው ዘመን በወገኖቹ ላይ ስለሚደርስባቸው ጉዳይ በሙሉ ገለጸለት። በዚህ ሳምንት ስለ ዳንኤል ጸሎት እንመለከታለን፤ በዳን.9:24-27 ወደተጠቀሰው ከፍተኛ ትንቢት የሚመራንም ይኸው ጸሎት ነው።

በዳንኤል 9:1 ላይ ዳንኤል መጸለይ የጀመረው ንጉሥ ዳርዮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት እንደነበር ይናገራል። ሜዶንና ፋርስን የገዛ ዳርዮስ የሚባል ሌላ ንጉሥ በ522 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደነበር ቢታወቅም (በዕዝራ 4:24፥ ሐጌ 1:1 እና ዘካርያስ 1:1 በተጠቀሰው መሠረት ግን) ዳንኤል የሚናገረው ስለሌላ ንጉሥ ዳርዮስ ነበር። እነዚህ ሁለት ነገሥታት የተለያዩ መሆናቸውን መረዳት አለብን። በዳንኤል የተጠቀሰው ዳርዮስ ከባቢሎን መውደቅ በኋላ የተነሣ የመጀመሪያው የሜዶንና ፋርስ ንጉሥ ነበር። ሌላው ዳሪዮስ የተነሣው ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ ሲሆን አይሁዳውያን ጀምረውት የነበረውን የቤተ መቅደስ ሥራ እንዲፈጽሙ የፈቀደላቸው ንጉሥ እርሱ ነው።

በዳንኤል 5:31 ሜዶናዊው ዳርዮስ ባቢሎንን ድል አድርጎ መንግሥቱን እንደወሰደ ተመልክተናል። በዳንኤል 6 ደግሞ ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ የተጣለው በንጉሥ ዳርዮስ ዘመን እንደነበር ተመልክተናል። በትምህርት 10 የታሪክ አዋቂዎች ዳርዮስ ከሁለቱ ሰዎች አንዱ ሳይሆን

እንደማይቀር የሰጡትን ሐሳብ አይተናል። አንዳንዶች በቂሮስ ሥር ሆኖ ባቢሎንን ይገዛ የነበረ ጋባሩ ይባል የነበረ ሰው ነው ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ዳርዮስ የመጀመሪያው የሜዶንና ፋርስ ንጉሥ የቂሮስ ሌላ ስም ነው ይላሉ። በዳንኤል 9 የተጠቀሱት ሁኔታዎች የተፈጸሙት ዳርዮስ ባቢሎንን ከያዘ በኋላ ቢሆንም በዳንኤል 6 የተጠቀሰው ሁኔታ ከመፈጸሙ በፊት ነው።

ዳንኤል ስለ ዳርዮስ አንዳንድ ነገሮችን ይጠቅሳል። አንደኛ:- ጸሎቱን የጀመረው ዳርዮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት እንደነበር ገልጾአል። እንዲህም ከተባለ ዳንኤል መጸለይ የጀመረው በ539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር ማለት ነው። የዳንኤል ጸሎት መልስ ያገኘው፥ አይሁዳውያንም ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ የተፈቀደላቸው ይኸው ዳርዮስ በነገሠበት የመጀመሪያ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ነበር።

ሁለተኛ:- ዳርዮስ ሜዶናዊ እንደነበር ገልጾአል። በሜዶንና በፋርስ ላይ ሊነግሥ የቻለው ሜዶናዊ በመሆኑ ስለነበር ለዳንኤል ይህን መጥቀስ በጣም አስፈላጊ ነበር።

ሦስተኛ:- ዳርዮስ የአሐሸዊሮስ ልጅ ነበር። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት ሰዎች አሐሸዊሮስ በሚል ስያሜ ስለሚታወቁ ልዩነታቸውን መረዳት አለብን። በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ አሐሸዊሮስ ተብሎ በዕዝራ 4:6 እና በመጽሐፈ አስቴር የተጠቀሰው ንጉሥ ከ486-465 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የነገሠ ነው። ይህንን ንጉሥ የዓለም ታሪክ አርጤክስስ በማለት ይጠራዋል።

የእንግሊዝኛውንና የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ብናስተያይ በፋርስ ነገሥታት አጠራር ላይ እንደሚለያዩ እንረዳለን። የግሪክኛውን የብሉይ ኪዳን ትርጉም የተከተለው የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በዕዝራ 4:6-7 እና በመጽሐፈ አስቴር የተጠቀሱትን ነገሥታት «አርጤክስስ» በማለት ይጠራቸዋል። የዕብራይስጡን ብሉይ ኪዳን ትርጉም የተከተለው የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በሁለት የተለያየ ስም ይጠራቸዋል። በዕዝራ 4:6 ላይ አሐሸዊሮስ ይላል፤ አሐሸዊሮስ የአርጤክስስ ሌላ ስሙ ነው። በዕዝራ 4:7 እና 7:1 ግን አርጤክስስ ይለዋል። ብዙ ምሁራን እነዚህ ሁለት የተለያዩ ነገሥታት መሆናቸውን ያምናሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን የተለያዩ የፋርስ ነገሥታት ለማወቅ የሚከተለውን ዝርዝር አጥና።

1. ቂሮስ (ምናልባትም ሜዶናዊው ዳርዮስ የሚባለው) /ኢሳ.44:28-45፤ ዕዝሬ 1:1-4፤ 5:13-15/ የገዛው ከ559-530 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

2. ካምብይሰስ ዳግማዊ (በቅዱሳት መጻሕፍት አልተጠቀሰም) የገዛው ከ530-522 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

3. ታላቁ ዳርዮስ /ዕዝራ 4:5፤ 5:6-7፤ 6:1፤ ሐጌ 1:1፤ ዘካ.1:1/ የገዛው ከ522-486 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

4. አሐሻዊሮስ (አርጤክስስ ቀዳማዊ የተባለው) /ዕዝራ 4:6 እና መጽሐፈ አስቴር/ የገዛው ከ486-424 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

5. አርጤክስስ ቀዳማዊ /ዕዝራ 4:7፤ 7:1፤ 21-26፤ ነህምያ 2:1-8/ የነገሠው ከ465-424 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

አሪተኛ:- ዳርዮስ በባቢሎን ላይ ገዢ እንዳሆነ እናነባለን። ዳሪዮስን በባቢሎን ላይ ማን እንዳነገሠው አናውቅም ዳንኤል ግን ይህን የጠቀሰው መንግሥቱን ለእርሱ የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑን ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም። ዳንኤል የሰዎችን መንግሥት ሁሉ የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር እንደሆነና የወደደውንም ሊሾምበት ሥልጣን እንዳለው እርግጠኛ ነበር። ምናልባትም ቂሮስ መንግሥትን ለዳርዮስ እንደሰጠው የሚያመለክት ፍንጭ ይሆናል።

ዳሪዮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ዳንኤል የነቢዩ ኤርምያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። የነቢዩ ኤርምያስ መጽሐፍ የተጻፈው በ586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ዳንኤል ወደ ምርኮ ከተወሰደ በኋላ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ተቀብለውት ስለ ነበር ዳንኤል መጽሐፉን ያነበበው ከተጻፈ ከ47 ዓመት በኋላ በ539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

ኤርምያስ ኢየሩሳሌም የምትቀጣው ለ70 ዓመት ብቻ እንዳሆነ ትንቢት ተናግሮአል፤ (ኤር.25:8-14፤ 29:10-14)። ቤተ መቅደሱም ሆነ የኢየሩሳሌም ከተማ ፈረርሰው ስለነበር ይህ ጊዜ «የመፈረረስ ጊዜ» ተብሎአል። ሰባው ዓመታት አይሁዳውያን በምርኮኛነት የሚቆዩባቸው ግምት ላይ የተመሠረቱ ዓመታት ናቸው። ስለዚህ 70 ዓመት ለመረዳት ሁለት አመለካከት ቀርቦአል። የመጀመሪያው:- ሰባው ዓመት የአይሁድን ሕዝብ ፖለቲካዊ ምርኮ ያመለክታል ይላል። ይሁዳ በመጀመሪያ በባቢሎናውያን የባርነት ቀንበር ሥር የወደቀቸው በ605 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። ይህም ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ከያዛትና እንደ ዳንኤል የመሳሰሉትን ጥቂት ዋና ዋና ሰዎችን በምርኮኛነት ከወሰደ በኋላ ነበር። የሰባው ዓመት ፍጻሜ በ539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አይሁዳውያን ወደ ሀገረቸው እንዲመለሱ ቂሮስ በፈቀደበት ዘመን ነበር። እንደዚህም ከሆነ ምርኮው የተፈጸመው በ70 ዓመቱ ሳይሆን በ67 ዓመቱ ነበር ማለት ነው።

ሁለተኛ:- የአይሁዳውያንን ሃይማኖታዊ ምርኮ ሊያመለክት ይችላል። ይህም የቤተ መቅደስ አምልኮ እንዲቋረጥ ከተነገረበት ጊዜ እንሥቶ እንዳገና

እንዲቀጥል እስከተፈቀደበት ጊዜ ድረስ ያለውን ዘመን ያሳያል፡፡ የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የፈረሰው በ586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን እስከ 516 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደገና አልተሠረም ነበር፡፡ ይህ ጊዜ ከሞላ ጐደል 70 ዓመት ይሆናል፡፡

በ539 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ዳንኤል 70 ዓመት እንደተፈጸመ ሆኖ ተሰማው፡፡ ስለዚህም የተስፋ ቃሉን እንዲያስብ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ጀመረ፡፡ ዳንኤል እግዚአብሔር የሚሠረውን ለማየት ብቻ እጆቹን አጣጥፎ አልጠበቀም፡፡ በቅዱሳኑ ጸሎት አማካይነት እግዚአብሔር ዓላማውንና ፈቃዱን እንደሚፈጽም ያውቃል፡፡ ስለ ሕዝቡ እንደገና መቋቋም የጸለየውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡

ዳንኤል ከ85 ዓመት ዕድሜ በላይ የነበረው ሽማግሌ ነበር፡፡ የሚኖረውም በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በመልካም ሁኔታ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ስለ ወገኖቹ እስራኤላውያን በጣም ያስብ ነበር፡፡ እሰጣችኋለሁ ብሎ ቃል ወደገባላቸው ምድር በመመለሳቸው እግዚአብሔር እንዲከበር ከፍተኛ ፍላጐት ነበረው፡፡ ስለዚህም ለሕዝቡ እንደገና መቋቋም መጸለይ ጀመረ፡፡

ጸሎት በዳንኤል ሕይወት ከፍተኛ ሥፍራ ነበረው፡፡ ስለ ሕዝቡ በጣም ያስብ ስለነበር የእግዚአብሔርን ፊት ለመሻት ራሱን አዘጋጀ፡፡ ለዚህም ዝግጅት ዳንኤል ሦስት ነገሮችን አድርጐአል፡፡ እነዚህም ሦስት ነገሮች ዳንኤል ራሱን ለጸሎት መስጠቱን መልስ እንደሚሰጠው በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ያመለክታሉ፡፡

በመጀመሪያ፡- ዳንኤል ጸመ፡፡ ለዳንኤል ጾም ማለት ከሥጋ መገለል ወይም ደግሞ እንደ እስላሞች ከጥዋት እስከማታ ምንም አለመብላት አልነበረም፡፡ ዳንኤል ሙሉ ጊዜውን ለጸሎት መስጠት እንዲያመቸው ፈጽሞ መመገቡን አቋረጠ፡፡ የምንጾምበትና የምንጸልይበት ምክንያት ጊዜያችንንና ሪሳችንን እንዲሁም ፍላጐታችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ነው፡፡ ምግብ መብላትን እንኳ ሳይቀር የጸሎት ጊዜያችንን የሚሻማብንን ማንኛውንም ነገር እናስወግዳለን፡፡

ሁለተኛ፡- ዳንኤል ማቅ ለበሰ፡፡ ለአይሁዳውያን ማቅ መልበስ ማለት የንስሐ÷ የልብ መሰበርና የሐዘን ምልክት ነበር፡፡ አይሁዳውያን ከፍተኛ ሐዘን ሲያጋጥማቸው ማቅ የመልበስ ልማድ ነበረቸው፡፡ ለጸሎቱ መልስ እንዲሰጠው ዳንኤል ወደ እግዚአብሔር የቀረበውም በሐዘንና በትካዜ ማቅ ለብሶ ነበር፡፡

ሦስተኛ፡- ዳንኤል አመድ ምናልባትም አፈር በራሱ ላይ ነሰነሰ፡፡ ይህ ደግሞ ምን ያህል ራሱን በእግዚአብሔር ፊት እንዳዋረደ የሚያመለክት ነው፡፡ በፍጹም ትሕትና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመርኩዞ የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር

እንዲልና ወደ ሀገረቸውም እንዲመልሳቸው ጸለየ።

እኛም ብንሆን በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ማዋረድ ይኖርብናል። በፍጹም ትሕትና በሕይወታችን እንዲሠረ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ መምሰል ደረጃ እንዲለውጠን ልንለምነው ይገባል። ስለ ቤተ ክርስቲያናችንም መጸለይ አለብን። እግዚአብሔር ወደ አገረችን ፊቱን እንዲመልስና እንዲፈውሳት መጸለይ አለብን። እነዚህ ነገሮች በጣም አሳስበውን በእግዚአብሔር ፊት በጾምና በጸሎት እንቀርባለንን? ወይስ ጸሎታችን የግል ፍላጎትና ምኞታችን ብቻ እንዲሟላልን ነው?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 9:4-14

ጥያቄዎች

10ኛ ጥያቄ:- በዚህ ክፍል ዳንኤል የዘረዘረቸውን የእስረኤላውያን ኃጢአት ዘርዝር።
11ኛ ጥያቄ:- በዚህ ክፍል ዳንኤል የዘረዘረቸውን የእግዚአብሔር ባሕርያትን ዘርዝር።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማብሪሪያ /ኮሜንታሪ/

ዳንኤል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአታቸው ካልተጠቀሰባቸው ጥቂት ሰዎች አንዱ ነው። ይህም ሲባል ዳንኤል ምንም ኃጢአት አልነበረበትም ማለት ሳይሆን፥ ሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ነበር ማለት ነው። ዳንኤል ስለ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር በሚቀርብበት ጊዜ እንደ ራሱ ኃጢአት አድርጎ ለሕዝቡ የኃጢአት ምሕረትን ይለምን ነበር። እንደ እኛ የሕዝቡን ኃጢአት የተለያየ ሽፋን ሊሰጠው አይፈልግም። ለኃጢአቱ ምክንያት አድርጎ ሌሎችን አያቀርብም። ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው በሙሉ የሕዝቡ ኃጢአትና በደል እንደነበር ገለጸ። በይሁዳ ግዛት የሚኖሩ አይሁዳውያን ነበሩ። በዋና ከተማቸውም ኢየሩሳሌም የሚኖሩ ነበሩ። በሰሜኑ መንግሥት ውስጥ የምትኖረው እስረኤልም የዚህ በደል ተካፋይ ነበረች። የአይሁድ ነገሥታት፥ የእስረኤል መሪዎችና እንዲሁም ተረው ሕዝብ ጭምር ኃጢአትን እንዳደረጉ ጠቀሰ።

የእስረኤል ታሪክ በጣም የሚያሳዝን ነው። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ሕዝብ ቢሆኑም ዳጋግመው ከእግዚአብሔር ይርቁ ነበር። የእስረኤል ታሪክ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጋር ይመሳሰላል። ክርስቲያኖች እያወቁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያፈርሳሉ። ከእውነት ፊታቸውን

ይመስላሉ። ስለዚህም እንደ እስራኤላውያን ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም የተለያየ ቅጣት ይደርስባታል። የቤተ ክርስቲያናችንን ኃጢአት መመርመርና ለእግዚአብሔር መናዘዝ ይኖርብናል። ቤተ ክርስቲያንን የሚፈውሳትና የሚባርካትም ያን ጊዜ ብቻ ነው።

ዳንኤል የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት ለማሳየት የተለያዩ ቃላትን ተጠቅሞአል። ሕዝቡ ኃጢአት እንዳደረጉ ተናገረ። በዕብራይስጥ ይህ ኃጢአት የሚለው ቃል ከፍተኛ ወንጀልን ለማመልከት የተሰነዘረ ቃል ነው። ርኩሰትን አድርገዋል፥ ዓመፅንም ፈጽመዋል። የእግዚአብሔር ሕግጋት ቢሰጣቸውም እነርሱ አውቀው ለሕጉ አልታዘዙም። ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመልሷቸው እግዚአብሔር በተከታታይ ነቢያትን ላከባቸው። እነርሱ ግን የእግዚአብሔርን ነቢያት አልሰሟቸውም። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ቢያደርግም ሌሎች አማልክትን በማምለክ ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ሆነው አልተገኙም።

12ኛ ጥያቄ:- የጥንት እስራኤላውያን የፈጸሙአቸው ኃጢአቶች የዘመናችን ክርስቲያኖች ከሚፈጽሙአቸው ኃጢአቶች ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ዳንኤል የኃጢአትንና ያለመታዘዝን ውጤት ያመለክታል። በመጀመሪያ:- እፍረት እንደደረሰባቸው ይናገራል፤ (ዳንኤል 9:7)። በኃጢአታቸውና ከእግዚአብሔርም ከደረሰባቸው ቅጣት የተነሣ ለማያምኑ ሰዎች መሳቂያ ሆኑ፤ ምስክርነታቸውም አልተከበረም።

ሁለተኛ:- በዓለም ሁሉ ተበታተኑ። ወደ ባቢሎን በምርኮኝነት ከመወሰዳቸውም ሌላ እስራኤላውያን በዓለም ሁሉ ተበታተኑ። በተበታተኑባቸውም አሕዛብ መካከል ተዋረዱ። ዛሬም እንኳ ቢሆን አይሁዳውያን እንደተበታተኑ ናቸው። በታሪክ ውስጥ ለረጅም ዘመን ተሰደው የነበሩ ሕዝብ ናቸው። ይህም ሁሉ የደረሰባቸው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ነበር።

ሦስተኛ:- በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጠቀሰው እርግማን በሙሉ ደረሰባቸው። (ለእግዚአብሔር የሚታዘዙ ስለሚያገኙት በረከት በማይታዘዙት ደግሞ ስለሚደርስባቸው እርግማን ዘዳግም 28ን አንብብ።)

እግዚአብሔር ከአይሁዳውያን ጋር ቃል ኪዳን ባደረገበትና ሕጉንም በሰጠበት ወቅት ቢታዘዙት ስለሚያገኙት በረከት በግልጽ ነግሮአቸው ነበር። በግል ሕይወታቸውም ይባረካሉ። ከዚህም በተረፈ ለሕግጋቱ ባይታዘዙ ስለሚደርስባቸው ቅጣትና እርግማን በግልጽ ነግሮአቸው ነበር። ባይታዘዙት እነርሱ፥ ቤተሰባቸውም፥ ምድረቸውና መንግሥታቸው ሁሉ የተረገመ ይሆናል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕጉን ካልጠበቁት ከሚደርሰው ቅጣት ማንም ሊያመልጥ አይችልም።

13ኛ ጥያቄ:- የአንድ ሰው ኃጢአት እርሱን፥ ቤተሰቡን፥ ቤተ ክርስቲያ
የሀገሩን ሕዝብ እንዴት ሊጐዳ እንደሚችል የሚያሳይ ምሳሌ
ስጥ::

በኃጢአታቸው ምክንያት እየተቀጡ ሳለ እንኳ እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስና ለሕጉም ለመታዘዝ አለመፈለጋቸው በጣም የሚያስገርም ነው፤ (ዳን.9:13):: ዳንኤል ግን እውነተኛ ንስሐ ምን እንደሆነ ያመለክታቸዋል:: በመጀመሪያ:- ሙሉ በሙሉ ከኃጢአታችን መመለስ አለብን:: ሁለተኛ:- ወደ እውነት መንገድ መመለስ አለብን:: በአፋችን ብቻ ንስሐ እያደረግን ከበደላችን የማንመለስ ከሆነ ንስሐችን ትክክል አይደለም ማለት ነው:: ከጠማማው ወደ ቀናው መመለስ አለብን:: ጽርጊታችን ሁሉ መለወጥ አለበት::

የራሱንና የሕዝቡን ኃጢአት ለእግዚአብሔር መናዘዝ ብቻ ሳይሆን ዳንኤል ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ከፍተኛ ግንዛቤ ነበረው::

በመጀመሪያ:- እግዚአብሔር ሩቅ እንዳልሆነና በሕዝቡም ሕይወት የሚደረገውን ሁሉ በቸልታ እንደማያልፈው ተገነዘበ:: ዳንኤል እግዚአብሔርን የእስራኤል አምላክ ብሎ ከመጥራቱ በላይ፥ «አምላኬ» እያለ ይጠራዋል::

ሁለተኛ:- ዳንኤል እግዚአብሔር ታላቅና አስፈሪ መሆኑን ተገነዘበ:: ብዙ ጊዜ ግን እግዚአብሔር ለችግሮቻችን መፍትሔ ይሰጠናል ብለን እናስብም:: ዳንኤል ግን እግዚአብሔርን የሚያውቀው በታላቅነቱ ነው:: በታላቅነቱ በምድር ከተነሡት ታላላቅ መንግሥታት እንዱም እንኳ አይወዳደሩትም:: የአሕዛብ መንግሥታትን ሁኔታ ሁሉ ይቆጣጠረል:: በሕዝቡ ሕይወት የሚደርሰውን ሁኔታ ሁሉ ይቆጣጠረል::

ሦስተኛ:- እግዚአብሔር በፍቅር ላይ ለተመሠረተው ቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው:: እኛን እንደመረጠው ሁሉ እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጣት ከፍቅሩ የተነሣ ነው:: ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ:: ቃል ኪዳኑን ያፈረሱት እነርሱ እንጂ እርሱ አልነበረም:: ምን ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ታማኝ ነው:: ነገር ግን ታማኝ የሚሆንላቸው ለሚወዱት ትእዛዛቱን ለሚጠብቁለት ብቻ ነው:: በኃጢአታችን የምንቀጥል ከሆነ ግን ይቀጣናል::

አራተኛ:- እግዚአብሔር ሕዝቡን በኃይል ይታገሣቸዋል:: እግዚአብሔር ሕግጋቱን ለእስራኤላውያን ሰጣቸው:: እነርሱ ግን ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ላይ ዓመጹ፤ ለሕግጋቱም አልታዘዙም:: እግዚአብሔር ግን ወዲያው አልቀጣቸውም፤ ከስሕተታቸው እንዲመለሱ የሚያስጠነቅቁ ነቢያትን ጸጋግሞ ላከባቸው:: የቀጣቸውም ሳይታዘዙ ብዙ ከቆዩ በኋላ ነው::

አምስተኛ:- እግዚአብሔር ጻድቅ ነው:: የእግዚአብሔር ጽድቅ በሁለት መንገድ ተገልጾአል:: በመጀመሪያ:- እግዚአብሔር የሚያደርገው ሁሉ ትክክል

ነው። በጭካኔ ተነሣሥቶ ምንም ነገር አያደርገም፤ ወይም ባሕሪውን አይለውጥም። ሲቀጣ እንኳ እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ነው። ሁለተኛ:- የእግዚአብሔር ጽድቅ ኃጢአትን በመቅጣቱ ይታያል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ለኃጢአት ተገቢውን ቅጣት ካልሰጠ ቅዱስ አምላክ መሆን አይችልም። ስለዚህም ሕዝቡ ኃጢአትን ሲያደርጉ ይቀጣቸዋል፤ በጥፋታቸውም ስለሚቀጣቸውም ጻድቅነቱ ይታያል። የሚቀጣቸውም ወደ እውነቱ እንዲመለሱ ለማድረግ ነው።

ስድስተኛ:- እግዚአብሔር መሐሪ ነው። ከምሕረቱ የተነሣ ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ነው። ለማይገባቸውም ሰዎች ሞገስን ይሰጣቸዋል። ይህ ባሕርዩ ነው ዳንኤልን ይበልጥ ያጽናናው። እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ በማመፅዋ በተገቢው መንገድ ቅጣትዋን እየተቀበለች መሆኑን ዳንኤል ተገንዝቧል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር እንደሚልና ምሕረቱን እንደሚያበዛላቸው ዳንኤል እርግጠኛ ነበር። ስለዚህ ነው ጸሎቱን በእስራኤል ጽድቅ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ የመሠረተው።

ሰባተኛ:- ምን ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ይፈጽማል። ይህም ተስፋ የበረከት ወይም የመርገም ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ቃሉን አያጥፍም። ሰው የሰጠውን ተስፋ ቢዘነጋም እግዚአብሔር ግን በተስፋ ቃሉ የታመነ ነው።

በትንቢተ ዳንኤል 9:4-14 ዳንኤል ስለ ኃጢአቱ ሲናዘዝ እንመለከታለን። የእግዚአብሔርን ባሕርያት ምን ያህል እንደተረዳም እንመለከታለን። ሕዝቡ በመበተናቸው የኢየሩሳሌም ከተማም በመፈረሱ እግዚአብሔርን በጸለኛ ሲያደርገው አንመለከትም። እግዚአብሔር ጻድቅ ለመሆኑ የማያወላውል እምነት ነበረው። ጥፋቱ የእግዚአብሔር ሳይሆን የሕዝቡ ነው። እኛም ብንሆን ስለበደላችን ስንቀጣ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም የለብንም። ምን ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። የረሳችንን ልብና የሌላውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ መመርመር አለብን። ኃጢአት ካለብን እንናዘዝ። እግዚአብሔር መሐሪ ስለሆነ ይቅር ይለናል።

14ኛ ጥያቄ:- አንዳንድ ጊዜ በኃጢአታቸው ምክንያት የተለያየ ችግር ሲደርስባቸው ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ ሲያማርሩ ይሰማል፤ ከእነዚህ ችግሮች ጥቂቶቹ ምንድናቸው?

<u>አረተኛ ቀን</u>  <u>ክፍል ሦስት:- ዳንኤል 9:15-19</u>

## <u>ጥያቄዎች</u>

15ኛ ጥያቄ:- በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የሠረውን ታላቅ

ተአምረት ዳንኤል የሚያመለክተው የትኛው ነው?

16ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር ያን ታላቅ ተአምር በፈጸመ ጊዜ ውጤቱ ምን ነበር?

17ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል ለእግዚአብሔር ያቀረበው ልመና ምንድነው?

18ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል «ስለ አንተ ስትል» ብሎ መጸለዩ ምን ለማለት ይሆን?

19ኛ ጥያቄ:- የጸሎቱ መልስ እንዳይዘገይበት ዳንኤል እግዚአብሔርን የጠየቀው ለምን ነበር?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ካደረገላቸው ድንቅ ነገሮች መካከል አንደኛው ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞአል:: ይኸውም እግዚአብሔር ከግብፅ ባርነት አውጥቷቸው የተስፋይቱን ምድር በሰጣቸው ጊዜ ነው:: በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ኃይሉንና እነርሱን ለመታደግ ፈቃደኛ መሆኑን አሳያቸው::

ዳንኤል በነበረበት ዘመን እስራኤላውያን በምርኮኝነት ነበሩ:: ስለዚህም ከግብፅ ምድር አባቶቻቸውን እንደታደገ ሁሉ እነርሱንም ከባቢሎን ምርኮኝነት እንዲታደጋቸው እግዚአብሔርን ይለምናል:: አሁንም እንደገና እግዚአብሔር በታላቅ ኃይሉ እንዲታደጋቸውና ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲመልሳቸው ያስፈልጋል::

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ በታደገበት ጊዜ እነርሱ ካገኙት ነፃነት ሌላ በዙሪያ የነበሩ አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንደሠረላቸው ተረዱ:: ስለዚህም የእስራኤልን አምላክ እጅግ ይፈሩና ያከብሩ ነበር::

20ኛ ጥያቄ:- ኢያሱ 2:8-13 አንብብ::

ሀ/ ከነዓናውያን ስለ እግዚአብሔር የሰሙት ምን ነበር?

ለ/ የሰሙትንስ ወሬ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነበር የተቀበሉት?

ዳንኤል በነበረበት ዘመን እንኳ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት ነፃ እንዳወጣቸው በዙሪያ የነበሩ አሕዛብ ይናገሩ ነበር:: እግዚአብሔርንም ይፈሩ ነበር:: እስራኤላውያን ግን ኃጢአት በመሥረታቸው ተዋረዱ፤ የእግዚአብሔርንም ስም አሰደቡ::

እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ነበሩ፤ ስለዚህም ዳንኤል በፍርድ ሳይሆን በምሕረትና በጽድቅ ሥራውን እንዲሠረና ሕዝቡን እንዲታደግ እግዚአብሔርን ይለምናል::

ዳንኤል እስራኤላውያን ጻድቅ በመሆናቸው እግዚአብሔር እንዲምራቸው አልጠየቀምᎨ እግዚአብሔር ጽኑቅ ሥራ እንዲያደርግ የጠየቀበት አራት ምክንያቶች ነበሩት።

1. የይሁዳ ዋና ከተማ ኢየሩሳሌም ልዩ ከተማ መሆንዋን ዳንኤል ያውቃል። ለእግዚአብሔርም የተለየች ነበረችᎨ ምክንያቱም÷ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር «ቅዱስ ተራራ» ናትና። ስሙ እንዲጠራባትም መርጧታል። በምድር ላይ ከሚገኘው ከየትኛውም ሥፍራ ይልቅ በዚያ እንዲመለክ ፈልጎአል። በሕዝቡ በእስራኤል ላይ እንደ እውነተኛ ንጉሥ የሚገዛውም በዚያ ከተማ ውስጥ ሆኖ ነው።

2. እግዚአብሔርን በእውነት ለማምለክ መቅደሱ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ዳንኤል ተረድቶአል። ዳንኤል «የፈረሰው መቅደስ» ይለዋል። በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዲመለክበት እግዚአብሔር የመገናኛው ድንኳን እንዲሠራ አዘረገ። በዚያ ሥፍራ ሰሙ ይከበር÷ ክብሩም ይገለጽ ነበር። ስለዚህም እንዳለፈው ዘመን እቅዱ በመቅደሱ ውስጥ እንዲመለክ ዳንኤል እግዚአብሔርን ይለምናል።

3. እስራኤላውያን በዓለም ከሚገኙት ሕዝቦች ሁሉ የተለዩ መሆናቸውን ዳንኤል ተገንዝቦአል። ልዩ የሆኑት ብርቱ በመሆናቸው ወይም ብዛት ስለነበራቸው አልነበረም። ልዩ የሆኑት በስሙ እንዲጠሩ እግዚአብሔር ስለመረጣቸው ብቻ ነበር። የእውነተኛው አምላክ ሕዝብ ይባሉ ነበር። ስለዚህም በስሙ የተጠሩ ሕዝብ በመሆናቸው እግዚአብሔር ፊቱን እንዲመልስላቸው ዳንኤል ይለምናል።

4. በዚህ ሁሉ የዳንኤል ዋናው ፍላጐት የእግዚአብሔር ስም እንዲከበር ነበር። እግዚአብሔር የሚገባውን ክብር እንዲያገኝ የዳንኤል ፍላጐት ነው። ስለዚህም «ስለ ራስህ» ስትል ሥራ በማለት እግዚአብሔርን ይጠይቀዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሚገባቸው ሲኖሩ÷ እነርሱ ከመባረካቸው በላይ የእግዚአብሔርም ስም በአሕዛብ መካከል ይከብራል።

እኛም ብንሆን የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ነን። የተመረጥነውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናስከብር ነው። ኃጢአት ስናደርግ ግን እንደ እስራኤላውያን ሁሉ የእግዚአብሔርን ስም እናሰድባለን። በኃጢአታችን እንቀጣለን÷ እናፍረለንᎨ ከዚያም አልፈን የእግዚአብሔርን ክብር እናቃልላለን። ከማንኛውም ነገር አብልጠን ለእግዚአብሔር ክብር ማሰብ አለብን። ኃጢአታችንን ተናዝዘን እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል በመካከላችን እንዲሠራ ስንጠይቀው ዋናው ዓላማችን እኛ እንድንባረክ ብቻ ሳይሆን እርሱ እንዲከበር መሆን አለበት። ለመሆኑ ለእግዚአብሔር ክብር ይህን ያህል እናስባለን?

21ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ክርስቲያኖች በኃጢአታቸው የእግዚአብሔርን ስም የሚያሰድቡት እንዴት ነው?
ለ/ በመታዘዛቸውስ እግዚአብሔርን የሚያስከብሩት እንዴት ነው?

ዳንኤል እግዚአብሔርን እንዲሠራ የጠየቀው ምሕረቱን መሠረት በማድረግ ነበር:: ሕዝቡን ወደ ሀገራቸው በመመለስ ብርታቱን እንዲያሳይ ጠየቀው:: በሚቀጥለው ሳምንት እግዚአብሔር ለዳንኤል ጸሎት የሰጠውን መልስ እንመለከታለን:: ለእርሱ የምንሠራውን ሥራ ሁሉ በጸሎት ስንጀምር እግዚአብሔር ደስ እንደሚለው ማስተዋል ይኖርብናል:: ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ÷ ሐሳባችንም እንደ ሐሳቡ ሲሆን÷ እግዚአብሔር በጸሎታችን ድንቅ ሥራ ይሠራል:: እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በግልጽ ሆኖ÷ በኅብረት ከማንኛውም ኃጢአት ንጹሐ መሆናችንን ማረጋገጥ ይገባናል:: ንስሐ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲሠራ በሩን ይከፍትለታል:: የእግዚአብሔር መንፈስ በታላቅ ኃይል በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ እየሠራ ነው ወይስ ሁኔታዎች ሁሉ ቀዝቅዘዋል? የራስህን ሕይወትና ቤተ ክርስቲያንህን መርምር:: እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን እንዲሠራና ስሙን በእኛ ውስጥ እንዲያስከብር የምንጠይቅበት ጊዜ አሁን ነው::

<u>አምስተኛ ቀን:-</u> የዚህን ሳምንት ትምህርት መከለስ::

<u>የሳምንቱ ስብሰባ</u>

1. የሳምንቱ የአምልኮት ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ/ የቤተ ክርስቲያንህን ታሪክ ከእስራኤል ታሪክ ጋር አነጻፀር::
1. እግዚአብሔር በመካከላችሁ በታላቅ ኃይል የሠራበት ጊዜ አለን?
2. እግዚአብሔር እናንተን የቀጣበት ጊዜ አለን?
3. ለቅጣቱ መንስኤ የሆነው ነገር ምንድነው?
4. ዛሬስ በታላቅ ኃይል እግዚአብሔር በመካከላችሁ እየሠራ ነውን?
5. እግዚአብሔር በታላቅ ኃይል እንደሠራ ቤተ ክርስቲያን ከኃጢአትዋ መንጻት እንዳለባት ታስባለህን? እግዚአብሔር እንዲያነጻችሁና ድንቅ ሥራውን እንዲሠራ የኅብረት ኑዛዜ አድርጉ::

ለ/ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዴት ለማወቅ እንደሚችሉ ተወያዩ።
1. ምን ማድረግ አለባቸው?
2. እግዚአብሔርን እንደሚገባ እንዳያውቁ የሚያደርጋቸው ምንድነው?
3. በጣም ወደ እግዚአብሔር የቀረቡ ለመሆናቸው የምትመሰክርላቸው የአንዳንድ ሰዎችን ስም ጥቀስ።
4. ሕይወታቸው ከሌላው ሰው ልዩ የሆነው በምን መልኩ ነው?

ሐ/ 1. የዳንኤል ጸሎት ስለ እግዚአብሔር ያለውን ዕውቀትና ፍቅር የሚያመለክተው እንዴት ነው?
2. ዛሬስ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን እውቀት እንዴት ነው በጸሎታቸው የሚገልጹት?

መ/ ከዳንኤል ጸሎት የምንማረቸውና በረሳችን ጸሎት ውስጥ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ነገሮች ምንድናቸው?

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥረ አምስት

## ዳንኤል 9:20-27

### የመጀመሪያ ቀን

ዓመፃን ይጨርስ÷ ኃጢአትንም ይፈጽም÷ በደልንም ያስተሰርይ÷ የዘላለምን ጽድቅ ያገባ÷ ራዕይንና ትንቢትን ያትም÷ ቅድስተ ቅዱሳኑንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥሮአል። (ዳን.9:24)

የትንቢተ ዳንኤል መሪ ሐሳብ፦ ምንም እንኳ የተለያየ ሁኔታ በምድር ላይ ቢፈጸምም እግዚአብሔር ሁሉንም የሚቆጣጠር መሆኑን ማሳየት እንደሆነ ተመልክተናል። እስራኤላውያን በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነበሩ፤ እንዲቀጡዋቸው ለባቢሎናውያን አሳልፎ የሰጣቸውም እርሱ ነበር። በዳንኤልና በሦስት ጓደኞቹ የተፈጸመው ሁኔታ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነበር። የአሕዛብ ነገሥታትን የሚቆጣጠረውም እርሱ ነው። ከዚህም በላይ ታሪክ ራሱ እንኳ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እንደሆነ አይተናል። ከዳንኤል ዘመን እንሥቶ እስከ ሮማውያን ዘመን ድረስ ስለሚነሡት ነገሥታት እግዚአብሔር በትንቢት ለዳንኤል ገለጠለት። ዛሬ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ በእስራኤላውያን

ላይ ስለሚደርሰው ሁኔታ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ለዳንኤል እንደተናገረው፥ የእስራኤልን ሕዝብ በተመለከተ የሚፈጸሙት ክንዋኔዎች በሙሉ የጊዜ ገደብ እንደተሰጣቸው ነው። ይህም የጊዜ ገደብ ሰባ ጊዜ ሰባት በመባል ይታወቃል።

የታሪክ ግቡ ወይም ዓላማው የእግዚአብሔርን ሕዝብ በተለይ በመከራ ውስጥ በሚያልፉበት ወቅት ማጽናናት እንደሆነ ተመልክተናል። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው የክፉ ፍጻሜው ምን እንደሚሆን በማመልከት ነው። አስቀድመን የዓለምን ታሪክ ተመልክተን ቢሆን ኖሮ በዳን.9:24 የተሰጠውን ትንቢት እንደሚገባ ለመረዳት በቻልን ነበር። አዳምና ሔዋን ከበደሉበት ጊዜ አንሥቶ ክፋት በምድር ላይ እየገዛ ነበር። ወንድም ከወንድሙ ይጋጫል። መንግሥታት ከእግዚአብሔር ይርቃሉ። ክፋት በየቦታው እየሰለጠነ ነው። ስለዚህም የዓለም ታሪክ የክፋትና የዓመፅ ታሪክ ሊባል ይቻላል። የእግዚአብሔር ሕዝብ አእምሮ አንዳንዴ ለዚህ ሁሉ ሥቃይና መከራ ፍጻሜ ይኖረው ይሆን? እያለ ይጠይቃል። አዎ፥ አንድ ቀን ክፋትና ዓመፅ እንደሚያከትም እግዚአብሔር ለዳንኤል ያረጋግጥለታል። በዳን.9:24 ላይ ኃጢአት እንደሚፈጸም፥ ጽድቅ እንደሚገዛ፥ እግዚአብሔርም ከሕዝቡ ጋር ፍጹም ኅብረት እንደሚኖረውና ምንም ትንቢት እንደማያስፈልግ ይነግረዋል።

ምናልባትም ስለዚህ ታላቅ ጊዜ በጸንብ የሚገልጸው የራዕይ መጽሐፍ ሳይሆን አይቀርም። «ታላቅም ድምፅ ከሰማይ:- እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ» (ራዕይ 21:3-4)።

1ኛ ጥያቄ:- ይህ ትንቢት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ክርስቲያኖችን ሊያጽናናቸው እንደሚችል ዘርዝር። በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖችስ እንዴት ያጽናናቸዋል?

ብዙ ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች ዓይኖቻችንን ችግሩችን ላይ ብቻ እናሳርፋለን። በሕይወታችን ወይም በአካባቢያችን ያለውን መከራ ብቻ እንመለከታለን። ስለ ስጸቱ ብቻ እናስባለን። በቤተ ክርስቲያንና በአካባቢያችን ያለውን ክፉ ነገር ተመልክተን «ይህ ሁሉ የሚስተካከልበት ጊዜ ይመጣ ይሆን?» በማለት እንጠይቃለን። አንዳንድ ጊዜም ተስፋ እንቆርጣለን። ዓይኖቻችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ማድረግን ከዳንኤልና ከሌሎች የትንቢት መጻሕፍት መማር አለብን። የእርሱን መመለስ እንጠብቅ፤ እነዚህ ችግሮች ሁሉ የሚያከትሙት ያን ጊዜ ነው፤ (2ቆሮ. 4:16-18 ተመልከት)። ዓይኖችህ በዘላለማዊው ነገሮች ላይ ናቸው ወይስ በዚህ ዓለም ባሉት ጊዜያዊ ነገሮች ላይ?

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ 2ቆሮ.4:16-18 አንብብ:: ዓይኖቻችንን ልናሳርፍባቸው ስለሚገቡ ዘላለማዊ ነገሮች ዘርዝር::
ለ/ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ዓይኖቻቸውን ስለሚያሳርፉባቸው ጊዜያዊ ነገሮች ዘርዝር::

3ኛ ጥያቄ:- ዳን.9:20-27 አንብብ:: ለዳንኤል የተሰጠውን ትንቢት በራስህ ቃላት ግለጸው:: ወይም በራስህ አነጋገር በጽሑፍ አስቀምጠው::

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 9:20-24

ጥያቄዎች

4ኛ ጥያቄ:- መጸለይ ከጀመረ ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነው ዳንኤል የጸሎቱን መልስ ያገኘው?
5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ለዳንኤል የጸሎቱን መልስ ይዞለት የመጣው ማነው?
ለ/ ከዚህ በፊት ይህ «ሰው» ወደ ዳንኤል የመጣው መቼ ነበር? ስለዚህ ሰው ምን እንደተባለ ትምህርት 13ን ተመልከት::
6ኛ ጥያቄ:- መልእክተኛው የመጣው መቼ ነበር?
7ኛ ጥያቄ:- ለዳንኤል የጸሎቱ መልስ የተሰጠው ለምን ነበር?
8ኛ ጥያቄ:- ሰባ ጊዜ ሰባትን የወሰነው ማነው?
9ኛ ጥያቄ:- ይህ ሰባ ጊዜ ሰባት የተባለው ጊዜ ምን ያህል ይመስልሃል?
10ኛ ጥያቄ:- ይህ ሰባ ጊዜ ሰባት ከተፈጸመ በኋላ ስለሚፈጸሙ ስድስት ነገሮች ግለጽ:: እነዚህ ነገሮች እያንዳንዳቸው ምን የሚያመለክቱ ይመስልሃል?

የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ባለፈው ሳምንት ትምህርት ስለ ዳንኤል ኑዛዜና ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ያደረገውን ጸሎት ተመልክተናል (ዳን.9:1-19):: ምንም እንኳ ዳንኤል ይህን ጸሎት የጸለየው እግዚአብሔር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ጸሎቱን እንደመለሰለት ለማሳየት ቢሆንም ሌሎች እስራኤላውያን የእርሱን ጸሎት ምሳሌነት እንዲከተሉ ይፈልጋል:: የእግዚአብሔርን በረከት ከማግኘታቸው በፊት ኃጢአታቸውን መናዘዝ እንዳለባቸው ሊያመለክታቸው ያስባል:: ከዚህም በተረፈ በጸሎታችን አማካይነት እግዚአብሔር ታላቅ ሥራን እንደሚሠራ ማወቅ ይገባናል:: በጸሎታችን በኩል የረሱ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ ሥራን ከመሥራቱ በፊት ግን ኃጢአታችንን መናዘዝና መንጻት አለብን::

ለዳንኤል ጸሎት የተሰጠውን መልስ በትንቢተ ዳንኤል 9:24-27 እናገኛለን። ይሁን እንጂ የተሰጠው መልስ ዳንኤል ከጠበቀው በጣም የተለየ ነው። እስራኤላውያን ወደ ሀገረቸው እንደሚመለሱና ኢየሩሳሌምን እንደሚገነቡ ነገረው። ይሁን እንጂ የሰጠው መልስ እርሱ ከጠየቀው በጣም ሰፋ ያለ ነው። ከዳንኤል ዘመን አንሥቶ ክፋትና ዓመፅ እስከሚወገዱበት ዘመን ድረስ በእስራኤላውያን ላይ ስለሚፈጸመው ሁኔታ ገለጸለት። ይህም የሚሆነው የዓለም ፍጻሜ በሚቃረብበት ወቅት ነው።

ገና ዳንኤል እየጸለየ እያለ ነበር እግዚአብሔር መልሱን የሰጠው። መልአኩን «ገብርኤልን» ላከለት። ከዚህ ቀደም ገብርኤል ወደ ዳንኤል መልእክተኛ ሆኖ እንደተላከ በ8:16 ተመልክተናል። ገብርኤል ወደ እርሱ የመጣው የሰው መልክ ይዞ ስለነበር:- «አስቀድሜ በራዕይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል ...» በማለት ይገልጸዋል። ገብርኤል ግን መልአክ እንጂ ሰው አይደለም። ዳንኤል ገብርኤልን በፍጥነት እየበረረ ወደ እርሱ ሲመጣ ተመልክቶት ይሆናል። እግዚአብሔር ገብርኤልን የላከው ገና ዳንኤል መጸለይ በጀመረበት ጊዜ ነበር። ዳንኤል ገብርኤልን ያየበትን ጊዜ እንደሚገባ ያውቀዋል። ጊዜው «የማታ መሥዋዕት» የሚቀርብበት ጊዜ ነበር። በዚያን ጊዜ ምንም መቅደስ ስላልነበረቸው መሥዋዕት አያቀርቡም ነበር፤ ይሁን እንጂ የኢየሩሳሌምን መቅደስ አሠራር ዳንኤል እንደሚገባ ያስታውሰዋል። መቅደሱ የፈረሰው በ586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። የማታ መሥዋዕት የሚቀርበው ከቀኑ 9 ሰዓት ነበር። ልክ በዚህ ሰዓት የአንድ ዓመት በግ ይሠዋል፥ የእህልና የመጠጥ ቁርባንም ለእግዚአብሔር ይቀርባል። ብዙ አይሁዳውያን ወደ እግዚአብሔር የሚጸልዩበት ጊዜ ነበር።

ዳንኤል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ታላላቅ ሰዎች አንዱ ነው። እንደ አብርሃምና እንደ ዳዊት ሁሉ የእግዚአብሔር ቅርብ ወዳጅ ነበር። እግዚአብሔር ለዳንኤል ራዕዩን የሰጠው በእግዚአብሔር እጅግ የተወደደ ስለነበር ነው። እኛም ብንሆን የእግዚአብሔር ወዳጅ ልንሆን እንችላለን፤ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ጋር ለመረመድና በፍጹም ልባችን ለመታዘዝ መወሰን አለብን።

በትንቢተ ዳንኤል ከተሰጡት ትንቢቶች ሁሉ ለመተርጐም በጣም የሚያስቸግረው ዳን. 9:24-27 ያለው ነው። ስለ እነዚህ ትንቢቶች አፈጻጸም የተለያየ ገለጻና አመለካከት ተሰንዝሮአል። ትንቢትን ስንተረጉም በአንድ አቋም ላይ ግትር መሆን የለብንም። ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች በትንቢት አተረጓጐማቸው አይስማሙም። ቀጥሎ ዳን.9:24-27ን ለመተርጐም የተሰነዘሩ የተለያዩ ገለጻዎችን እንመለከታለን።

1. ጥቂት ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት የሚያመለክተው በ167 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ቤተ

መቅደሱን ስላረከሰበት ጊዜ እንደሚያመለክት ይናገራሉ። በዚህም ምክንያት አይሁዳውያን ዓመፁ፤ ነፃ የአይሁዳውያን መንግሥትም መሠረቱ። ይሁን እንጂ ይህን መቀበል ያዳግተናል።

2. አንዳንዶች ደግሞ ይህ ትንቢት የተፈጸመው ኢየሱስ በመጀመሪያ በመጣበትና ከሞተ በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር ይላሉ። የሰባ ጊዜ ሰባት መጨረሻ በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም በተደመሰሰችበት ጊዜ ነበር።

3. ሌሎች ደግሞ ሰባ ጊዜ ሰባት የሚለው አባባል ቃል በቃል የሚተረጐም ሳይሆን ምሳሌያዊ አነጋገር እንደሆነ ያስባሉ። 7 ቁጥር ፍጹምነትን ያመለክታል። ስለዚህም በውስጠ ታዋቂነት እግዚአብሔር እቅዱ ወደሚፈጸምበትና ዘላለማዊነት ወደሚጀመርበት ወደ ዘመናት መጨረሻ እያመለከተ ነው። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መጥቶ ለሺህ ዓመት የሚቆይ መንግሥት ይመሠረታል የሚለውን አነጋገር አይቀበሉም።

4. ምናልባትም ይህ ቃል በተለያየ ጊዜ የሚፈጸሙ ሁኔታዎችን የሚያመለክት ትንቢት ሳይሆን አይቀርም። አንደኛ ኢየሱስ መጀመሪያ በመጣበት ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ በዘመናት መጨረሻ ላይ እንደሚፈጸም ይጠበቃል።

5. በመጨረሻም አንዳንድ ሰዎች ሰባ ጊዜ ሰባት የሚለው ቃል በትክክል እግዚአብሔር ለታሪክ የሰጠው የጊዜ ገደብ እንደሆነ ያመለክታሉ። በስድሳ ዘጠነኛው ሱባዔ ኢየሱስ ይመጣል፥ ይገደላል፥ ኢየሩሳሌምም ትወድማለች። ሰባኛው ሱባዔ ግን የወደፊት ጊዜን የሚያመለክት ሲሆን የሚፈጸመውም ታላቅ መከራ በሚሰፍንበት በክርስቶስ ተቃዋሚ ዘመነ መንግሥት ነው። ይህን ክፍል ለመተርጐም በምናደርገው ሙከራ ስለ እነዚህ አመለካከቶች በሰፊው እንመለከታለን።

11ኛ ጥያቄ:- እነዚህን 5 አመለካከቶች በሚገባ አጥናቸው። ከዚያ በኋላ ዳን. 9:24-27 እንደገና አንብብ። በእነዚህ አመለካከቶች ላይ ተመርኩዘህ ይህን ክፍል እንዴት የተለያየ ትርጓሜ ሊሰጠው እንደሚቻል እይ።

ዳን.9:24 የሚያመለክተን እግዚአብሔር ያለውን አጠቃላይ ዕቅድ ነው። ስለዚህም እነዚህን ቁጥሮች በጥንቃቄ መመልከት ይኖርብናል። ለወደፊት ያለው ዕቅድ በ70 ሱባዔ ውስጥ እንደሚፈጸም እግዚአብሔር ለዳንኤል ነግሮታል። ምንም እንኳ አንዳንዶች ይህ 70 ሱባዔ ምሳሌያዊ አነጋገር እንጂ ቃል በቃል የሚተረጐም አይደለም በማለት ቢናገሩም በምርኮ የቆዩበት ሰባ ዓመት ቃል በቃል እንደተተረጐመ ሁሉ ይህም ቃል በቃል ቢተረጐም ተገቢ ነው እንላለን። ለመሆኑ «ሱባዔ» ስንል ምን ማለታችን ነው? ሳምንት ነው ወር ወይስ ዓመት? ሱባዔ ማለት 7 ማለት ነው።

አይሁዳውያን ግን የተለያየ ትርጉም ሊሰጡት ይችሉ ይሆናል። በሳምንት ውስጥ ሰባት ቀን እንደመኖሩ መጠን ምናልባት አንድ ሳምንት የሚያመለክት ይሆናል። ዳንኤል ግን ስለ ሰባው የምርኮ ዓመታት ያስብ ነበር፤ ከዚህም በላይ አይሁዳውያንም ዓመታትን በ7 እየመደቡ የመመልከት ልምድ ነበረቸው። (ለምሳሌም ያህል ዘፀ.23:10-11፤ ዘሌ.25:8-24 እና 2ዜና 36:20-21 ተመልከት።) ከዚህ እንደምንመለከተው እያንዳንዱ ሱባዔ ሰባት ዓመት ይወክላል ብሎ ማሰቡ ጥሩ ይሆናል። እንዲህም ከሆነ ዳንኤል የሚናገረው 70 X 7 ወይም ስለ 490 ዓመት ነው ማለት ነው። በዓመት ውስጥ 360 ቀን ያላቸው አይሁዳውያን ብቻ ናቸው። በዚህም መሠረት የተጠቀሰውን ጊዜ በትክክል ስናሰላው 490 X 360 ቀን መሆኑ ነው።

በሕዝቡ (በእስረኤላውያን) እና በኢየሩሳሌም (በተቀደሰቸው ከተማው) ላይ 70 ጊዜ ሰባትን ወይም 70 ሱባዔውን እግዚአብሔር እንደወሰነው ለዳንኤል ነግሮታል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ባለው ዓላማ አሕዛብ አንዳንድ ድርሻ ሊኖረቸው ቢችልም ይህ ቃል የተሰጠው በአይሁዳውያንና በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ ወደፊት የሚፈጸመውን ሁኔታ ለዳንኤል ለማመልከት ነበር። ዳንኤል ሲጸልይበት የነበረው ጉዳይም ይኸው እንደነበር ታስታውሳለህ።

ዳንኤል 9:24 እግዚአብሔር ለአይሁዳውያንና ለመላው ዓለም ስለሚሰጠው በረከት በአጭሩ የሚያስረዳ ነው ለማለት ይቻላል። ስድስቱ በረከቶች በዘመናት መጨረሻ የእግዚአብሔር ዓላማ ከተፈጸመ በኋላ ስለሚኖረው ጊዜ ነው የሚያመለክቱት። የመጀመሪያዎቹ ሦስት በረከቶች በዓለማችን ስለበዛው ኃጢአት የሚያመለክቱ ናቸው።

1. «ዓመፃን ይጨርስ» ይህ ቃል በአጠቃላይ መልኩ ኃጢአትን ያመለክታል። የእስረኤል ዓመፅና ኃጢአት ስለሚያከትምበት ጊዜ የሚያመለክት ትንቢት ነው። ምንም እንኳ ሰዎች የኃጢአትን ስርየት የሚያገኙት በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ቢሆንም÷ ዛሬም ቢሆን በዓለም ላይ እጅግ ብዙ ኃጢአት አለ። አንድ ቀን ግን ኃጢአትና ዓመፅ በሙሉ ያከትማል።

2. «ኃጢአትን ይፈጽም» ይህ ቃል «ኃጢአትን በማኅተም ያትም» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። በቁጥር አንድ እንደተመለከተነው ሁሉ ኃጢአት ከምድር ላይ በፍጹም ስለሚወገድበት ጊዜ ያመለክታል። ይህ ከሆነ ደግሞ መከረና ጥፋት በምድር ላይ ያከትማል።

3. «በደልንም ያስተሰርይ» ይህ ቃል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ያመለክታል። ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር በመስቀል ላይ የኃጢአታችንን ዋጋ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ። እንደ መልካም መሥዋዕት ለክፋታችን ማስተሰሪያ ሆነ። ማስተሰረይ በግድግዳ ላይ ያለውን

ጉድፍ በቀለም ከመሸፈን ጋር ይመሳሰላል:: በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን ሸፈነልን:: በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆነን የምንታየውም በዚህ ምክንያት ነው::

ምንም እንኳ እነዚህ ሦስት በረከቶች ያገኘነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ቢሆንም በመስቀል ላይ የተጀመረው የሥራ ውጤት በሙላት የሚታየው ኢየሱስ ዳግም ሲመለስ ነው:: ያን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ይነግሣል፥ ኃጢአትና ውጤቱ በሙሉ ይደመሰሳሉ:: የአዳምን ኃጢአት ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ እግዚአብሔር ያለው ዓላማም ይፈጸማል::

በዘመናት መጨረሻ ደግሞ እነዚህ ሦስት ተጨማሪ በረከቶች ይፈጸማሉ::

4. «የዘላለምን ጽድቅ ያገባ» ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ የእርሱ ጽድቅ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ እንዲደርስ አድርጉአል:: ብዙዎች ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን ባለመፈለጋቸው ምክንያት ጻድቃን አይደሉም:: አንድ ቀን ግን የዘላለም ጽድቅ ይነግሣል:: ይህም የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስና ኃጢአት ሲወገድ ነው:: የኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅን ግዛት ይመሠረታል::

12ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ቁጥሮች ተመልክተህ ስለዚህ የጽድቅ ጊዜ የተነገረውን ትንቢት አስተውል:: እውነተኛ ጽድቅ ሲመሠረት በምድር ላይ ስለሚሆነው በረከት ግለጽ:: ኢሳ.11:2-5፤ ኤር.33:15-18::

5. «ራዕይንና ትንቢትን ያትም» በደብዳቤ ላይ ማኅተም የሚደረገው በተጻፈው ላይ ምንም እንዳይጨመርበት ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሲመለስ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ላይ ምንም መጨመር አያስፈልገንም:: ያን ጊዜ ትንቢቶቹ ሁሉ ይፈጸማሉ፤ የእግዚአብሔርም ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ይነጋገራሉ:: አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ ቃል የተነገረው አዲስ ኪዳን ተጽፎ ስላለቀበትና ትንቢት ስለተዘጋበት ጊዜ ነው ብለው ያስባሉ::

6. «ቅዱስ ቅዱሳኑንም ይቀባ» በግልጽ ስላልተነገረ የሚቀባው ምን እንደሆነ እርግጠኛ አይደለንም:: በብሉይ ኪዳን ዘመን የተቀደሱ ወይም የተለዩ መሆናቸውን ለማሳየት አንዳንድ ነገሮች በዘይት ይቀቡ ነበር:: ምናልባትም ይህ ክፍል በእግዚአብሔር ላይ ስለሚታመን መሪ የተነገረ ይሆናል:: በዚህም ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ይህ ቃል ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀባቱ የሚገልጽ እንደሆነ ያስባሉ:: ይሁን እንጂ ይህ ቃል ስለ ሥፍራ የሚያመለክትም ሊሆን ይችላል:: ስለዚህም አንዳንድ ሰዎች ሺሕ ዓመት ለመግዛት ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ስለምትቀባው ቤተ መቅደስ ወይም አዲስቱ ኢየሩሳሌም ለዘላለም እንደምትቀባ የሚያመለክት እንደሆነ ይናገራሉ::

ይህ ትንቢት እኛን እንደሚያጽናናው ሁሉ በጊዜው ዳንኤልን ሳያጽናናው እንዳልቀረ ጥርጥር የለውም:: እስቲ አስቡትI አንድ ቀን ኃጢአት ሁሉ ተወግዶ ጽድቅ ይመሠረታል:: የዚህ ትንቢት ፍጻሜ ኢየሱስ መጀመሪያ በመጣበት ወቅት የተጀመረ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው ደግሞ በሚመጣበት ጊዜ ነው:: ይህንንም በናፍቆት እንጠብቃለን:: ዮሐንስ በራዕዩ መደምደሚያ ላይ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና! (ማራናታ) ብሎ እንደጸለየ ሁሉ እኛም ይህንን ጸሎት እንጸልያለን:: ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ተዘጋጅተሃልን?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 9:25-26

## ጥያቄዎች

13ኛ ጥያቄ:- መሢህ ከመምጣቱ በፊት ስንት ሱባዔ ያልፋል?
14ኛ ጥያቄ:- በሰባው ሱባዔ መጀመሪያ ላይ የሚሆነው ምንድነው?
15ኛ ጥያቄ:- ስለ ኢየሩሳሌም የተሰጠው ተስፋ ምንድነው?
16ኛ ጥያቄ:- ስለ መሢህ የተሰጠው ተስፋ ምንድነው?
17ኛ ጥያቄ:- በከተማይቱና በመቅደሱ ላይ ምን ይሆናል?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

በዳንኤል 9:25-27 ላይ ስለ ሰባ ሱባዔ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ተሰጥቶታል:: ይህ ሰባ ሱባዔ በሦስት ይከፈላል:: በመጀመሪያ 7 ሱባዔ÷ ቀጥሎ 62 ሱባዔ÷ በመጨረሻም 70ኛው ሱባዔ::

ትንቢቱም እንደሚገባ እንዲያስተውል ለዳንኤል ተነገረው:: ይሁን እንጂ÷ አብዛኛው የተነገረው ትንቢት ግልጽ አልሆነለትም ነበር:: የትንቢቱ አብዛኛው ክፍል በተፈጸመበት ዘመን ያለነው እኛ እንኳ ዛሬ ትንቢቱን እንደሚገባ ለመረዳት ችግር አለብን::

ለሰባው ሱባዔ መነሻ የሆነው አንድ ጉዳይ ነው:: ይህም የኢየሩሳሌም ከተማ እንድትሠራ የወጣው ዓዋጅ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ የትኛውን ዓዋጅ እንደሚያመለክት የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የተለያየ ሐሳብ አላቸው:: ለዚህም ጊዜውን በተመለከተ አራት አመለካከቶች ቀርበዋል::

1. አይሁዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው መቅደሱን እንዲጠግኑ ቂርስ በ538 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ያስነገረው አዋጅ÷ (2ዜና

መዋዕል 36:22-23፤ ዕዝራ 6:1-5)።

18ኛ ጥያቄ:- ስለ ቂሮስ ዓዋጅ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት።
ዕዝራ 1:1-4 እነዚህ ጥቅሶች የሚያመለክቱት
የኢየሩሳሌምን ከተማ መገንባት ነው ወይስ
የመቅደሱን?

ምንም እንኳ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህ ዓዋጅ በዳን.9:25 የተነገረው እንደሆነ ቢያስቡም ቂሮስ ያስነገረው ዓዋጅ ግን ቤተ መቅደሱን እንጂ ከተማይቱን የሚመለከት አልነበረም።

2. ቂሮስ ያወጣውን ዓዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ ዳርዮስ ያስነገረው ዓዋጅ፤ (ዕዝራ 6:6-12)። ይህን አመለካከት የሚቀበሉ በጣም ጥቂት ምሁራን ናቸው።

3. ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ አርጤክስስ ያስነገረው አዋጅ፤ (ዕዝራ 7:11-26)። ይህም የሆነው በ457 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር።

4. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ የኢየሩሳሌምን ቅጥርና ደጆች እንዲሠራ አርጤክስስ የሰጠው ፈቃድ (ነህ.2:1-8)። ይህም የሆነው በ445 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። አንዳንድ ምሁራን ግን የኢየሩሳሌም ቅጥር እንዲሠራ ምንም የተነገረ ዓዋጅ ስለሌለ ይህ አመለካከት ትክክል ሊሆን እንደማይችል ይናገራሉ። ነህምያ የኢየሩሳሌምን ግንቦች እንዲሠራ ፈቃድ ተሰጠው እንጂ ምንም ዓዋጅ አልተነገረም። ዕዝራ 4:12-21 እና 9:9 በመጥቀስ ኢየሩሳሌም እንደገና ተሠርታ እንደነበር ይናገራሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ጥቅሶች የኢየሩሳሌም ከተማን እንደገና መሠረት በግልጽ የሚያመለክቱ አይደሉም። ከመጽሐፈ ነህምያ እንደምንረዳው ከሆነ፥ ዕዝራ ከተመለሰ ከአሥራ ሦስት ዓመት በኋላ እንኳ የኢየሩሳሌም ቅጥር አለመሠራቱን ነው። ስለዚህም ከሌሎቹ አመለካከቶች ይልቅ ሰባው ሱባዔ የሚጀምረው ከዚህ ላይ ነው ማለት የሚሻል ይመስለናል።

19ኛ ጥያቄ:- ነህ.2:11-20 አንብብ። ነህምያ ኢየሩሳሌምን በጎበኘበት
ወቅት ስለ ከተማይቱ የሰጠው ገለጻ ምንድነው?

የመጀመሪያውን የሱባዔ ክፍል ማለትም ስድሳ ዘጠኙን ሱባዔ ለምን እግዚአብሔር ለሁለት እንደከፈላቸው እርግጠኛ አይደለንም። ሕዝቡ የኢየሩሳሌምን ከተማ እንደገና መሥረት፥ መንገዶቸዋንና አደባባዮቾዋን መጠገን የጀመሩበት ወቅት በመጀመሪያው የ49 ዓመታት ክፍለ ጊዜ (7 X 7) ነበር። «በጭንቀት ዘመን ትሠራለች» የሚለው ቃል ከተማይቱን ሲሠሩ ዕዝራና ነህምያ ስለደረሰባቸው ችግር የሚያመለክት ነው።

ሁለተኛው ክፍል (መደብ) 62 ሱባዔን ይዞአል። ይህም በአጠቃላይ 434 ዓመት መሆኑ ነው። አንዳንድ ምሁረን ከ445 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ተነሥተን 483 ዓመት ብንቆጥር (ማለትም 69 ሱባዔዎች) ወደ 32 ዓ.ም. እንደርሳለን። ይህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገደለበት ዓመት ነው። ይሁን እንጂ ጌታ የሞተው በየትኛው ዓመት እንደሆነ እርግጠኛ ሆነን ለመናገር ያዳግተናል። ይሁን እንጂ «አለቃና መሢሁ» ተብሎ የተጠራው ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በ69ኛው ሱባዔ መጨረሻ ላይ መሆኑን እናውቃለን።

«መሢህ ወይም የተቀባው አለቃው» የሚለው ቃል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት ካህናት፥ ነቢያትና ነገሥታት በዘይት ይቀቡ ነበር። በኋላ ግን አይሁዳውያን ይህ «የተቀባው ወይም መሢህ» የሚለውን ቃል በመጨረሻ የሚመጣውን የእስራኤል ንጉሥ ለማመልከት ብቻ ይጠቀሙበት ጀመር። ይህ የዳንኤል ትንቢት ፍጻሜውን ያገኘው በመሢሁ በኢየሱስ (በግሪኩ ክርስቶስ) መወለድ ነው። የመሢሁም መወለድ ወደ 69ኛው ሱባዔ መጨረሻ ያደርሰናል።

ስድሳ ዘጠኙ ሱባዔ ከተፈጸመ በኋላና ሰባኛው ሱባዔ ከመጀመሩ በፊት ሁለት ሁኔታዎች እንደሚከናወኑ ተነግሮአል። የመጀመሪያው መሢሁ እንደሚገደል ነበር። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን ሞት በግልጽ የሚያመለክት ነው። «በእርሱ ዘንድ ምንም የለም» የሚለውን ቃል ለመተርጐም አስቸጋሪ ነው። ምናልባትም መሢህ በእስራኤል ላይ የመንገሥን ሥልጣን አለመቀበሉን የሚያመለክት ይሆናል። በጣም የሚያስገርመው ግን ከመወለዱ ከ500 ዓመት በፊት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መጀመሪያ መምጣትና መሞት ትንቢት መነገሩ ነው። እንደዚህ ዓይነት ትንቢቶች በትክክል ሲፈጸሙ የምናየው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው።

ሁለተኛው:- የኢየሩሳሌም ከተማና መቅደሱ ይፈርሳሉ። ይህንንም የሚያደርገው «የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ» እንደሆነ ተገልጾአል። ይህ «የሚመጣው አለቃ» የተባለለት መሢህ ሳይሆን ሌላ መሪ ነው። ብዙ ምሁረን እንደሚስማሙበት ይህ ክፍል የሚያመለክተው ስለሮማውያን ነው። በ70 ዓ.ም. በቲቶ ቬስፓሲአኑስ የሚመራው የሮም ሠራዊት ከተማይቱንና መቅደሱን አፈረረሰ። ከዚያ ወዲህ እስከ ዛሬ ድረስ ምንም መቅደስ አልተሠራም። በሌላ አነጋገር የሌላ አዲስ ቤተ መቅደስ መሠረትንና፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ ትንሽ ቀደም ብሎ የዚህን ቤተ መቅደስ መፍረስ የሚያመለክት ትንቢት ሊሆን ይችላል። በዚህም መልኩ ይህ ትንቢት ስለ ሁለት የተለያዩ ትንቢቶች ፍጻሜ ያመለክታል።

በዳንኤል 9:26 ላይ «ፍጻሜውም» የሚለው ቃል ስለ ምን ፍጻሜ እንደሚያመለክት እርግጠኛ አይደለንም። ይህ ፍጻሜ እንደጐርፍ ፈጥኖ

እንደሚመጣ ግን ተገልጾአል። ምናልባትም በ70 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ ስለደረሰው ጥፋት የሚያመለክት ይሆናል። ወይም ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ስለሚመጣው ጦርነት የሚያመለክት ትንቢትም ሊሆን ይችላል። ከኢየሩሳሌም ጥፋት አንሥቶ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤል ያለው ዓላማ እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ ጦርነትና ጥፋት እንደሚኖር ግልጽ ነው።

20ኛ ጥያቄ:- ከ70 ዓ.ም. ወዲህ የዓለም ታሪክ «ጦርነትና ጥፋት» የሞላበት መሆኑን የሚያመለክቱ ነገሮች ምንድናቸው? አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ።

በመጨረሻም ይህ ሁሉ እንደተወሰነ ወይም እንደተቀጠረ ተነግሮናል። እግዚአብሔር የወሰነው በመሆኑ በጊዜው ይፈጸማል። የዓለማችን የወደፊት ሁኔታ ሁሉ በእግዚአብሔር ተወስኖአል፤ ሁኔታዎቹን ሁሉ የሚቆጣጠረውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። ጌታ ይመስገን!

አረተኛ ቀን ክፍል ሦስት:- ዳንኤል 9:27

## ጥያቄዎች

21ኛ ጥያቄ:- «እርሱ» የሚለው ቃል ማንን የሚያመለክት ይመስልሃል?
22ኛ ጥያቄ:- «ብዙ ሰዎች» የተባሉት እነማን ናቸው?
23ኛ ጥያቄ:- በመጨረሻው ሰባት አጋማሽ ላይ ምን ይሆናል?
24ኛ ጥያቄ:- ዳን.9:27 የመጨረሻው ክፍል የሚያመለክተውን ነገር በራስህ ቃላት ለመግለጽ ሞክር።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ትናንትና የሰባውን ሱባዔ ሁለት ምድቦች (ክፍሎች) አጥንተናል። የመጀመሪያው 49 ዓመት ከነህምያ ዘመን አንሥቶ ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ መገንባት የሚናገር ሊሆን እንደሚችል ተመልክተናል። ሁለተኛው 434 ዓመት ኢየሱስ ክርስቶስ በመጀመሪያ ወደመጣበት ዘመን ያደርሰናል። ዛሬ ደግሞ 7 ዓመትን ስለያዘው የመጨረሻው ሱባዔ እንመለከታለን። ምንም እንኳ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በመጀመሪያ 69 ሱባዔ ዋና ዋና ሐሳብ ላይ ቢስማሙም፥ ስለ ሰባኛው ሱባዔ ግን ብዙ የተለያየ አመለካከት አላቸው።

ዋናው ጥያቄ:- «ሰባው ሱባዔ በቅደም ተከተል አማካይነት የሚፈጸም ነው ወይስ በስድሳ ዘጠነኛውና በሰባኛው ሱባዔ መጀመሪያ መካከል የጊዜ

ክፍተት አለ?» የሚል ነው። አንዳንድ ምሁረን ሰባው ሱባዔ ያለምንም ክፍተት ቀጸም ተከተሉን ተከትሎ የሚጓዝ ነው ይላሉ። ይህም ማለት ስድሳ ዘጠነኛው ሱባዔ ሲያልቅ ሰባኛው ይጀምረል ማለት ነው። ይህንን አመለካከት የሚከተሉ ሰዎች 490ውን ዓመት ቃል በቃል መውሰድ እንደሌለብን ይናገረሉ። እንደዚህ ከሆነ ሰባኛው ሱባዔ የሚፈጸመው ኢየሱስ ከሞተ ከሰባት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ ስለ ሰባው ሱባዔ የተነገረውን ትንቢት የሚመስል ኢየሱስ ከሞት ከሰባት ዓመት በኋላ የተፈጸመ ነገር የለም። ስለዚህም ሰባኛው ሱባዔ የተፈጸመው በ70 ዓ.ም. ቲቶ ኢየሩሳሌምን በጸመሰሰበት ጊዜ ነው ይላሉ። ይህም ኢየሱስ ከሞተ ከ38 ዓመት በኋላ ነው ማለት ነው። በዳን.9:26 የተነገረው ሁኔታ የሚፈጸመው በሰባኛው ሳምንት ውስጥ ነው።




ስዕል 6

ሰባው ሱባዔ ቃል በቃል መተርጐም እንዳለበት የሚያምኑት ሌሎች ምሁረን ደግሞ በስድሳ ዘጠነኛው ሱባዔና በሰባኛው ሱባዔ መካከል የጊዜ ክፍተት እንዳለ ይናገረሉ። በዚህ ጥቅስ መሠረት በታሪክ ውስጥ የተፈጸመ ይህ ነው የምንለው ሁኔታ ባለመኖሩ ምናልባት ይህ ክፍል ስለ ወደፊቱ የሚያመለክት ትንቢት መሆን አለበት ይላሉ።




* በቤተ ክርስቲያን ዕድሜ ውስጥ ይህ የጊዜ ልዩነት ምን ያህል ዓመት እንደነበር አይታወቅም።

በትንቢት ውስጥ «የጊዜ ክፍተት ወይም ልዩነት» ያልተለመደ
አይደለም። ስለ ኢየሱስ መጀመሪያ መምጣትና ዳግም መመለስ በተነ
ትንቢቶች ውስጥ የጊዜ ክፍተት ይታያል፤ ይሁን እንጂ ትንቢቶች በ
እስኪፈጸሙ ድረስ በመካከላቸው ረጅም የጊዜ ክፍተት መኖሩን
አያሳዩም።

25ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ተመልከት። ኢዩ.2:
እና የሐዋ/ሥራ 2:16-21። እነዚህ ጥቅሶች በ
ትንቢትና ትንቢቱ በተፈጸመበት መካከል ያለውን የጊ
የሚያመለክቱት እንዴት ነው?

እንደዚህ አመለካከት ከ69 ሱባዔ በኋላ መሢሁ ተወግቶ ይሞ
አይሁዳውያን መሢህን ስለናቁትና ስለገደሉት ለጊዜውም ቢሆን እግዚ
ለአይሁዳውያን ያለው እቅድ ተቋርጦ ነበር። በዚህም ምክንያት
ክርስቲያን ዘመን» ተጀመረ። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ለአይሁ
እቅድ አለው÷ (ሮሜ 11:1-27 ተመልከት)። እግዚአብሔር አ
ወደ ቤተሰቡ የሚጠረበት «የአሕዛብ ዘመን» ሲፈጸም እግዚአ
ለአይሁዳውያን ያለውን እቅድ ይፈጽማል፤ ሰባኛው ሱባዔ የሚጀም
ያን ጊዜ ነው። ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት ባሉት በመጨረሻዎቹ
ዓመታት አይሁዳውያን ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ። በታላቁ የመከራ
ጊዜ አይሁዳውያን ኢየሱስ ክርስቶስን ይቀበላሉ። ከዚያ በኋላ ዘላ
መንግሥቱን ለመመሥረት ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለሳል።

የዚህ ጽሑፍ አቀረቢ እንደሚያምኑበት ከሆነ÷ እነዚህ ትንቢቶ
በሙሉ የሚፈጸሙት ወደ ፊት እንደሆነ ማሰቡ መልካም ይመስለኛል

ምንም እንኳ በቁጥር 27 ላይ «እርሱም» የሚለው ቃል እ
ቃል ኪዳን ስለፈጸመው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገር እንደሆነ የ
እምነት ቢሆንም ትንቢቱ የሚያመለክተው ወደፊት ስለሚነሣው መሪ
ማሰቡ የሚሻል ሳይሆን አይቀርም። ይህ «እርሱም» የሚለው ቃ
ክርስቶስ ተቃዋሚ ወይም ደግሞ ስለ ታናሹ ቀንድ (ዳንኤል 7)÷
ደግሞ ስለ ዓመፅ ሰው (2ተሰ.2:3-4)÷ ወይም ደግሞ ስለ አው
የሚገልጽ (ራዕይ 13) ሊሆን ይችላል።

ወደፊት የሚነሣው ክፉ የዓለም መሪ የሚከተሉትን ነገሮች ያደ

1. ከብዙዎች ጋር ቃል ኪዳን ያጸናል። ይህ ክፍል የሚና
አይሁዳውያን በመሆኑ (ሕዝብህ ቁ.24) «ብዙዎች» የሚለውም
እነርሱን የሚመለከት ሳይሆን አይቀርም። ይህ ክፉ መሪ በአንዳንድ
ከአይሁዳውያን ጋር ቃል ኪዳን ያጸናል። ምናልባትም ይህ ቃል ኪ
መቅደሳቸውን እንዲሠሩና እንደቀድሞው ሥርዓት መሥዋዕት እንዲያቀ

ሊሆን ይችላል።

2. በሰባኛው ሱባዔ አጋማሽ ማለትም ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ (ይህ ጊዜ በራዕይ 11:1-3፤ 12:6፤ 14 ላይ 42 ወር 1260 ቀን ተብሎ ተጠርቶአል።) በሆነ መንገድ ቃል ኪዳኑ ይፈርሳል፤ መሥዋዕቱም ይቀረል። አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ ሞት የመሥዋዕቱ ሥርዓት ሁሉ ስለተፈጸመ ከእንግዲህ ወዲህ ቤተ መቅደሱ አይሠረም። መሥዋዕትም አይቀርብም የሚል መከረከሪያ ሐሳብ ያቀርባሉ።

26ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:- ዕብ.9:25-26፤ 10:8-9። ስለ መሥዋዕት ምን ይላሉ?

ምንም እንኳ የዕብራውያን መጽሐፍ የእንስሳት መሥዋዕት ከኃጢአት ሊያነጻ ባለመቻሉ እንደሚወገድ ቢያመለክትም÷ ወደ ፊት መቅደስ አይኖርም፤ መሥዋዕትም አይቀርብም ማለቱ አይደለም። ወደፊት በሚሠረው መቅደስ ውስጥ መሥዋዕት የሚያቀርቡት የሚያምኑት አይሁዶች ይሁኑ የማያምኑት አይሁዶች አልተገለጸም። ከሕዝቅኤል ምዕራፍ 40 እንደምንመለከተው ግን ሌላ መቅደስ እንደሚሠረ የሚያጠረጥር አይደለም።

የትንቢተ ዳንኤል 9:27 የመጨረሻ ክፍል ብዙም ግልጽ አይደለም። ባልታወቀ ሁኔታ መቅደሱ ስለሚረክስ እግዚአብሔርን በዚያ ሥፍረ ማምለክ የሚቋረጥ ይመስላል። ምናልባትም ጣዖታት የሚመለኩበት ወይም ደግሞ የክርስቶስ ተቃዋሚው ራሱ የሚመለክበት ሥፍረ ይሆን ይሆናል። ስለዚህ ሁኔታ ዳን.11:31 ስናጠና በሰፊው እንመለከታለን። ምንም እንኳ ይህ ትንቢት በከፊል በአንጦኪዮስ ኢጲፋንዮስ ዘመን ቢፈጸምም ሙሉ በሙሉ የሚፈጸመው ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ በሚመጣበት ወቀት ነው፤ (ራዕይ 13:1-7)። በማቴ.24:15-26 ላይ ይህ ሁኔታ የሚፈጸመው እርሱ ከምምጣቱ ጥቂት ቀደም ብሎ እንደሆነ ኢየሱስ ራሱ ተናግሮአል።

የወደፊቱ ሁኔታ ምንም ያህል ከፉ ቢሆንም ፍጻሚው ተወስኖአል። ዛሬ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የሚዋጉ የዓመፀኛ መሪዎች መንግሥት የሚያከትምበት ወቀት ይመጣል÷ ይፈርድባቸዋል። በሕዝቡ ላይና በተቀደሰቸው ከተማው ላይ የሚሆነውን ሁሉ እግዚአብሔር ራሱ ይቆጣጠረል። ፍጻሚው በእግዚአብሔር የተወሰነ በመሆኑም ዳንኤል መጨነቅ የለበትም።

ብዙ ሰዎች የምንኖረው በመጨረሻው ዘመን በመሆኑ በቅርቡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመለስ ይናገራሉ። ምንም እንኳ ቀኑንና ዘመኑን ማወቅ ለእኛ ባይሰጠንም (የሐዋ/ሥረ 1:6-7) ብዙ ሁኔታዎች ክርስቶስ በቅርቡ እንደሚመልስ ያመለክታሉ። አይሁዳውያን ወደ ጳለስጢና እየተመለሱ ናቸው። የዓለም ሕዝብም በሚቀጥሉት የመከረ ዓመታት የሚመረውን መሪ የሚጠብቅ

ይመስላል። ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመናችን ይመጣ ይሆን? ሁኔታዎቹ ግን በዘመናችን እንደሚመለስ ያመለክታሉ።

27ኛ ጥያቄ:- እኛ ክርስቲያኖች በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸንም ምፅዓት መዘጋጀት እንደሚገባን ዘርዝር።

አምስተኛ <u>ቀን</u>:- ትምህርቱን ከልስ።

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ በቤተ ክርስቲያንህ ያሉትን ሰዎች ትንቢት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ሊያጽናናቸው እንደሚችል ግለጽ።
2/ በተለይ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉት የብሉይና የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ምንድናቸው?

ለ. 1/ ስለ ዳን.9:24-27 ከተሰጠው ገለጻ የትኛው አመለካከት ትክክል ይመስልሃል? ለምን?
2/ በዚህ መጽሐፍ ከተገለጸው ሌላ እነዚህን ትንቢቶች የምትረዳበት የተለየ መንገድ አለን?

ሐ. 1/ ዳን.9:24 መሠረት በማድረግ በስድስቱ በረከቶች ላይ ውይይት አድርጉ። ትርጉማቸው ምንድነው?
2/ እነዚህ ስድስት በረከቶች ዛሬ እንዴት ሊያጽናኑን ይችላሉ?

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥራ ስድስት

## ዳን.10:1-11:1

### የመጀመሪያ ቀን

የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፤ እነሆም፥

ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት:: (ዳን.10:13)

እግዚአብሔር በምድር የሚደረጉትን ሁኔታዎች ሁሉ እንዴት እንደሚቆጣጠር ከዳንኤል መጽሐፍ ጸጋግመን ስንመለከት ነበር:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን እኛ ሰዎች የማንገነዘበው ታላቅ ውጊያ በሰማያዊ ሥፍራ በመካሄድ ላይ መሆኑን ይናገረል:: ይህ÷ እግዚአብሔርና መላእክቱ ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ጋር የሚያደርጉት ውጊያ ምድረዊ ሁኔታዎችንም ይነካል:: እግዚአብሔር ከሰይጣን ይልቅ ታላቅ እንደሆነና በመጨረሻም እንደሚያጠፋው ብናውቅም ሰይጣን ዛሬም ቢሆን በዚህ ምድር ላይ ታላቅ ኃይል አለው::

ለዳንኤል ራዕይ እንዲሰጠው ከመጣው መልአክ በሰማይ ስለሚደረገው ውጊያ በመጠኑም ቢሆን ሰምተናል:: ሰይጣን ምን ያህል ኃይለኛ መሆኑንም ተመልክተናል:: «የፋርስ መንግሥት አለቃ» የሚለው ቃል ሰይጣንና አጋንንቱን ያመለክታል፤ ሰይጣንና አጋንንቱ በምድረዊ መንግሥት ላይ የተወሰነ ሥልጣን አላቸው:: ይህ «አለቃ» የተባለው ምድረዊ «አለቃ» ሳይሆን የፋርስ ንጉሥ ከነበረው ሰው በስተጀርባ ሆኖ የሚሠራ አጋንንታዊ ኃይል ነው:: «የፋርስ መንግሥት አለቃ» የተባለውም በዚህ ምክንያት ነው:: ሰዎች ሁሉ ከእርሱ ቁጥጥር ሥር እንዳይወጡ ሰይጣን በተለያዩ ሀገሮች የሚደረገውን ሁኔታ መቆጣጠር ይፈልጋል:: እግዚአብሔር ለዚያ ሕዝብ ያለውንም እቅድ ማፍረስ ይፈልጋል::

1ኛ ጥያቄ:- ዮሐ.12:31 እና 2ቆሮ.4:4 አንብብ:: በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ሰይጣን ምን ተብሎአል?

በዳንኤል 10:13 ሰይጣን ምን ያህል ብርቱ እንደሆነ እንመለከታለን:: አንዱ የእግዚአብሔር መልአክ ራሱ እንኳ ሚካኤል የሚባለው ሌላ መልአክ ባይረዳው ኖሮ ሊቋቋመው ባልቻለም ነበር÷ (ይሁዳ 1:8-9 ተመልከት):: ስለሰይጣን እንደሚገባ ለማወቅ ምናልባት አራት ጥያቄዎችን ማቅረብ አስፈላጊ ሳይሆን አይቀርም::

1. ሰይጣን ማነው? ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንረዳው ሰይጣን እግዚአብሔር ከፈጠረቸው ታላላቅ መላእክት አንዱ ነበር:: ይሁን እንጂ በትዕቢት ተነሣስቶ እንደ እግዚአብሔር ታላቅ ለመሆን በመፈለጉ ኃጢአት አደረገ፤ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ትልቁ የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑን በግልጽ እናያለን::

2ኛ ጥያቄ:- ሕዝ.28:11-17 አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች የሰይጣንን መውደቅ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው የሚያመለክቱት?

ምንም እንኳ እነዚህና በኢሳ.14:12-15 ያሉት ጥቅሶች ስለ ባቢሎንና ስለ ጢሮስ ነገሥታት ትዕቢት የሚያመለክቱ ቢሆኑም በተጨማሪ ስለ ሰይጣን ውድቀት እንደሚያመለክቱ ብዙ ክርስቲያኖች ይናገራሉ:: ሰይጣን ከሰማይ በተጣለበት ጊዜ ታላቅ ዓመፅ ቀስቅሶ÷ ብዙ መላእክትንም ይዞ ነው የወደቀው::

2. የሰይጣን እቅድ ምንድነው? ከወደቀበት ጊዜ አንሥቶ ሰይጣን የእግዚአብሔርን እቅድ ለማፍረስ ይፈልጋል:: አዳምና ሔዋንን በኃጢአት በመፈተኑ የእግዚአብሔርን ውብ ተፈጥሮ አበላሸ:: በዚህ ምድር ላይ ታላቅ ኃይል ስላለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ «የዚህ ዓለም ገዢ» ተባለ:: ዛሬም ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ለመሆንና የሚቆጣጠረው ሰፊ ግዛት እንዲኖረው ይፈልጋል:: የእግዚአብሔር ሕዝብ በኃጢአት እንዲወድቁና ቤተ ክርስቲያን እንድትደክም የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል:: በራዕይ መጽሐፍ ላይ የእግዚአብሔርን እቅድ ለማጨናገፍ ሰይጣን የሚያደርገውን የመጨረሻ ሙከራ እንመለከታለን:: እግዚአብሔር ግን ሰይጣንን በመጨረሻ ያሸንፈዋል::

3. ሰይጣን የተሸነፈው እንዴት ነው? ምንም እንኳ ታላቅ ኃይል እንዳለው የታወቀ ቢሆንም÷ ሰይጣን በክርስቶስ ተሸንፎአል:: በሌላ አነጋገር ሰይጣን በእኛ ላይ ያለው ኃይል ተሰብሮአል:: (ቆላ.2:13-15 ተመልከት::) እዚህ ላይ አለቆችና ሥልጣናት የሚላቸው ሰይጣንና አጋንንቱን ነው:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ ከሰይጣን እሥራት ነፃ ወጣን::

4ኛ ጥያቄ:- ራዕይ 20:1-10 አንብብ:: በዘመናት መጨረሻ ሰይጣን ምን ይደረጋል?

4. ክርስቲያን በሰይጣን ኃይል <u>ላይ</u> ያለው ሥልጣን ምንድነው? ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ አጋንንትን በማውጣት ሥልጣኑን አሳይቶአል:: ለክርስቲያኖችም በስሙ አጋንንትን እንዲያወጡ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል:: ይህም ማለት የኢየሱስን ሥልጣንና ኃይል በመጠቀም በሰዎች ውስጥ ያለውን አጋንንት ውጣ ብለን ማዘዝ እንችላለን ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ቃል ስንቃወመው ሰይጣን እንደሚርቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ (ያዕ.4:7፤ 1ጴጥ.5:8-9):: ይሁን እንጂ ሰይጣንን ከመቃወማችን በፊት እግዚአብሔር ባዘጋጀልን መሣሪያዎች መዘጋጀት እንደሚገባ ጳውሎስ ያስጠነቅቃል፤ (ኤፌ.6:10-18)::

ይህን ከተረዳን ዓለም ለምን እየከፋች እንደምትሄድና ችግሮች ለምን እንደሚበዙ መገንዘብ አያዳግተንም:: ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ የሰይጣን መንግሥት ነው:: እኛ ክርስቲያኖች ትልቅ ዋስትና አለን:: ይኸውም እግዚአብሔር ከሰይጣን ይልቅ ታላቅ መሆኑ ነው:: ምንም እንኳ ዛሬ በሰማይም ሆነ በምድር ዊጊያ እየተካሄደ ቢሆንም እግዚአብሔር ስለመንግሥታት ያለው እቅድ ግን አይሻርም:: ሰይጣን ተቀጥቅጦአል፤ አንድ ቀን ደግሞ

እስከ መጨረሻው እንደሚደመሰስ እርግጠኞች መሆን አለብን።

5ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ክርስቲያን በሰይጣን ላይ ያለውን ኃይል በምን ዓይነት ሁኔታ ነው በቤተ ክርስቲያንህ ተገልጾ ያየኸው?
ለ/ ሰይጣንን ድል እንዲያደርግ ክርስቲያን በመሣሪያዎቹ የሚዘጋጀው እንዴት ነው?
ሐ/ ብዙ ክርስቲያኖች «በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ የወደቁት ለምን ይመስልሃል?

6ኛ ጥያቄ:- ዳን.10-11:1 አንብብ።
ሀ/ ዳንኤል ራዕዩን የተቀበለው የት ሆኖ ነው?
ለ/ ራዕዩን ሲያገኝ ዳንኤል ምን እያደረገ ነበር?
ሐ/ ራዕዩን በሚያይበት ጊዜ ዳንኤል ምን እንደሆነ በራስህ ቃላት ግለጽ።

## ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 10:1-9

### ጥያቄዎች

7ኛ ጥያቄ:- በማን መንግሥትና በዘመኑ መንግሥቱ በስንተኛው ዓመት ነበር ዳንኤል ይህን ራዕይ የተቀበለው?

8ኛ ጥያቄ:- ለራዕዩ ራሱን ለማዘጋጀት ዳንኤል ምን አደረገ?

9ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል በራዕዩ ስላየው «ሰው» በራስህ ቃላት ግለጽ።

10ኛ ጥያቄ:- ከዳንኤል ጋር በነበሩት ሰዎች ላይ ራዕዩን ያስከተለው ውጤት ምን ነበር?

### የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

በትንቢተ ዳንኤል ከምዕራፍ 10-12 ያለው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ የመጨረሻ ራዕይ ነው። ዳንኤል 10 የዚህ ራዕይ መግቢያ ነው፤ ዳንኤል 11-12:4 ደግሞ ራዕዩ ራሱ ሲሆን÷ ዳንኤል 12:5-13 ደግሞ የራዕዩ መደምደሚያ ነው። በዚህ ሳምንት በዳንኤል 10:1-11:1 ያለውን የራዕዩን መግቢያ እናጠናለን።

እንደ ትንቢተ ዳንኤል 9:1-23 ሁሉ ትንቢተ ዳንኤል 10 ራዕዩን በተቀበለበት ወቅት ስለነበረው ሁኔታ ይገልጻል። በብዙ መንገድ እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ተመሳሳይነት አላቸው። ሁለቱም ራዕዮች የጸምና ጸሎት ውጤት ናቸው። ሁለቱም ወደፊት በአይሁዳውያን ላይ ምን እንደሚሆን ያመለክታሉ።

ዳንኤል 10:1 ነቢዩ ራዕዩን የተቀበለበትን ዓመት ይገልጻል:: ራዕዩን ያገኘው ቂሮስ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት ነበር:: ይህም ማለት በዳንኤል 1 ያለውን ራዕይ የተቀበለው በ536 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ማለትም በዳንኤል 9 ካለው ራዕይ ከሁለት ዓመት በኋላ ነበር ማለት ነው:: ከምዕራፍ 10-12 ያለው ራዕይ በዳንኤል ሕይወት የተፈጸመ የመጨረሻ ሁኔታ ሲሆን፥ በዚያን ጊዜ በምርኮኛነት ከኢየሩሳሌም ወደ ባቢሎን ከተወሰደቻም 72 ዓመት ሆኖ ነበር::

ዳንኤል 10:1 ስለሚመጣው ራዕይ ፍንጭ ይሰጣል:: ራዕዩ ስለ «ታላቅ ጦርነት» ነው:: ራዕዩን ማጥናት ስንጀምር ደግሞ የሚናገረው ስለ ብዙ ተከታታይ ጦርነቶች እንደሆነ እንረዳለን:: ዳንኤል መልእክቱ ወይም ትንቢቱ የታመነና እውነተኛ መሆኑን ያረጋግጣል:: ከእግዚአብሔር የተሰጠ በመሆኑ እውነተኛ ነው:: የወደፊቱን ሁኔታዎች በሙሉ የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ራሱ ስለሆነ እውነተኛነቱ አያጠራጥርም::

ምክንያቱን ባናውቅም ይህ ራዕይ ከመሰጠቱ በፊት ዳንኤል ለተወሰነ ጊዜ ሲያዝንና ሲተክዝ ነበር:: የንጉሡ አገልጋይ ስለነበር ማለፊያ ምግብ ቢዘጋጅለትም ለተወሰነ ጊዜ አይበላም ነበር:: ሥጋ አልበላም ወይም አልጠጣም፤ ቀባትም አልተቀባም:: ለትካዜውና ለኃዘኑ ምክንያት የሆነው ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ሀገረቸው የተመለሱት አይሁዳውያን በችግር ላይ መሆናቸውን በመስማቱ እንደሆነ አንዳንድ ሰዎች ይገምታሉ:: ወይም አይሁዳውያን ወደሀገረቸው ከተመለሱ በኋላ የተጀመረው የቤተ መቅደሱ የእድሳት ሥራ ተቋርጦ ይሆናል እናውቃም፥ (ዕዝራ 4):: ስለዚህም ይህን ራዕይ በተቀበለበት ወቅት ዳንኤል ተስፋ እንዳደረገው ቤተ መቅደሱ አልተሠረም ነበር:: አሁን መልካሙን ምግብና ሥጋ ባለመብላት፥ ወይን ጠ ባለመጠጣት፥ ዘይትም ባለመቀባት ዳንኤል የልቡን ሐዘንና ትካዜ ለመግለጽ ፈለገ:: በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ይጸልይ ነበር፤ ዳንኤል 10:12 እንደሚነገረን እግዚአብሔር መልስ የሰጠው ጸሎቱን ከሰማ በኋላ ነው::

በትንቢተ ዳንኤል 10:4 እንደምናየው ራዕዩን የተቀበለው በመጀመሪያው ወር ከወሩም በ24ኛው ቀን ነበር:: ዳንኤል ይህን የሚነግረን የመጀመሪያው ወር ለአይሁዳውያን ልዩ ትርጉም ስለነበረው ነው አዲስ ዓመት ሲመጣ ከፍተኛ የጾስታና የጽግስ ጊዜ የማድረግ ልማድ አላቸው:: ፋሲካ የሚውለው በመጀመሪያው ወር አሥረ አረተኛ ቀን ላይ ነበር:: ይህ ቀን ከግብፅ ባርነት የወጡበት ቀን ሲሆን፥ ልዩ በሆነ ሁኔታ እንዲያከብሩት እግዚአብሔር ራሱ አዝዞአቸዋል:: (ዘፀ.12:1-13 እና ዘሌዋውያን 23:4-8 ተመልከት::)

11ኛ ጥያቄ:- ፋሲካ እና የቂጣ በዓል የሚሉትን ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ ተመልከት:: እነዚህ በዓሎች

የሚከበሩት በየትኛው ወር ነው? ለምን ያህል ቀን ነበር የሚከበሩት?

ፋሲካ የሚከበረው ለአንድ ቀን ብቻ ነው:: ወዲያውኑ ደግሞ የቂጣ በዓል በተከታታይ ለ7 ቀን ይከበረል:: በዚህ ጊዜ እስረኤላውያን የቦካ ቂጣ (እንጀረ) አይበሉም፤ ይህም ከግብፅ ምድር በችኰላ መውጣታቸውን ለማመልከት ነው:: የቂጣ በዓል የመጨረሻ ቀን የሚሆነው በመጀመሪያው ወር ሃያ አንደኛ ቀን ሲሆን ይህም ዳንኤል ረዕዩን ከመቀበሉ ጥቂት ቀን ቀደም ብሎ ነበር ማለት ነው::

ዳንኤል የነበረበት የባቢሎን ከተማ የምትገኘው በኤፍረጥስ ወንዝ ላይ ነው:: በመጀመሪያው ወር ሃያ አረተኛ ቀን ላይ ግን ዳንኤል በጤግሮስ ወንዝ አካባቢ ነበር:: የጤግሮስ ወንዝ ከኤፍረጥስ ወንዝ 43 ኪሎ ሜትር ይርቃል:: ይህንን ሰው መሳይ ፍጡር ያየው በጽንገት በመንዝ ላይ እያለ ነበር:: ዳንኤል ከሚሰጠን ገለጻ ግን ተረ ሰው እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል:: ይህ ሰው ማነው? ማንነቱን በትክክል ማወቅ አንችልም:: አንዳንድ ምሁረን እንደ ገብርኤልና ሚካኤል ያለ ሌላ ታላቅ መልአክ እንደሆነ ይናገረሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ረሱን ሲገልጥ ነው ብለው ያምናሉ::

12ኛ ጥያቄ:- በዳንኤል 10:4-6 ያለውን ረዕይ ሕዝ.1:22-28 እና ረዕይ 1:12-17 ካለው ጋር አነፃፀር::

ሀ/ ረዕዮቹ የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

ለ/ ረዕዩን ያዩት የሦስቱም ሰዎች ሁኔታ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

በሕዝቅኤል ላይ ያለው ረዕይ ስለ እግዚአብሔር ሲሆን፥ በዮሐንስ ረዕይ ያለው ደግሞ ስለ ጌታ ኢየሱስ መሆኑን እርግጠኞች ነን:: በጣም ተመሳሳይ በመሆናቸውም በዳንኤል 10:4-6 ያለውም የረሱ የእግዚአብሔር ረዕይ እንደሆነ ብዙዎች ይናገረሉ::

ሦስቱም ረዕዮች የተሰጡት በምሳሌያዊ ቋንቋ መሆኑን መረዳት አለብን:: ረዕዩን ያዩት ሰዎች ስለ ረዕዩ ሊገልጹልን የሚችሉት ከዚህ በፊት ካዩት ምድረዊ ነገር ጋር በማገናዘብ ነው:: ሦስቱም ረዕዮች በጣም ታላቅ ከመሆናቸው የተነሣ ያዩዋቸው ሰዎች ሁሉ በፍርሃት ወድቀዋል::

በሦስቱም ረዕዮች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለመረዳት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተመልከት::

| ዳንኤል | ሕዝቅኤል | ዮሐንስ |
|---|---|---|
| እንደ ሰው | እንደ ሰው | እንደ ሰው ልጅ |
| ልብሱ - በፍታ (ናይለን) ወገቡን በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ | በዙፋኑ ተቀምጦ ነበር | ልብሱ - ረጅም ቀሚስ በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ |
| አካሉ - እንደ ብርሌ | ከወገቡም በላይ የሚያ ብለጨልጭ ወርቅ አምሳያ | ፀጉሩ - እንደ ጥጥ ነጭ |
| ፊቱ - እንደመብረቅ | ከወገቡም በታች እንደ እሳት አምሳያ | ዓይኖቹ - እንደ እሳት ነበልባል |
| ዓይኖቹ - እንደሚንበለበል ፋና | በዙሪያው ፀዳል ነበር | እግሮቹ - እንደጋለ ናስ |
| | ድምፁ - እንደ ታላቅ ሠራዊት ድምፅ | ድምፁ - እንደብዙ ውሆች ድምፅ |
| ክንዶቹና እግሮቹ - እንደጋለ ናስ | | ከዋክብት ይዞ ነበር |
| ድምፁ - እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ | | ከአፉ ሰይፍ ይወጣ ነበር |

በዚህ ራዕይ የምናያቸው ነገሮች ለዳንኤል ምን ያህል ምሳሌያዊ ነገር እንደነበሩ መገመት አንችልም። የበፍታ (ናይለን) ልብሶች ምን ጊዜም ነጭ ናቸው። ካህናትና መላእክት የሚለብሱት የዚህን ዓይነት ልብሶች ነበሩ፥ (ዘፀ.28:39-43፤ ሕዝ.9:2-10:7)። ነጭ የቅድስና ምልክት ነው። በወገባቸው የታጠቁት ወርቅ በጣም የጠረ ነበር፤ ምናልባትም አፌዝ ከሚባለው ሥፍራ ከሚገኘው ወርቅ ጋር ይመሳሰላል። አካላቸውን ከሚያንጸባርቅ ነገር ጋር ወይም ከቢረሌ ጋር አመሳስለውታል። ቢረሌ አንድ ዓይነት ዕንቁ ነው። ዓይኖቹ እንደ ፋና፥ እግሮቹና ክንዶቹ እንደሚ ያንጸባርቅ ናስ፥ ፊቱ በኃይል እንደምታበረ ፀሐይ ነበር። የራዕዩ ዓላማ በራዕይ የተገለጸለት ሰው ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ለዳንኤል ለማሳየት ነው። ምንም እንኳ መላእክት ተመሳሳይ ልብስ ለብሰው፥ በተመሳሳይ ሁኔታ ቢገለጹም፥ (ራዕይ 15:6) በብዙ ሁኔታ ይህ ዳንኤል በራዕይ ያየው ሰው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን አይቀርም።

አብረው የሚጓዙ ሰዎች ቢኖሩም ራዕዩን ያየው ዳንኤል ብቻ ነበር። ይሁን እንጂ አንድ ያልተለመደ ሁኔታ መፈጸሙን ስለተረዱ ፈርተው ሸሹ። ዳንኤልም ራዕዩን ሲያይ በጣም ፈራ። ኃይሉም ስለረቀው ወደ ምድር ወደቀ። በምድሩ ላይ ወድቆ እያለ «ሰውዬው» ተናገረው። ምን እንደተናገረ ግን አናውቅም። ነገር ግን ዳንኤል በከባድ እንቅልፍ ውስጥ እንዳለ ሰው ራሱን ሳተ።

አምላካችን እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ዳንኤል መጠነኛ ገለጻ ይሰጠናል። በፍርሃት ራሱን ሰጥቶ በምድር ላይ መውደቁ በጣም የሚገርም ነው። ዳንኤል፥ ሕዝቅኤል፥ ኢሳይያስና ዮሐንስ ያዩት ራዕይ በአእምሮአችን እንዲቀረጽ እግዚአብሔር ይፈልጋል። ኃጢአተኛነታችንን አውቀን ራሳችንን ዝቅ የምናደርገውም እግዚአብሔርን በዚህ ሁኔታ ስናስበው ነው። ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 10 ከእግዚአብሔር ታላቅነት ጋር ሲነፃፀር ሰው ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ያሳየናል።

13ኛ ጥያቄ:- እስቲ ለጥቂት ጊዜ ዳንኤል ስላየው ታላቅና አስፈሪ ራዕይ አሰላስል። እግዚአብሔርን ስለ ታላቅነቱ አመስግነው። በታላቁ አምላካችን ፊት ራስህን አዋርድ።

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 10:10-11:1

## ጥያቄዎች

14ኛ ጥያቄ:- ዳንኤልን የነካውና በእግሩ እንዲቆም ያደረገው የማን እጅ ይመስልሃል?

15ኛ ጥያቄ:- መልእክተኛው መልእክቱን ለዳንኤል ለመንገር መጀመሪያ
የተላከው መቼ ነበር?
16ኛ ጥያቄ:- መልእክተኛው ወዲያውኑ ወደ ዳንኤል እንዳይመጣ ያገደው
ማን ነበር?
17ኛ ጥያቄ:- መልእክቱን ለዳንኤል እንዲያደርስ መልእክተኛውን የረዳው
ማነው?
18ኛ ጥያቄ:- መልእክቱ የትኛውን ሕዝብ የሚመለከት ነበር?
19ኛ ጥያቄ:- መልእክተኛው ሁለት ጊዜ ዳንኤልን ምን በማለት ጠራው?
(ቁ.11፤ 19)
20ኛ ጥያቄ:- መልእክቱን ካደረሰ በኋላ ተመልሶ የሄደው ከማን ጋር
ለመዋጋት ነበር?
21ኛ ጥያቄ:- መልእክተኛውን በውጊያው የረዳው ማነው?
22ኛ ጥያቄ:- ዳርዮስ በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት ላይ መልእክተኛው
ምን አደረገ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ /ኮሜንታሪ/

ትናንትና በጾምና በጸሎቱ ምክንያት ዳንኤል ራዕይ እንዳገኘ ተመልክተናል:: በራዕዩም ያየው ሰው ነበር:: ይህ ሰው ማን እንደሆነ በትክክል ለማወቅ እንደማይቻልም ተመልክተናል:: ይህ ሰው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም ከታላላቅ መላእክት አንዱ ይሆናል::

ዳንኤል ራዕዩን ሲያይ ራሱን ስቶ በምድር ላይ ወደቀ:: በወደቀበት ቦታ አንድ እጅ ዳሰሰው:: የማን እጅ ይሆን? በጤግሮስ ወንዝ ዳርቻ ያየው ሰው እጅ ይሆን? ወይስ የሌላ መልአክ እጅ ይሆን? ከሁለት አንዱ ትክክል ይሆን ይሆናል? በራዕይ ያየው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለን የምናምን ከሆነ÷ የዳሰሰው እርሱ ራሱ ሊሆን ይችላል:: ይህ ወደ ዳንኤል የተላከው ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሆነ÷ ከሰይጣን ጋር በተደረገው ውጊያ ሚካኤል የተባለው መልአክ እንዲረዳው ባላስፈለገም ነበር:: እዚህ ላይ ዳንኤል በራዕይ ያያቸው ሁለት ሰዎች ናቸው ብሎ ማሰቡ ጥሩ ነው:: የመጀመሪያው:- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን÷ ሁለተኛው ደግሞ:- በፋርስና በግሪክ መንግሥት ላይ ሥልጣን ያለው መልአክ ሊሆን ይችላል::

ይህ እጅ (በኋላ ላይ «የሰው ልጅ የሚመስለው» ተብሎ የሚነገርለት) ዳንኤልን በዳሰሰው ጊዜ በመጀመሪያ በጉልበቱ ለመንበርከክ የሚችልበት ኃይል ሰጠው:: በኋላ ግን መልእክቱን ለመቀበል ቀጥ ብሎ በእግሩ ለመቆም ቻለ:: መልእክተኛውም ዳንኤል በእግዚአብሔር ፊት የተወደደ እንደሆነ ነገረው÷ (ዳን. 10:11፤ 19):: በዳንኤል 9:23 እንደተመለከትነው ሁሉ ዳንኤል ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ሕብረት የነበረው

ሰው ነበር። ይህን ታላቅ ራዕይ እግዚአብሔር የገለጸለትም ከዚህ ሕብረት የተነሣ ነበር።

መልአኩ ስለ እስራኤል ሕዝብ የወደፊት ሁኔታ እንዲነገረው የተላከው ዳንኤል መጾምና መጸለይ በጀመረበት ጊዜ እንደነበር ነግሮታል። በፋርስ አገር ውስጥ ይኖር ወደነበረው ወደ ዳንኤል በመምጣት ላይ ሳለ «የፋርስ መንግሥት አለቃ (ንጉሥ)» የሚባል ጠላት አጋጠመው።

ይህ መልእክተኛ መልአክ በመሆኑ አለቃውም ክፉ መንፈስ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል። ይህ ክፉ መልአክ የፋርስን ሁኔታ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ የሚጠቀምበት የሰይጣን መልእክተኛ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤል ያለውን ዓላማ ለማጨናገፍ ሰይጣን በዚህ መልእክተኛው ይጠቀማል። ምናልባትም ለብዙ ዓመታት የቤተ መቅደሱ ሥራ የተቋረጠው በዚህ ክፉ መልአክ ምክንያት ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል። ዳንኤል ለሦስት ሳምንት ያህል ሲጾምና ሲጸልይ በነበረበት ወቅት የእግዚአብሔር መልአክና ሰይጣን ውጊያ ላይ ነበሩ። ሁለቱም አልተሸናነፉም። በመጨረሻም «ከዋነኞቹ አለቃ» የሕዝብ አለቃ የተባለው ሚካኤል መልአኩን ለመርዳት መጣ። ክፉውን መልእክተኛ ከአሸነፋት በኋላ ነበር መልአኩ የጸሎቱን መልስ ይዞለት ወደ ዳንኤል የመጣው።

ከዚህም ቀደም ብለን የእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኛ ስለሆነው ስለ ታላቁ መልአክ ስለ ገብርኤል አጥንተናል። ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ የተጠቀሰ መልአክ ስለ ገብርኤል አጥንተናል። ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ የተጠቀሰ መልአክ ሚካኤል ብቻ ነው። ከእግዚአብሔር ታላላቅ መላእክት አንዱ ሊቀ መልአክ ተብሎአል፥ (ይሁዳ 1፡9)። በወታደሮች መካከል የሥልጣን ደረጃ እንዳለ ሁሉ በመላእክትም መካከል የሥልጣን ደረጃ መኖሩን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል። ለሌሎች መላእክት ሚካኤል ጄኔራላቸው ነው ማለት ይቻላል፥ (ራዕይ 12፡7)። ሊቀ መላእክት የተባለውም በዚህ ምክንያት ነው። ሚካኤል ከእግዚአብሔር ሕዝብ ከእስራኤላውያን ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው። ስለዚህም «አለቃችሁ ሚካኤል» በኋላም «ስለ ሕዝብ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል» ተብሎአል፥ (ዳን.12፡1)።

በጣም ከምንጽናናባቸው ነገሮች አንዱ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑ ነው። ከዚህም በተረፈ ለሕዝቡ ልዩ ጥንቃቄና ጥበቃ እንዲያደርጉላቸው እግዚአብሔር መላእክቱን እንደሚያዝዝ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጠቅሶአል። ምንም እንኳ በዓይኖቻችን ባናያቸውም እነዚህ መላእክት በየዕለቱ ከተለያየ አደጋ ይጠብቁናል። እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያደርገው ጥበቃና እንክብካቤ አስደናቂ አይደለምን?

የመልእክቱ ዋና ዓላማ ወደፊት በእስራኤል ሕዝብ ላይ ስለሚሆነው

ነገር ለማመልከት እንደሆነ፥ መልአኩ ቀደም ብሎ ለዳንኤል አስታውቆት ነበር። በምዕራፍ 11 ላይ መልአኩ ወደፊት በእስራኤል ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ሁኔታን ሲገልጽለት እንመለከታለን። ስለ ሬዕዩ ከመንገሩ በፊት ግን መልአኩ ስለ ራሱ ሥራ ነገረው። መልአኩ የመጣው «በእውነት መጽሐፍ የተጻፈውን» ሊነገረው ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የተለያዩ መጻሕፍት እንዳሉት ይናገራል። እነዚህ መጻሕፍት አንዳንድ ነገሮችን እንዳይረሳ እግዚአብሔርን የሚረዱት ሳይሆኑ፥ እኛ ከዘመናት በፊት የታቀደው የእግዚአብሔር እቅድና ዓላማ እውነተኛ መሆኑን እንድንገነዘብ ነው። የእግዚአብሔር እቅድ ተፈጽሞአል። አንዳንድ ጊዜ በሕይወታችንም ሆነ በሀገራችን በሚደርሰው ሁኔታ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ሁሉ መቆጣጠሩን እንዘነጋለን፤ ይሁን እንጂ ሁኔታዎች ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን በማሰብ መጽናናት አለብን። የሚሆነው ሁሉ አስቀድሞ በእውነት መጽሐፍ የተጻፈ ነው። በእውነት መጽሐፍ ላይ የተጻፈው የእግዚአብሔር እቅድና ዓላማ መፈጸሙ የማይጠረጠር ነው።

23ኛ ጥያቄ:- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት:- መዝ.69:28፤ 139:16፤ ራዕይ 20:12። እነዚህ ጥቅሶች ስለምን ዓይነት መጻሕፍት ይናገራሉ።

በሰማይ ቢያንስ ሁለት የተለያዩ ዓይነት መዝገቦች አሉ። አንደኛው መዝገብ ታሪክ የተመዘገበበት ነው። ያደረግነው ሁሉ:- ክፉም ሆነ በጐ የሚመዘገበው በዚህ መዝገብ ውስጥ ነው። እግዚአብሔር የሚፈርድብንም በዚህ መዝገብ በተጻፈው መሠረት ነው። በዚህ መዝገብ ወይም በሌላ መዝገብ ውስጥ የተጻፈው ታሪክ በዓለም ላይ የሚሆነውን ሁሉ ሊያካትት ይችላል። ከእግዚአብሔር እቅድና ዓላማ ውጭ የሚሆን ምንም ነገር የለም።

ሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ «የሕይወት መዝገብ» ይባላል። በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑት እውነተኛ አማኞች የሚመዘገቡት በዚህ መዝገብ ውስጥ ነው። ወደ ገሃነም ወይም መንግሥተ ሰማይ የምንሄደውም እዚህ መዝገብ ውስጥ በተጻፈው መሠረት ነው።

24ኛ ጥያቄ:- ስማችን በሰማያት በመጻፉ ምን ያህል እንጽናናለን፥ ምን ያህልስ በተሻለ ሁኔታ እግዚአብሔርን እንድናገለግል ያደርጉናል?

መልእክቱን ለዳንኤል ካደረሰ በኋላ መልአኩ እንደገና ተመልሶ ከፋርስ መንግሥት አለቃ ጋር መዋጋት ነበረበት። ያ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ደግሞ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ከሚሞክረው ከግሪክ መንግሥት አለቃ ጋር ይዋጋል። የፋርስ መንግሥት በግሪክ መንግሥት ድል መደረጉን ምናልባት ካለፋት

ትምህርቶች ታስታውስ ይሆናል:: የምዕራፍ 11 አብዛኛው ክፍል የሚናገረው ስለ ግሪክ በመሆኑ በግሪክ ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ይኖርብናል:: መልአኩ ሲዋጋ የነበረው ብቻውን ነበር:: በኋላ ግን ሚካኤል ሊረዳው መጣ::

ዳርዮስ በነገሠበት ጊዜ ሊያበረታውና ሊያጸናው ቆሞ እንደነበር መልአኩ ለዳንኤል ነገረው:: እስራኤላውያን ወደ ሀገረቸው እንዲመለሱ ንጉሡ እንዲፈቅድ የረዳው እርሱ መሆኑን መልአኩ ለዳንኤል ሊያስታውስ ይፈልጋል:: የአረማውያን ነገሥታት ውሣኔ እንኳ ከእግዚአብሔር ተፅዕኖ ውጪ አይደለም::

25ኛ ጥያቄ:- ይህ እውነት አንተንና የቤተ ክርስቲያንህን ሰዎች ምን ያህል ያጽናናችኋል?

የምድር ነገሥታትን ውሣኔ እግዚአብሔር በመላእክቱ አማካይነት መቆጣጠር መቻሉን በመረዳቱ ዳንኤል ተጽናንቶአል:: የምድር ነገሥታት እንደፈቃዳቸው እንዲወስኑ እግዚአብሔር አይፈቅድላቸውም:: ስለዚህም በእያንዳንዱ ሀገር የሚደረገው ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው:: በምዕራፍ 11 ላይ እግዚአብሔር መንግሥታት በሕዝቡ ላይ ተፅዕኖ ሲያደርጉ እንዴት አድርጎ እንደሚቆጣጠር በግልፅ እንመለከታለን::

አረተኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ትምህርት ክለስ

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ በምድር በሚደረገው ሁኔታ እንዴት የሰይጣንን ኃይል ለማየት እንደምንችል አንዳንድ ሐሳቦችን ጥቀስ::
2/ ሰይጣንን ለማሸነፍ ሥልጣን እንዳላቸው ክርስቲያኖች ምን ያህል እርግጠኞች ናቸው?
3/ ብዙ ክርስቲያኖች በሰይጣን ወጥመድ የሚወድቁት ለምን ይመስልሃል?
4/ የሰይጣንን ጥቃት ለመከላከል በመንፈሳዊ መሣሪያዎች እንዲጠቀሙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምዕመናንን እንዴት መርዳት ይችላሉ? (ኤፌ.6:10-16 ተመልከት::)

ለ. 1/ ዳን.10:4-6፤ ሕዝ.1:22-28፤ ራዕይ 1:12-17 አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔርን ታላቅነት

የሚያሳዩት እንዴት ነው?
2/ እንዳንዶቹ ገለጻዎች ምንን ያሳያሉ?
3/ የእግዚአብሔርን ታላቅነት እንደሚገባ መረዳት ለእርሱ የምንሰጠውን አገልግሎት እንዴት ሊያበረታው ይችላል?

ሐ. 1/ በሰማይ ያሉት የተለያዩ መጻሕፍት ዓላማ ምን እንደሆነ ግለጽ።
2/ እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩና እንደሚገባ እንዲያገለግሉት ይህ እውነት ክርስቲያኖችን ምን ያህል የሚያበረታታቸው ይመስልሃል?

5. ጸሎት።

## ትምህርት አሥረ ሰባት

## ዳንኤል 11:2-35

### የመጀመሪያ ቀን

እስከ ተወሰነውም ዘመን ይሆናልና ከጥበበኞቹ አያሌዎቹ እስከ ፍጻሚ ዘመን ይነጥሩና ይጠሩ ይነጡም ዘንድ ይወድቃሉ። (ዳን.11:35)

በትንቢተ ዳንኤል ጥናታችን እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት ሕዝቡን እስራኤልን እንደቀጣቸው ተመልክተናል። እስራኤላውያን በአሦራውያን እንዲማረኩ አደረገ። አይሁዳውያን ደግሞ በባቢሎናውያን እንዲማረኩ አደረገ። ሕዝቡ በዚህ ፍርድ ውስጥ ማለፍ ይገባው ነበር። እግዚአብሔር ሊያስተምራቸውና ትክክለኛውን መንገድ እንዲይዙ ሊያደርጋቸው ይፈልጋል። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ይህን ያደርጋል። ስለ ኃጢአታችን ሲባል በተለያዩ መንገድ የምንቀጣበት ወቅት አለ። እንደ ጥንት እስራኤላውያን ሁሉ ወደ ቀናው መንገድ ሊመልሰን ይፈልጋል፥ (ዕብ.12:5-11)።

1ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በኃጢአትህ ምክንያት እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደቀጣህ ዘርዝር።
ለ/ ከዚያስ ቅጣት ምን ተማርህ?

ምንም ኃጢአት ሳናደርግ ስለሚደርስብን መከራና ችግርስ ምን ታስባለህ? በዚያስ ውስጥ እግዚአብሔር ዓላማ ይኖረው ይሆን?

በዚህ ሳምንት አይሁዳውያን ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ የመንግሥታት የጦር አውድማ እንደሆኑ እንመለከታለን። ከከፋ መሪዎች የተነሣ ሰላም ለማግኘት እንዳልቻሉና የተለያዩ ስደት እንደደረሰባቸው እንመለከታለን። ስለ

ኃጢአታቸው እየተቀጡ ነበር ወይስ እግዚአብሔር የራሱ ዓላማ ነበረው?

ትንቢተ ዳንኤል 11:35 የችግር ጊዜ እንደሚያጣራና እንደሚያነጻ ይናገራል:: ብርና ወርቅ ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት በእሳት እንደሚያልፉ ሁሉ እኛም ከኃጢአት እንድንነጻና ለአገልግሎቱ የተዘጋጀን እንድንሆን÷ የተለያየ መከራ እንዲደርስብን ያደርጋል:: የእግዚአብሔር ቃል እንደሚ ያስተምረን ይህ የመከራ ጊዜ በሕይወታችን ላይ ብዙ ነገሮችን ያደርጋል::

2ኛ ጥያቄ:- ኢሳ.1:25፤ 48:10:- ችግርና መከራ ምን ያደርጋሉ?

በመጀመሪያ:- መከራ ያጠራል:: በመልካሙ ጊዜ በሕይወታችን ስላለው ኃጢአት ደንታ አይኖረንም:: ስለዚህም ሕይወታችንን ከኃጢአት ለማጥራት እግዚአብሔር የተለያየ ችግር እንዲደርስብን ያደርጋል::

ሁለተኛ:- መከራ የእምነታችንን ጥራት ይፈትናል፤ በእምነት እንድናድግም ያደርገናል÷ (1ጴጥ.1:6-7 ተመልከት):: እንዲሁ በተለምዶ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡትና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን እውነተኞችን አማኞች የሚለዩት በስደት ጊዜ ነው::

ሦስተኛ:- ችግሮች ፈርሃ እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲኖር÷ ራሱ እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ናቸው::

ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል እግዚአብሔር ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች አንዱ መከራ ነው:: የችግር ጊዜ ትዕግሥትንና ብስለትን ከማስተማሩም በላይ እግዚአብሔርን የመምሰል ባሕርይ እንዲኖረንም ያደርጋል÷ (ያዕ.1:2-4)::

4ኛ ጥያቄ:- በደረሰብህ ችግር ምክንያት እነዚህ ሦስት ባሕርያት በሕይወትህ እንዴት እንዲኖሩህ እንዳደረገ ግለጽ::

በዚህ ሳምንት ዳን.11:2-35 እናጠናለን:: ባለፈው ሳምንት ዳንኤል ስለ ጦርነት ስላየው ራዕይ መማራችንን ታስታውሳለህ? (ዳን.10:1) በእነዚህ ጦርነቶች ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን አልጣላቸውም:: ይልቁንም እነዚህ ጦርነቶች ሕዝቡን ለማጥራትና ለማንጻት ተጠቅሞባቸዋል::

5ኛ ጥያቄ:- ትንቢተ ዳንኤል 11:2-35 አንብብ::
ሀ/ የማያቋርጥ ውጊያ ያደርጉ የነበሩ ሁለቱ መንግሥታት ነበሩ?
ለ/ በእነዚህ ቁጥሮች የተጠቀሱትን የተለያዩ ጦርነቶች ግለጽ::

ሁለተኛ ቀን    ክፍል አንድ:-  ዳንኤል 11:2-4

## ጥያቄዎች

6ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ከፋርስ ምን ያህል ነገሥታት ይነሣሉ?
ለ/ አረተኛው ንጉሥ ምን ይመስላል?
ሐ/ ምን ያደርጋል?
7ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የሚቀጥለው ንጉሥ ከየት ይመጣል?
ለ/ በመንግሥቱ ላይ ምን ይሆናል?
8ኛ ጥያቄ:- እነዚህ ትንቢቶች በትንቢተ ዳንኤል ምዕረፍ 8 ካሉት ትንቢቶች ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብሪሪያ /ኮሜንታሪ/

ትንቢተ ዳንኤል 11 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለየ ምዕረፍ ነው:: ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ከዚህ ምዕረፍ የበለጠ በየትም ሥፍረ አልተገለጸም:: በዚህ ምክንያት ብዙ ምሁረን ይህ ምዕረፍ ጠቅላላ መጽሐፉ እንኳን ባይሆን የተጻፈው በ1967 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት  በምዕረፉ ውስጥ ያሉት ብዙዎቹ ትንቢቶች ከተፈጸመ በኂላ ነው ብለው እንዲያምኑ አድርጎቸዋል::  ከ200  ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት  እስከ 200 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በብሉይ ኪዳን የነበሩትን የታላላቅ ሰዎች ስም በመጠቀም አንዳንድ አይሁዳውያን  ጸሐፊዎች መጻሕፍት ያዘጋጁ ነበር::  በዚያ ዘመን የነበሩት አንባቢዎችም ምንም እንኳ ጽሑፉ ከብሉይ ኪዳን ሰዎች የእንዱ እንዳልሆነ ስለሚረዱ ጽሑፉን ይቀበሉ እንደነበር የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁረን ይናገረሉ::

በዚህ ምዕረፍ የተጠቀሱት ትንቢቶች የተጻፉት  ሁኔታዎቹ ከመጻፋቸው ሦስት መቶ  ዓመት በፊት ነበር::  እግዚአብሔር  ማንኛውም ነገር ከመሆኑ በፊት እንደሚያውቀው  እናውቃለን::  ስለዚህም ወደፊት የሚሆነውን ነገር ሁኔታው ከመፈጸሙ በፊት በስፋት ማመልከቱ አያዳግተውም::  ትንቢተ ዳንኤል ምዕረፍ 11 በብዙ መልኩ  ከምዕረፍ 8 ጋር ይመሳሰላል::  ትንቢተ ዳንኤል ምዕረፍ 11 ግን ትንቢቱን የሚያቀርበው ሰፋ ባለ መልኩ ነው::

በዳንኤል 11 ካሉት ትንቢቶች ምን ያህሉ እንደተፈጸሙ÷ ምን ያህሉ ደግሞ  ወደፊት እንደሚፈጸሙ  የመጽሐፍ ቅዱስ  ምሁረን የተለያየ ሐሳብ አቅርበዋል:: በሚቀጥለው ሳምንት ዳንኤል 11:36-45 ስናጠና ስለ እነዚህ የተለያዩ አስተሳሰቦች በሰፊው እንመለከታለን::

በዚህ ዘመን ለምንኖር ሰዎች ዳንኤል 11፡2-35 ታሪክ ነው። ከ500 እስከ 150 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የተፈጸሙትን ነገሮች በታሪክ መጻሕፍት ላይ ተጽፈን ካላወቅን በቀር እነዚህን ትንቢቶች እንደሚገባ ልንረዳቸው አንችልም። እነዚህን ትንቢቶች እንዴት መተርጐም እንዳለብን የሚያሳዩንና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተፈጸሙ የሚያስረዱን የዓለም የታሪክ መጻሕፍት ናቸው።

ከ400 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንሥቶ ክርስቶስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ያሉት ዓመታት «400 የዝምታ ዓመታት» ይባላሉ። በእነዚህ ዘመናት ምን እንደተፈጸመ በእግዚአብሔር ቃል አልተገለጸም፤ ነቢያትም አልተነሡም። በብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይሰጠው የነበረው ራዕይ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ተቋርጦ ነበር፥ (ዕብ.1፡1-2 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ወደፊት ምን እንደሚሆን የተሟላ ታሪካዊ ገለጻ ለዳንኤል አልሰጠውም። ይሁን እንጂ በጣም አጭር በሆነ ሁኔታ ለመረዳት የሚያዳግቱ ትንቢቶችን ሰጥቶታል። እግዚአብሔር እነዚህን ራዕዮች ለዳንኤል የሰጠው ወደፊት በሕዝቡ ላይ ስለሚደርሰው ሁኔታ ሊያመለክተው ነበር፥ (ዳንኤል 10፡14 ተመልከት)። እስራኤል የአሕዛብ መንግሥታት የሚዋጉባት የጦር ሜዳ እንደምትሆን አሳየው። ምንም እንኳ የምርኮው ጊዜ ቢያከትምም ወደፊት የሚመጣውን መሢህ ለመቀበል እንድትነጻና እንድትጠራ በተለያየ መከራ ማለፍ ነበረባት።

ዳንኤል ይህን የመጨረሻ ራዕይ ያገኘው ንጉሥ ቂሮስ ይገዛ በነበረበት ዘመን እንደነበር ታስታውሳለህ። የፋርስ መንግሥት ከመውደቁ በፊት አራት ነገሥታት በተከታታይ እንደሚነሡ መልአኩ ለዳንኤል ገለጸለት። ታሪክ እንደሚያመለክተን የፋርስ መንግሥት በግሪክ መንግሥታት ከመተካቱ በፊት በተከታታይ ቢያንስ ዘጠኝ ነገሥታት ተፈራርቀውበታል። ስለዚህም በዚህ ትንቢት የተጠቀሱት የትኞቹ አራት ነገሥታት እንደሆኑ የታሪክ ምሁራን በትክክል አናውቅም። ብዙዎቹ ግን በትንቢቱ የተጠቀሱት አራት ነገሥታት የሚከተሉት እንደሆኑ ይስማማሉ።

1. ካምብይስስ (ከ529-522 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) ይህ ንጉሥ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሰም።
2. ሲዶ ስሜርዲስ (ከ522-521 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) የዚህም ንጉሥ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሰም።
3. ዳርዮስ ቀዳማዊ ሒስታስፐስ (ከ521-486 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) የዚህ ንጉሥ ስም በመጽሐፈ ዕዝራ 5-6 ተጠቅሷል።

ስለ እነዚህ ሦስት ነገሥታት መልአኩ ለዳንኤል ሰፋ ያለ ገለጻ አልሰጠውም።

4. አርጤክስስ (ከ486-465 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) ይህ ንጉሥ በዕዝራ 4:6 አሐሸዊሮስ ተብሎ ተጠርቶአል። አራተኛው ንጉሥ አርጤክስስ በፋርስ ከተነሡት ነገሥታት ሁሉ ታላቅ ነው። እጅግ ባለጸጋ ስለነበር ብዛት ያለው የጦር ኃይል አደረጀ። ከእስያ ወደ አውሮፓ ተሻግሮ ግሪክን አጠቃ። ይሁን እንጂ በግሪኮች ድል ተደረገ፤ (ዳን.11:2)።

በዕብራይስጥ «ሦስት ... አራት» የሚለው አገላለጽ በጣም የተለመደ በመሆኑ በትክክል ሦስትና አራት ነገሥታት ማለቱ አይደለም፥ (ምሳሌ 30:15-29፤ አሞጽ 1:3-6) ከአርጤክስስ በኋላ ሌሎች ብዙ ነገሥታት ገዝተዋል። የፋርስ መንግሥት እስከ 332 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ አልወደቀም ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህ ቀሪዎቹ ነገሥታት በትንቢቱ ውስጥ ሥፍራ የላቸውም።

የፋርስ መንግሥት አስቀድመው ከተነሡት መንግሥታት ሁሉ ይበልጥ ታላቅ ነበር። እንደ አሦር ወይም እንደ ባቢሎን ምርኮኞቹን አያስጨንቅም ነበር። በባቢሎን ዘመን የነበሩትን ምርኮኞች ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀዱላቸው። እያንዳንዱ ሕዝብም የየግሉን ሃይማኖት እንዲከተል ፈቀዱለት። አይሁዳውያን ወደ ሀገራቸው የተመለሱት፥ መቅደሱንና የኢየሩሳሌምንም ከተማ እንደገና ለመሥራት የቻሉትም በዚህ ዓዋጅ መሠረት ነበር። ምንም እንኳ የፋርስ መንግሥት የበላይ ተቆጣጣሪነት ሥር ቢሆኑም፥ አይሁዳውያን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት ነበራቸው። በዘመኑ የነበረውም ሊቀ ካህን የመሪነት ሥልጣን ነበረው።

ከፋርስ መንግሥት ውድቀት በኋላ የግሪክ መንግሥት ተነሣ። ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 8ን ባጠናህበት ወቅት የመጀመሪያው የግሪክ ንጉሥ ታላቁ እስክንድር እንደነበር ተመልክተሃል። ምንም እንኳ መናገሻ ከተማው መቄዶንያ ቢሆንም ግዛቱ መላውን ግሪክ፥ የሕንድንም ድንበር ይዞ ግብፅን ሁሉ ያጠቃልል ነበር። ታላቁ እስክንድር በታላቅ ኃይል ነበር ሕዝቡን ሲመራ የነበረው። እስክንድር ይህን ሁሉ ድል ያገኘው ከ336-323 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ባሉት ዓመታት ውስጥ ነበር። አንድ ታሪክ እንደሚለው ታላቁ እስክንድር ወደ ኢየሩሳሌም በመጣበት ወቅት ሊቀ ካህናቱና ሌሎች ካህናት ልብሰ ተክህኖአቸውን እንደለበሱ ሄደው ተቀበሉት፤ ስለ እርሱም በትንቢተ ዳንኤል (ዳን.11:3) የተነገረውን ትንቢት አሳዩት። ታላቁ እስክንድር ገና ከመቄዶንያ ከመነሣቱ በፊት በሪዕይ ሊቀ ካህኑ ማንኛውንም መንግሥት በእግዚአብሔር ስም ድል እንዲያደርግ ሲያዘው ማየቱን ተናግሮአል። ምንም እንኳ አመጣጡ የኢየሩሳሌምን ከተማ ለመደምሰስ ቢሆንም በኋላ ግን ለከተማይቱ ካለው አክብሮት የተነሣ ሳያጠፋት ቀረ፤ የእግዚአብሔርንም አምልኮ እንዲቀጥሉ ፈቀደ። ከዚያ በኋላ ኢየሩሳሌም የሃይማኖት ክልል ሆና ስለ ተገመተች እስከ 200 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ግሪኮች ምንም ችግር አልፈጠሩባትም ነበር።

ከእስክንድር ሞት በኋላ መንግሥቱ ለአራት ተከፈለ፤ አራቱንም ግዛት አራቱ ጄኔራሎቹ ያስተዳድሩ ነበር። ምንም እንኳ እስክንድር ልጆች ቢኖሩትም በተነገረው ትንቢት መሠረት ሁሉም ተገድለዋል። ግሪክ ግዛቷ በመከፋፈሉ ምክንያት በእስክንድር ዘመን የነበረትን ዓይነት ጥንካሬ ሊኖረት አልቻለም፥ (ዳን.11:3-4)።

እስክንድር ዓለምን ለመግዛት ከመነሣቱ ከ200 መቶ ዓመት በፊት ምን እንደሚደረግ በእግዚአብሔር ተወስና ነበር። የግሪክ መንግሥት እንደሚከፋፈል እንኳ እግዚአብሔር ትንቢት ተናግሮአል። ደጋግመን እንደተመለከትነው የዓለም የጥንት ታሪክ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነበር። በዘመናችንም ቢሆን መንግሥታት የሚነሡትም ሆነ የሚወድቁት በእርሱ ፈቃድ ነው። አምላካችን ዘላለማዊ ነው፤ ከዘላለም እስከዘላለምም ይነግሣል።

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 11:5-20

## ጥያቄዎች

9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተደጋግሞ የሚጠቀሱት ሁለት የነገሥታት ሐረጎች የነማን ናቸው?
ለ/ እነዚህ ነገሥታት የትኞቹን አገሮች ይወክላሉ?
10ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በትንቢተ ዳንኤል 11:5-9 የተነገሩትን ትንቢቶች በራስህ አባባል ጻፋቸው።
ለ/ በዚህ ዘመን ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ የነበረው የትኛው መንግሥት ነበር?
11ኛ ጥያቄ:- በትንቢተ ዳንኤል 11:10-20 ውስጥ ታላቅ የነበረው መንግሥት የትኛው ነው?
12ኛ ጥያቄ:- በትንቢተ ዳንኤል 11:10-20 የተነገሩትን ትንቢቶች በራስህ አባባል ጻፋቸው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ጠቅላላውን የግሪክ ታሪክ ከመመርመር ይልቅ መልአኩ ሰፋ ያለ ማብራሪያ የሚሰጠው ስለ ሁለቱ የግሪክ ግዛቶች ማለትም ስለ ግብፅና ስለ ሦርያ ነበር። እነዚህ ሁለት ክፍሎች ከ320 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንሥቶ የሮም መንግሥት እስከተነሣበት ጊዜ ድረስ ሲገዙ የነበሩ ሁለት የነገሥታት ወገንን ይወክላሉ። (64 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት)

ከ320 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ 200 ዓመት ከክርስቶስ

ልደት በፊት ድረስ ደቡባዊው የግብፅ መንግሥት ጠንካራና ብርቱ ነበር። ይህ መንግሥት ከ323-285 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲገዛ በነበረው በቀዳማዊ በጥሊሞስ ሶተር ዝርያዎች የሚመራ በመሆኑ የበጥሊሞሳውያን መንግሥት ተብሎአል። ሰሜናዊው የሦርያ መንግሥት ደግሞ በቀዳማዊ ሴሌውከስ ኒካቶር ዝርያዎች ይመራ ስለነበረው የሴሌውከስ መንግሥት ተብሎአል። ቀዳማዊ ሴሌውከስ ኒካቶር ከ312-281 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ገዝቶአል።

ዳንኤል 11:5-20 በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን። ከቁጥር 5-9 ያለው የመጀመሪያው ክፍል ጳለስጢና በደቡብ መንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበረችበት ወቅት ነው። ይህም በታሪክ ከ323-200 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። ከቁጥር 10-20 ያለው ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጳለስጢና በሰሜኑ መንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበረችበት ወቅት ነው። ይህም ከ200-142 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። በዓለም ታሪክ መጻሕፍት አጋዥነት ትንቢቱን በሚከተለው ሁኔታ ልንረዳው እንችላለን።

ከእስክንድር ምርጥ ጄኔራሎች አንዱ የነበረው በጥሊሞስ የግብፅ ገዢ ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሳይታወቅበት ግብፅን ታላቅና ገናና መንግሥት አደረጋት። ግዛቱን ለማስፋፋት ካለው ዓላማ የተነሣ ሌሎቹን የግሪክ ጄኔራሎችን ማጥቃት ጀመረ። ሴሌውከስ የበጥሊሞስ ተባባሪ ነበር። ሁለቱ በአንድነት ሆነው ሌሎቹን ጄኔራሎች በማሸነፍ ሰፊ ግዛት ያዙ። መናገሻ ከተማውን በእስክንድርያ ያደረገው ደቡባዊ መንግሥት መላውን ጳለስጢና በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። ሴሌውከስ ደግሞ ሦርያን ያዘ። ምንም እንኳ በበጥሊሞስ ሥር የነበረ «አዛዥ» ቢሆንም የኋላ ኋላ ከታናሹ እስያ እስከ ሕንድ ድረስ ግዛቱን ለማስፋፋት ችሏል። ይህም ከረሱ ከበጥሊሞስ ግዛት የበለጠ ነበር። ዋና ከተማውም በሦርያ ውስጥ በነበረችው በአንጾኪያ ነበር። አንጾኪያ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን የታወቀች ከተማ ነበረች፥ (ዳን.11:5)።

በዘመኑ ኢየሩሳሌም የንግድ መናኸሪያ ስላልነበረች በጥሊሞሳውያን በአይሁዳውያን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን አልፈለጉም። ይህችን ትንሽ ሀገር የሚገዛው ካህኑ ነበር። ኢየሩሳሌም ግን የግብፅ ንጉሥና የሦርያ ንጉሥ ሲያደርጉት ለነበረው ጦርነት መተላለፊያና የጦር ዓውድማ ሆነች።

«ከብዙ ዓመታት በኋላ» ግን ዳግማዊ በጥሊሞስ ፊላደልፈስ የሚባለው የግብፅ ንጉሥ (285-246 ዓመት ከክርስቶስ ለደት በፊት) በሁለቱ መንግሥታት መካከል እርቅ እንዲኖር ፈለገ። በጥንቱ ዘመን ይህን ያደርጉ የነበሩት በሁለቱ ሀገር የነበሩትን ንጉሣውያን ቤተሰቦችን በማጋባት ነበር። አንጢዮኮስ ዳግማዊን የሦርያ ንጉሥ አደረገው (261-246 ዓከክልበ)፤ የመጀመሪያ ሚስቱንም ፈትቶ ቤሬኒስ የምትባለውን የበጥሊሞስን ልጅ አገባ።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ በጥሊሞስ ሞተ። ወደያውኑ አንጦኪዮስ ፈትቶአት የነበረውን የመጀመሪያ ሚስቱን እንደገና አገባ። በተደረገባት ግፍ በጣም ተናድዳ ስለነበር እርሱን፥ ሁለተኛ ሚስቱንና ልጁን ገደለቻቸው። ስለዚህም ሁለቱን መንግሥታት ለማስተባበር ተደርጐ የነበረው ሙከራ ምንም የረባ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ፥ (ዳን.11:6)።

ከዚያ በኋላ በጥሊሞስ ሣልሳዊ ኢውሬጌቴስ የተባለው የቢርኒስ ወንድም (ከቀርብ ዘመዶቸዋ አንዱ) የግብፅ ንጉሥ ሆነ። ሦርያውያንን ወግቶ ድል አደረጋቸው። እህቱን የገደለቸበትንም ሴት ገደላት። በሦርያ ቤተ መንግሥት የነበረውን ሀብትና ጣዖታትን ሁሉ ዘረፈ። ከሦርያ ግዛት ጥቂቱን ከግብፅ ግዛት ጋር ደባለቀ። ከዚህ ጦርነት በኋላ የጥቂት ዘመን ሰላም ተገኘ። በ240 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሴሌውከስ ካሊኒከስ የተባለ የሦርያ ንጉሥ (ከ247-226 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት) ግብፅን ለማጥቃት ሞክሮ ሳይሳካለት በመቅረቱ ሸሽቶ ሦርያ ገባ፥ (ዳን.11:7-9)።

ከዚህ በኋላ ከሴሌውከስ ልጆች አንዱ ታላቁ አንጢዮኮስ ሳልሣዊ (223-187 አክልበ) ሥልጣን ያዘ። እርሱ ኃይል የማገኘቱን ያህል ግን የግብፃውያን ኃይል መዳከም ጀመረ። ከግብፃውያን ጋር በተደጋጋሚ ተዋጋ ከጳለስጢና ግዛት ውስጥ ጥቂቱን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። በመጨረሻም እጅግ ብዛት ያለው ሠረዊት ይዞ (70 000 እግረኞች) በ217 አክልበ ከግብፅ ንጉሥ ጋር ባደረገው ታላቅ ውጊያ ብዙ ሕዝብ ስላለቀበት መሸሽ ግድ ሆነበት። የሦርያ ጦር በዚህ ሁኔታ ተዳክሞ በነበረበት ወቅት እስከ መጨረሻው ማጥቃት ቢኖርበትም የግብፅ ንጉሥ ግን ትቷቸው ወደ ሀገሩ ተመለሰ፤ (ዳን.11:10-12)።

አንጢዮኮስ ትኩረቱን ወደሌሎች አገሮች አደረገ። ከሕንድ ብዙውን አገር በቁጥጥሩ ሥር አደረገና ብዙ ሀብት ለማከማቸት ቻለ። አይሁዳውያን ለግብፅ ግብር አንከፍልም ብለው ያመፁት በዚህ ጊዜ ነበር። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ኢየሩሳሌምን እንደ ሃይማኖታዊ ክልል ስለቆጠሩዋት ግብፃውያን ምንም ጥቃት አላደረሱባትም ነበር፤ በኋላ ግን የጦርነት አውድማ አደረጉዋት፥ ስለዚህም ኢየሩሳሌም ከተለያየ አቅጣጫ ለሚዘምተው ሠረዊት ተጋለጠች። የግብፅ ንጉሥ የሞተው በጣም ሕጻን የነበረው ልጁን አንግሦ ሲሆን በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም አንጢዮኮስ እንደገና ግብፅን ወጋ። (201 ዓመት አክልበ) ምንም እንኳ በጥሊሞሳውያን አይሁዳውያንን በገለልተኝነት ቢተዉአቸውም ብዙ አይሁዳውያን ከአንጢዮኮስ ጋር ተባብረው በግብፅ ላይ ዘመቱ። ይሁን እንጂ የአይሁዳውያን ጦር ከበጥሊሞሳውያን ጄነራሎች በአንዱ ድል ሆነ። በዚህም ምክንያት:- «ከህዝብህም መካከል (አይሁዳውያን) የዓመፅ ልጆች ራዕዩን ያፀኑ ዘንድ ይነሣሉ፤ ነገር ግን ይወድቃሉ» የሚለው ትንቢት ተፈጸመ፥ (ዳንኤል 11:10-14)።

አንጢዮኮስ ግን ግብፅን መውጋቱን አላቋረጠም፥ ስለዚህም አሸነፋቸው። በመጀመሪያ «ተመሽጋ የነበረቸውን» የሲደንን ከተማ ያዘ። መልካሚቱን ምድር ኢየሩሳሌምን ጨምሮ መላው ጳለስጢና በሦርያውያን ቁጥጥር ሥር ሆነ። ይህም የሆነው በ197 አክልበ ነበር፥ (ዳንኤል 11፡15-16)።

ሁለቱን አገሮች ለማዋሃድ በነበረው ዓላማ አንጢዮኮስ ቀዳማዊት ኪሊዮፓትረ የምትባለውን ሴት ልጁን የ7 ዓመት ልጅ ለነበረው ለበጥሊሞስ 5ኛ ዳረለት። አንጢዮኮስ ይህን ያደረገው ግብፅን ለመቆጣጠር እንዲያመቸው ቢሆንም ኪሊዮፓትረ ግን ለባልዋ አግዛ ስለተዋጋቸው አንጢዮኮስ ግብፅን ለመያዝ ሳይችል ቀረ፥ (ዳንኤል 11፡17)።

ይህ ሁሉ ሲሆን በስተምሥራቅ በኩል ብዙ ማይልስ ርቀት ላይ ሌላ መንግሥት እየተነሣ ነበር። ይህም የሮማውያን መንግሥት ነው። ከግሪኮች ውድቀት በኋላ የተነሣው የሮም መንግሥት እንዳነበር ሳታስታውስ አትቀርም። አንጢዮኮስ ግሪክንና ትንሹ እስያን ማጥቃቱን ቀጠለ። በኋላም ከሮማውያን ጋር ተጋጨ። የሮማውያንን አምባሳደር ካዋረደ በኋላ በ190 አክልበ የሮም ሠረዊት ድል አደረገው። በዚህም እርሱ በጣም ተዋረደ። ለሠረዊቱና ለሮማውያን የሚከፍለው ከፍተኛ የገንዘብ ዕዳ ስለነበረበት ደኸየ። በመጨረሻም በአንድ የአረማውያን ቤተ መቅደስ ላይ በቃጣው ወረረ ምክንያት ተገደለ፥ (ዳን.11፡18-19)።

ሴሌውከስ ፊሎፓቶር አረተኛ የተባለው የአንጢዮኮስ ልጅ ከአባቱ ያገኘው ነገር ቢኖር ትቶለት የሄደውን ዕዳ ብቻ ነበር። ስለዚህም ገንዘብ እንዲሰበስቡለት ግብር ሰብሳቢዎችን ወደተለያዩ አገሮችና ወደ ኢየሩሳሌም ላካቸው። ገንዘቡን እንዲሰበስቡ የተላኩት ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ቤተ መቅደሷ ሲመጡ ከአይሁዳውያን ከፍተኛ ተቃውሞና ዓመፅ ገጠማቸው። ግብር ሰብሳቢዎቹ ከመመለሳቸው በፊት ሴሌውከስ ተገደለ። «ነገር ግን በቁጣው ሳይሆን በሰልፍም ሳይሆን በጥቂት ቀን ይሰበረል» (ዳን. 11፡20)።

እግዚአብሔር ስለእነዚህ ሁኔታዎች ለምን ለዳንኤል በተብረረ ሁኔታ እንዳነገረው መረዳቱ አዳጋች ነው። ይሁን እንጂ ይህ ትንቢት የተሰጠው ወደፊት በአይሁዳውያን ላይ ስለሚደርሰው ጉዳይ ለማመልከት መሁኑን ልንዘነጋ አይገባም። ለብዙ ዓመታት የሁለት ታላላቅ መንግሥታት የጦርነት አውድማ ሆነው ኖሩ። በኢየሩሳሌም አካባቢ የነበረውን ሞትና ኃዘን መገመት የሚያደግት አይሆንም። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ በህዝቡ በአይሁዳውያን ላይ ይፈጸም ዘንድ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነበር። ጊዜው ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም ሁኔታዎቹ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነበሩ።

አረተኛ ቀን:-      ክፍል ሦስት   ዳን.11:21-35

## ጥያቄዎች

13ኛ ጥያቄ:- ስለሚቀጥለው ገዢ የተሰጠው ገለጻ ምንድነው?
14ኛ ጥያቄ:- ይህ ንጉሥ ሥልጣን የሚይዘው እንዴት ነው?
15ኛ ጥያቄ:- ከደቡብ ንጉሥ ጋር በሚያደርገው ጦርነት ምን ይሆናል?
16ኛ ጥያቄ:- የሰሜኑ ንጉሥ ወደ ግብፅ እንዳይገባ ያገደው ማነው?
17ኛ ጥያቄ:- የሰሜኑ ንጉሥ በተስፋይቱ ምድር ላይ ያደረገውን ግለጽ?
18ኛ ጥያቄ:- «አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ» ምን ያደርጋሉ?
19ኛ ጥያቄ:- ጠቢባኑስ ምን ይሆናሉ?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያ (ኮሜንተሪ)

እስካሁን ድረስ ያጠናነው  የዚህ ራዕይ ክፍል የራዕዩ መግቢያ ነው ማለት ይቻላል:: ራዕዩ የሚያተኩረው በታሪክ ውስጥ አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ አረተኛ በመባል በሚታወቅ ሰው ላይ ነው::  ምንም እንኳ በዓለም ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የማይሰጠው ተራ ሦሪያዊ ንጉሥ ቢሆንም  በቅዱሳት መጻሕፍት ግን ሰፋ ያለ  ግምት ያለውን ሥፍራ ይዞአል:: ይህም የተባለበት ምክንያት ከፋርስ÷ ከግሪኮችና ከሌሎችም መንግሥታት ይልቅ አይሁዳውያንን ጨርሶ ለመደምሰስና እውነተኛው አምላክ በኢየሩሳሌም እንዳይመለክ ከነበረው ጽኑ ዓላማ የተነሣ ነው::  በአይሁዳውያን አንጻር ስናየው ታላቁ ጠላታቸው ነበር::  አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ አረተኛ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ለተነሡት መሪዎች በተለይም  በመጨረሻው የሚነሣው የክርስቶስ  ተቃዋሚ ዓይነተኛ ምሳሌ መሆኑን ወደፊት በሚኖረን ጥናት እንመለከታለን::

የሮም መንግሥት እየበረታ ሲሄድ የሦርያ  መንግሥት ደግሞ መዳከም ጀምሮ ነበር:: አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ ሥልጣን የያዘው በዚህ ወቅት ነበር:: ከማንኛውም ሦርያዊ ንጉሥ ይልቅ «ሔሌናዊ» የተባለው  የግሪክ ባሕልና ሃይማኖት እንዲስፋፋ ከፍተኛ ትግል አድርጎአል:: ይህም በብሉይ ኪዳን ትምህርትና እምነት ሕይወታቸውን  ለመምረትና እውነተኛውን  አምላክ ለማምለክ ከሚፈልጉት ጋር እንዲጋጭ አደረገው:: «ችግር ፈጣሪው» ተብሎ የተጠረውም በዚህ ምክንያት ነበር::  ሰዎች እንደ አምላክ እንዲያመልኩት ስለፈለገም  ስሙን «ኤጲፋንዮስ» አሰኘ::  ይህም  ማለት «የአማልክት መገለጽ» ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማሳደዱ በጋጠወጥ አኗኗሩና የፈለገውን  ለማግኘት በሚጠቀምበት  የማጭበርበር ዘዴው  የታወቀ ሰው ነበር::

አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ አረተኛ የሴሌውክስ ፊሎፓቶር አረተኛ ወንድም ነበር። በትክክለኛው መንገድ ከሆነ ሴሌውክስ ሲሞት ልጁ ዲሚትሪስ መንገሥ ነበረበት። የሴሌውክስን ሞት የሰማው አንጢዮኮስ ግን ይኖር ከነበረበት ከሮም ወደ አንጾኪያ በመምጣት አንዳንድ ሰዎችን አሳድመና መንግሥቱን ከዲሚትሪስ ወሰደ። «የመንግሥቱንም ክብር አይሰጡትም» በኋላም የተለያዩ አገሮችን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ጀመረ። ምንም እንኳ ግብፅ ከፍተኛ ጦር ቢኖራትም በ170 አክልበ ድል አደረጋት። ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ የግሪኮችን ባሕልም ሆነ ኃይማኖት ይቃወም ከነበረው ሊቀ ካህን ጋር ተጋጨ። ስለዚህም እርሱን ሻረና የግሪክ ሃይማኖትና ባሕል ደጋፊ የነበረውን የሊቀ ካህኑን ወንድም ሾመ። በኋላም አንጢዮኮስ የበፊቱን ሽማግሌ ሊቀ ካህን አስገደለ። በዚያ ዘመን የቃል ኪዳኑን ሕዝብ እስረኤላውያንን ያስተዳድር የነበረው ሊቀ ካህኑ እንደነበር ታስታውሳለህ። ከእግዚአብሔር አንጻር ሲታይ ማንኛውም በሕዝቡ ላይ የሚቃጣ ጥቃት በእርሱ ላይ እንደተቃጣ ሆኖ ነው የሚያየው፤ (ዳን. 11:21-22)።

20ኛ ጥያቄ:- በክርስቲያኖች ላይ ዛሬ የሚደረግ ጥቃት በእግዚአብሔር ላይ እንደተደረገ ጥቃት ሆኖ የሚቆጠረው በምን መልኩ ነው?

አንጢዮኮስ በገንዘቡና በዘዴው ብዙ ባልንጀሮችን አፈራ። ከተለያዩ አገሮች ወዳጆች ቢያፈራም እነርሱን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ በድንገት ጥቃት ይሰነዝርባቸው ነበር። ግብፅን ቶሎ ብሎ በአንዴ በማጥቃቱ ብዙ ገንዘብ ለማከማቸት ቻለ። በዚህም ገንዘብ ከሌሎች መሪዎች ጋር ተወዳጀበት። በመጨረሻም ሙሉ በሙሉ ግብፅን በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ታጥቆ ተነሣ። ብዛት ያለው ጦር ይዞ በግብፅ ላይ ዘመተ። አንዳንድ የሠረዊቱ አባላት «መብሉንም የሚበሉ ሰዎች» የግብፅን ንጉሥ አይፈልጉም ነበር፥ ስለዚህም አንጢዮኮስ በቀላሉ ግብፅን ድል ለማድረግ ቻለ። ይሁን እንጂ የመጨረሻውን የግብፃውያን ኃይል ከመደምሰሱ በፊት በግዛቱ ሌላ ክልል ውስጥ ዓመፅ ስለተቀሰቀሰ ጦርነቱን አቋርጦ መመለስ ግድ ሆነበት። አንጢዮኮስና የግብፅ ንጉሥ ስምምነት ቢያደርጉም በልባቸው አይተማመኑም ነበር። ስለዚህም ሙከረቸው ዘላቂ ሰላም አላስገኘላቸውም። ባለመስማማታቸው ሳይሆን «ፍጻሜው እስከ ተወሰነው ጊዜ» በመሆኑ እቅዳቸውን ለማሟላት አልቻሉም። በምድር የሚሆኑትን ሁኔታዎች የሚወስነው እግዚአብሔር ራሱ ነው። የግሪክ መንግሥት የሚወድቅበትን ጊዜ እርሱ ራሱ ወስኖት ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ሰላምን ለማስገኘት ሲያደርግ የነበረው ሙከራ ሁሉ አጥጋቢ ውጤት ሊያስገኝለት አልቻለም፤ (ዳን.11:23-27)።

21ኛ ጥያቄ:- ይህ በዘመናችን ሰላምን ለማስገኘት በመንግሥታት መካከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ ብዙ እምነት እንዳይኖረን በምን መልኩ ነው የሚያስጠነቅቀን?

ከግብፅ ብዙ ሀብትን ከዘረፈ በኋላ አንጢዮኮስ ወደ ሦርያ ተመለሰ። እግረ-መንገዱን «በተቀደሰው ቃል ኪዳን» በኢየሩሳሌም ያልፍ ስለነበር በእግዚአብሔር መቅደስ ውስጥ ያገኘውን ሀብት ሁሉ ወሰደ። ከመቅደሱ አጠገብ ሠረዊቱ የሚሰፍርበትን ካምፕ አሠረ። በዚያም ወቅት ብዙ አይሁዳውያን ተገደሉ፥ (ዳን.11፡28)። ቆይቶም አንጢዮኮስ እንደገና ግብፅን ለመውረር ተነሣ። ግብፅን ለማሸነፍ ጥቂት ሲቀረው የሮም አምባሳደር (በቆጵሮስ መርከቦች) ደረሰበት። ፊት ለፊት ተገናኝተው ወደ ሀገሩ እንዲመለስ አስጠንቅቆት ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ ግን የሮም ጦር ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያደርስበት ነገረው። ከፍርሃትም የተነሣ አንጢዮኮስ ከግብፅ ተመለሰ። በጣም ተናድዶ ስለነበረም እግረ-መንገዱን ወደ ሀገሩ ሲመለስ በአይሁዳውያን ላይ ተነሣ። አባቶቻቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉትን ቃል ኪዳን ትተው እግዚአብሔርን በከዱት አይሁዳውያን እርዳታ ወደ ቤተ መቅደሱ ውስጥ ገባ። እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው «ዜዉስ» የተባለውን የግሪኮች ጣዖት እንዲያመልኩ አዘዘ። ከግሪክ አማልክት አንዱን ለማክበር ሲል በቤተ መቅደሱ ባለው መሠዊያ ላይ አሳማ ሠዋ። ይህ ጸግሞ አይሁዳውያንን በጣም ነበር ያስቆጣቸው። «የጥፋት ርኩሰት» በመሆኑም እግዚአብሔርን በዚያ መሠዊያ ላይ ለማምለክ አይቻሉም። ለሦስት ዓመት ያህል በዚያ ቤተ መቅደስ ውስጥ እግዚአብሔርን አላመለኩም። በድርጊቱ አይሁዳውያን በጣም በመቆጣታቸው በኢየሩሳሌም «የሃይማኖት ጦርነት» አስነሡ። እግዚአብሔርን ለመከተል የወሰኑት ግን «አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ» ምንም እንኳ አልቂት እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁም እስከመጨረሻው ድረስ አንጢዮኮስን ለመዋጋት ቆርጠው ተነሡ፤ (ዳን.11፡29-32)።

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ. «አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ» በዘመናችን ክፋትን የሚቃወሙት እንዴት ባለ ሁኔታ ነው?
ለ. በምን ዓይነት መንገድ ነው የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክፋትን የምትቃወመው?

ይህንን የሃይማኖት ጦርነት የቀሰቀሱት አንድ ካህንና አምስት ልጆቹ ናቸው። የሙሴን ሕግ እንዳይከተሉና እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ የወጣውን ትእዛዝ በመቃወም ይህ ካህን በአንጢዮኮስ ላይ ዓመፅና ለውጊያ ተነሣ። በ167 አክልበ በኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መቅደስ ውስጥ ለአረማውያን ጣዖት ዓሣማ ለመሠዋት ይዘጋጅ የነበረውን አይሁዳዊ በዚያው ቤተ መቅደስ ውስጥ ገደለው። አምልጦ ከኢየሩሳሌም ከወጣ በኋላ ቆራጥ የሆኑ ሰዎችን አሰባስቦ ለውጊያ ተዘጋጀ። «ጠቢባን» ተብለው ከሚጠሩት የካህናት ወገን ብዙዎች ተባበሩዋቸው። በእግዚአብሔር እንዲታመኑና የሃይማኖት ተቃዋሚዎችንም እንዲዋጉ ያደረጉት ቅስቀሳ ብዙ ሰዎችን ሦርያን እንዲወጉ አነሣሣቸው። በጦርነቱ በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳውያን አለቁ። ይሁን እንጂ የኋላ ኋላ ድል ለማግኘት ችለዋል። በ164 አክልበ ቤተ መቅደሱን ከአሕዛብ አምልኮ ካነጹ በኋላ እንደገና ለእግዚአብሔር መሰዋት ጀመሩ። ብዙ ነዓነት

ወጳጳቶም ተባበሩዋቸው። በመጨረሻም በ142 አክልበ ነፃነታቸውን አገኙ። ከ586 አክልበ ወዲህ ነፃ ሲሆኑ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር። ይሁን እንጂ በነፃነታቸው የቆዩት ሮማውያን ኢየሩሳሌምን እስከያዙበት ማለትም እስከ 63 አክልበ ድረስ ብቻ ነበር። አንጢዮኮስ ራሱ በ164 አክልበ ሞተ፤ (ዳን.11:33-34)። ስለዚህ ውጊያ በኦርቶዶክሶችና በካቶሊኮች መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ እና በ2ኛ መቃባውያን ላይ ማንበብ ትችላለህ።

ይህ የመከራ ጊዜ በአይሁዳውያን ምንን አስከተለ? ጊዜው አይሁዳውያን የሚነጹበት ጊዜ ነበር። ብዙ አይሁዳውያን የግሪኮችን ሃይማኖትና ባሕል ለመከተል ፈቃደኛ ነበሩ። እንደ አንዳንድ የዘመናችን ክርስቲያኖች ሁሉ ዓለምን ከመቃወም ይልቅ ከዓለም ጋር ተመሳስሎ ለመኖር ፈቃደኞች ነበሩ። እግዚአብሔርን ለመከተል ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆኑት ግን በመከራው ነጠሩ፥ ነጹ። እየግሪኮች ባሕል የተቀደሰውን ሃይማኖታቸውን እንደሚያረክስባቸው መረዳቱ አላዳገታቸውም። ብዙ ጊዜ ስደት የሚመጣው እውነተኛ አማኞችን ለማጥራት ነው። ስደት እውነተኛ አማኞችን እንዲሁ ለልማድ ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚሄዱት ይለያቸዋል። ሞትን ሳይፈሩ እግዚአብሔርን ለመከተል የወሰኑት የዓለም ወዳጆች ሊሆኑ አይችሉም። እምነታቸው የጠራ በመሆኑም እግዚአብሔር ይባርካቸዋል። ማንኛውም የችግር ጊዜ:- «በተወሰነው ጊዜ ፍጻሜው እንደሚመጣ» ማስ ክርስቲያኖችን ያጽናናቸዋል። በስደት ጊዜ እንኳ ሁኔታዎች ሁሉ በእግዚአብ ቁጥጥር ሥር ናቸው። ስደቱ የሚያከትምበትንም ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ ወስኖታል። እስከዚያ ድረስ ግን በእምነት ጸንተን መቆም አለብን።

23ኛ ጥያቄ:- ስደት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው ቤተ ክርስቲያንህን ያጠራት?

አምስተኛ ቀን:- ትምህርቱን ከለስ፤ የውይይት ጥያቄዎችንም እንደገና ተመልከት።

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ አምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. የስደት ጊዜ ክርስቲያኖችን:-
1/ እንዴት እንደሚያጠራቸው
2/ እንዴት በእምነት እንደሚያሳድጋቸው
3/ እንዴት ክርስቶስን ወደመምሰል ደረጃ እንደሚያደርሳቸው

ተወያዩ። ቤተ ክርስቲያንህ በመንፈሳዊ ሕይወት እንድታድግ ስደት ምን ያህል ረድቶአታል?

ለ. በሕዝቡ ላይ የሚቃጣውን ጥቃት እግዚአብሔር በእርሱ ላይ እንደተቃጣ ጥቃት የሚመለከተው ለምንድነው?

ሐ. 1/ «ስደቱ የሚያከትምበት ጊዜ» በእግዚአብሔር መወሰኑ እንዴት ሊያበረታታን ይችላል?
   2/ ማስጠንቀቂያስ የሚሆነው በምን መልኩ ነው?

መ. 1/ እግዚአብሔርን ማወቅ ክፋትን እንድንቃወም የሚረዳን እንዴት ነው?
   2/ ጥቂት ምሳሌዎችን ስጥ
   3/ በቤተ ክርስቲያንህ ያሉ ሰዎች ያለማቋረጥ በታታሪነት ክፋትን ይቃወማሉን? እንዴት?

5. ጸሎት

## አሥራ ስምንተኛ ትምህርት

(ዳን 11:36-45)

### የመጀመሪያ ቀን

«ቁጣም እስኪፈጸም ድረስ ይከናወንለታል፥ የተወሰነው ይደረጋልና» (ዳን.11:36)

ከትንቢተ ዳንኤል ከምንማረው ዋና ዋና ትምህርቶች አንዱ ማንኛውም ሁኔታ በእግዚአብሔር የተወሰኑ መሆኑ ነው። ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንደሚገባ ለመረዳት ባንችልም፥ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሁኔታው ዓላማ የለሽ መስሎ ቢታየንም፥ እግዚአብሔር የዓለም ታሪክ ተቆጣጣሪ መሆኑ ግን ተደጋግሞ ተነግሮናል። እርሱ መሪዎችን ያስነሳል፥ ፈቃዱን ከፈጸሙ በኋላም ይጥላቸዋል።

ዛሬ በምድር ላይ ስለሚነሣው የመጨረሻው ክፉ መሪ እናጠናለን። በዚህ ዘመን ብዙ ክፉ መሪዎች መኖራቸው የሚያከራክር አይደለም። እንደ ሙሶሎኒ፥ ሒትለርና እስታሊን የመሳሰሉ ሌሎችም ብዙ ክፉ መሪዎች ተነሥተዋል። በእነዚህ መሪዎች ምክንያት በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በጭካኔ ተገድለዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት እጅግ በጣም ክፉ መሪ እንደሚነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እንደ

አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስ ሌሎችም የዘመናችን ክፉ መሪዎች የዚህ የመጨረሻ ክፉ መሪ ምሳሌዎች ናቸው:: ያለጥርጥር በዚህ ክፉ መሪ ዘመን፥ ሰዎች የእግዚአብሔር ዓላማ ምን ይሆን? በማለት ይጠየቃሉ:: «ሁኔታዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ከሆኑ ታዲያ ክፋት ይህን ያህል እንዲበረታ ለምን ይፈቀዳል?» የሚል ጥያቄ ይሰነዘራሉ:: ይሁን እንጂ፥ ክፋት ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ እንኳ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው:: ክፋት ቢበረታም ለጊዜው ነው:: በዚህም ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በዚህ ዓመፀኛ ዓለም ላይ ይወርዳል:: (ራዕይ 6-19) በመጨረሻም እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ክፉው መሪ ይደመሰስና፥ የእግዚአብሔር መንግሥት እውነተኛ ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥቱን ይመሠርታል::

1ኛ ጥያቄ:- ትንቢተ ዳንኤል 11:36-45 አንብብ::
ሀ. የንጉሡን አጠቃላይ ባህርይ ግለጽ::
ለ. ንጉሡ ሲደመሰስ ፍጻሜው ምን ይመስላል?

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 11:36-39

ጥያቄዎች

2ኛ ጥያቄ:- የንጉሡ ሕይወት በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆኑን እንዴት እናውቃለን?
3ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ከ«አማልክት» ጋር ስላለው ግንኙነት ግለጽ::
4ኛ ጥያቄ:- ንጉሡ ተከታዮቹን የሚያከብረቸው እንዴት ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ / ኮሜንተሪ /

ባለፈው ሳምንት ዳንኤል ያየውን የመጨረሻ ራዕይ የመጀመሪያ አጋማሽ አጥንተናል:: ይህ ራዕይ ከሜዶንና ፋርስ መንግሥት አንሥቶ እስከ ግሪክ መንግሥት ድረስ የተደረጉትን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በዝርዝር ያመለክታል:: በመጨረሻም አንጢዮኮስ ኤጲፋነስ ስለተባለው ክፉ መሪ ተመልክተናል:: በትንቢተ ዳንኤል 11:21-35 የተሰጠው ትንቢት በአብዛኛው በዚህ ሰው መፈጸሙን ተመልክተናል::

ዛሬ ደግሞ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በታሪክ ውስጥ ስላልተፈጸሙ ትንቢቶች እንመለከታለን:: በዳንኤል 11:36-45 ያለው ትንቢት ሙሉ በሙሉ በታሪክ ውስጥ ባለመፈጸሙ፥ ትንቢቱ ስለማን እንደሚያመለክት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በትክክል አልተረዱትም፥ በዚህም ምክንያት የተለያየ አስተሳሰብ ይዘዋል:: ከቀረቡት ዋና ዋና አስተሳሰቦች ሦስቱ የሚከተሉት ናቸው:-

1. እነዚህ ትንቢቶች በአንጢዮኮስ ኤጲፋነስ ዘመን ተፈጽመዋል።

2. እነዚህ ትንቢቶች በአንጢዮኮስ ኤጲፋነስ ዘመን በከፊል ቢፈጸሙም፥ በታሪክ ውስጥ ስለሚነሡት ክፉ መሪዎች የቀረቡ ምሳሌዎች ናቸው። በመጨረሻ በሚነሣው ክፉ መሪ ግን ትንቢቱ ሙሉ በሙሉ ይፈጸማል።

3. እነዚህ ትንቢቶች የሚያመለክቱት በመጨረሻ በዓለም ላይ ስለሚነሣው ክፉ መሪ ነው። ትንቢቶቹ የሚገልጹትም ስለፀባዩና ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ስለሚደረገው የመጨረሻ ጦርነት ነው።

ስለ መጨረሻው ክፉ መሪ ሌሎች ጥቅሶች ከሚሰጡት ሐሳብ ጋር በማዛመድ ከተመለከትነው ሁለተኛውና ሦስተኛው ሐሳብ የተሻለ አተረጓጐም ሊሆን የሚችል ይመስለናል። ትንቢቶች በቅርቡ የሚደረገውን አመልክተው በዘመናት ፍጻሜ አካባቢ ወደሚሆነው ትንቢት በፍጥነት የመሸገር ባህርይ አላቸው። በመካከሉ ስለሚኖረው ዘመን ብዛት ግን ምንም ገለጻ አይሰጡንም፤ (ለምሳሌ ያህል የሐዋርያት ሥራ 2፥16-21 ተመልከት)።

በዳንኤል 11፥36-39 በመጨረሻ ስለሚነሣው ክፉና ጨካኝ መሪ ፀባይ አንዳንድ ነጥቦች ተሰጥተዋል፦

1. ይህ መሪ ያለ ገደብ ሥልጣን ይኖረዋል። ደስ የሚያሰኘውን ነገር ሁሉ ያደርጋል። ማንም የሚቃወመው አይኖርም።

2. ራሱን ከሌሎች አማልክት ሁሉ በላይ እንደሆነ አድርጐ ይቆጥራል። ስለዚህም ሰዎች ሁሉ እንዲያመልኩት ያደርጋል። ይሁን እንጂ ይህ ሰው በፍፁም በእግዚአብሔር የማያምን ከሓዲ መሆኑ ተገልጿል፤ (ራዕይ 13፥14-17)።

3. ይህ መሪ የአማልክት ሁሉ አምላክ የሆነው የእስራኤልን አምላክ አምልኮ ይቃወማል። የሰይጣን አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን እውነተኛውን አምላክ ለማምለክ የሚፈልጉትን ሁሉ ይቃወማል፤ (ራዕይ 13፥1-10 ተመልከት)።

4. የእግዚአብሔርን ቁጣ አስፈጻሚም በመሆኑ ለጊዜው ይሳካለታል። ይህም ቢሆን እግዚአብሔር ጽርጊቱንና በዘመነ መንግሥቱ የሚቆይበትን ጊዜ ይቆጣጠረል።

5. የአባቶቹን አምላክ ይተዋል። ይህ አባባል አንዳንድ ምሁራንን ምናልባት ይህ ሰው የአብርሃምን አምላክ አምልኮ ፈጽሞ የተወ አይሁዳዊ ሳይሆን አይቀርም ወደሚል አስተሳሰብ መርቶአቸዋል። ነገር ግን ይህ ክፉ ገዢ አማልክቶቹን ሁሉ የሚቃወምና በተለይ የአባቶቹን አምላክ አምልኮቱን

ለመደምሰስ ቆርጦ እንደተነሣ አድርጐ መመልከቱ ይሻላል። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ የተጠቀሰው እውነተኛው አምላክ ይሁን የአሕዛብ አማልክት እርግጠኞች አይደለንም።

6. የሴቶችንም ምኞት አይመለከትም። ይህ አባባል ግልፀ አይደለም። በዳንኤል ዘመን በጣም የተለመደው ሃይማኖት ታሙዝ የሚባለውን ጣዖት ማምለክ ነበር። የሰብሎችን ማደግ የሚቆጣጠር ይህ ጣዖት ነው የሚል እምነት ስለነበረቸው ብዙ ሴቶች ይህን ጣዖት ያመልኩ ነበር፤ (ሕዝቅኤል 8:14-15)። ስለዚህም የሴቶችን ምኞት አይመለከትም ሲል ስለዚህ ጣዖት እያሰበ ነው የሚል ግምት አለ። አንዳንዶች ደግሞ ይህ ክፍል የሚያመለክተው ስለመሢሑ ነው ይላሉ። በኦሪት ዘፍጥረት 3:15 ላይ መሢሕ ከእርስዋ እንደሚገኝ ለሔዋን የተሰጣት ተስፋ ትዝ ይልህ ይሆናል። በዚህ ምክንያት የአይሁድ ሴቶች አንድ ቀን መሢሕ ከእኛ ይወለድ ይሆናል የሚል «ምኞት» ነበረቸው። እንግዲህ ይህ አተረጓጐም ትክክል ከሆነ በመጨረሻ የሚነሣው ክፉ መሪ በጠላትነት የሚነሣው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ሳይሆን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ጭምር ነው ማለት ነው።

7. «የአምባዎችን አምላክ ያከብረል» በዚህ ክፍል ላይ ስለየትኞቹ አማልክት እንደሚናገር ግልጽ አይደለም። ይሁን እንጂ በሕይወታችን ከፍተኛውን ሥፍረ የያዘና ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር ሁሉ አምላካችን እንደሚሆን ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። እንደሚታወቀው ይህ ዓመፀኛ መሪ በእግዚአብሔርም ሆነ በመንፈሳዊው ዓለም የሚያምን አይደለም። ከዚህ ይልቅ ግን በሁለት ነገሮች የሚታመን ይመስላል። አንደኛ፥ በገዛ ኃይሉና፥ በወታደረዊ ብርታቱ ይታመናል። ዓለምን ሁሉ ሊቆጣጠር በሚችል ብርቱና ታላቅ ሠረዊቱ ስለሚተማመን ሌላ አምላክን ማክበር አስፈላጊ አለመሆኑን ያምናል። ሁለተኛ፥ በወርቅ፥ በብርና በከበሩ ድንጋዮች ወዘተ ይታመናል። ለኃይሉና ለብልፀግናው ምክንያት የሚያደርጋቸው እነዚህን ነገሮች ነው እንጂ እግዚአብሔርን አይደለም። ስለዚህም ይህ ክፉ መሪ የሚታመነው በገዛ ኃይሉና በሀብቱ ብዛት ነው እንጂ፥ በመንፈሳዊ ነገር አይደለም።

8. «ባልታወቀው አምላክ እርዳታ» ምሽጎችን ያጠቃል፥ ታላላቅ መንግሥታትንና ሠረዊታቸውንም ሁሉ ድል ያደርጋል። ተከታዮቹንም በተሸነፉት አገሮች ላይ መሪዎች በማድረግ ያከብረቸዋል። ስለሚገዙትም ምድር ዋጋ ያስከፍላቸዋል።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ባህርያት በታሪክ ውስጥ በተነሡ የተለያዩ መሪዎች ላይ ታይተዋል። እነዚህ መሪዎች በሠረዊታቸውና በገንዘባቸው ብዛት እንጂ በእግዚአብሔር የሚታመኑ አልነበሩም። ይሁን እንጂ በመጨረሻ የሚነሣውን መሪ በመጠኑም ቢሆን የሚወክሉ ምሳሌዎች ናቸው። ይህ ዓመፀኛ መሪ «የዓመፅ ሰው»፤ (2ተሰሎንቄ 2:3-10) «የክርስቶስ ተቃዋሚ» (1ዮሐንስ 2:18)፤ እንደገና ደግሞ

በራዕይ 13:5-8 «አውሬው» ተብሎአል። ኃይሉን የሚያገኘው ከራሱ ከሰይጣን ነው። ዓለምን ለመቆጣጠርና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመጸምሰስ ሰይጣን ይጠቀምበታል። እርሱን የሚያጠፋው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

5ኛ ጥያቄ:- ራዕይ 13:10ን ተመልከት። ይህ ሁሉ ችግር ሲደርስባቸው የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁኔታውን እንዴት ሊቀበሉት ይገባል?

6ኛ ጥያቄ:- ወደፊት ስለሚሆነው አስቀድመን ማወቃችን የዛሬው አኗኗራችን እግዚአብሔርን የሚያስደስት እንዲሆን የሚረዳን እንዴት ነው? (2ጴጥሮስ 3:1-13)።

የመጨረሻውን ዘመን በሚመለከት ረገድ እግዚአብሔር ሦስት ዋና ዋና እውነቶችን እንድንረዳ ይፈልጋል። በመጀመሪያ:- ሁሉ ሁኔታዎች አስቀድመው በእግዚአብሔር የተወሰኑ መሆናቸውንና እርሱም የሚቆጣተረቸው መሆኑን፥ ማስታወስ አለብን። ሁለተኛ:- ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ዝግጁዎች ለመሆናችን ሕይወታችንን መመርመር አለብን። ሦስተኛ:- በዘመናችን ስላለው የዓመፅ ብዛት መደነቅ የለብንም። ይልኩንስ በእምነታችን መጽናት ይኖርብናል። አንድ ቀን እግዚአብሔር ክፋትን ሁሉ አስወግዶ በክብርና በጽድቅ እንደሚነግሥ እርግጠኞች ነን። ለዚያ መንግሥት ተዘጋጅተናል?

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት ዳንኤል 11:40-45

## ጥያቄዎች

7ኛ ጥያቄ:- በሰሜን ንጉሥና በደቡብ ንጉሥ መካከል ጦርነት የሚደረገው መቼ ነው?

8ኛ ጥያቄ:- በጦርነቱ የሚያሸንፈው የትኛው ንጉሥ ነው?

9ኛ ጥያቄ:- ከምሥራቅና ከሰሜን ብዙ ሠራዊት እንደመጣበት ሲሰማ ወዴት ይመለሳል?

10ኛ ጥያቄ:- ዓመፀኛው መሪ ምን ይሆናል?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ (ኮሜንተሪ)

ትናንትና በመጨረሻ ስለሚነሣው ክፉ መሪ ተመልክተናል። በዳንኤል 11:36-39 የተሰጠው ገለጻ እስካሁን ድረስ በታሪክ ውስጥ ለተነሱት መሪዎች ለአንዱም እንኳ እንደማይስማማ ተመልክተናል። ይህም እነዚህ ገለጻዎች የሚያመለክቱት ወደፊት ስለሚነሣው መሪ ነው ወደሚል ሐሳብ አምጥቶናል።

በዳንኤል 11:36-39 የተሰጠው ገለጻ ሙሉ በሙሉ የሚስማማው ለዚህ ሰው መሆኑንም አጥንተናል። በጣም ከመታበዩም በላይ እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ይፈልጋል። በሠራዊቱ ኃይል ይታመናል። ስለዚህም ማንም የሚደፍረው አይመስለውም። ይሁን እንጂ ሁኔታዎች ሁሉ በእግዚአብሔር እንጂ በእርሱ ቁጥጥር ሥር አይደሉም።

ከዚህም ሌላ በዚህ ክፍል የተሰጡት ገለጻዎች የመጨረሻውን ዘመን የሚያመለክቱ መሆናቸውን ተመልክተናል። (ቁ40) የዘመን መጨረሻ በምድር ላይ የመጨረሻው ጦርነት የሚደረግበት ጊዜ ሊባል ይችላል። የክርስቶስ ተቃዋሚው መንግሥት ይፈረርሳል። ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ይዋጋል፤ የመጨረሻው የጦር ሜዳ የምትሆነው ግን እስራኤል ናት።

የመጨረሻውን ጦርነት የሚጀምረው የደቡብ ንጉሥ ነው። ከዚህ አስቀድመን ይህ ንጉሥ የግብፅ ንጉሥ መሆኑን ተመልክተናል። ይሁን እንጂ ይህ ታላቅ ሠራዊት በግብፅ ብቻ ሊወሰን አይችልም። ምናልባትም ይህ ሠራዊት ከሊቢያ÷ ከኢትዮጵያና ከሌሎችም አገሮች የተውጣጣ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ይህ ጦር የተባበረው የአፍሪካ ሠራዊት እንደሆነ ይናገራሉ። የክርስቶስ ተቃዋሚ ብዙት ያለውን ሠራዊት ይዞ በደቡብ ንጉሥ ላይ ይዘምትበታል። ልክ እንደ ታላቅ ጐርፍ የደቡብን ሠራዊት ያጠፋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ በመልካሚቱ ምድር ያልፋል። ግብፅን÷ ሊቢያን÷ ኢትዮጵያንና ሌሎች ብዙ አገሮችን ድል ያደርጋል። ሀብታቸውንም ሁሉ ይዘርፋል።

በሰሜኑ ንጉሥ እጅ የማይወድቁ ሦስት አገሮች ብቻ እንደሆኑ ተጠቅሶአል። እነርሱም:- ኤዶም÷ ሞዓብና አሞን ናቸው። እንዴት በእጁ ከመውደቅ እንዳመለጡ ግን እርግጠኞች አይደለንም።

የደቡብ መንግሥታትን በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ የክርስቶስ ተቃዋሚው÷ ሁለት መንግሥታት እርሱን ለመውጋት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ይሰማል። እነዚህ ከምሥራቅና ከሰሜን የመጡ ሠራዊት ናቸው። የክርስቶስ ተቃዋሚው በዚህ ነገር ከመናደዱ የተነሣ በመንገዱ ያገኘውን ሁሉ ይገድላል። ወደ እስራኤል ምድር ይመጣል። ንጉሣዊ ድንኳኑንም «በባሕርና በከበረው በቅዱስ ተራራ መካከል ይተክላል» የተጠቀሱት ሁለት ባሕሮች:- ሙት ባሕርና ሜዲትሬኒያን ባሕር ሲሆኑ ቅዱሱ ተራራ የተባለችው ደግሞ ኢየሩሳሌም ናት። እስራኤል በምድር ላይ የመጨረሻው ታላቅ ውጊያ የሚደረግባት ጦር ሜዳ ትሆናለች። የክርስቶስ ተቃዋሚውና ሠራዊቱ የምሥራቁንና የሰሜኑን ሠራዊት ይቋቋማሉ። በድንገት ግን የክርስቶስ ተቃዋሚው ይወድቃል። ማንም ከጥፋት አያድነውም። ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ በታላቅ ክብሩ ሲመለስ ነው። በዚህም ጊዜ የሰዎች መንግሥታት ተወግደው ዘላለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ይመሠረታል።

11ኛ ጥያቄ:- ዘካርያስ 14:1-4 እና ራዕይ 19:11-21 አንብብ::
ሀ/ በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ስለተጠቀሰው ስለ መጨረሻው ጦርነት ግለጽ::
ለ/ የጦርነቱ ፍጻሜ ምንድነው?

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በመጨረሻ በዚህ ምድር ስለሚደረገው ጦርነት ተገልጾአል:: ሕዝቅኤል በጐግ ማጐግ የሚደረግ ጦርነት ይለዋል:: እነዚህ አገሮች በዘመኑ ሩስያ አጠገብ የሚገኙ ጥንታዊ መንግሥታት ናቸው፥ (ሕዝ.38-39):: ምንም እንኳ በእነዚህ የተለያዩ ጦሮች ውስጥ ይሳተፋሉ ብለን የምንገምታቸውን በዘመናችን ያሉ አገሮችን ስም መጥቀስ ቢቻልም፥ በዚህ አቋማችን ግትር መሆን የለብንም:: ዋናው ቁም ነገር የሚከተሉትን ዋና ዋና ትንቢቶች መረዳቱ ነው::

1. የዓለም ታሪክ በሚፈጸምበት ወቅት ዓለምን የሚገዛ አንድ መሪ ይነሣል፤ የዓለም መንግሥታትን ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር ያደርጋል:: ሰዎች ሁሉ ይከተሉታል፥ ያመልኩታል:: ለእግዚአብሔር ልጆች ይህ ትልቅ የስደት ጊዜ ይሆንባቸዋል::

2. በመጨረሻው ግን የዚህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ኃይል ይደክማል፤ መንግሥታት ሁሉ ኃይላቸውን አስተባብረው ይወጉታል:: ከደቡብ፥ ከምሥራቅና ከሰሜን ሠራዊት ይነሣበታል::

3. የመጨረሻው ጦርነት በእስራኤል ምድር ይደረጋል::

4. እርስ በርስ ለመዋጋት ኃያላን መንግሥታት ሲሰበሰቡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያዊው ሠራዊቱ ጋር ይመጣል፤ እርስ በርስ መዋጋታቸውን ትተው ከእርሱ ጋር ይዋጋሉ::

5. ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን መንግሥታት ድል ያደርጋቸዋል፤ በመጨረሻም ያጠፋቸዋል:: የጽድቅ መንግሥቱን ይመሠርታል፤ በስደቱ ጊዜ ለእርሱ ታማኝ የሆኑትንም ይሸልማቸዋል::

ዛሬ ታላላቅ መንግሥታት የጦር ኃይላቸውን በጣም ባደረጁበት ወቅት ነው ያለነው:: እነዚህ መንግሥታት በመካከላቸው ሰላም እንዲሰፍን እየጣሩ ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ግን ሰዎች በሚያስገኙት ሰላም ላይ ሙሉ በሙሉ እምነታችንን እንዳንጥልበት ያስጠነቅቃል:: አንድ ቀን በመካከላቸው የተፈጠረው ሰላም ይፈርስና እርስ በርስ መዋጋት ይጀምራሉ:: በምድር ላይ ታላቅ የጸም መፍሰስ ይሆናል:: በዚህ ጨለማና አስፈሪ ዘመን ጸንተን እንቆም ይሆን? በኢየሱስ ክርስቶስ ያለን እምነት ምን ያህል ጽኑ ነው? እርሱን ከመካድ ይልቅ ለእርሱ ለመሞት ዝግጁ ነን?

ይሁን እንጂ በእነዚህ ትንቢቶች አማካይነት መጽናናትን ልናገኝ እንችላለን። ጊዜው ምንም ያህል ክፉ፥ ጦርነቶቹም ምንም ያህል ታላቅ ቢሆኑም አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል፤ የሰው ክፋት ሁሉ ይደመሰሳል፤ ኢየሱስም የጽድቅ መንግሥቱን ይመሠርታል። ስለዚህ ወንድሞቼና እህቶቼ ተስፋችንን በቅርቡ በሚመለሰው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እናድርግ። ኢየሱስ ራሱ:- «እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ» ብሎአል፥ (ራዕይ 22:12)። ስለዚህም ከዮሐንስ ጋር «አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና» እንበል።

<u>አራተኛ ቀን:-</u> <u>የዚህን</u> ሳምንት ትምህርት ክለስ

1. ጸሎት
2. የሳምንቱ አምልኮ ጊዜ
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጥያቄዎች

    ሀ. 1/ የክርስቶስ ተቃዋሚን ባሕርይ በየጊዜው በታሪክ ውስጥ ተነሥተው ከነበሩ ክፉ መንግሥታት ጋር አነጻጽር። የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?
    2. የሚለያዩት እንዴት ነው?
    3. የክርስቶስ ተቃዋሚን ባሕሪ በማሳየት እግዚአብሔር ሊያሳውቀንና ሊያስጠነቅቀን የፈለገው ነገር ምን ይመስልሃል?

    ለ. የክርስቶስ ተቃዋሚው የሚነሣበት ወቅት በጣም አስከፊ ጊዜ ይሆናል፤ ታዲያ እኛ ክርስቲያኖች ራሳችንን ለዚያ ጊዜ የምናዘጋጀው እንዴት ነው?

    ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ድል እንደሚያገኝ ማመናችን፥ ታማኝ እንድንሆንና ጌታን እንድናገለግል እንዴት ሊያበረታታን ይችላል?

    መ. የቤተ ክርስቲያንህ ሰዎች በእምነታቸው እንዲበረቱ እነዚህን እውነቶች እንዴት ልታስተምራቸው እንደምትችል ዘርዝር።

5. ጸሎት

## ትምህርት አሥራ ዘጠኝ

ዘላለም ሕይወት፥ አኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና» (ዳን.12:2)።

ክርስቲያን ታላቅ ተስፋና መጽናናት የሚያገኝበት አንድ እውነታ አለው። ይህም ከሙታን ስለመነሣት የተሰጠው ተስፋ ነው። ብዙዎች ሞትን ይፈራሉ። ሞት የሕልውናቸው ፍጻሜ ይመስላቸዋል፤ ከሞት በኋላ ምን እንደሚሆንም አያውቁም። ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ሞትን ከሚገባ በላይ የሚፈሩትና አንድ ሰው በሞት ሲለያቸው በጣም የሚያለቅሱት በዚህ ምክንያት ነው።

ክርስቲያን ግን ሞትን በታላቅ ሐዘንና ተስፋ ቢስ በሆነ ፀፀት የሚመለከትበት ምንም ምክንያት የለውም፥ እንዲያውም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የምናልፍበት በር ነው። (ዮሐ.11:25 ተመልከት)። ኢየሱስ ከሞት መነሣቱ፥ እኛም ከሞት እንደምንነሣ ማረጋገጫ ሊሆነን ይችላል፥ (1ቆሮ.15:20-23)።

1ኛ ጥያቄ:- 1ተሰ.4:13-18 አንብብ። በጌታ አምነው ስለሚሞቱት የተሰጠው ተስፋ ምንድነው?

የሙታን ትንሣኤ የሚሆነው መቼ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ በሆነ ሁኔታ አያስረዱም። በዚህ በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ ጻድቃንም ሆኑ ኃጢአተኞች ከሙታን እንደሚነሡ እንመለከታለን። ግን ይህ የሚሆነው በተመሳሳይ ጊዜ ነው?

አንዳንድ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥቱን ከመመሥረቱ በፊት አንድ አጠቃላይ ትንሣኤ እንደሚኖር ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ቢያንስ ሁለት ትንሣኤ እንደሚኖር ይናገራሉ። የመጀመሪያው የጻድቃን ትንሣኤ እንደሚኖር ይናገራሉ። የመጀመሪያው የጻድቃን ትንሣኤ ነው። አንዳንዶች ይህ ትንሣኤ የሚሆነው በሁለት ደረጃ እንደሆነ ያምናሉ። በመጀመሪያ:- ኢየሱስ በአየር ላይ ሲመጣ አምነው ለሞቱት ትንሣኤ ይሆናል። አስቀድመው የሚነሡት ግን ሙታን ናቸው። ከዚያ በኋላ በጌታ የሚያምኑ ሕያዋን እርሱን ለመቀበል በአየር ይነጠቃሉ፥ (1ተሰ.4:13-18)። የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የሚነሡት በዚህ ወይም በሚቀጥለው ትንሣኤ ይሆናል።

ነገር ግን ሌላ የጻድቃን ትንሣኤ የሚኖር ይመስላል። ይህም በስደት ወቅት ስለ ጌታ የሚሞቱ አማኞች ትንሣኤ ነው፥ (ራዕይ 20:4-6 ተመልከት)። እነዚህ ሁለት ትንሣኤዎች አብረው የመጀመሪያው ትንሣኤ ተብለው ሊሰየሙ ይችላሉ።

ሁለተኛውና ዋነኛው ትንሣኤ ደግሞ:- የኃጢአተኞች ትንሣኤ ነው።

ኃጢአተኞች ከሙታን ይነሡና በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ፤ የዘላለም ቅጣትም ይበየንባቸዋል:: ይህም «ሁለተኛው ትንሣኤ» ይባላል፥ (ራዕይ 20:12-15 ተመልከት)::

እንግዲህ የሰው ልጅ በሙሉ የትንሣኤ ተስፋ እንዳለው አረጋግጠናል ማለት ነው:: ዋናው ጥያቄ ግን «እኔ የምነሣው በየትኛው ትንሣኤ ነው?» የሚለው መሆን አለበት:: ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ሆነን በመኖር የመጀመሪያው ትንሣኤ ተካፋይ እንሆናለን? ወይስ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለማመናችን ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ጋር የሁለተኛው ትንሣኤ ተካፋይ እንሆናለን? በየትኛው ትንሣኤ እንደምንነሣ የሚወሰነው አሁን በምናደርገው ምርጫ ነው:: ዛሬውኑ ራስህን መርምር፤ ለደህንነትህ እምነትህን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ ማድረግህንም አረጋግጥ::

2ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ለክርስቲያን የተሰጠው የትንሣኤ ተስፋ:- ተስፋና መጽናናትን የሚሰጠን እንዴት ነው?
ለ/ ያላመነው ሰው ከሞት እንደሚነሣና እንደሚፈረድበት መገለጹ፥ ኃጢአቱን አሁን ባለው ጊዜ እንዲናዘዝ ሊያደርገውና ሊያሳስበው የሚችለው እንዴት ነው?

3ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 12ን አንብብ::
ሀ/ ስለ መጨረሻው ዘመን መልአኩ ለዳንኤል የሰጠው ተጨማሪ ትንቢት ምንድነው?
ለ/ በእግዚአብሔር ፊት መልአኩ የሰጠው ተስፋ ምንድነው?

ሁለተኛ ቀን ክፍል አንድ:- ዳንኤል 12:1-4

ጥያቄዎች

4ኛ ጥያቄ:- ስለ ሚካኤል የተሰጠው ገለጻ ምንድነው?
5ኛ ጥያቄ:- በቁጥር 1 የተገለጸው ምን ዓይነት ጊዜ ነው?
6ኛ ጥያቄ:- በመጽሐፉ ውስጥ ስማቸው የተጻፈው ሰዎች የተሰጣቸው ተስፋ ምንድነው?
7ኛ ጥያቄ:- ከሙታን የሚነሡት ሁለት የተለያዩ ወገኖች እነማን ናቸው?
8ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ለ«ጠቢባን» የተሰጠው ተስፋ ምንድነው?
ለ/ እነዚህ «ጠቢባን» ተብለው የተሰየሙት ሰዎች እነማን ናቸው?
9ኛ ጥያቄ:- ሀ/ ለዳንኤል የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?
ለ/ ይህስ ምን ማለት ነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ላለፉት ሦስት ሳምንታት የዳንኤልን የመጨረሻ ራዕይ በተከታታይ ስናጠና ነበር፥ (ዳንኤል 10-12)። ባለፈው ሳምንት በመጨረሻ ስለሚነሣው ክፉ መሪ እና ስለመጨረሻው ጦርነት ተመልክተናል። በዚህ ሳምንት ደግሞ እግዚአብሔር ለዳንኤል የሰጠውን የመጨረሻ መመሪያ እንመለከታለን።

ዳንኤል 12፡1-4 በመጨረሻ ጊዜ ስለሚኖረው የሙታን ትንሣኤ የሚናገር ራዕይ ነው። ምናልባትም ባለፈው ሳምንት በመጨረሻ የሚነሣው ክፉ መሪ እንደሚደመሰስና ማንም ሊረዳው እንደማይችል የተማርነውን ታስታውስ ይሆናል፥ (ዳን.11፡45)።

አሁን ደግሞ የመጨረሻዎቹ ቀናት ምን እንደሚመስሉ ትንሽ ተነግሮናል። ይህ ጊዜ:- «... እስከዚህ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ <የመከራ ዘመን> ይሆናል» የተባለለት ነው። የዮሐንስ ራዕይ 6፡1-19 በዚያ ዘመን ስለሚሆነው መቅሠፍት፥ ጦርነትና የእግዚአብሔር ፍርድ ሰፋ ባለ ሁኔታ ያመለክታል።

በዚያ የመከራ ዘመን ማክተሚያ ላይ ታላቁ መልአክ ሚካኤል ይነሣል። የሚካኤል እንዳኛው ልዩ አገልግሎትና ተግባር የዳንኤል ሕዝብ የሆኑትን እስራኤላውያንን መታደግ እንደሆነ ማስተዋል አለብን። ስለዚህም ከኢየሱስ ክርስቶስና ከሌሎች ሰማያውያን መላእክት ጋር ሆኖ ዓመፀና መንግሥታትን ያለጥርጥር ለማጥፋት ይነሣል። በመከራ ጊዜ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑት ሰዎች ከዚህ ጊዜ ይታደጋሉ። እዚህ ላይ ታማኝ ሆነው የሚቆሙት ስማቸው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ ሰዎች መሆናቸውን አስተውል። ያለ ጥርጥር ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ልጆች ስም የተጻፈበት «የሕይወት መጽሐፍ» ነው፥ (ራዕይ 13፡8፤ 20፡15፤ 21፡27 ተመልከት)።

በዘመናት ፍጻሜ የሚሆን ሌላው ከፍተኛ ሁኔታ ደግሞ የሙታን ሁሉ ትንሣኤ ነው። የጻድቃን ትንሣኤ ይሆናል፤ የዚህ ትንሣኤ ውጤት የዘላለም ሕይወት ነው። ይህ ትንሣኤ የሚሆነው የኃጢአትን ትንሣኤ ከሚሆንበት ጊዜ በተለየ ጊዜ ሊሆን ይችላል ብለን ነበር። የኃጢአት ትንሣኤ ውጤት ዘላለማዊ እፍረትና ጉስቁልና ነው።

በሁለቱ ትንሣኤ መካከል ስላለው ልዩነት የተነገረን በእነዚህ የመከራ ዘመናት በእምነታችን ጸንተን እንድንቆም ነው። ሰዎች ሥጋን ሊገድሉ ይችላሉ። ይህን ልንፈራ አይገባንም፤ እንዲያውም የሙታን ትንሣኤ እንደሚሆን ማሰብ አለብን። ዛሬ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንደሚኖሩ ማስተዋል ይገባናል። ሕይወታቸውን ለማዳን ብለው በማያምኑ ሰዎች መንገድ የሚሄዱ ግን በትንሣኤ ጊዜ ለዘላለም ይወገዛሉ።

10ኛ ጥያቄ:- ማቴ.10:26-28፤ 37-39 አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች ይህን እውነት የሚያስተምሩት እንዴት ነው?

በታማኝነታቸው ለሚጸኑ ሁሉ የሚጠብቃቸው ሽልማት ምን እንደሆነ ለዳንኤል ተናግሮታል:: እጅግ ይከብረሉ፤ ከዋክብት በብርሃናቸው ጌታን እንደሚያከብሩ ሁሉ እነርሱም የእግዚአብሔርን ብርሃን ያበረሉ:: ታማኝ የሆኑት ሁለት መለያ ነጥቦች አሏቸው::

1. እነርሱ «ጠቢባን» ናቸው:: ይህም ማለት ብዙ ዕውቀት ወይም መረጃ አካብተዋል ማለት አይደለም:: «ጠቢባን» የሆኑት የዘመናቸውን ሕዝብ ክፋት በመረዳታቸውና የዓለምን መንገድ በመናቃቸው ነው:: ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተዋል፤ ለሕግጋቱም ይታዘዛሉ፤ ስደትና ሞት እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁም እርሱን ይከተሉታል::

11ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በምን ዓይነት መንገድ ነው የዘመናችን ክርስቲያኖች ጠቢባን መሆን የሚገባቸው?
ለ/ ክርስቲያኖች በፈሪሃ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ ጥበብን እንዴት ማሳየት እንደሚችሉ አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ::

2. ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑት «ብዙ ሰዎችን ወደ ጽድቅ» ይመራሉ:: የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ ራሳቸው ብቻ ሳይሆን ወደ ጥፋት ለሚሄዱትም ሰዎች ሸክም ተሰጥቷቸው ማሰብ ይኖርባቸዋል:: የእግዚአብሔር ሰዎች የሚጠፉትን ወደ ጽድቅ መንገድ መልሰው የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት መንገር ይኖርባቸዋል::

12ኛ ጥያቄ:- አንተና ሌሎች የቤተ ክርስቲያንህ ሰዎች በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ብዙዎችን ወደ ጽድቅ በመመለስ ላይ እንዳላችሁ ግለጽ::

በመጨረሻም ዳንኤል መጽሐፉን እንዲዘጋና እንዲያትም ተነገረው:: ይህም ማለት መልእክቱን ለማጥናት ከሚፈልጉ ሰዎች መጽሐፉን መደበቅ ሳይሆን፥ በስደቱና በመከራው ጊዜ ለሚኖሩት አማኞች መጽናኛና ጥበብ እንዲሆናቸው መጽሐፉ ተጠብቆ ይቀመጥ ማለት ነው:: ለዳንኤል የተሰጡት ትንቢቶች የመጨረሻውን ጊዜ የሚያመለክቱ ናቸው:: ይሁን እንጂ በተለያየ ጊዜ በመከራ ውስጥ ለሚያልፉትና በተለይም በመጨረሻው ዘመን ስደት ለሚደርስባቸው ምዕመናን እንዲበረቱና በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ተጽፎአል::

ሌላው የመጨረሻው ዘመን ምልክት ደግሞ ሰዎች ሁሉ ዕውቀትን የሚፈልጉበት ጊዜ መሆኑ ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል ስለናቁ በዘላለማዊነት

ዓይን ሲታይ ምንም ዓይነት ጥበብ አያገኙም። በዚህ በትንቢተ ዳንኤል የተሰጠውን መልእክት የሚረዱት ጥበበኞች እግዚአብሔርን የሚወዱና ለሕግጋቱም የሚታዘዙት ብቻ ናቸው፥ (ዳን.12፡10 ተመልከት)።

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ የዘመናችን ሰዎች ዕውቀት ለመፈለግ ሲሉ እዚህም እዚያም ይሄዳሉ ለማለት የምንችለው በምን ዓይነት መንገድ ነው?
ለ/ የእግዚአብሔር ልጆች ላልሆኑት የእግዚአብሔር እውነት ተጸብቆባቸዋል የሚባለው በምን መልኩ ነው? (1ቆሮ.2፡6-16 ተመልከት)።

ሦስተኛ ቀን ክፍል ሁለት:- ዳንኤል 12፡5-13

ጥያቄዎች

14ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል በወንዙ ዳርቻ ምን አየ?
15ኛ ጥያቄ:- ምን ጥያቄ ጠየቀ?
16ኛ ጥያቄ:- ሰውዬው ጥያቄውን ሲመልስ በእግዚአብሔር ፊት ምን መሐላ አደረገ?
17ኛ ጥያቄ:- በመጨረሻው ዘመን ጻድቃን ምን ይሆናሉ?
18ኛ ጥያቄ:- በመጨረሻው ዘመን ኃጢአተኞች ምን ያደርጋሉ?
19ኛ ጥያቄ:- 1290 ቀናት ከመጀመረቸው በፊት የሚታዩት ሁለት ምልክቶች ምንድናቸው?
20ኛ ጥያቄ:- እስከ ስንት ቀን ፍጻሜ ድረስ የሚቆይ ነው ምስጉን ነው የተባለው?
21ኛ ጥያቄ:- ለዳንኤል የተሰጠው የመጨረሻ ተስፋ ምንድነው?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /ኮሜንታሪ/

ዛሬ የዳንኤልን ራዕይና የመጽሐፉን ፍጻሜ እንመለከታለን። ዳንኤል ራዕዩን ያገኘው በጤግሮስ ወንዝ አካባቢ እንደነበር ታስታውሳለህ፥ (ዳን.10፡4)። ዳንኤል አንዱ ከወዲህ ሌላው ደግሞ ከወንዙ ወዲያ ሆነው ሁለት ሰዎች ሲነጋገሩ ሰማ። አንደኛው በፍታ (ናይለን) ለብሶ ነበር። ትንቢተ ዳንኤል 10 ስናጠና ባገኘነው ሐሳብ መሠረት ምናልባት ይህ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን እንደማይቀር ገምተን ነበር። ሁለት ሰዎች ያስፈለጉበት ምክንያት ለሚሰጠው ትንቢት ምስክር ለመሆን የሁለት ሰዎች መኖር አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

በትንቢተ ዳንኤል 11፡36-12፡4 የተሰጠው አስጸናቂ ትንቢት

የሚፈጸመው መቼ እንደሆነ አንደኛው መልአክተኛ ሌላውን ጠየቀው። በፍታ የለበሰው ሰው ሁለት እጆቹን ወደ ሰማይ አንሥቶ በዘላለማዊው አምላክ ስም ማለ። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን ማስተዋል ይኖርብናል።

1. ሰውየው ሁለት እጆቹን ወደ ሰማይ አነሣ። በአይሁድ ባሕል መሠረት ሰዎች መሐላ ሲያደርጉ አንድ እጃቸውን ብቻ ወደ ላይ የማንሣት ልምድ አላቸው። በዚህ ጊዜ ግን መሐላው የምሩ ለመሆኑ ለማሳየት ሰውዬው ሁለት እጆቹን በማውጣት አረጋገጠ።

2. እግዚአብሔር «ለዘላለም ሕያው ሆኖ የሚኖረው» ተብሎ ተሰይሟል። ሰውየው የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት አረጋገጦ ተናገረ። ሰዎች ይሞታሉ፤ ጊዜም ያልፋል። ፍጻሜው ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሺህ ዓመታት ያልፋሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ዘላለማዊው እግዚአብሔር በዙፋኑ ጸንቶ ይኖራል።

ይህ ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ «ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ እንደሆነ ተናግሮአል።

22ኛ ጥያቄ:- ስለዚህ አባባል የተለያዩ ትርጓሜዎች ተሰንዝረዋል። ይህንንም ለመረዳት የትንቢተ ዳንኤል 7:25 ጥናታችንን ተመልከት። ታዲያ የዚህ አባባል ትክክለኛ ትርጓሜ ምን ይመስልሃል?

ምንም እንኳ አንዳንዶች ይህ አባባል የመከራውን ጊዜ አጭርነት ለማስረዳት የተሰጠ ምሳሌያዊ ገለጻ እንደሆነ ቢናገሩም ይህ ጊዜ የሚያመለክተው ሦስት ዓመት ተኩል ነው። ሰውዬው እነዚህ ትንቢቶች ለመፈጸም ሦስት ዓመት ተኩል የሚያህል ጊዜ እንደሚወስድበት ይናገራል። እነዚህ ጌታ ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት የሚኖሩን የመጨረሻዎቹ ዓመታት ናቸው።

በተጨማሪም ሰውዬው በዚህ ጊዜ ውስጥ «የተቀደሰው ሕዝብ» ኃይል እንደሚበተን ተናግሮአል። ይህ እስረኤላውያንና በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሁሉ ስለሚጠብቃቸው የመከራ ጊዜ የሚያመለክት ነው። ብዙዎች ስለሚገደሉ ጨርሶ የጠፉ የሚመስልበት ወቅት ይመጣል።

ዳንኤል እነዚህን ትንቢቶች መረዳት አልቻለም። ስለዚህም የመጨረሻው ፍጻሜ ምን እንደሚሆን መልአኩን ጠየቀው። መልአኩ ግን ራዕዩን ለመረዳት ምንም ሙከራ እንዳያደርግ ለዳንኤል ነገረው። የትንቢቱ ቃል ተዘግቶአል፥ ታትሞአል። ይህም ማለት ማንም ትንቢቱን እንዳይረዳው ተደርጎአል ማለት ሳይሆን በመጨረሻ ዘመን የእግዚአብሔር ልጆች ሊረዱት እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ተጠብቆ መኖር አለበት ማለት ነው።

የመጨረሻው ዘመን በሰዎች ላይ የተለያየ ውጤት ያስከትላል።

1. እግዚአብሔርን በፍርሃት የሚከተሉትን ሰዎች ያጠረቸዋል። ወርቅና ብር በእሳት እንደሚጠሩ ሁሉ እግዚአብሔርም ሕዝቡን በዚህ የመከራና የስደት እሳት ያጠረል።

23ኛ ጥያቄ:- ስደትና መከራ ያገኘንና የቤተ ክርስቲያንህን ሰዎች ሕይወት ያጠረው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

2. እግዚአብሔርን የካዱ ዓመፀኞችን ግን ይህ የችግር ጊዜ ይበልጥ እንዲያምፁ ያደርጋቸዋል። ክፉ ምኞታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። በዳንኤል መጻሕፍት የተነገሩትን ትንቢቶች መረዳት አይችሉም። የዓለም ፍጻሜ መድረሱንና በቅርቡ እንደሚፈረድባቸውም አይረዱም። እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚታዘዙት «ጠቢባን» ግን የመጨረሻው ጊዜ መቃረቡን ስለሚረዱ በእምነታቸው ይጸናሉ። ሁኔታዎችን ሁሉ የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር እንደሆነ ስለሚረዱ ከፍተኛ መጽናናት ይኖረቸዋል።

መልአኩ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ ሁለት ቀኖች ለዳንኤል ነገረው። የመጀመሪያው 1290 ቀናት ነው። ስለዚህ ቁጥር ትርጉም ለመረዳት የተለያየ አስተያየት ተሰጥቶአል። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. ይህ 1290 ቀን የሚያመለክተው መሥዋዕቱ የተቋረጠበትን ማለትም በአንጦኪዮስ ኤጵፋንዮስ ዘመን አሣማን በመሠዋታቸው ቤተ መቅደሱ ከረከሰበት ጊዜ አንሥቶ እንደገና መሥዋዕት እስከተጀመረበትና መቅደሱ እስከነጻበት ያለውን ጊዜ ያመለክታል።

2. ይህ 1290 ቀን የስደቱንና የመከራውን ዘመን እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያሳጥረው ለማሳየት የተሰጠ ምሳሌያዊ ቁጥር ነው።

3. ይህ 1290 ቀን በመጨረሻው ዘመን በእግዚአብሔር ሕዝብ እና በእስራኤላውያን ላይ የሚደርሰውን ታላቅ የመከራ ጊዜ ያመለክታል። በቅዱሳት መጻሕፍት ተደጋግሞ የተገለጸው ይህ የመከራ ጊዜ ሦስት ዓመት ተኩል፥ ወይም 42 ወሮች፥ ወይም 1260 ቀን ነው፥ (ዳን.7:25፤ 12:7፤ 11:2፤ 12:6፤ 14፤ 13:5 ተመልከት)። ይሁን እንጂ ትርፉ 30 ቀን የተጨመረው ጌታ ኢየሱስ የሚመለስበትንና በሕዝብ ሁሉ ላይ የሚፈርድበትን ጊዜ ለመሸፈን ነው።

24ኛ ጥያቄ:- ማቴ.25:31-46 አንብብ።
ሀ/ በዚህ ጊዜ የሚፈረድባቸው እነማን ናቸው?
ለ/ ፈራጁስ ማነው?

ስለ 1335 ቀኖችስ ምን ታስባለህ? ለምንድነው ሌላ 45 ቀን የተጨመረው? ይህ 1335 ቀን እስኪያበቃ የሚደርስ ሰው ምስጉን እንደሆነ ለዳንኤል ተነግሮታል:: ይህም ጊዜው የታላቅ መከራና ስደት እንደመሆኑ መጠን እምነታቸውን ጠብቀው በመቆየታቸው ጌታ በሚመለስበት ጊዜ ስለማይፈርድባቸው ነው:: እነዚህ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ በሚመሠርተው መንግሥት ውስጥ ተሳታፊዎች ይሆናሉ:: ይህ ተጨማሪ 45 ቀን ጌታ ኢየሱስ መንግሥቱን እስከሚመሠርት ድረስ ያለውን ጊዜ ያመለክታል::

ትንቢቱ ለዳንኤል ግልፀ እንዳልነበር ሁሉ ለእኛም ግልፀ አይደለም:: ትንቢቱን የምንረዳው ባለን የግንዛቤ ደረጃ መጠን ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ ትንቢቱን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ባለመቻሉ እንዳይጨነቅ መልአኩ ለዳንኤል ነገረው:: እንደማንም ሰው ሁሉ እርሱም አንድ ቀን ይሞታል:: በመጨረሻው ጊዜ ግን ሽልማትን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ከቅዱሳን ጋር ይነሣል:: ይህ እኛንም ሊያጽናናን ይገባል:: ብዙ የማንረዳው ነገር ሊኖር ይችላል:: ግን ልክ እንደ ዳንኤል እስከ መጨረሻው ድረስ ታማኝ መሆን ይኖርብናል:: ከዚያ በኋላም ብንሞት ወይም ጌታ ኢየሱስ እስኪመለስ ድረስ በሕይወት ብንኖር እርሱ ራሱ ተስፋ የገባልንን ውርስ እናገኛለን:: የእግዚአብሔር ተከታይ በመሆንና እርሱንም በማገልገል እስከ ፍጻሜው ድረስ ታማኝ ትሆናለህ? እርሱ መቼ ዳግመኛ ተመልሶ እንደሚመጣ እርግጠኞች አይደለንም፤ ስለዚህም በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ታማኝ ሆነን መጠበቅ ይኖርብናል፥ (ሉቃ.12:35-48)::

25ኛ ጥያቄ:- ገላ.6:9 አንብብ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅርብ ጊዜ መመለሱን እያሰብን ሳለ ይህ ምክር ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው?

አረተኛ ቀን:- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ:: ጊዜ ካለህ በሚቀጥለው ሳምንት ለሚሰጠው ፈተና ለመዘጋጀት ከ1-19 ድረስ ያለውን ትምህርት እንደገና ተመልከት::

## የሳምንቱ ስብሰባ

1. የሳምንቱ የአምልኮ ጊዜ
2. ጸሎት
3. ትምህርቱን መከለስ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1/ የትንሣኤው እውነተኛነት ክርስቲያኖችን ምን ያህል ያጽናናቸዋል?
2/ ይህ እውነት ክርስቲያኖችን ምን ያህል ለታላቅ አገልግሎት

ያነሣሣቸዋል?

3/ ይህ እውነት ክርስቲያን ያልሆኑት ወደ ጌታ እንዲመለሱ ምን ያህል ያበረታታቸዋል?

ለ. 1/ «ጠቢብ» ክርስቲያን ምን ዓይነት እንደሆነ ግለጽ::

2/ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረት ምን ይመስላል?

3/ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ለቤተ ክርስቲያን÷ ለአገልግሎት÷ ለዓለምና ላልዳኑት ሰዎች ያለውን አመለካከትና ግንኙነት ሊለውጠው የሚችለው እንዴት ነው?

ሐ. ስደት ጸጽቃንን የሚያጠረው ዓመፀኞችን ደግሞ ይበልጥ እንዲያምፁ የሚያደርገው እንዴት ነው?

መ/ ሉቃ. 12:13-48 አንብብ:: ቤተ ክርስቲያንህ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት የተዘጋጀች ለማድረግ ይህንን ምንባብ እንዴት አድርገህ ልትጠቀምበት ትችላለህ?

5. ጸሎት::

## ትምህርት ሃያ

## ክለሳ

<u>የመጀመሪያ ቀን</u> ትምህርት አንድ እስከ አረት

በዚህ ክፍል እስካሁን ድረስ የተማርናቸውን ትምህርቶች እንደገና ለመከለስ እንሞክረለን:: የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ ትምህርቱን እንደገና ተመልክተን ከዕለታዊ ሕይወታችን ጋር እንድናገናዝበው ነው::

የዳንኤልን መጽሐፍ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት አስቀድመን የእስረኤልንና በዙሪያዋ ስለነበሩት የአሕዛብ መንግሥታት ታሪክ ተመልክተናል:: ስለ ትንቢት ክርስቲያኖች የሚያቀርቧቸውን የተለያዩ አስተያየት ተመልክተናል:: እስኪ እነዚህን ሦስት ነጥቦች በአጭሩ እንመልከት::

1ኛ ጥያቂ:- እግዚአብሔር የእስረኤልን ሕዝብ የመረጠው ለምንድነው? ምን ዓላማ ነበረው? ዘፀ.19:3-6 እና ኢሳ. 49: 1-7 ተመልከት::

ምንም እንኳ ታናሽና ከቁጥር የማይገቡም ቢሆን እግዚአብሔር እስረኤልን የመረጠበት ምክንያት ለሌሎች መንግሥታት ብርሃን እንዲሆኑ ነበር:: የእውነተኛውን አምላክ መንገድ ለዓለም ሕዝብ ማሳየት ነበረባቸው:: ምንም እንኳ በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን ገናና መንግሥት ቢሆኑም ወዲያውኑ

በኃጢአት ወደቁ። እግዚአብሔር ራሱ በሲና ተራራ ከእነርሱ ጋር የጸረገውን ቃል ኪዳንም ናቁ። ሐሰተኛ አማልክትን ማምለክ ጀመሩ። ምንም እንኳ ኃጢአታቸው ስለሚያስከትልባቸው ጥፋት እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት ቢያስጠነቅቃቸውም እነርሱ ሊሰሙት አልፈለጉም። ከሰሎሞን በኋላም የእስራኤል ሕዝብ ለሁለት ተከፈሉ። እስራኤል በመባል የሚታወቀው ሰሜናዊው መንግሥት የቆየው ከ930 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ነበር።

2ኛ ጥያቄ:- ሰሜናዊውን የእስራኤል መንግሥት የደመሰሱ እነማን ነበሩ?

እርሱን ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እግዚአብሔር በሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት ላይ ፈረደባቸው፤ ለአሦራውያን ምርኮኝነትም አሳልፎ ሰጣቸው። ከዚህም ጊዜ አንሥቶ በጥንታዊው ዓለም ውስጥ ተበታትነው ቀሩ፤ በመንግሥትም ደረጃ ወደ ሀገራቸው አልተመለሱም።

ደቡባዊው መንግሥት ደግሞ ይሁዳ በመባል ይታወቃል። በይሁዳ የነገሡ ነገሥታት በሙሉ የዳዊትና የሰሎሞን ዝርያ ነበሩ። ነገር ግን እንደ ዳዊት እግዚአብሔርን የሚወዱና ለሕግጋቱ የሚታዘዙ አልነበሩም። እነርሱም እንደ እስራኤላውያን ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ በነቢያቱ በኩል እግዚአብሔር የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ አልተቀበሉም። ምንም እንኳ ይህ መንግሥት ከሰሜናዊው መንግሥት ይልቅ ረዘም ላለ ጊዜ ቢቆይም፥ (ከ930-586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ) በመጨረሻ ይሁዳም በምርኮኝነት ተወስዶ ነበር።

3ኛ ጥያቄ:- አይሁዳውያንን በምርኮኝነት የወሰዷቸው እነማን ነበሩ?

አይሁዳውያን በምርኮኝነት ወደ ባቢሎን የተወሰዱት በሦስት ደረጃ ነበር። በመጀመሪያ:- በ605 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ግብር ከሰበሰበ በኋላ የሀገሪቱን መሪዎችና ታላላቅ ሰዎች በምርኮኝነት ወሰዳቸው።

4ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 1:1-2 አንብብ።
ሀ/ በዚህ ጊዜ በምርኮኝነት የተወሰደው ማነው?
ለ/ ሌላስ ከኢየሩሳሌም የተወሰደው ነገር ምንድነው?

በዚህ የመጀመሪያ የምርኮ ጊዜ ዳንኤልና የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች ተማርከው ወደ ባቢሎን ተወሰዱ። በ597 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በተደረገው ምርኮ ደግሞ ነቢዩ ሕዝቅኤል ተወሰደ። ኢየሩሳሌም በመጨረሻ የተደመሰሰችው ግን በ586 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ በምርኮኝነት የተወሰዱት በኃጢአታቸው ምክንያት ነበር። ይሁን እንጂ ከ70 ዓመት በኋላ እግዚአብሔር አይሁዳውያን ከምርኮኝነት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደላቸው።

5ኛ ጥያቄ:- በእርሱ ላይ እምፀን ኃጢአታችንን እንናዘዝም ስንል እግዚአብሔር ለምርኮኞነት አሳልፎ የሚሰጠን ወይም ቤተ ክርስቲያንን አሳልፎ የሚሰጣት በምን መልኩ ነው? እንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ::

ዳንኤል የኖረው ሁለት ታላላቅ የዓለም መንግሥታት በነበሩበት ዘመን ነበር:: የመጀመሪያው ባቢሎን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሜዶንና የፋርስ መንግሥት ነበር:: ይሁን እንጂ ሌሎች ሁለት መንግሥታት ማለትም የግሪክና የሮም መንግሥት እንደሚነሡ እግዚአብሔር ነገረው:: እነዚህ መንግሥታት ምን ያህል ሰፊ እንደነበሩ ለመረዳት በመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት::

ትንቢተ ዳንኤል÷ «የትንቢት መጻሕፍት ቁልፍ» በመባል ይታወቃል:: ይህም ከማንም ነቢይ ይልቅ ስለ መንግሥታት መነሣትና መውደቅ እንዲሁም ስለሚነሡበት ወቅት እግዚአብሔር ለዳንኤል በግልጽ ስላሳየው ነው:: ዳንኤል ስለ ባቢሎን መንግሥት÷ ስለ ሜዶንና ፋርስ መንግሥት÷ ስለ ግሪክ መንግሥትና ስለ ሮም መንግሥት መነሣት ትንቢት እንደተናገረ ከጥናታችን ተመልክተናል:: ኢየሱስ ክርስቶስ ከመመለሱና የእግዚአብሔር መንግሥት ከመመሥረቱ በፊት ስለሚነሣውም ክፉ መሪ ዳንኤል ትንቢዮአል::

ክርስቲያኖች ሁሉ ስለ ትንቢት መረዳት ያላቸው ማስተዋል አንድ ዓይነት አይደለም:: እግዚአብሔር መንግሥቱን እንዴት እንደሚመሠረት ሦስት የተለያዩ አስተያየቶች ተሠንዝረዋል:: ስለ እነዚህ የተለያዩ አስተያየቶች ከመመልከታችን በፊት ግን ሁለት ነገሮችን መገንዘብ ይኖርብናል::

በመጀመሪያ:- ክርስቲያኖች ሁሉ በዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች ይስማማሉ::

6ኛ ጥያቄ:- እንደገና ትምህርት ሁለትን ተመልከት:: ስለ መጨረሻው ዘመን ክርስቲያኖች ሁሉ ስለሚስማሙባቸው አራት ነጥቦች ግለጽ::

ምንም እንኳ ክርስቲያኖች ሁሉ በመንግሥተ ሰማይና በገሃነም÷ በመለኮታዊ ፍርድ÷ በትንሣኤና በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ቢስማሙም እነዚህ ነገሮች ስለሚፈጸሙበት ቅደም ተከተል ግን የተለያየ አስተያየት አላቸው::

ሁለተኛ:- ስለ ወደፊቱ ጉዳይ የተሰጠው ትንቢት በጣም ግልጽ ስላልሆነ ከእኛ የተለየ ሐሳብ ያላቸውንም ሰዎች አስተያየት በጽሞና ማዳመጥ ይኖርብናል:: በመካከላችን ሊፈጠሩ የሚችሉት እነዚህ ልዩነቶች ጸህንነታችንንም ሆነ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ሊያፋልሱ እንደማይችሉ አስተውል::

7ኛ ጥያቄ:- እንደገና ትምህርት ሁለትን ተመልከት።
ሀ/ ሦስቱን የተለያዩ ትንቢታዊ አመለካከቶች ዘርዝረህ ከጻፍክ በኋላ ስለ እያንዳንዱ ገለጻ ስጥ።
ለ/ አንተ የምትከተለው የትኛውን ትንቢታዊ አመለካከት ነው? ለምን?

ትንቢታዊ አመለካከቶች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነዚህ ሦስት ትንቢታዊ አመለካከቶች በኢየሱስ ክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

1. አንዳንዶች:- ቤተ ክርስቲያን በጣም ስለምታድግና ስለምትስፋፋ በዓለም ላይ የረጅም ጊዜ ሰላም ይሰፍናል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሺህ ዓመት እንደሚገዛ የተነገረው ትንቢት ቃል በቃል የሚወሰድ አይደለም፤ ይህ የሰላምና የብልጽግና ጊዜ ካበቃ በኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመለስና ዘላለማዊ መንግሥቱን ይመሠርታል ይላሉ። በአሁኑ ጊዜ ይህ አመለካከት ብዙ ተከታዮች እንደሌሉት ባለፈው ትምህርታችን ተመልክተናል።

2. አንዳንዶች:- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት የተነገረው ትንቢት ቃል በቃል የሚወሰድ አይደለም ብለው ያምናሉ። በምድር ላይ ዓመፅና ሁከት ይበዛል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሲመለስ ግን ዓመፅን ሁሉ አጥፍቶ ወደ ደውኑ ለዘላለም ይነግሣል ይላሉ።

3. ሌሎች ደግሞ:- በመጨረሻው ዘመን ታላቅ መከራና ስደት ይሆናል ብለው ያምናሉ። ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ይመለስና የሺህ ዓመት መንግሥቱን ይመሠርታል። የመጨረሻው ዓመፅ ከተደመሰሰ በኋላ ግን እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ይመሠርታል፤ ከዚህ በኋላ ዘላለማዊነት ይጀመራል።

ስለ ትንቢተ ዳንኤል ያለን መረዳት የሚወሰነው በእነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች ላይ ባለን አስተያየት ነው።

ዳንኤል በምርኮኛነት የተወሰደው በ605 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን እስከ 537 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ድረስ ቆይቶአል። ለ70 ዓመት ያህል በፖለቲካ መሪነት በባቢሎንና በፋርስ መንግሥታት ውስጥ እየሠራ እግዚአብሔርን በታማኝነት አገልግሎአል። በተጨማሪም እንደ ነቢይነቱ:- ዳንኤል ከራሱ ጊዜ አንሥቶ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያለውን ትንቢት በታማኝነት ተንብዮአል። ይህም ዳንኤልን በዓለም ላይ ከተነሡት ነቢያት ሁሉ የበላይ አድርጎታል።

8ኛ ጥያቄ:- የዳንኤልን ሕይወት በተረዳከው መጠን እንደ ምሳሌነቱ ልንከተላቸው የሚገቡን የአኗኗር ዘዴዎቹ የትኞቹ እንደሆኑ ታስባለህ?

፱ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል 2:21፤ 4:25፤ 34-35 አንብብ:: ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ ምንድነው?

የትንቢተ ዳንኤል ዋነኛ መሪ ሐሳብ:- በዓለም ላይ የሚሆኑ ሁኔታዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው የሚለው እንደሆነ ደጋግመን ተመልክተናል:: በሚወዱት ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚፈጸመው ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነው:: በማኅበረ-ምዕመናን ሕይወት የሚሆነው ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ነው:: የአሕዛብ ነገሥታት ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር ናቸው:: ታሪክ በእርሱ ሥልጣን ሥር ነው:: ሁሉም ከኢየሱስ ክርስቶስ ቁጥጥር እስከሆነ ድረስ ሁኔታዎችን ሁሉ የሚመረው እርሱ ነው፥ (1ቆሮ.15: 22-28 ተመልከት)::

10ኛ ጥያቄ:- የትንቢተ ዳንኤል ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ምንድናቸው? (ትምህርት ሦስትን ተመልከት::)

ትንቢተ ዳንኤል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሎአል:: ከዳንኤል 1-6 ያለው የመጀመሪያው ክፍል:- እግዚአብሔር ልጆቹን፥ አሕዛብንና በታሪክ ሂደት ውስጥ እንደሚቆጣጠር ያመለክታል::

ከ7-12 ያለው ደግሞ እግዚአብሔር የልጆቹንና በትንቢት የታዩትን ወደፊት የሚነሡትን መንግሥታት ሁሉ እንደሚቆጣጠር ያሳያል::

11ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር በልጆቹ ሕይወት የሚፈጸመውን ሁሉ መቆጣጠር መቻሉን እንዴት እንደሳየ ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ አንድን በመመልከት ጥቂት ነጥቦችን ግለጽ:: (ዳን.1፥ 2፥ 6፥ 9፥ 15፥ 17)

ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 1 የመጽሐፉ መግቢያ ነው:: ከዳንኤልና ሐናኒያ፥ ሚሳኤልና አዛርያ ከሚባሉ ከሦስት ጓደኞቹ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅነው በዚህ ምዕራፍ ነው:: እንዴት ወደ ባቢሎን እንደመጡ፥ እግዚአብሔርም እንዴት እምነታቸውን እንዳከበረላቸውና ወደ ከፍተኛ ሥልጣን እንዳደረሳቸው የምናየው በዚህ ምዕራፍ ነው::

ከምዕራፍ አንድ ጀምረን የእግዚአብሔር እጅ በሥራ ላይ መሆኑን እናያለን:: ዳንኤልን ጨምሮ ጠቅላላ ሕዝቡን በናቡከደነፆር እጅ አሳልፎ የሰጠው እግዚአብሔር ራሱ ነው፥ (ቁ.2):: የባቢሎን መሪዎች ወደሚሰለጥኑበት ትምህርት ቤት የእርሱ ሕዝብ ገብተው እንዲማሩም ሁኔታዎችን ሁሉ ያመቻቸውም እርሱ ነው:: ብዙ ወጣቶች ቢኖሩም ዳንኤልና ጓደኞቹ በዚህ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ተመረጡ፥ (ቁ.6):: በትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች ፊት እግዚአብሔር ሞገስን ሰጣቸው:: ስለዚህም ከንጉሡ ቤት መብል ይልቅ አትክልትን እንዲበሉ

ያደረጉትን ውሣኔ ተቀበሉአቸው:: ከንጉሡ ገበታ ከሚበላው ምግብ ይልቅ የአትክልቱ ምግብ የበለጠ ተስማሚ እንዲሆን ያደረገው እግዚአብሔር ነው፥ (ቁ.15):: ከሌሎች የበለጠ ሕዝብን የሚያስተዳድሩበትን ጥበብ የሰጣቸውም እግዚአብሔር ነው:: ከዚህም የተነሣ ትምህርታቸውን ፈጽመው በባቢሎን የአስተዳደር ሥራ ላይ ተሰማሩ::

12ኛ ጥያቄ:- ዳንኤል በንጉሡ መብል እንዳይረክስ ወሰናአልI እኛስ ከዚህ
የምንማረው ምንድነው?

ለመጨረሻው ፈተና እንዲረዳህ በመጽሐፍ ቅዱስ ማብረሪያዎቹ እየተጠቀምክ የመጀመሪያዎቹን አረት ትምህርቶች ከልስ::

ሁለተኛ <u>ቀን:ᐧ</u> .<u>ትምህርት</u> አምስት እስከ <u>አሥር</u>

13ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በምዕራፍ ሁለት ናቡከደነፆር ስላየው ሪዕይ ገለጻ ስጥ::
ለ/ በምዕራፍ ሁለት የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሁሉ በእግዚ
አብሔር ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን የምንረዳው እንዴት
ነው::

ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 2 ከምዕራፍ 7-12 ያሉትን ትንቢቶች እንድንረዳ የሚያደርገን ዋና መሠረት ነው:: ስለዚህም በነገው ትምህርታችን ስለዚህ ምዕራፍ በሰፊው እንመለከታለን:: ከትምህርቱ በስተጀርባ ያለው ዋነኛ ትምህርት ግን በምድር የሚነሡ መሪዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን ነበር:: አማኝ ባልሆነው በአረማዊው ንጉሥ አማካይነት እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚነሡት የሚደንና ፋርስ፥ የግሪክና የሮም እንዲሁም በመጨረሻ ስለሚቋቋመው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት አስቀድሞ ገለጸ:: እነዚህ ነገሥታት ከመነሣታቸው ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የትኛው ከየትኛው በኋላ እንደሚነሣ በእግዚአብሔር ተወስና ነበር::

ከዚህም በተረፈ በሰይጣን በሚመረው ሰብዓዊ ጥበብና በእግዚአብሔር በሚመነጨው መለኮታዊ ጥበብ መካከል ስለተጀመረው ውጊያ የምንመለከተው በዚህ ምዕራፍ ላይ ነው:: ታላቅ ጥበብና ዕውቀት አለን የሚሉት የሃይማኖት መሪዎች የንጉሡን ሕልም መተርጎም አልቻሉም:: እግዚአብሔር ግን ለሕዝቡ ትክክለኛ ጥበብና ማስተዋል ሰጣቸው:: የባቢሎን ጠቢባን አቅቷቸው ዳንኤል ሕልሙን መተርጎም የቻለውም በዚህ ምክንያት ነው::

14ኛ ጥያቄ:- በእግዚአብሔርና በሰው ጥበብ መካከል የሚደረገው ውጊያ
በግል ሕይወትህና በቤተ ክርስቲያንህ እንዴት ይታያል?
(ተጨማሪ ምሳሌ እንዲሰጥህ 1ቆሮ.1:18-2:16
ተመልከት::)
15ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በምዕራፍ ሦስት ላይ ሲድረቅ፥ ሚሳቅና አብድናጐ

የቀረበላቸው ፈተና ምንድነው?
ለ/ እግዚአብሔር የሁኔታዎቹ ሁሉ ተቆጣጣሪ መሆኑን ይህ ምዕራፍ የሚያመለክተው እንዴት ነው?

ዳንኤል ምዕራፍ 3 ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ታማኝ ሲሆኑ ስለሚደርስባቸው ችግር የሚገልጽ የመጀመሪያ ምሳሌ ነው። ሲድራቅ፥ ሚሳቅና አብድናጎ በባቢሎን መንግሥት ውስጥ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ነበሩ። ወዲያውኑ ግን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነት የሚፈተንበት ጊዜ ደረሰ። እኔን ብቻ አምልኩ ብሎ ያዘዘውን እግዚአብሔርን ማምለክ ወይም ደግሞ ንጉሡ ያወጣውን ትእዛዝ በመቀበል ጣዖትን የማምለክ ምርጫ ቀረበላቸው። ናቡከደነፆር አንድ ታላቅ ሐውልት አሠርቶ በመንግሥቱ ውስጥ ያሉ ባለሥልጣኖች በሙሉ ለዚያ ሐውልት እንዲሰግዱ አዘዘ። ይህ ሐውልት የራሱ ይሁን፥ ወይም በረዕይ ያየው ምስል እርግጠኛ አይደለንም። እነዚህ ሦስት የአይሁድ ወጣቶች ግን ለዚያ ሐውልት መስገድ አልፈለጉም፤ ስለዚህም መሪዎቹ (ኮከብ ቆጣሪዎቹ) ለንጉሡ ከሰሱአቸው። «ከእጄስ የሚያድናችሁ ማነው?» በማለት ናቡከደነፆር በተቈረረ ጊዜ እነዚህ አይሁዳውያን፡- «የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ሊያድነን ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል። ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምከውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት ዕወቅ አሉት።» ምንም እንኳ በእግዚአብሔር አዳኝነት ቢያምኑም በዚያ ወቅት ግን ሊያድናቸው ፈቃዱ ይሁን አይሁን እነዚህ መጣቶች አላወቁም ነበር። ይሁን እንጂ በእምነታቸው ጸንተው ቆሙ፤ ሕይወታቸውን ለማዳን ሲሉ እግዚአብሔርን አልካዱም። ወደ እሳት ተጣሉ፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር መልአክ (ምናልባትም ኢየሱስ ክርስቶስ) መጥቶ አዳናቸው። ከእንደዚያ ዓይነት እሳት ማንም ሊያድን እንደማይችል ናቡከደነፆር ራሱ አመነ። በዚህም ገጠመኝ አማካኝነት በልጆቹ ላይ የሚፈጸመው ሁኔታ በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እንደሆነ እንመለከታለን። እነዚህን ወጣቶች እግዚአብሔር ከፈተና አላዳናቸውም። ወደ እሳቱ እቶን እንዲጣሉ ፈቀደ። ይሁን እንጂ ትልቅ ችግር ባጋጠማቸው ወቅት እግዚአብሔር ታደጋቸው። እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት ይጠነቀቃል። ልንታዘዘው የሚገባን የመጨረሻው ባለሥልጣን እግዚአብሔር ራሱ ነው። ከእርሱ ትእዛዝ ጋር የሚቃረን ሆኖ ካገኘነው የባለሥልጣኖችን ትእዛዝ እንኳ መቀበል እንደሌለብን ከምዕራፍ 3 እንማረለን። ሕይወታችንን ለማዳን ስንል ሰዎችን ከምንታዘዝ፥ በቅድሚያ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይኖርብናል።

16ኛ ጥያቄ:- እነዚህ ሦስት ወጣቶች ያለፉበት ፈተና አንተ ካለፍከበት ፈተና ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ፈተናውን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ተቀበልከው?

17ኛ ጥያቄ:- በምዕራፍ 4 ላይ እግዚአብሔር የማያምኑ መሪዎችን ሕይወት እንኳ መቆጣጠር መቻሉን ያሳየው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው?

ምዕራፍ 4 እግዚአብሔር የምድረዊ መሪዎችን ሕይወት እንደሚቆጣጠር ያሳያል:: ብዙ ጊዜ ግን መሪዎች የማይሸሩና የማይሞቱ ይመስላቸዋል:: ሁሉንም የሚቆጣጠሩ ስለሚመስላቸው የእነርሱን ሕይወት የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ዘንግተዋል:: ምንም እንኳ የሚደርስበት ምን እንደሆነ በረዕይ ቢያስጠነቀቀውም ናቡከደነፆር ልቡን በእግዚአብሔር ላይ አስታበየ:: እግዚአብሔር ናቡከደነፆርን ለሰባት ዓመት ያህል ወደ እንስሳነት ደረጃ ላይ አድርኮ አዋረደው:: በኋላ ግን ከምሕረቱ የተነሣ እንደገና ወደዙፋኑ እንዲመለስ አደረገው:: ያን ጊዜ ነበር ናቡከደነፆር እግዚአብሔር በሰዎች መንግሥት ላይ ሥልጣን እንዳለውና ለወደደውም እንደሚሰጠው የተረዳው:: ናቡከደነፆር የነበረው እምነት ለደኅንነት የሚያበቃ መሆኑን እርግጠኛ አይደለንም:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በሕይወቱ ላይ ሥልጣን እንዳለው ሳይወድ በግድ መቀበል ነበረበት:: በትዕቢት የተወጠሩትን ሊያዋርዳቸው እንደሚችል ተረድቷል:: እኛም ብንሆን እንዳንታበይ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን:: ያለን ችሎታ ሁሉ፥ የምንሠራው ሥራ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው:: ክብር ሁሉ የእርሱ ነው:: ክብሩን የምንሻማ ከሆነ ግን ያዋርደናል::

18ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር ትዕቢተኛን ሲያዋርድና ትሑታንን ከፍ ሲያደርግ ያየኸው እንዴት ነው?

19ኛ ጥያቄ:- የእግዚአብሔር የበላይ ተቆጣጣሪነት በምዕራፍ 5 የሚታየው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው?

ምዕራፍ 5 የባቢሎንን መንግሥት ፍጻሜ ያመለክታል:: ናቦኒዳስ ከተባለው አባቱ ጋር አብሮ ይገዛ የነበረው ብልጣሶር አብዛኛው ግዛቱ በሜዶንና ፋርስ መንግሥት ተወሰደበት:: ያልተወሰደው የባቢሎን ከተማ ብቻ ነበር:: ምን ጊዜም ቢሆን ጽሉ የባቢሎን እንደሚሆን ፍጹም እምነት የነበረው ብልጣሶር ግን ከፍተኛ ግብዣ አዘጋጀ:: ከትዕቢቱና ከድፍረቱ የተነሣ የቤተ መቅደስ ዕቃዎችን አረከሰ:: ይህም በእግዚአብሔር ላይ የተቃጣ ጥቃት ነበር:: እግዚአብሔር የብልጣሶር መንግሥት እንደተመዘነና ቀልሎ እንደተገኘ በግድግዳ ላይ ጻፈላቸው:: ስለዚህም የብልጣሶር መንግሥት ለሜዶንና ፋርስ ነገሥታት ተሰጠ:: በዚያው ሌሊት ባቢሎን ጽል ተደረገች፤ የመንግሥትም ፍጻሜ ሆነ:: እንደገና እግዚአብሔር የሁኔታዎች ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪ መሆኑን አሳየ:: «ትንፋሽህንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ አላከበርከውም» በማለት ዳንኤል ብልጣሶርን ወቀሰው:: የብልጣሶር ሥራ እንደተመዘነ ሁሉ የእያንዳንዳችንም ሥራ ይመዘናል:: በዚህ ሚዛን ሲመዘን እንደ ብልጣሶር ቀልሎ ይገኝ ይሆን? ወይስ ፈተናውን ያልፍ ይሆን? (1ቆሮ.3:10-15)

20ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በምዕራፍ 6 የዳንኤል እምነት የተፈተነው እንዴት ነው?
ለ/ ይህ ፈተና በምዕራፍ 3 ከተሰጠው ፈተና የሚለየው እንዴት ነው?

በምዕራፍ 6 የተጠቀሰው ሁኔታ የተፈጸመው በሜዶንና ፋርስ መንግሥት ውስጥ ነው። በዚያን ጊዜ ሸማገሌው ዳንኤል ከፍተኛ ሥልጣን ነበረው። ይሁን እንጂ ብዙ ጠላቶች ነበሩት። ከሃይማኖቱ በቀር ምንም ሰበብ ሊያገኙበት እንደማይችሉ የተረዱት ተቃዋሚዎቹ ለ30 ቀን ያህል ለንጉሡ ካልሆነ በቀር ማንም ወደ አምላኩ እንዳይጸልይ ዓዋጅ እንዲያስነገር አደረጉ። በምዕራፍ 3 የቀረበው ፈተና እግዚአብሔር የከለከለውን ጣዖት ስለማምለክ ንጉሡ ያወጣው ትእዛዝ ነበርI በምዕራፍ 6 የቀረበው ፈተና ግን የንጉሡን ትእዛዝ በመፍራት እግዚአብሔርን ከማምለክ መገታት ነበር። በምዕራፍ 3 ላይ እንዳሉት እንደ ሦስቱ ሰዎች ዳንኤል ምንም እንኳ አታምልክ የሚል ትእዛዝ በገዛቱ ቢታወጅም እምነቱን ለመደበቅ አልፈለገም። ነገር ግን እግዚአብሔርን በግልጽ ማምለክ ስለቀጠለ በአንበሶች ጉድጓድ ተጣለ። እግዚአብሔርም እምነቱን አከበረለትI ስለዚህም አዳነው። በዚህም እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ሰዎች እንደሚታደግ በተጨማሪ አሳየ።

21ኛ ጥያቄ:- ከምዕራፍ 6 የምንማረው ዋነኛው ትምህርት ምንድነው?

22ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በመጀመሪያዎቹ 6 ምዕራፎች እግዚአብሔር የሁኔታዎች ሁሉ የበላይ ተቆጣጣሪ መሆኑን እንዴት እንደገለጸ በራስህ ቃላት አስረዳ።

ለ/ ከእነዚህ ምዕራፎች የተማርካቸውን ዋና ዋና ትምህርቶች በዝርዝር ጻፍ።

ለዚህ ሳምንት ፈተና ለመዘጋጀት ከ5-10 ያሉትን ትምህርቶች አጥና።

ሦስተኛ ቀን:- ትምህርት <u>አሥረ</u> አንድ እስከ <u>አሥረ</u> ዘጠኝ

የትንቢተ ዳንኤል ሁለተኛው ክፍል (ከምዕራፍ 7-12 ያለው) የሚያመለክተው:- እግዚአብሔር የወደፊቱን ጊዜ በተመለከተ ለዳንኤል የሰጠውን ራዕዮች ነው። በእነዚህ ምዕራፎች የተሰጡትን ትንቢቶች የምናብራራው ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ በመጠቀም ነው። የእነዚህ ምዕራፎች ዋነኛ ትምህርት ግን እግዚአብሔር የታሪክ ተቆጣጣሪ መሆኑን ማሳየት እንደሆነ አትዘንጋ። ታሪክን በእቅዱ መሠረት ይመረዋልI የመንግሥታት መውደቅና መነሣት የዚህ እቅዱ ክፍል ነው። ጅማሬን ሆነ ፍጻሜን የሚወስነው እርሱ ነው። ምንም እንኳ ጊዜው እጅግ ክፉ ቢሆንም አንድ ቀን እግዚአብሔርና ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነግሥበት ቀን ይመጣል። እግዚአብሔር ዘላለማዊ በመሆኑ ሕልፈት የለውምI ማንም ሊደመስሰው አይችልም።

በትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 2÷ ምዕራፍ 7-8 እና ምዕራፍ 10-12 ያለውን ዋና ዋና ትንቢት ለመረዳት የሚከተለውን ሠንጠረዥ አጥና። ከዚያ በኋላ ግን የራስህን ሠንጠረዥ ሠርተህ ባዶ ቦታዎቹን በመሙላት የትንቢቱን ዋና ዋና ክፍል ማወቅህን እርግጠኛ ሁን።

| ምዕራፍ 1 | ምዕራፍ 7 | ምዕራፍ 8 | ምዕራፍ 11 | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| ምስሉ | አውሬው | እንስሳት | ነገስታት | መንግስታት |
| የወርቁ ራስ | አንበሳ | | | ባቢሎን |
| የብር ደረትና ክንዶች | ድብ | ወጠጤ | አራቱ ነገሥታት | ሜዶንና ፋርስ |
| የናስ ሆድና ወገብ | ነብር | ትንሽ ቀንድ ያለው ፍየል | የሰሜኑ ነገስታትና የደቡብ ነገሥታት | ግሪክ የበጠሊሞስ ነገሥታት የሴሌውከው ነገሥታት |
| የብረት ጭኖች | አስፈሪው አውሬ | | | ሮም |
| የብረትና የሸክላ እግሮች | 10 ቀንዶችና 1 ትንሽ ቀንድ | | የመጨረሻው የሰሜኑ ንጉስ | የአንሰራራው የሮም መንግሥትና የክርስቶስ ተቃዋሚ |
| የድንጋዩ ታላቅ ተራራ መሆን | በዘመናት የሸመገለውና የሰው ልጅ | | | የእግዚአብሔር የዘላለም መንግስት |

በመጀመሪያ መሠረታዊ የሆነውን ምዕራፍ ማለትም ምዕራፍ ሁለትን እንመለከታለን። በምዕራፍ ሁለት ናቡከደነፆር ታላቅ ሐውልት አየ። ራሱ የወርቅ ሲሆን፥ ይህም የባቢሎንን መንግሥት ያመለክታል። ቀጥሎ የመጣው የብር ደረቱና እጆቹ ናቸው። ይህ ሁለተኛውን መንግሥት ማለትም ሜደንና ፋርስን ያመለክታል። ሦስተኛው ደግሞ ሆዱና ጭኖቹ ነሐስ እንደሆኑ ታየ። ይህም የግሪክ መንግሥትን ያመለክታል። አራተኛው የብረት እግሮች የመጨረሻውን የሮም መንግሥት ያመለክታሉ። እግሮቹ የብረትና የሸክላ ድብልቅ ነበሩ። ይህም የሰው መንግሥት ተሰባሪ መሆኑን ያመለክታል። አንዳንዶች ግን ይህ በመጨረሻ ጊዜ ከሮም መንግሥት ውስጥ የሚነሣውን የመጨረሻ የዓለምን መንግሥት ያመለክታል ይላሉ። ይህም መንግሥት ሆነ ሌሎች መንግሥታት ዓለቱ የተፈረ ከምር እንደሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ይደመሰሳሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት ሐልፈት የለበትም።

እንደ ምዕራፍ 2 ሁሉ ምዕራፍ 7 ደግሞ ራዕይ ነው። ራዕዩ የታላቅ ምስል ሳይሆን ስለ አራት የተለያዩ አራዊት ነው። ይሁን እንጂ በሁለቱም ምዕራፍ የተነገረው ትንቢት የሚያመለክተው እላይ ስለጠቀስናቸው ተመሳሳይ መንግሥታት ነው። የመጀመሪያው አውሬ አንበሳ ሲሆን የባቢሎንን መንግሥት ያመለክታል። ሁለተኛው ድብ ሲሆን የሜደንና ፋርስ መንግሥትን ያመለክታል፤ ሦስተኛው ነብር ሲሆን የግሪክን መንግሥት ያመለክታል፤ አራተኛው በቃል ለመግለጽ የሚያዳግት አውሬ ሲሆን እርሱም የሮም መንግሥትን ያመለክታል። ራዕዩ የሚያተኩረው በመጨረሻው አውሬ በተለይም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ከፍተኛ ሙከራ ባደረገው ቀንድ ላይ ነው። ይህ ታናሽ ቀንድ የሚያመለክተው በመጨረሻ በምድር ላይ የሚነሣውን ክፉ መሪ ወይም የክርስቶስ ተቃዋሚን ነው። ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች በበላይነት የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ራሱ ነው። «በዘመናት የሸመገለው» መንግሥትንና ሥልጣንን «የሰው ልጅ ለሚመስለው» እና ለቅዱሳኑ ሰጣቸው፤ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የሆነውም አውሬ ተደመሰሰ። ምንም እንኳ ዛሬ የዓለም መንግሥታት ዘላለማዊ መስለው ቢታዩም አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር የማይለወጠውን መንግሥትን ይመሠርታል።

23ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያንህ ያሉትን ሰዎች ሊያበረታታ ይችላል ብለህ የምታስበውን ከምዕራፍ 2 እና 7 ያገኘኸውን ትምህርት ዘርዝር።

ትንቢተ ዳንኤል 8 የሚያተኩረው በሁለት መንግሥታት ላይ ብቻ ሲሆን እነዚህም መንግሥታት የሜደንና የፋርስ መንግሥትና የግሪክ መንግሥት ናቸው። እነዚህን መንግሥታት ለማሳየት የአውሬ በግና የአውሬ ፍየል ምስል ተሰጥቶአል። በመጀመሪያ የታየው ሜደንና ፋርስን የሚወክለው አውሬ በግ ሲሆን እርሱም እስከ ጊዜው ድረስ ድልን ተቀዳጅቶአል። (የታላቁ እስክንድር ምሳሌ የሆነው) አንድ ቀንድ ብቻ ያለው አውሬ ፍየል ግን

አሸነፈው። አንዱ ቀንድ ተሰብሮ በምትኩ አራት ቀንዶች በቀሉ። ይህም የግሪክ መንግሥት በአራት መከፋፈሉን ያሳያል። ከቀንዶቹ አንዱ የሴሊውሲድ መንግሥት እጅግ በረታና ኢየሩሳሌምን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። ይህ የሚያመለክተው አንጦኪዮስ ኤጲፋንዮስን ሲሆን እርሱም ለብዙ ዓመታት ያህል ለእግዚአብሔር የሚቀርበው መስዋዕት እንዲቋረጥ አድርጐአል። በተጨማሪም ብዙ አይሁዳውያንንም ገድሎአል። አንዳንድ ምሑራን ይህ የመጨረሻ ቀንድ ወደፊት የሚነሣው ክፉ መሪ ምሳሌ ነው፤ ይህ መሪ መስዋዕተ እግዚአብሔር እንዲቋረጥ ያደርጋል፤ ብዙ አይሁዳውያንንም ይገድላል በማለት ያስባሉ።

ለጊዜው ምዕራፍ 9 ላይ ምንም ገለጻ አናደርግም። ከዚህ ይልቅ ግን በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ የመጨረሻዎቹ ታላላቅ ራዕዮች የሆኑትን ምዕራፍ 10-12 እንመለከታለን። የመጨረሻው ራዕይ የሚያተኩረው በሁለቱ የግሪክ መንግሥት ክፍሎች ሲሆን፥ እነርሱም:- በግብፅ የነበረው የበጥሊሞሳውያን መንግሥትና በሦርያ የነበረው የሴሊውሰድ መንግሥት ናቸው። በመጀመሪያ የተስፋይቱን ምድር ይቆጣጠር የነበረው የበጥሊሞሳውያን መንግሥት ኃያል ነበር። በመጨረሻ ግን የሴሊውሰድ መንግሥት ኃይል አገኘና የተስፋይቱን ምድር መቆጣጠር ቻለ። ይህ ምዕራፍ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሲፈጸም የነበረውን ሴራ እና ውጊያ በአስደናቂ ሁኔታ ይገልጻል። ይሁን እንጂ ምዕራፉ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው የሴሊውሰድ መንግሥት ወገን የሆነውን አንድ ሰው ነው፤ ይህም አንጢዮኮስ ኤጲፋንዮስን ነው። ክፉ በሕርዩና በአይሁዳውያን ላይ ያደረገው ግፍ ሁሉ ተገለጾአል። ይህ ሰው በመጨረሻው ዘመን ተነሥቶ ቅዱሳንን የሚያሳድደው መሪ ምሳሌ ነው። ስለ መጨረሻው ጦርነትና ስለ ክርስቶስ ተቃዋሚ መደምሰስ ተገልጾአል። በዚያ የመከራ ዘመን የሚኖሩ ጻድቃን ተስፋ ግን ትንሣኤ ሙታን መኖሩና ከሞት ከተነሡ በኋላ የሥራቸውን ዋጋ እንደሚከፍላቸው ማወቁ ነው። አንድ ቀን ክፉ መንግሥታት እንደሚደመሰሱና የእግዚአብሔር መንግሥት እንደምትመሠረት ይገነዘባሉ።

ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 9 ለመተርጐም ብዙ የተለያዩ አስተሳሰቦች ተሰንዝረዋል። ስለዚህም ብዙ አለመግባባት ፈጥሮአል። ይሁን እንጂ ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ ግልፅ በሆነ ሁኔታ የተገለጸው በዚህ ምዕራፍ ነው።

24ኛ ጥያቄ:- በትምህርት 15 ስለ ሰባው ሱባዔ የተሰጠውን ሠንጠረዥ እንደገና አጥና። በሁለቱ ሠንጠረዦች መካከል ያሉት ዋና ዋና ልዩነቶች ምንድናቸው?

ትንቢተ ዳንኤል 9 የሚጀምረው አይሁዳውያን ወደ ሀገረቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ዳንኤል ባቀረበው ጸሎት ነው። ምንም እንኳ የዳንኤል ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ቢደርስም፥ እግዚአብሔር ስለ 490

ዓመት ወይም ስለ ሰባ ሱባዔው ነው ለዳንኤል ራዕይ የሰጠው። ከሰባው ሱባዔ በኋላ የእግዚአብሔር እቅድ ይፈጸማል፤ ጽድቅም ይሰፍናል። እነዚህ ሰባ ሱባዔዎች በሦስት ተከፍሎአል።

1. 49 ዓመታትን የያዘው የመጀመሪያው ሰባት ሱባዔ የሚጀምረው በ445 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው። ይህም የኢየሩሳሌምን ከተማ ገንብ ለመሥራት አዋጅ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ ከተማይቱን የመጠገን ሥራ እስከሚጠናቀቅበት ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

2. 62 ሱባዔ የያዘ 434 ዓመታት። በእነዚህ ሱባዔዎች ፍጻሜ መሢህ ይመጣል፤ ከዚያ በኋላ ይገደላል፤ መቅደሱና የኢየሩሳሌም ከተማም ይደመሰሳሉ።

3. ሰባት ዓመት የያዘው የመጨረሻው ሱባዔ:- ምንም እንኳ አንዳንዶች ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኋላ በ70 ዓ.ም. ቤተ መቅደሱ በሮማውያን በተደመሰሰበት ወቅት ይህ የመጨረሻ ሱባዔ ተፈጽሞአል የሚል ሀሳብ ቢያቀርቡም፥ የመጨረሻው ሰባት ዓመት የሚፈጸመው ገና ወደፊት እንደሆነ እናስባለን። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመመለሱ በፊት ያለው የመጨረሻው ሰባት ዓመት ነው። እነዚህ ዓመታት ክፉ መሪ የሚገዛባቸውና ጦርነት የሚበዛባቸው ዓመታት ናቸው። ምንም እንኳ ይህ ክፉ መሪ ከአይሁዳውያን ጋር በመጀመሪያ ቃል ኪዳን ቢያደርግም ቃል ኪዳኑን በማፍረስ መቅደሱን ያረክሳል፤ እስከመጨረሻውም አይሁዳውያንን ይዋጋቸዋል። በኋላም ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣና ይነግሣል።

25ኛ ጥያቄ:- ሀ/ በእነዚህ ራዕዮች:- ሁኔታዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆናቸው የተገለጸው እንዴት ነው?
ለ/ ስለሚመጣው ታላቅ መከራ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያስጠነቀቀን ለምን ይመስልሃል?

ገና ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር በዓለም ላይ ስለሚሆነው ኃጢአትና ጦርነት አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ስለ ኃጢአታችን እንዴሞት ልጁን መላክ እንደነበረበትም ያውቃል። ምን ዓይነት መንግሥታትም እንደሚነሡ ያውቃል። በዚህ ሁሉ የራሱ እቅድና ውሣኔ አለው። ፍጻሜው መቼ እንደሚሆንና ዘላለማዊ መንግሥቱን የሚመሠርተውም መቼ እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል። የእግዚአብሔርን ጊዜ እኛ ባናውቅም:- ሁሉም ነገር በእርሱ ቁጥጥር ሥር መሆኑን ግን እናውቃለን። የእግዚአብሔርን መንግሥት እየጠበቅን የሚመጡትን የመከራ ዘመናት መታገሥና በእምነታችን ጸንተን መቆም አለብን። ከዚህ ካለንበት የጨለማ ዘመን በኋላ የጌጋት ፀሐይ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ይዞ ይመጣል። እስከዚያው ግን ታማኝ እንሁን።

ለመጨረሻው ፈተና ለመዘጋጀት ከትምህርት 11-20 ያለውን ከልስ።

<u>አረተኛ</u> ቀን፦ በዚህ ሳምንት ለሚኖርህ የመጨረሻ ፈተና ለመዘጋጀት ከ1-20 ያለውን ትምህርት ክለሳ አድርግ።

## የሳምንቱ ስብሰባ

ሀ. የሳምንቱ አምልኮ ጊዜ
ለ. ጸሎት
ሐ. የመጨረሻ ፈተና
መ. ትንቢተ ዳንኤልን ስታጠና ያገኘኸውን ትምህርት ለሌሎች አካፍል።
ሠ. ጸሎት።

## የሚከተሉትን ካርታዎች ከመጽሐፉ በስተጀርባ አኑር

1. የግብፅንና የተከፋፈለውን መንግሥት
2. የባቢሎንን መንግሥት
3. የሜዶንና ፋርስን መንግሥት
4. የበጥሊሞሳውያንና የሴሌውሲድ መንግሥትን ግዛት የሚያሳይ የግሪክ ካርታ
5. የሮም መንግሥት


ታላቁ ባሕር
እስራኤል
ይሁዳ
ምድረ በዳ
የዓረብ
ምድረ በዳ
ግብፅ
የኤርትራ
ባሕር



ጥቁር ባሕር
ካስፒያን ባሕር
የአሲሪያ ግዛት
አርማንያ
ሜዲያን
ቆጵሮስ
ሶርያ
ኤፍራጥስ
ባቢሎንያ
ጤግሮስ
ኤላም
ይሁዳ
እየሩሳሌም
ባቢሎን
የፋርስ ባሕረ ሰላጤ
ዓረብ
ግብፅ
ዓባይ ወንዝ
የቀይ ባሕር
ካባ ሳባዊያን
ሼባ ሳባውያን
የባቢሎናውያንን ግዛት ያሳያል


ጰንጦስ ጥቁር ባሕር
ቢታንያ
ቀጰዶቅያ
ኪልቅያ
ሶርያ
ሰማርያ ይሁዳ
ኢየሩሳሌም
ግብጽ
የኤርትራ ባሕር
ኢትዮጵያ
አረቢያ
የካስፒያን ባሕር
ፓርትያ
ሶግድያና
ባክትሪያና
አርያን
ፋርስ
የፋርስ ባሕረሰላጤ
ኢንዱስ ወንዝ
የፋርስን ግዛት ያሳያል



የግሪክ፣ የሴሉሲድ እና ፕቶለሚክ ግዛቶች


N
የእንግሊዝ
አገር
የፈረንሳይ
አገር
እስጳንያ
ኢጣሊያ
መቄዶንያ
ጥቁር ባሕር
የካስፒያን
ባሕር
ትንሹ
እስያ
ግሪክ አገር
ሶርያ
አፍሪቃ
ታላቁ ባሕር
የዓረብ
አገር
ግብፅ
የሮማ
መንግሥት ግዛት